


@OLDBOOKSPDF

ዓለማየሁ ገላጋይ

# ሐሰተኛው

በእምነት ሥም

፳፻፲፪ ዓ.ም

@OLDBOOKSPDF

©የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።
All rights reserved.
ሐምሌ ፳፻፲፪ ዓ.ም አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የመጀመርያ ህትመት ሐምሌ ፳፻፲፪ ዓ.ም

2ተኛ ህትመት ሐምሌ ፳፻፲፪ ዓ.ም

የሽፋን እና የውስጥ ገጽ ቅንብር ሙሉቀን አሥራት
@OLDBOOKSPDF
0913450005 / Email.mlknasrt@yahoo.com

# ማረፊያ

*እጅ እግር በሌለው፣ ቅጥ አንባሩ በጠፋ የድህነት ህይወት ውስጥ ሙልቅቅንና ድልቅቅን አሳይተው ላሳደጉኝ አያቴ **ለወ/ሮ በቀለች ገ/ማርያም፤** ውለታዎ ከኔ ባሻገር ላሉ አንባቢዎች ሁሉ ተርፏልና እነሆ ስለእኔ ለባጀ ቀልብዎ የመታሰቢያ ማረፊያዎ!*

@OLDBOOKSPDF

# ክፍል አንድ

## ወደ ቅንብበት ሰዎች



@OLDBOOKSPDF

ሐሰተኛው

# መታሰበያነቱ

ለደራሲና ጋዜጠኛ ዓለማየሁ ገላጋይ


(1960-1999)

ከዘጠና ሰባት ግርግር በኋላ በኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ላይ የወረደውን ዋዕይ መዓልቱን፣ ቁር ለሊቱን፣ ድምፀ መንግሥቱን፣ ፀብአ ህዝብ ደህንነቱን. . . መታገስ ቢሳነው በገዛ እጁ ከህይወት ወደ ሞት አፈገፈገ፡፡ ይሄ ክፍል መታሰቢያው ይሆንለት ዘንድ ቅርበታችን ግድ አለኝ፡፡ አሌክስ ነፍስህ በሰላም ትረፍ!!!

(አልአዛር ቢዘን)


@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፩






@OLDBOOKSPDF



@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፩

# የንስሃ - ነገር

ህይወት ሲኖሩዋት ቁልቁለት፣ ሲያምሰለስሏት አቀበት እንደሆነች የተረዳነው እኔና ጠቢቡ ሰለሞን ብቻ ነን!!

"...የሰው ልጅ በከንቱ ተፈጥሯልና፣ ከተፈጠረም በኋላ እንዳልተፈጠረ ሆኗልና... በአፍንጫችን ያለ ትንፋሻችንም እንደጢስ ነውና... ሰውነታችን እንደምጣድ ብልጭልጭታ ናትና..." ይላል ጠቢቡ!

...እና?

...በከንቱ ከተፈጠርኩ፣ ከመፈጠሬ በኋላ እንዳልተፈጠረ ከሆንኩ... ከአፍንጫዬም ያለ ትንፋሼ እንደ ጢስ ከሆነ... ሰውነቴ እንደምጣድ ብልጭታም ካጠረ... ስለምን የህይወትን ማጋጣነት ታገስኩ? እንደምን የርኩሰቷን ሰቀቀን በማኀሌት እንደተሟሸ እንደበት ቆጥሬ በብሉኮ ግርዶሽ ታጠንኩ?...

...የተፈጠርነው በግደሊሽነት፣ በእዝህባልነት እና በማን አለብኝነት ተራድኦ እንደሆነ መቀበል ነፍስን እንደሻህላ የሚበላ እውነት ነው። አንጋዳነት የእዚመኛው ፈጣሪ ብቸኛ ውርሳችን አይደለምን? የነፍሳችን ደጃፍ ዘርማንዘሩን በከዳ ወሰላታ ተክል የተወረረች ናት። የማናውቀው ስለክፋት የተፈጠረ ዕፅ ከቦናል። ሃከና አቃትማ፣ ደንደርና አሜኬላ፣ ኮሸሽላና ዶቢ፣ ቀርቀሃ፣ ቱልት፣ መቅመቆና እንብአይ፣ ሣማና ኩርንችት፣ አቃቅማና አምጃ... መኖሪያችን በጠማማ አፀድ የተዋጠች ሥርቻ ናት...

...የሥርቻ ውስጥ ክሱት ህይወት ነች። አምኜ መዳረሻ፣ ክጄ መነሻ ያጣሁ ንጡል...። ፈጣሪ እርን ያሉ መጥፎ ፈቃዱን ይከዳሉ። ከሱትነታቸውን የተቀበሉ ምንምነት ላይ ይወድቃሉ። አማክኘ ላይ መገኘት በሰው ከንቱነት ለሚያምን የመጠሳወል እረፍት ማጣትን ያስከትላል። ባለቅኔው ዊትማን እንዳለው ነው። "Be it life or death, we seek only reality" ህይወት ሆነ ሞት ለእኔ ምኔም አይደለም።



@OLDBOOKSPDF

ብቻ እውነታው ምንድነው? የሚለው ነው ጥያቄው፡፡ ከ"እግዚአብሔር ሞቷል" ይበልጥ "የሰው ልጅ ሞቷል" የሚለው ተስፋ መቁረጥ ጥው ያለ ዘላለማዊ አዘቅት ነው፡፡ ለዝንት አለም ሲወድቁ መኖር የዚህ ዘመን ፍርጃ ሆኗል፡፡

የንውዘት ጥሻዬን ፈራሁት፣ የሚያናግጥበኝ ሐሳብ ለማግኘት ወደ ድንኳ መጽሐፍ መደርደሪያዬ ማተርኩ፡፡ ሸንጠ መልካሞቹን መጻሕፍት ብቻ ካለሁበት ሆኜ ርዕሳቸውን ለማንበብ ቻልኩ፡፡ የመጀመሪያው ተተናኮለኝ፡፡ "IDIOT'S" አልሁን ለባጀሁበት የሀሳብ መናወዝ ምላሽ መሰለኝ፡፡ ደደብነቴን ያልተቀበለ ለደደቦች የተዘጋጀ መጽሐፍ ይገዛል? ቀጣዩ "What Good is God?" እግዚአብሔር ከመጥፎነት የተነጠለ ጥሩነት ይኖረዋል? ይሄንን የማይመስል መኖሸ ለማረጋገጥ የሚዳክር ደራሲ የፃፈው ነው፡፡ ግማሽ ደርሼ እንዳቆምኩት ትዝ አለኝ፡፡ "Before the Beginning" መጽሐፍ የምንነምንት "ቅዱስ" መዝገብ ነው፡፡ ዘፍጥረት አለው፡፡ ከቁስአካልነት ወደ ህይወት እንዴት ሽግግር እንደተካሄደ በማተት መላምቱን የዕውቀት ረድፍ ውስጥ ለመክተት ይጥራል፡፡ ሳይንስ ከተጨባጭነት ወደ ምናባዊነት አፈግፍጓል፡፡ በአጭሩ ልቦለድ ሆኗል የሚያስብል ደረጃ ላይ ነው፡፡

"መጻሕፍትህን ንገረኝና ማንነትህን ልንገርህ" የሚል ተዘበት ቢቃርብበኝ መልሴ እንደ አዳም "እራቁቴን ስለሆንኩ ፈራሁ ተሸሸግሁም" ይሆን ነበር፡፡

"ዕራቁትህን እንደሆንህ ማን ነገረህ?"

"ከእኔ ጋር እንዲሆኑ የፈቀድኩላቸው መጻህፍት አፈጣጠር ሀፍረት እንዳለበት ገለሁልኝ፡፡ ማፈርና መሸሸግ ሰው የመሆን ተቀጥላዎች ሆኑ፡፡"

አፍራለሁ፣ እሸሸጋለሁ፡፡ በይበልጥ በአጥቂነት ተማሪዎችን ለማሳወቅ እፈታቸው በቅም፣ አይግ ማፈር መደበቅ ይከጅለኛ ነበር፡፡ ማስተማር የምታውቀውን የመጠየቅ አለበት፡፡ "What is Philosophy?" ትላለህ ትንፋሽ ለጥተህ እንደዘራህበት ሁሉ በፈጣሪነት መታብይ፡፡ ተማሪው ሲሞክር ፈገግታ ታሸማቅቃለህ፡፡ የተማረውን በንፍና አግለህ ታበሳለህ፡፡ የተማሪና የአስተማሪ ጉዳይ የረድፍ ሰልፍ ብቻ መምህር ከሆንክ ተማሪህን አንብበህ ስትሰጠው ብቻ ታደርገዋለህ፡፡ ሁሉም ... ትሰለፋለህ...

@OLDBOOKSPDF

አንድ ቀን ከዚህ ሀፍረተቢስ መምህርነት ቆርጬ ሸሸሁ። ሴሚስተሩን እንደጨረስኩ የተማሪዎቹን ውጤት ለፕሬ ጠፋሁ። በዚያ ሰሞን አንድ ባዕድ ፊት ደጃፌን ገፋ አድርጎ ቤቴ ገባ። ደነገጥኩ።

"What's wrong?" አለኝ የፍልስፍና ዲፓርትመንት ሀላፊው ዶክተር አሮን ነበር።

"ሰለቸኝ" አልኩት፤ በእሱ አስተያየት ሰጪነት በትርፍ ሰዓት መምህር ሆኜ ስለተቀጠርኩ ስለቅ ቢያንስ እሱን ማማከር እንደነበረብኝ አስቤ ተፀፀትኩ።

"ምኑ ነው የሰለቸህ?" ከጉዝጓዙ ፊት ለፊት ያለ አልጋዬ ጫፍ ላይ ተቀመጠ። ሁልጊዜም የመልኩ እና የአማርኛ ዘዬው አለገጣጠም እያለኝ የጆሮዬና የአይኔን ቅንጅት እጠራጠራለሁ። ፈረንጅ ነው። ንግግሩ የጠራ ጎንደሬ፤

"ቢሮክራሲው"

"የምኑ ቢሮክራሲ?"

"በትርፍ ጊዜ መምህራን ላይ የተጣለው ገደብ። ክፍያው በየሴሚስተር መጨረሻ መሆኑ፣ ለእኛ ብቻ ቢሮ መከልከሉ፣ ተማሪ የምናማክረው ከመደበኛ መምህሮች ሲተርፍ መሆኑ..."

እውነት ይሄ ነበር ከዚያ ግቢ ብር አድርጎ ያጠፋኝ? እራሴን ጠየኩ።

"ከደሞዛችን ላይ ሰላሳ ከመቶ መቆረጡ"

ትክ ብሎ አየኝ፤ በድምዳሜዬ እንዳፍር ፈልጎ ይሆን? ጠባብ አፉ ያስአባቱ ጥይት እንዳጎረሰ ጠበንጃ የሚተፋውን አረር መሰል አማርኛ በእርግጠኝነት ጠበኩ። እንደሱ ሰው ሁሉ ለሙያው ሁለመናውን እንዲሰጥ ይጠብቃል። ለበጎ አድራጎት የቀረበ ህይወት እንዲኖረው ይሻል። በጉዳት ውስጥም ቢሆን ለሀገር መኖርን መፅናኛ ያደርጋል...

...እና...

"ትክክል እንዳልሆነ ይሰማኛል። ግን ዩኒቨርሲቲው ይሄንን መተዳደሪያ አድርጎ አፅድቋል። ከነባሮቹ ደብተሮች መካከል

@OLDBOOKSPDF

የመምህርነት ክብሩንና ጥቅሙን ለማስጠበቅ የተበተበው የተንኮል ህግ ይመስለኛል። ግን ምን ይሁን? እነሱ ስለገፈተሩ ምላሹ መገፍተር መሆን አለበት? አገርስ? ወገንስ? ሙያስ?..." ሀገርና ወገን የማይወክል ሉጫ ፀጉሩን ገለጥ ያለ እናቱን ለመሸፈን በመዳፉ አስተኛው።

"ዶክተር..." ስል

"ዶክተሩን ተወው፤ አሮን ይበቃል።"

ሁልጊዜም ወቃሽ ፊት አለው? ወይስ ምንድነው? የተንጮለጮለች አይኑ ከመነፅሩ ጀርባ ተወሽቃ ስትታይ ለትዝብት ያቆበቆበች ትመስላለች። ለነገሩ ቢወቅስም፣ ቢታዘብም ለዚች ሀገር ካለው ፍቅር አንፃር የሚያንስበት ሰው አይደለም።

"ዛሬ ልንገርህና ለመጀመሪያ ጊዜ በሀሳብ አንተን ያስተዋወቀኝ ፈጣሪ ነብሱን በቀኝ ያኑራትና ጠናጋሻው ነበር። ያኔ ይነግረኝ ከነበረው ነገር በመነሳት ለትርፍ ጊዜ መምህርነት recommend አደረኩህ። አሁን ደግሞ ትክክለኛ ምርጫህ መምህርነቱን መተው ከሆነ ባንተ lifestyle ውስጥ ገብቶ የመዘባረቅ mandate እንደሌለኝ እገነዘባለሁ። ይሁንና አንተን ከሚያስወቅሱህ ነገሮች አራቅ"

"እንዴት ያሉ ነገሮች?"

"ቅሬታ ያላቸው ተማሪዎች በራንክ አስጣጥህ ላይ አመልክተዋል"

"ታዲያ ለሬጂስትራር ውጤቱን አስረክቤአለሁኮ"

"ቢሆንም በግንባር ቀርበህ..."

መጀመሪያ ጠናጋሻውን ፈጣሪ ነፍሱን በቀኝ እንዲያኖራት ስ... ድንገተኛ ደራሽ ሳቅ ተናንቆኝ ነበር። አሁን ደግሞ በግንባር ቀርበህ ሲለኝ መቋቋም ተስኖኝ ሳቅሁ... በጥያቄ መልክ አየኝ።

"ይቅርታ አድርግልኝና አማርኛህ..."

አልጋው ላይ ቆነጥነጥ ብሎ ፀጉሩን ለተራቆተ እናቱ አለበሰ

"ይቅርታ..."

@OLDBOOKSPDF

"ግዴለም፤ ግዴለም፤ የጥንቱ አማርኛ ይማርከኛል። አዘውትሬ ነባሮቹን የታሪክ ሥራዎች የማነበው ገለፃቸውን የራሴ ለማድረግ ነበር። በአንተ ትችት መሰረት ጥረቴ ሳይዝልኝ የቀረ አይመስለኝም።"

"ይዞልሃል እንጂ"

ተሳሳቅን፤

"ሌላ ደግሞ..." ብሎ አንጠልጥሎ ተወው።

"ሌላ ምን?"

"የኢትዮጵያን ነባር እውቀቶች በአለማቀፉ የፍልሥፍና ሥልት ውስጥ አስገብቶ የመተንተንና "አርካኢቭ" የማዘጋጀት ህልም እንደነበረህ ስትናገር ነበር። እኔም ላንተ ቃል ባልገባም በውስጤ በዚህ ትልቅ ሥራ ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እንደማደርግ ደምድሜ ነበር። እንዴት ልታደርግ ነው?"

"እሱን ለመሥራት የግድ እዛ ግቢ ውስጥ..."

"ሳይሆን..."

"እህስ?"

"መረጃውን፤ I mean ቤተ መጻሕፍቱን ለመጠቀም... ለነገሩ እሱም ቢሆን ከውጭ ሆነህ..."

ዶክተር አሮን እኔን ለማግባባት ከሞከረበት ዕለት አንስቶ ብዙም በመምህርነት አልቆየም። ለቅቆ በደፈናው "ሌላ ጠቃሚ ሥራ የምሰራው አለኝ" አለኝና ወደ እንግሊዝ መመላለስ ጀመረ። ለረድኤት ድርጅቶች ፈንድ የማፈላለግ ሥራ ቀጠለ። ዘወትር በለንደን ጎዳናዎች ላይ፣ በፎቅ ጣካዎች ተውጦ፣ ለለዘብተኛ አላፊ አግዳሚ ባርኔጣውን አውልቆ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ምፅዋት ሲጠይቅ ይታየኛል።

"ከእኔ ጋር አትሠራም?" ሲለኝ

በልመና የተገኘውን መቀራመት ስለመሰለኝ ይቅርብኝ አልኩት።

"በአንተ Lifestyle ውስጥ ገብቶ የመዘባረቅ mandate የለኝም" ብሎ ሳይከራከረኝ ቀረ።

@OLDBOOKSPDF

* * *

አሁኔን አሰስሁ…

…ከጉዝጓዜ ተንኳትቼ መጽሐፍ መደርደሪያውን ቀረብኩ ከአሜጭርና ከቀጫጭኖቹ መጽሐፍት መካከል ጥቂት አመሀኞችን አገኘሁ፡፡ "What life should mean to you" የሚል ተጋፋጭ ርዕስ ያላትን መጽሐፍ ዶክተር አሮን ነበር ያመጣልኝ፡፡ ገና ርዕሷን ስመለከት ከዶክተር አሮን እንዲደርሰኝ የተፈለገ የሐበሻ ሽሙጥ ያለባት ስለመሰለኝ ያኔውኑ ጥንቅቅ አድርጌ አነበብኳት፡፡ መጽሐፏ ልበ ድፍን ግን ክስማና ጀግና ትመስላለች፡፡ መዘዝኳት፡፡

እውነት! ህይወት ለኔ ምን ማለት ናት?…

…ህይወት ከከንቱ ውልደት ወደከንቱ ሞት የመንገዝ ከንቱ መናወዝ አይደለምን? ስል ለራሴ ምላሽ ሰጠሁ፡፡

የመጽሐፉ ደራሲ ዶክተር አልፍሬድ አድለር ማንኛውንም ሰው 'የህይወት ፍቺው ምንድነው?' ብለን ብንጠይቅ ምላሽ የለውም' ብሉ ደምድሟል፡፡ የሰው ልጅ በተናጠል ያለበት ደካማነት ወደ ጋርዮሽ ስለሚገፋው ለብቻው ያለውን የመኖር ግብ ልብ እንዳይለው ተደርጓል፡፡

የሰው ልጅ በተናጠል ለመኖር ስለማይችል ጥምናውን በጫጫታ፤ ቁምነገሩን በጫዋታ እያድበሰበሰ ተላላ ህይወት ያስተናግዳል፡፡ ሳይኖር ይሞታል፤ ይሄ ተፈጣሪን ብቻ ሳይሆን ፈጣሪንም ኪሳራ ውስጥ የሚከት ጉዳይ ነው፡፡ በምፅአት ቀን፦

"እንደምን ኖረህ መጣህ?" ይለኛል ፈጣሪ፤

"እንደምን እንደኖርኩ እንጃ" እለዋለሁ፡፡

በመክሰሩ ተሀፅኖ እግዚአብሔር ያለቅሳል፡፡ ስላከሰርኩት እኔም አለቅሳለሁ፥ እንላቀሳለን፡፡

የመጨረሻው መላቀስ ይሆናል፡፡

አውራ ዶሮ ሲጮኽ ተሰማኝ፡፡ መለስ ብዬ ያልተሸገረ ድንበሬን ማተርኩ፤ ጭላንጭል አይታይም፡፡ የትኛውን ጎህ መቅደድ አይቶ አውራ ዶሮው ጮኸ? እን[illegible] በህይወት ግራ የተጋባና በሐሳብ የናወዘ አውራዶሮ ብትት እንዳለ በግምት መንጋቱን አወጀ፡፡

@OLDBOOKSPDF

እውራ ዶሮው ዳግም ጮኸ፤ ዳግም ተሳሳተ? በስህተት ውስጥ መመሳሰስ የፍጥረት ሁሉ ዕጣ-ፈንታ ሳይሆን አይቀርም። የፍጥረት ሁሉ ስህተት የተፈጥሮን ብሎም የፈጣሪን አለመሟላትና ፍፅምና ማጣት የሚያመላክት አይሆንም? ሠሪው በተሠሪው ውስጥ አይደለምን? "ታላቁ ተጠራጣሪ" በመባል የሚታወቀው Robert Ingersoll ምን ሲል ተናገረ? "An honest God is the noblest work of man" ሳቁ አመለጠኝ። ፈጣሪ ይሄንን የተፈጣሪ ድምዳሜ ሲሰማ አይስቅ ይሆን?

"ምን ምን አልክ አንተ?" ብሏል እግዚአብሔር ይሄኔ ንግግር አሳማሪው አሜሪካዊ ወደ እርሱ የሄደ ዕለት።

Ingersoll እየተልሞሰሞሰ ዝም፤

"አይዞህ አልተቀየምኩም፤ ካንተ ልሰማው ፈልጌ ነው"

Ingersoll ይበረታታል

"እህ? ምን ምን አልክ?"

"ሁነኛው አምላክ የሰው ልጅ አስደናቂ ፈጠራ ውጤት ነው ነበር ያልኩት።"

እግዚአብሔር ሣቀ፤ ሣቁን መንበረ ፀባዖት መሸከም ተሳናት፤ ወደ ኢዮር ወርዳ የካህናተ ሠማይን የደቅርታ መዝሙር አደናቀፈች። ወደ ምድር መጥታ የሚያስከካ መብረቅ ሆነች፤ ብዙ ሰው ላይ ባረቀች። ሰዎች ያደረባቸውን ድንጋጤ መቋቋም ሳይሆንላቸው ቀረ...።

እውራ ዶሮው ስህተቱን ለማስተባበል ሳይሆን አይቀርም ዳግም ጮኸ። ዛሬ እንደ ጴጥሮስ ጌታውን ሦስት ጊዜ የሚክድ ሰው ሳይኖር አይቀርም። መቼም እኔ አልሆንም፤ ብሆንስ? ከጉዳቱ ጥቅሙ ጎልቶ ታየኝ፤ ጴጥሮስ እንደትንቢቱ ሦስቴ ክዶ ካጠናቀቀ በኋላ ያወረደው የንስሃ እንባ ነፍሱን አላነፃችለትም? ሌላ ሰው አላደረገችውም? ያቺን የንስሃ እንባ ከእኔ ጭምር ይሄ ዓለም ተነፍጓል፤ ሦስት፣ ሠላሳዎስት ጊዜ ጌታውን ቢክድም እረፍት የምትሰጠውን የንስሃ እንባ አጥቶ ቅብዝብዝ ሆኗል።

መጽሐፉን ወደቦታዋ መልሼ ወደትዝታዬ ተንኳተትኩ። እልጋ ቢኖርም ስፍሬበት አላውቅም። የቤት ዕቃዎቹ ስረጅም ጊዜ እንደ

@OLDBOOKSPDF

አይነት ቡና የሚቀመጡ አንድ አይነት ናቸው። ቤት ስቀያይር እንኳን የዕቃዎቹን መቀመጫ አፋርሼ አላውቅም። ታዲያ ብዙ ጊዜ ከውስጥ ሃሳቤ ወይም ከእንቅልፌ ስነቃ የት ሠፈር የተከራየሁት፣ የትኛው ቤቴ ውስጥ እንዳለሁ ማወቅ ይሳነኛል።

ዛሬም እራሴን ፈተንኩ። አውራዶሮው ጊዜ እንጂ ቡና አልሳተም፤ እኔስ? የእውነት ጠፋኝ። የትኛውም ቤቴ ከየትኛውም መኖሪያዬ ልዩ ቅርፅና ድባብ የለውም። ስናገረው ለእኔም ውሸት እየመሰለኝ ነው፤ ግን እውነት ነው፤ ያለሁበት ጠፋኝ!! ይሄንን ለረጅም ጊዜ አድርጌዋለሁ፤ የምኖርበት ቤት ውስጥ ሆኜ የምኖርበትን ቡና አላውቅም። ካደኩበት ሠፈር አንስቼ ከተከራየሁ ወር ሳልሞላ የለቀቅሁትን ሁሉ ደረደርኩ...

...ጦሩታ ድልድይ? ሠባራ ባቡር? ባሊያን ሠፈር? ገዳም ሠፈር? አባኮራን? ጨዋተራ? ጠላፊ ሠፈር፣ ዘበኛ ሠፈር? ቃሚ ሠፈር? ቄስ ሠፈር? ጠበንጃ ያዥ ሠፈር? ጅሩ ሠፈር? ደጃችውቤ? ሠንጋ ተራ? በግተራ?...

ከራሴ ጋር እልህ ተጋባሁ። በተዋረድ የተከራየሁባቸውን ሠፈሮች ደርድሬ የመጨረሻው ላይ ለመድረስ ሙከራ አደረኩ፤ ከንቱ ሆነብኝ። በመጨረሻ ስለተሸነፍኩ ያልተሸኀረ ደጃፌን ከፍቼ ከቤቴ ወጣሁ። ወዲያው ቡናዋን ለየኋት-ቅንብቢት። በጨለማ ብርቱ ተጀቡና ቀረበችልኝ።

ቅንብቢት ከሚቹ ቀበና ወንዝ ጎን በቁመቷ ገና ብላ ተኝታለች። የቀበና ቢስ ገላ ሽታው ይጋረፋል። ቀድሞ ሲል ቀበና በህይወት ሳለ የልጆች የደስታ ምንጭ ነበር አሉ። ይዋኛሉ፤ እንቁራሪትና የእንቁራሪት ዓሣ ያጠምዳሉ፣ በፈጠረው ልምላሜ ሥር ከቢራቢሮና ከጥንዚዛ ጋር ይባረራሉ። ዛሬ ቀበና መካነ መቃብሩን በውስጡ አስናውና በቁም እንደፈረሰ ገላ ገና ሰገና ከሩቅ በመጥፎ ሽታ ይጋረፋል። ይብላኝ ለቅንብቢት እንደተረት ዓለም ፍቅረኛ አስከሬን ታቅፋ ለቀረችው።

ቅንብቢት ከቀበና ጋር የተዋደደችበት የአፍላ ዘመኗ መቶ አመትም የማይጠቅመው ነው አሉ።

"የቀበናን ውኃ ቀዳነው በወንፊት

አንተ ነህ ወይ እኔ የከዳነው በፊት" እያለ የዘፈነው አዝማሪው የፍታሐኔ አዚህ ግድም ከመምጣቱ በፊት በፊት፤ ደጃዝማች ቁንን የእኔ

@OLDBOOKSPDF

ነሀ እምዬ ምኒልክን ተከትለው ከቡልጋ አዲስ አበባ ሲመጡ አምስት ወንድሞቻቸውን አስከትለው ቀበና ላይ ሰፈሩ። ወደ ቡልጋቸው ለመመለስ እንዳቀበቀቡ ትድሚያ ድንኳን ነበር ያስጣሉ፤ ኋላ ላይ መቃኞ ቤት አሰሩና ለጊዜው ተቀመጡ። ምኒልክን ደጅ ጠንተው "መሄዱ ነው" አሉ።

"ከት?" የምኒልክ ጥያቄ ነበር።

"አገሬን፣ ቡልጋ"

"አይ ቁንን፣ እዛ ሌላ ጌታ አለህ ወይ?" ብለው ጃንሆይ የለበጣ ሳቁ።

ደጃዝማች ቁንኑ ቁርጣቸውን ሲያውቁ የቀበናን ጥግ-ጥግ ጎጆ አስታጠቁት። እስከ ጠንቋይ ማረፊያ ያለውን አቀበት በዓይን ገመድ እየመተሩ ለወንድሞቻቸውና ለአገልጋዮቻቸው አከፋፈሉ።

ግራዝማች ዋለሉ፣ ቀኛዝማች ቆርቾ፣ አዛዥ ገብረየሥ ኩርፋ፣ በጅሮንድ ግፋወሰን ሹምዬ... ሁሉ ከነጭፍራዎቻቸው እዚሁ ሠፈሩ። አካባቢው ሞቅ፣ ደመቅ ሲል ሠፈሩ በደጃዝማች ሥም "ቁንኒት" ተብሎ ነበር አሉ። ጃንሆይ ይሄን ሲሰሙ አሁንም በለበጣ ስለሳቁ ደጃዝማች "ወዲያውም የመጣንበትን ቡልጋን ያስታውሳል ቅንብቢት በሉት" አሉ፤ በዚሁ ፀና።

ውሽታሙ አውራዶሮ አልያዘለትም። ከእኔ በስተቀር በሠፈሩ የነቃ ሰው የለም። አንቅልፍ የላቸውም የሚባሉት ቤት አከራዬ እንኳን ሲያንኮራፉ ይሰማል። አንዳንዴ ቀድመውኝ ከጭለማው ጋር እየተሟገቱ እደርስ ነበር። ሲያዩኝ አይኑ ውኃቸውን ምን እንደሚነካባቸው እንጃ ያዩትን ተጠራጥረው ያጠራጥሩኛል።

"ምነው ልጄ፣ ፊትህ ልክ አይደለም፤ ተውተው እንጂ ለፊትህ አዘንለት" ይላሉ።

"ምነው? ፊቴ ምን ሆነ?"

"ሞለል ብሏል፣ አይታወቅህም?"

ያን ሰሞን ቢያንስ ለሁለትና ለሦስት ቀን ፊቴ ተሟሎ የማየው ሁሉ ይዛባብኛል። በእጄ ፊቴን ከመነካካት አልፌ መስታወት ተውሼ እየዋለሁ። አልተሟሰልኩም፤ ግን አላምንም።

@OLDBOOKSPDF

"ዋልጂ ፊት እንደው ድንገት፣ ከመሬት ተነስቶ በአንድ ጎን ድልድል ብሎ አበጠ፣ ዋ-እቴ ያየሁት መከራ! በስንት ስለት መሰለህ እንደተሚሰለ ያልቀረው:: ለፊትህ እዘንለት::"

በኢህአፓ ጊዜ ለሞተ ልጃቸው የገቡለትን ስዕለት አሁንም አላቋረጡም:: ልጅ በመሀል ከሞተ የስዕለት ውል አይፈርስም?

"ስለስለት ስለልደታ·ማሪያም! ልደታ·ማሪያም ስለታችሁን ትስማላችሁ" እያሉ ዶቂት ቃርመው ለቤተክርስቲያን አስቀዳሾች አነባበሮ ያድላሉ::

ኮንኪናዋ እህታቸው ብቻ ይቃወሟቸዋል:: ዘወትር የሚፈለትቁትን ጥጥ እርግፍ አድርገው ጥለው ጥፍጥሬ የገባበት በሚመስለው አፍንጫቸው ይንኮናኮናሉ:: ፊተ ሰፊ፣ ሆደ ሰፊ፣ ደረተ ሰፊ፣ እግረ ሰፊ ናቸው::

"የግራዝማች ዋለሉ ያለህ፤ ምን ሆነሻል? ባደለሽ ልጅሽን ባተረፈልሽ ነበር፣ በሞተ በስንት አመቱ ስለት ታስገቢያለሽ? ኧረ ወዲያ!" ጥጣቸውን ያነሳሉ::

እንደ አባቴ ጥይት ጥፍጥሬዋን ሆንብለው በአፍንጫቸው ስበዋት ይሆን? ሰርናቸው ውስጥ ተወትፋ የቀረችው?

አከራዩ ተነስተው ፊቴን እንዳያሚልሉብኝ በመፍራት ተገላመጥኩ የሉም::

በፊራ ተባ ደጃፌን ለቅቂ የጉብታ ድንበሩን ወዳስከበረው ግቢ ወጣሁ:: ሰጋ ጨረቃ በተሃ ብርሃኗን ትታለባለች:: የቅንብቢት ዳገት ቲፍ-ብሎ ሞልቶ ማንዠቅገርቅ የጀመረ የወተት ሙሙ መስሏል:: ኮረታማ የመንገዶቹ ስብጥር የጨው ፊለግ የተወ የደሃ እንጀራ ያስታውሳሉ:: "ብቅእንቅ" ድረስ ሁሉም ነገር እየተጭለመለመ ይታያል:: ከዚያ ወዲያ ከልደታ ማሪያም እስከ "ጠንቋይ ማረፊያ" ድረስ ያለው ጥርጊያ በእዘቅትና በአረህ ተውጧል::

የቅንብቢትን ክፍልፍል ሥፍራ አሲያየም ሳስብ ህይወቴ ተረት-ተረት የሆነ ይመስለኛል:: ብቅ እንቅ... ድሬ...ልደታ... ጠንቋይ ማረፊያ... ግራዝማች ለጋስ ሠፈር... ቀኛዝማች ቆርቾ ግቢ... ወሎ ሠፈር... ዋሻው ተክለኃይማኖት... እንቆርጫ... ደብረሃል ሚካኤል... የካተራራ... የፍ[illegible] መዝገብ ወደሆነው ሰማይ እየቀረቡ

@OLDBOOKSPDF

መሄድ... ሄራን መላዕክት ለሰው ልጆች ሁሉ ምህረትና ይቅርታን ሲለምኑ ለማድመጥ ጆሮን እንደፈረስ ኮቴ መፎገር... የምድር ባጥ...

...እዚያ ላይ አዲስ አበባ የፈሳሽ መስፈሪያ ባዶስ መስላ ትታያለች፡፡

ሲጃራ ሸተተኝ፡፡ ናትራ ናት፡፡ በሌሊት ትንባሆ የመለኮስ ሱስ ያለባት እርሷ ናት፡፡ አንዳንዴ የማይሸጎር ደጃፌን በሌሊት ገፋ አድርጋ "ሴሽ አለህ?" ትለኛለች፡፡

"የምንሴሽ?"

"ሲጃራ"

"የለኝም" ካልኳት ከተስፋ መቁረጥ ጋር ትቀመጣለች፡፡

"አለኝ" ካልኳት ተቀብላኝ ትሄዳለች፡፡ "የሞተ ግንድ ላይ ተቀምጣ፣ አንድ እግሯን አጥፋ ሌላውን ለምጣ፣ አይኗን እያጨነቆረች ትንባሆዋን ትለመጥጣለች፡፡ ከሄድኩባት ሲጋራ የያዘ እጇን አንስታ ጨረቃዋን ትጋብዘኛለች፡፡ እናቴ ስነጫነጭ "የማይናገረውን እንጀራ ብላ" እንደምትለኝ፡፡

"የማትናገረውን ጨረቃ እይ"

በአፍንጫዬ ተመርቼ ሳላያት በፊት የጭስ ምሪቴ ተቋረጠ፡፡ ቀን ከሆነ ደግሞ የሌሊት ልብሷን እንደለበሰች ነው፡፡ እግሯ እንደወይን ጠጅ የሰው ልጅ ደስ ያሰኛል፡፡

"አልዩ"

"ወዬ ፈተናዬ" እላታለሁ፡፡

"ለምን ፈተናዬ ትለኛለህ?"

"አንቺን ሳለማስቀየም እንዴት እንደምፈተን ባየሽ፡፡ አሁን እያሰብኩ ድንገት ስታቋርጪኝ..."

"አንተም ሀሳብ አለብህ? አቤት እኔ ያለብኝ ሀሳብ? ከዚህ ቤት ይበልጣል፡፡"

@OLDBOOKSPDF

"ለምን ነበር የመጣሽው?" ንግግሬን ማለዘብ እፈልጋለሁ። "አንድ ነገር ልትጠይቂኝ ነበር" ፀሐይ ከበስተኋላዋ ከደጃፉ ባሻገር መሬት ላይ ተነጥፋ ከስስ የሌሊት ልብሷ ጋር ትንቅንቅ ይዛለች።

"እ-እዎ፣ ቴፕ አለህ?"

"ብዙ ጊዜ ጠይቀሽኝ የለኝም ብዬሽ ነበር"

የሌሊት ልብሷ ወገብ ላይ ባለ የላስቲክ ሽብሽብ አጣብቃ የያዘችውን እሮጌ የቴፕ ካሴት ከር ታወጣለች።

"ብዙዬን ላዳምጣት ነበር፣ ምናለ ቴፕ ብትገዛ?"

"አሁን አልችልማ! ወደፊት..." (እገዛለሁ እንዴ? እንጃ!)

ትወጣለች።


የዞረበት አውራ ዶሮ ለአራተኛ ጊዜ ጮኸ። ለዚህ ዶሮ "ዶሮ ሳይጮህ" ማለት ስንት ሰዓት ነው? ኩኩላው እንደተበላሽ የተፈጥሮ ሰዓት ፍጡርን ሁሉ የማሳሳት አቅም ሳይኖረው ይቀራል? ለስህተት ያለው ትጋት።

እምስተኛው የዶሮ ጩኸት ላይ እዚያ ወዲያ እንቅስቃሴ ያየሁ መሰለኝ። በሲጋራ ፈልግ ያላገኘኋትን ናትራን... አይደለችም፣ ቋክ ነው። እሮጌው ውሻ በዶሮው ጩኸት ተታሎ ቀና አለ። ከውሻው ጋር በደንብ እንተዋወቃለን። ስለእርጅናው ተፈጥሮ በእኔ ውስጥ ርህራኄ እንዳሳየችው ያወቀ ውሻ። ፊቱ ዘብዘብ ቆዳው መንጋጭላው ላይ ተልጦ ወርዷል። የአይኑ ታችኛው እቃፊ ወደታች የዘነበ ነው። የፊት እግሮቹ ላይ በእገጩ ግርጌ እረፍ ሲል ያዘበዘበ ቆዳው ፊቱ ስር ይሰበሰብና ቀሰስተኛ ፈገግታ የከጀለው ይመስለኛል።

ገንዘብ የነበረኝ ጊዜ አልጨክንበትም ነበር። እንደቋክ ሆኖ ብሎ የተፈጥሮን ብያኔ መቀበል የሰው ልጅ ተነፍጓል። ከተፈጥሯችን ከውስጥ ተፈጥሮን ቀምሎ አውጥቶ ሰው ሠራሽ ምድረበዳንን እስፍኗል። ተፈጥሮን የማያስጠጋ የተፈጥሮ አካል ሆነናል።

እሁሁሁሁ!! ደከመኝ፣ ከበላሁ ስንት ቀንና ስንት ሌሊት ሆነኝ?

@OLDBOOKSPDF



# ምዕራፍ ፫

"ሠላም ለድሃው አልአዛር" ፊዕሞ የማይዘጋ ደጃፌን ገፋ አደረገው "ሠላም ድሃው አልአዛር ለወደተብሽ የባለፀጋው ታዛ"

ደጃፌን ሲፋጭር የቆየው ሸባ ውርጭ ረድ ሠርዌን ታክኮ ቤቱን ናኘው።

የረድ ሠርዌን ሁኔታ ስመለከት ዓለም አንድ አሰቃቂ ድራማ ፍፃሜ ላይ የደረሰች መሰለኝ። ቅዝቃዜ ሥጋ ለብሶ እነሆ እፊቴ ቆሟል። ለቀናት መቀመቅ ወርዶ ድንገት ጌታው ብቻ በሚያውቀው መጠራት አፈሩን አራግፎ የተከሰተ ሆኖ ተሰማኝ። ውርጩ የሞት መንፈስን ወክሎ ህይወትን ይፃረራል።

ከሠሌን የተሰራ አኩፋዳውን አውርዶ አልጋው ጫፍ ተቀመጠ። አፈር አፈር ሸተተኝ።

"የት ጠፋህ?" አልኩት

"የኔታን ወደ ብሔረ ብፁአን ሸኝቼ መጣሁ። ገዳም ስናቋርጥ ሌላ ገዳም፣ ገዳም አልፈን ሌላ ገዳም። አገራችን ገዳም ብቻ አይደለች እንዴ? በኋላ የብሔረ ብፁአን መሳፈሪያ፣ ሰማይ የሚደርሰው ዛፍ መጥቶ እንደግመል ሲያጎነብስላቸው አባቴ እንደቅዱስ ዞሲማስ ተፈናጠጡ፣ ዛፉ እራሱ ለሌላ ዛፍ እያቀበለ፣ ከዛፍ ዛፍ እየተጋቡ ሲሄዱ እንደላንቲካ ተመለከትኩ። 'ኢይመውዖ ለሚዕ ለርእይ' የተባለው ደረሰ። መስማት ማየትን አያሸንፈውም። አሁን ስነግርህ የቃዠሁ ያህል ነው።"

ከጉዝጓዜ ተነስቼ ክፍት የተተወውን ደጃፍ መለስ አደረኩት።

"ለማን ይነገራል? ቢነገርስ ይታመናል? እሆሆይ!"

ወደጉዝጓዜ ተመለስኩ። የላሳችውን ብርድልብስ ስቤ እግሬን አለበስኩ። ረድ ሠርዌ [illegible] @OLDBOOKSPDF ጠራው አገር ሄድኩ ከሚል ይልቅ

እንደ አቤሮን ምድር ተከፍታ ውጣኝ ነበር ቢል ባመንኩት ነበር። ከመከሰቱ የተነሣ ቸንቹ አፍጥጧል። ዓይኖቹ ተሸሽገዋል።

"ይሄ፣ ያልከው ቦታ የት ነው?"

"የቱ?" እንደመባተት ብሎ።

"አባትህን የሸኘህበት"

"እሱማ ብሔረ ብፁአን ይሉታል አንዳንዶች፣ ሀገረ ብፁአንም የሚሉት አሉ። እግዚአብሔር ካላቅናናልህ የማትሄድበት የፃድቃን፣ የሰማዕታት መኖሪያ ነው። እንግዲህ እግዚአብሔር ሲያብቃቃልህ ሁሉ የተመቻቸ ይሆናል። አራዊቱ ገራም ሆነው ትፈናጠጣቸዋለህ፣ ማዕበሉ የባህር ፈረስ ሆኖ ያደርስሃል፣ መንገዝገሩ ብዙህ ነው።"

"እዚሁ ምድር ላይ ነው?"

"ተደበቀ እንጂ አዎ፣ ከአምስቱ ዓለማተ መሬት አንዱ ብሔረ ብፁአን ነው። እንደገነት የተሸሸገ የፃድቃን መኖሪያ ነው። የሰው ብልጠት ሆነ የሳይንስ ዕውቀት አይደርስበትም። እስካሁን ካለንበት ወደብሔረ ብፁአን የሔዱት ሁለት ሰዎች ናቸው። ቅዱስ ዞሲማስ እና ሐዋርያው ማቴዎስ ብቻ።"

ጠማማ ወንጀል መርማሪ ብሆን ኖሮ ሪድ ሠርዌ አባቱን ገድሎ ቀብሯቸዋል እል ነበር።

"ባለፈው ተጣልታችሁ ነበር"

ቀና ብሎ አየኝ። መመለስ የፈለገ አይመስልም።

"መተሃቸው ነበር" ምን አደረቀኝ? የአፈር እምድ መስሎ ቀና አለ። ልወነጅለው ነው እንዴ?

"በምን ታርቀሃቸው ሸኘኻ አሉህ?" ቤት የገባው ውርጭ ሲታገለ የሪድ ሠርዌ አፈር-አፈር መሽተት ገነነ።

"ሦስት ቀን፣ ሦስት ሌት ተከራከርን። እኔን በመሣሣታቸው ትኮነናለህ አሉኝ። እኔ ምን ሲደረግ አልኩ። አክብር አባከወ እመለ የሚለውን ጨዋኳ የማይስተውን የጨዋ ህግ ጥሰሃል አሉኝ።

@OLDBOOKSPDF

"እኔ የመንፈስ እንጂ የሥጋ ብቻ ልጅዎ አይደለሁም" አልኩ።

"ቢሆንስ? ትቀጣለህ አሉኝ።

ሊቁ "'ወዑንዑ ውስተ ኅድዓት' አላለም?

"ቢባልሳ..."

"በዕድሜ ብዛት ገደፉ፤ እንኳን በተዓቅቦ ሊፀኑ፣ በጥምጥምዎ ማማር፣ በእንበለ ክብር ማለሉ 'ማዕረግ ሉዓላዊ' እና 'ማዕረግ ታሕታዊ' ተሳትም እንደ አዲስ ደብተራ ሁሉን አክብሩኝ አሉ።

"እናሳ ያልከው ቢሆን እንኳ ረቂቅ ፀሐይ ከሚሆን ከጌታ ብርሃኑ ፀጋን እንፈጋለሁ እንጂ በወለድሁት እዳኛለሁ? አባትነቴንስ እገፈፋለሁ?...

"...ተከራከርን፣ ተከራከርን፣ ተከራከርን... ምኑ ቅጡ! መጽሐፍ ሁሉ ተዘረጋ... በመጨረሻ አቡነ ኢየሱስ ሞአ ላይ ረጋ።"

"እንዴት?" ከቀልቡ መሆኑም አጠራጠረኝ።

"አቡነ ኢየሱስ ሞአ አቡነ ተክለሃይማኖትን 'ልጄ ስትሆን አባት ሁነኝ' ብለዋላ። ጠቀስኩ። ለኔና ለየኔታ መለኮት ያወረደው መገላገያ ሆነን። ከሦስት ቀን በኋላ የነታ ዝም አሉ። እርምሞአቸው አስፈሪ ነበር። ቆይተው ከተግሳስ ማነብነብ ጀመሩ።

". . . . . . . .

ወእንተስአ ዘትቤ ዘንተ ትብልበር ስከ ኅስማተ ብዙኃተ
ወእመ ኢወደሱከ ትትመዓዕ ወታንጎረጉር
እያእመርከኑ አፍቁር ከመ አንተ ትትዋነደ
በእንተ ግብር ዘአይደሉ ደትዋነዩ ባቲ
ወባሕቱ ንሕነስ ናሴስል ውዳሴያተ እም
ካልኣኒነ በጸሕቅ ወትጋህ እንዝ ንፈቅድ ፍድፋዴሃ
ወእኮ በጸሊአ ወደጎኖ ኪያሃ
እላ ፈቂደነ ሐታቲሃ
ወኹሉ ግዕዝነ ዘሀሎነ ባቲ ለንዒወ ክብር
ወእኮ ለአድምዖ ጸድቅ
ወበእንተ ዝንቱ እሰመኮሉ ግብርነ ከንቱ ውእቱ
ወእልቦቱ ረባሕ
. . . . . "

@OLDBOOKSPDF

በረጅሙ ተነፈሰ! ከአፍንጫው የአፈር ብናኝ እየናገ ሲናኝ ያየሁ መሰለኝ። አጠገቡ ያኖራትን አኩፋዳ በመሃል እጁ እየዳሰሳት ቆየ።

"እናም ባርከኝና ልሂድ አሉኝ።" ብሎ ድንገት እንባው ተዘረገፈ። ሲያለቅስ ቸንቹ የበለጠ ፈጠጠ።

መንፈሴ ተንቀራጠጠ! የምለው ጠፋኝ።

"እግዚሃር በዕድሜኝ የባረኩት. . .ስል አቋረጡኝ።

"ያንን ሁሉ ዘመን ብኖርበት ያንተን ያህል አላጠኩበት። ይልቅስ ባርከኝ! ልጅ ስትሆን አባት ሁነኝ ጉልበትህን አትንፈገኝ! መተናነሴን ተቀበለኝና ባርከኝ አሉኝ። ማሸነፍ ውስጥ መሸነፍ፣ መሸነፍ ውስጥ ማሸነፍ እንዳለ ያኔ ገባኝ። የትኛውም የድል በዓል ጀርባው የሽንፈት ንክኪ አለው።"

ለመጀመሪያ ጊዜ ረድ ሠርዌ ሲያለቅስ አየሁት። ድርቅ ድርቅርቅ ካለው የእብደት ንኪኪ ይበልጥ ልብ የሚሸነትረው እንባው ሲወርድ ማየት እንደሆነ አወቅሁ።

"እና ጉልበትህን. . . . ." ስል...

በሩ ተበርግዶ ናትራ ገባች።

"ሴሽ የላችሁም?"

ለወትሮው ቢሆን ረድ ሠርዌ "አቤት! ሥምሽን እንዴት ቻልሽው?" ይላት ነበር።

"አይከብድም!..."

"አይከብድም?" በሽሙጥ

"እም! ሲጠሩኝ ዞር እልበታለሁ፣ እመዘገብበታለሁ፣ እተዋወቅበታለሁ... ቢቃ! ምን ይከብዳል?"

"ምንም! ለማያውቅ ምን ይከብዳል? ዕዳው ሲያውቅ ላንቺ ስም ያደረገው እንጂ..."

@OLDBOOKSPDF

"ቤሽ የላችሁም?" ደግማ ጠየቀች። ለአለባበሷ ቅጥ እንደሌላት ባውቅም የዛሬው ባሰ። አጭር ርዝ ቀለም ያለው ስስ የሌሊት ቀሚስ ጡቷ መካከል የአበባ ሽብሽብ ሆኖ ቀሚጭን እጥፋቶች እየተዝለገለጉ በመውረድ ጭኗ ጋ አድርሰው ይቆማሉ።

"ዛሬ ደሞ በቀን ልታጨሺነው?" አልኳት።

"አይ ለሌሊቱ ነው። ሰሞኑን ጨረቃ ሙሉ ናት። እሷን እያየሁ ሲጋራ ሳጨስ ልዩ ስሜት ይሰጠኛል። ሌላ ጊዜኮ አላጨስም።"

"እኔ የለኝም" ተንታርኬ፣ ተንታርኬ የለኝም ማለቴ ከነከነኝ

"የቆሎ መምህርስ?"

አይባልም ብላትም ስላልሰማችኝ ትቻታለሁ። "የቆሎ ተማሪ ይባል የለ? የቆሎ ተማሪውን የሚያስተምረውስ?" እውነቷንኮ ነው።

ረድ ሠርዊ የሰሌን አኩፋዳውን ፈታትሾ እንዴት የተጣጠፈችና በርጥበት የራሰች ብር አውጥቶ ሰጣት።

"ናይስ" ብላ ሄደች። ለጥቂት ጊዜ የሌሊት ልብሷ ቀለም ከእኛ ጋር ቆየ፤ በውስጡ ዋኘን። ቀለሙ ጋብ ሲል የረድ ሠርዊ አፈር እፍንጫችን ላይ መደነሱ ተገለጠልን።

"ከየገዳማቱ ችምቻሚ ሰብስቤአለሁ። ወዲያውም ቡራኬ ነው።" አኩፋዳውን ከፈተ።

ችምቻሚ ሲል ችምችም ብሎ የበቀለ እንዳች የገዳም ውስጥ ምግብ ጠበኩ። ብድግ ብሎ የአኩፋዳው አፍ አፌቱ አቀረበው። እጄን ሰድጄ የማላየውን ነካካሁ። እንደቂጠማ የተቸመቸመ ሳይሆን ጥሬ-ጥሬ ነገር ሆኖ አገኘሁት።ለምርምር ያህል ቆነጠርኩ።

"ይሄማ ቆሎና ንፍሮ አይደለም እንዴ? ስሙን ስትለውጠው. . ."

"ችምቻሚ ታዲያ ምንድነው? ጥሬ እንደልብ ከተበላ ሥሙ ነው፣ ይልቅ ብደንብ ዝገን።"

ዘገንኩ፣ ከፉኛ እርቦኝ ነበር። ያለሀፍረት አፌ ውስጥ ሞጀርኩት። ጥርሴ እንደ እግር ይደነቃቀፍ ጀመር። እንዱሽዱሽ ባቄላ፣ እንግርግርብ ሽንብራ፣ የለዘዘ የሰነፍ ቆሎ፣ የአተር ንፍሮ፣ ተፈልፍሉ

@OLDBOOKSPDF

በፈነዳው የተቆላ በቆሎ እሸት... በረሃብ ጊዜ የማገኛትውም ምግብ መጣፈጥ ብዙ የመብላት የተፈጥሮ ግፊት እንደሆነ ገባኝ።

አኩፋዳውን አቀረበልኝ አፈስኩ...

አቀረበልኝ...

...አፈስኩ።

ለመብላት ባሳየሁት ስስት ሰው መሆኔ አልሰማኝ አለ። ሰውነትና ህይወት ለየቅል ናቸው። ሰው እና እንስሳት የሚለዩበትን ነጥቦች በዝርዝር ማተት አንዱ ፍልስፍና ትምህርት ዘርፍ ነበር። እንስሳት ቀጥተኛ የተፈጥሮ ጥገኞች ሲሆኑ የሰው ልጅ ግን ከተፈጥሮ ተገንቶ ተፈጥሮን የራሱ ግኝት ለማድረግ የሚጥር እንግዳ ፍጡር ነው። ተፈጥሮ እንደ ረድ ሠርዌ አባት 'ልጅ ስትሆን አባት ሁነኝ' ብላ የሰውን ልጅ ጉልበት በፈቃዷ ስማለች እያልኩ አስተምሬአለሁ። የሰሞኑ ሁኔታዬ ቀድሞ ቢደርስብኝ ኖሮ ይሄንን አስተምህሮ አፈን ጥልቼ ለተማሪዎች አቀብል ነበር? የሰው ልጅ የኑሮ እቅድ ከተፈጥሮ እጅ ወጥቶ በራሱ በሰው ብቻ የሚመራ ነፃ ነው? የሰው ልጅ ፈጠርኩት የሚለው የመኖር ዋስትና ተፈጥሮ ለእንስሳት ከሰጠችው የመሉ ምግዚትነት አስተዳደር የተለየ አስተማማኝነት አለው? ካለው እኔና የቀሩት ሁሉ ለምን ተራብን? ሰው ያመረተው ይቅር፣ ተፈጥሮ በጥሬው የቸረችኝ ፋንታችን የት ደረሰ?. . .

አቀረበልኝ. . .

. . .አለማፈስ አልቻልኩም። እጄን እስከ አኩፋዳው ግርጌ ድረስ በመስደድ የችምቻሚውን መጠን ለመለካት ሞከርኩ። በረሃብ መተማት ያስከተለው ሥጋት፣ ስስት፣ ቅትት... እንደሆነ አላጣሁትም ግን ግፊቱ ከራሴ የተደበቀ ሆኖ አስቸገረኝ።

ረሃቡ ጋብ ሲልልኝ ሰው መሆኔ ተመለሰልኝ። ረድ ሠርዌ እየበላ እንዳልሆነ አየሁ። ቸንቹ ከከንፈሩ ዘልቆ እስኪታይ አልተራበምን? ያንን የመብላት የተፈጥሮ ግፊት እንዴት ተቋቋመው? የሚበላ ለመምሰል አንድ ፍሬ ባቄላ አውጥቶ አፉ ውስጥ ያንገዋልላል።

ዝም አልኩ፤ በዝምታዬ ውስጥ ስንቀዋለል በረድ ሠርዌ ተገኘሁ... አኩፋዳውን ገፋ አደረገው።

@OLDBOOKSPDF

'...ከማሁ ጤስ ዘኖዓርግ እምውስተ ከርሥ ይሜውራ ለጥበብ እግዚአብሔር ልዑል እምነ ነፍስከ።" ይለዋል ማር ይስሃቅ።

የበሰለ ፈገግ ሲል ቸንቹ ፈጠጠ!

"እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ማስራብ እንደ ዘዴ ይዞታል። አብዝቶ መመገብ የሐልዮ ኃጢያት መቀስቀሻ ነው ተብሎ አረግቷል። ጥጋብ ከእግዚአብሔር የምትገኝን ጥበብ ከሰውነትህ ይሰውራታል ይላሉ አባቶች።"

የምሰው ጠፋኝ፣ በአበሳሌ ታዘበኝ? ወይንስ የተፈጥሮን ምስጢር ገለጠልኝ?

"ወዘያፈቅር ለሥጋሁ ኢይረክብ ጸጋሁ ለእግዚአብሔር፣ ይልብሃል ማር ይሳቅ። ሰውነቱን የሚወድ ሰው ጸጋ እግዚአብሔርን አያገኝምና ማለቱ ነው።"

የምግብ እጦትን የምንከድበት መጽናኛ መሆን አለበት። የቸምቻሚው ቅራት በየጥርሴ መካከል ተሰግስጎ ነፃነት አልሰማህ አለኝ። ሬድ ሁርዊ ሥጋው የደከመ ነፍሱ የታከተ ይመስላል። እግሩ ወደታች እንደተንጠለጠለ በጎኑ ጋደም አለ። ጥቂት ቆይቶ የሰሌን አክፋዳውን ሳብ አድርጎ ተንተራሰው። ትንሽ ቆይቼ እግሩን ከነጫማው ወደ አልጋው ላይ አውጥቼ ከቤት ውልቅ አልኩ። ከፍልጥ እጥሩ ላይ ስንጥር ለመስንጠር አይኔን አንቀዋለልኩ። ፍልጡ ተንጋዶ ወድቆ መገላገያውን ይታብዛል። አቧራ! ዝናብና ፀሐይ ተፈራርቆበት የእድፍ ብልክ ደርቧል። ስንጥሮቹን ሁለት ጊዜ ገልፍፌ የተሻለ ንፁህ ለማግኘት ሞከርኩ። ሆዴ ቅራታ ማሰማት ጀምሯል። አኩፋዳ የተሳተለውን ሆድ አንድ ያደርገዋል? በዚህ ላይ ሆዴ የሰመደውን ረሃብ ማስታመም ሳላናጥበው የቀረሁ አይመስለኝም። ረሃብ ድንኩላ ፈረስ ነው! ከነራኹው እንዳለኝህ ታስግረዋለህ። በረሃብ የተጫለሁትን ዓለም አሁን ይቅርታ ጠይቄ መታረቅ አሰኘኝ።

ጊዜው ተሲአት ይመስላል። ቅንብቢት ድስት ተራ መስላለች። ብዙ አዳዲስ ቤቶች ተራራዎቿን እየወረሩ ነው። ነገ የልደታ ካልሆነም የተክልዬ ክብሩ በአል እንዳለ በታቦታሩ ለማኞች በታ መያዝ አውቅሁ። እዚህ አገር ሰራተኛው ሳይሆን ለማኙ ነው ትጉ። ጃክ በሁለት የኔብጤዎች መካከል ተኝቷል። በቀሰስታ ቀና ብሎ አይቶኝ መልሶ እግሮቹ ላይ አገጩን አስደገፈ። ፊቱ ዘብገዘብ ቆዳው መንጋጭላው ላይ ቀልጦ ወረደ። የትዝብት ፈገግታ ያየሁበት መሰለኝ።

@OLDBOOKSPDF

እርግፍ አድርጌ ጥርስ መጎርጎሪያዬን ጣልኩ። ጥዬው በመብላቴ ተፀፀትኩ? ጥሬ ከብስል ለመብላት የተፈጠረው ሰው ነው። ለመብላት ያልተዘጋጀንበት ነገር የለም ማለት ይቻላል። ጥሬ-ጥሬ፣ ቅጠላቅጠል፣ ፍራፍሬ፣ ሥጋ፣ እንቁላል፣ ወተት፣ ማር፣ ጣዝማ፣ የሚበረውን፣ የሚዋኘውን፣ የሚሽከረከረውን፣ ሥራ ሥሩን፣ እህሉን…

ለመሆኑ

"ምድርን መኗት" ነው የተባልነው ወይስ "ምድርን ብሏት?" የሰው ልጅ ምድርን ብቻ ሳይሆን ሰማየ ሰማያቱንና ዕድቱን በሚበላ መልካም ነገር እየሞላ ያልማል። ከህይወት እስከ ሞት፣ እንደገና እስከወዲያኛው ህይወት መብላት።

ጃክ ድንገት ብድግ ብሎ ወደ እኔ እቅጣጫ ለመምጣት መሽመድመድ ጀመረ። ሲወቅሰኝ? አንድ በወል ያለየሁት ዕለት "ጃክ እባላለሁ" ብሎ የተዋወቀኝ ይመስለኛል። ድምፁ እንደ ቢቢ ጆንስ የጎረነነ፣ የብሉዝ ሙዚቃ መዝፈኛ አይነት ነው።

ጥላ ፈልጎ ኖሮ እንዲት ሰንሰል ስር ጭንቅላቱን ብቻ ወሸቀ። ጀርባው ለዘመናት የተጠበጠበ ከበሮ ይመስል ፀጉሩ ረግፏል። ሰው ቢሆን ስንቱን ባማረረ ነበር። ፈጣሪውን፣ ጡረታ ድርጅቱን፣ ልጆቹን፣ የልጅ ልጆቹን፣ ሚስቱን፣ ዘመድ አዝማዱን… የሰው ልጅ ብቻ ነው መጥፎ ዕጣፈንታውን ሌሎች እንዲጋሩት የሚሻ….

"ምነው ልጄ" አሉኝ አከራዩ ከበስተኋላ መጥተው ምነው፣ እረ ፊትህ ልክ አይደለም፣ እዘንለት እንጂ" ስለት መሰብሰቢያ ቀረጢት አጣጥፈው በጉያቸው ይዘዋል። ለወትሮው የማይዙትን በትር ከፊታቸው አስቀድመው የሚረግጡትን ይጠቁማሉ…

እንግዲህ ሰሞኑን ፊቴ የተሟለለ እየመሰለኝ ልሰቃይ ነው። በመስታወት አይቼ እንኳን አላምንም።

"ደግሞ ሥራ ፈትሃል፣ ምን ይሁን ብለህ ነው በወር ሁለቴ ቤት ኪራይ የምትከፍለው? ተው፣ አንተ ልጅ ተው ለኪስህ እዘንለት። የችግር ቀን ይመጣል፣ ዋ-እቴ!!" ሄዱ።

ማን መጥቶ የቤት ኪራዩን ሰጥቷቸው ይሆን? ዶክተር አሮን? ሬድ ሠርዌ? ወይስ?…

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፬

"ድሃው አልአዛር ተኛህ?" አለኝ ለሦስተኛ ጊዜ ቀስቅሶኝ።

"አዎ" ስለው

"ትኝት፣ ትኝት?"

"አዎ" ለመነጫነጭ እየከጀለኝ።

"ተኛ"

ማታ ያንን ችምቻሚ ቻምችሜ በሆድ ቁርጠት ልሞት ነው። የአከራዬ እህት በጥጥ ፍሬ በተደፈነ አፍንጫቸው እየተኮናኮኑ ግማሽ ስኒ አረቄ ሰጡኝ። ሆዴን በጉልበቴ ጨብጬ እንደያዝኩ የሞት ያህል ተኛሁ። ከሙታን መካከል የጠራኝ ረድ ሠርዌ ነበር።

"ድሃው አልአዛር ተኛህ?"

"አዎ"

"ትኝት? ትኝት?" ቸንቹ አይኔ ላይ ተጋረጠ

"አዎ"

"ሄደን ደሞዛችንን እማንጠይቅ?"

"እሺ"

እግዚአብሔር አስርቦ ከሚያፈላስፍ አጥግቦ ማስተኛት አይሻለውም ኖሯል? በተራብኩበት ሌሊቶች አብጠለጠልኩት፣ በመጥገቤ እግዚአብሔር ዛሬን ከጉትጎታዬ አፎይ ብሎ አላደረም? ታዲያ...

@OLDBOOKSPDF

የጥጋብ ህመም ከሆነው እንቅልፍ በግድ ተፈውሼ ፊቴን ቧንቧ ውሃውጋ ሄጄ ታጠብኩ። አከራዩ በስለት የሰበሰቡትን ዶቂት ወደ እንባበሮነት ቀይረው ከቤት ወጡ። ገና በቅጡ አልነጋም ኖሯል። የአከራዩ እህት ከጃክ ጋር እየተጣሉ ብቅ አሉ።

"ዋግራዝማች ዋለሉ ያለህ፣ አንተ ቱሲያም ደጃፌ ላይ ትዘፈዝፈው?"

ጃክ ምን በልቶ የሰው ደጃፍ አበላሽ? እንደ እኔ ጥሬጥሬ ትምቻሚ መብላት ጀምሮ ይሆን?...

ከረድ ሠርዊ ጋር ተያይዘን ወጣን

"ሠላም ለኪ ቅንብቢት" አለ ረድ ሠርዊ ምእመኑ ተቸምችሞ የሚተምበትን አቀበት እየተመለከተ።

"ቅንብቢት የየካተራራ ቤተ መምኅኗን ናት። ዐመፀኛ፣ ወንጀለኛ፣ ነፍሰገዳይ፣ ቀማኛ... ሁሉ የፍርድ ቀን ከመምጣቱ በፊት በደሌኩን፣ ማረኝ ብሎ የሚማጠንበት፣ መማጠኛ ቤት እንድትሆን ለቅንብቢት ተሰጥቷል። ሠላም ለኪ ለመምኅኗን ቅንብቢት!"

ህዝቡ በለማኞች ታሊም ውስጥ ሲተም አረፋ የደፈቀ ቀሰስተኛ ደራሽ ይመስላል። ቀጥብሎ ወደላይ የሚምዘገዘግ አቀበት። ብቅ እንቅ ላይ ፋታ ወስዶ ዳግም ወደ ሰማየ ሰማያት ለመድረስ ይፋጭራል።

ረድ ሠርዊ በቅንብቢት እንደተመሰጠ ነው።

የሚታወቀው ዳገት ምናልባትም ከማይታወቀው አቀበት ጋር የሚገጥምበት አንድ ነጥብ ሳይኖር አይቀርም።ይሄ የሚታወቀው ዓለም፣ ከማይታወቀው ዓለም ጋር ገጥሞ ጉዞ ወደ ሰማየ ሰማያት ይሆን ይሆናል። ጀርመናዊው ካንት በሰው ልጅ አቅም ማወቅ የሚችላቸው እና ማወቅ የማይችላው ሁለት ዓለማት አሉ ያለው ቅንብቢት ላይ ይሰራ ይሆናል። ማወቅ የምንችለው በጊዜና በቦታ የተወሰኑትን ብቻ ነው። እኔን፣ ረድ ሠርዊን፣ ጃክን፣ ናትራን፣ አከራዩን፣ እህታቸውን፣ የጋዜጣውን ባለቤት....

...ዶሞዝ ይሰጠን ይሆን? ረድ ሠርዊ ምን ታይቶት ዛሬ እንጠይቀው አለ? ከከለከለን ቆይቶ የለም?

@OLDBOOKSPDF

"ስለልደታማሪያም" አለች እንደ ፍቁርወልዳ ልጇን የታቀፈች ሴት

"ለካ ባይጤን አልያዝኩትም" አለ ረድ ሠርዌ ከሀሳቡ ብትት ብሎ

"ምንድነው እሱ?"

"ችምቻሚ የያዝኩበትን"

"እኩፋዳህን?"

"እኩፋዳ አይደለም ባይጥ ነው የሚባል፤ እዚያ ውስጥ ጥቂት ሳንቲሞች ነበሩ"

ከችምቻሚው ጋር በልቻቸው ይሆን?

"ስለልደታማሪያም"

"ልደታ ትስጥልኝ፣ ልደታ ትስጥልኝ" እያለ ያልለመኑትንም አካተተና "ለእመ ብከ ሀብ ወለ እሙ አልብከ ኀሲ" ትኩር ብዬ ሳየው ኀለሀ ስጥ፣ ከሌለህ እዘን ይላል ወልደህይወት እንፍራንዛዊ:: አላነበብከውም?

"እንብቤዋለሁ፣ በአማርኛ እንደውም ኮርስ ሰጥቼዋለሁ" ኮከበፅባህ ትምህርት ቤት እስከንደርስ ምዕመኑ እንቅፋት ሆኖን መጨዋወት ሳንችል ቀረን:: በደበልጥ ረድ ሠርዌ ትከሻው በምዕመኑ ትከሻ እየተነገለ ነበር የሚሄደው::

ከበስተኋላዬ ስሜን የሰማሁ መሰለኝ:: መለስ ብዬ ስመለከት ምዕመኑ ጀርባውን ሰጥቶኝ እየተመመ ነው:: የኔብጤዎቹ ብቻ ፊታቸው ወደ ምዕመኑ መምጫ የዞረ ነው:: ጆሮዬን ተጠራጥሬ መንገዴን ስይዝ ተደገመ::

"ታለ፣ ታለ፣ ታለዬ"

አሁን አልተጠራጠርኩም:: ይሁንና ረድ ሠርዌ ጨዋታ ጀምሮ ቀልቤን ሳበው:: ግን በዚህ ሥም ቅንብቢት ውስጥ የሚጠራኝ ማነው?

"እየህልኝ የቅንብቢት ደጃፍ?" አለ::

@OLDBOOKSPDF

"ትምህርት ቤት እኮ ነው።

"መች አጣሁት፣ ስያሜው ትልቅ ምስጢር ይዟል።ኮከበ ጽባሕ ዛያደድል ውስተ ገጸ ሰማይ ትብሏላ። ከመምንኛን ትንበቢት ጋር ይናበባል።"

ግዕዝ ማስተርጎም ስልችቶኝ ዝም አልኩ። ለመሆኑ በግዕዝ ያልተባለ ነገር ምንድነው? ረድ ሠርዌ ፊት ለፊቴ እየተራመደ ጨዋታውን ወደኋላ ይልከ ጀመር።

"ታዲያ ምን ይሆናል ያ መናጢ መጥቶ ድንኳን ይጥልበታል።"

"የቱ መናጢ?"

"ሐሰተኛው መሲህ"

"እዚህ ቅንብቢት?"

"አዎ፣ በወርቅ የተዘመዘመ ድንኳኑን ይተክላል። የድንኳኑ ተራዳና ካስማው ወርቅ ነው አሉ። እሱ ግን ጉፍጫ ነው። ቁመተ መላላ፣ አንገተ ሰላላ፣ ጭንቅላተ ሞላላ፣ ቀኝ አይኑ የተከላሸች፣ ግራ አይኑ የተቅላላች።"

ሱሪው እላዩ ላይ ይወናወናል። የእኔስ እንዴት ሆኖ ይሆን? የረድ ሠርዌ ትውፊታዊ አረማመድ ከእካሉ ጋር ከስቶና ማመቶ ሳይጠፋ አልቀረም። ከተክሴ አቋቋም የተቀዳው አረማመድ ለመከራ ጊዜ አይሆንም ማለት ነው?

"ሊቁን ሁሉ እንደቦሩ ማዳ ማን ያከራከረው? የየራሱን፣ የማለለበትን ብቻ ሳይመረምር ታቅፎ ቀርቷል። የኔታን ጨምሮ አንዳንዶች አንገተ ሰላላው፣ ጭንቅላተ ሞላላው፣ ቁመተ መለላው የእኛ ሳይሆን የእስራኤሉ ሐሰተኛ መሲህ ነው ይላሉ።ሐሰል ተራራ ላይ ከሴቲቱ እንደሚወለድ ትንቢት አለ። "እኔ አምላክ ነኝ" እያለ፣ በብዙ ተአምር ብዙዎችን አስቶ ከርሱ ወገን ይደባልቃቸዋል ይላል፤ ሙታንን ያስነሳ ዘንድ ሥልጣን ይሰጠዋል። ራዕየ ሳቤላ ላይ ይህ ሁሉ ተነግሯል። ኢየሩሳሌም ይደርሳል፣ ከደብረ ጽዮን በታች ተራዳ ድንኳን ይተከላል የሚል አለ። ታዲያ ምን ይሆንልሃል እኔ በአይኔ በብረቱ ትንበቢት ውስጥ አይቼዋለሁ። ብቻ ገና የወርቅ ድንኳኑን የተከለ አይመስለኝም። ፊልጎ አትችዋለሁና።"

@OLDBOOKSPDF

ብዬ! ብዬ የሐሰተኛው መሲህ ተጎራባች ልሆን? ቡና ልጠራራ? በርበሬ ቅመስ ልባባል?... ቅድም በልጅነት ሰሚ ድምፁን አቅጥኖ የጠራኝ እሱ ይሆን እንዴ? መቃለድ ልንጀምር?....

ዮሐንስ አፈወርቅ "ወበመ-ሂ ካዕበ ያድኅኖሙ ለእልክቱ" የሚለውን ጥቅስ ትኩረት ሰጥቶበታል። ጌታ አህዛብን ከእስራኤል ጋር እንደሚያድናቸው ተስፋ ሲያደርግ ነው። ታዲያ ምን ይሁን ጥቅሷ በተለይ ለኢትዮጵያ ብዙ የተሳተ መንገድ ከፈተች።"

ጨዋታው እንዲቀጥል ባልፈልግም "እንዴት?" ለማለት ተገደድኩ

"እንድምታው ብዙህ ነዋ! አንዳንድ ሊቆች ጌታ እስራኤልን ካዳነ በኋላ ወደኛ እንደሚመጣ ነገረን ይላሉ። እየደለም፣ እስራኤልን እንዳዳነ እንዲሁ ያድናል ማለቱ ነው የሚሉ ተነስተዋል። ሦስተኞቹ ግን ምሳሌሆመ- ለእርሳቸው (ከእስራኤል) ጋራ አህዛብን ያድናቸዋል እያለ ነው ሲሉ ይፈታሉ"

"ታዲያ እንዴት ለኢትዮጵያ የተሳተ መንገድ ሆነ?"

"እየህ፣ እስራኤልን ካዳነ በኋላ ለእኛ ዳግም ይወለዳል በሚል ሐበሻውን ኢየሱስ ይጠብቃሉ። እስራኤልን እንዳዳነ ከእኛ ተወልዶ አዲስ መታደግ ይታደገናል ሲሉ ነው እውነት እላቸው መሰል..."

ምግብ በማጣት ሳይሆን ይሄን በማምስልሰል ከሰውነት ተራ የወጣ መሰለኝ። ምዕመኑ ተቃለው መንገዱ ነፃ ስለወጣ በመካከላችን ክፍተት ተፈጥሯል። እስፋልቱን ሲሻገር ጨዋታውን (ማስፈራሪያውን ልበል እንጂ) ጋብ አድርጎ መልሶ ካቆመበት ይቀጥላል።

"...ሐበሻው ኢየሱስ ካንድም ሁለት ሦስቴ መጥቶ እንደነበር ታሪክ ያወሳል። ይሄንን እለታ ተክለኢየሱስ ዋቅጅራ እና አቶ ተክለፃድቅ መኩሪያ ፅፈውታል። ቤተክነት ሐሰተኛ መሲህ እንደሆኑ ከመጥተስ ውጭ መነሻ ምንጩን አዳፍናለች።"

የሚያስበው ከመስላቱ የተነሳ አይኑን ጨፍኖ የሚሄድ መሰለኝ ተጠጋሁት። ዓይኖቹ የተጨፈኑ ያህል በዝለው ወደውስጣቸው በማተኮር ላይ ናቸው። ጨዋታውን ስለፈራሁት የማይያያዝ ጥያቄ አቀረብኩለት።

@OLDBOOKSPDF

"ደሞዙን የሚሰጠን ይመስልሃል?"

"አይመስለኝም"

"ታዲያ እዚህ ድረስ ለምን ለፋን?"

"ደጅ ማስጠናቱን ወዶታል"

"እና?"

"ደጅ እንጥናለታ"

ምን የሚሉት መስጠት ነው? ቀጣሪያችን ደሞዝ መክፈል ያቆመው ከግርግሩ በፊት ነበር:: ተሰብስበን አማነው፣ ቀጣሪያችን ሀሜት አልፈራም... ተሰብስበን በግልፅ አወገዝነው፣ ቀጣሪያችን ውግዘት አልበገረውም... እየተንጠረበበ "ገንዘብ የለም" ይላል::

ሥራ ግን ነበር፤ ለፀጥተኛው የረሃብ ዕልቂት ታጨን:: ሳንበላ ለምናልባቱ ሥራ ሄድን፤ ሳንበላ ሰራን፣ ሳንበላ ወደየመጠለያችን ተመለስን::

"ትንሽ ታገሱ" ይላል በመብል እርካታ ቀፈቱን እያሻሸ:: ከዕልቂቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ቀጣሪያችን የራሱን መፍትሔ ይዞ መጣ::

"ሒዱና ከወፍጮ ቤት ያሻችሁን እህል አስር አስር ኪሎ ውሰዱ:: ከደሞዛችሁ ይቆረጣል" አሮን

እኔ አሻፈረኝ አልኩ:: ረድ ሠርዌ ግን እህሉን ለመውሰድ ሲሰለፍ የግዴን ተራዬን ያዝኩ::

ወፍጮ ቤቱ የወንድሙ ነው ይባላል እንጂ የጋዜጣችን ሥራ አስኪያጅ እንደሆነ ማንም ያውቃል:: ያደገው ትንሽ የገጠር መንደር ውስጥ ነው (ስሟን ዘነጋሁት) የተማረው በከፍተኛ ድህነት እንደነበር ሲናገር አከብረው ነበር::

"የመንደሩን አህያ ሁሉ አሰባስብና በሳምንት አንድ ቀን የነዋሪውን ሁሉ እህል ወስጄ እስፈጫለሁ:: አስር አመት ስመላለስ አንድ አህያ ጠፍቶብኝ አያውቅም::"

ቀፈቱን በጥጋብ ፍተሻ ያሻሻል

@OLDBOOKSPDF

"እንዳንዴ የወፍጮ ቤቱ መዛኝ በከፋት ወረፋዬን ያዘገይብኛል። ከሩቅ እንደመጣሁ እያወቀ፣ እህሎቼን ጅብ እንዲበላብኝ። እኔ ግን..."

የሰው ሁሉ ጦርሜዳ ይለያያል። የእሰቃችን ጀግንነት ወፍጮ ቤት ውስጥ ተከናውኗል። የትኛውንም ድል ከእህያ መንዳት ስኬት አያስበልጥም። ጋዜጣው አገር አቀፍ እውቅና አትርፏለች። ለእሱ ምንም አይደለም። እሳታሚ ድርጅቱ ብዙ ትርፍ ያጋብሳል፤ ለእሱ የወፍጮ ሚዛን ሥር ከመንደር እናቶች መቀነት ተፈትቶ ከሚከናወነው ክፍያ በላይ አይደለም።

"እኔ ትምህርቴን ለመቀጠል ወደ አዲስ አበባ ስመጣ የነበረ ለቅሶ! የሞትኩ ያህል ደረት ተመቃልኝ። ማን እህያችንን ይንዳልን? ማን እህላችንን ያስፈጭልን?... ተባለ። ምኑ ቅጡ።"

የሆድ ምርመራውን በመዳፉ አከናወነ።

"አይዟችሁ፣ ወንድሜ እኔን ተክቶ ይሰራል አልኳቸው። ማን እንደ አንተ አሉኝ..."

እሰቃችን መኪና ሲነዳ ቅድሚያ የሚሰጠው ለእህያ ነጂ ብቻ ነው። ጀብዷቸውን ሲናገር የአገር መከላከል ተልዕኮ ይሰጠዋል።

"ስንቱን አቀበት፣ ስንቱን ቁልቁለት ከጅብ ጋር አንገት ላንገት ተናንቆ፣ የተረበሹትን እህዮች አረጋግቶ፣ ጭነታቸው ሲያጋድል... እኔ ብሆን ለአገር መሪነት የምመርጠው እህያ ነጂ ነው።"

ወፍጮ ቤት ተራችንን ጠብቀን የመረጥነውን እህል አስመዘንን፤ እኔ ምስር ስመርጥ የእሰቃችን ወንድም የእሰቃችንን ዐይን ዐይን እያየ "ምስር ከሆነ ኪሎው ይቀንሳል" አለ።

"ይሁን፣ ይቀንስ"

"ሰባት ኪሎ ብቻ?"

"ይሁን"

ወስጄ ለአከራዩ እህት ሰጠኋቸው። አንድ ቀን ምስር ወጥ፣ ሁለተኛ ቀን ስንዴ ቅልቅል የምስር ንፍሮ አብልተው በሦስተኛው ፊት ነሱኝ።

@OLDBOOKSPDF

"የግራዝማች ዋለሉ ያለህ እኔን ቀላቢው ማድረጉ ነው?"

* * *

ቀጥታ ወፍጮ ቤቱ ወደሚገኝበት ይብሳ ህንፃ ሄድን:: ሥንቱ ኮላሽ ሰፈር ይባል እንደነበር ተነግሮኛል:: የጥይት ቀለህ አረር እየተጣባ አርሳስ ይከደን ነበር:: ወፍጮ ቤቱ በር ላይ የአለቃችን መኪና ቆማለች:: ወፍጮ ቤቱን ከሩቅ ሲያዩት አቧራ የጠጣ ካኪ ባርኔጣ ይመስላል:: ደጁ ላይ ብዙ ሴቶች ተኮልኩለዋል:: ታዛው ሥር ጭንታቻቸውን ያራገፉ አህዮች ይታያሉ:: አንዳንዶቹ እግራቸውን ተስንክለው በመገለል ይራመዳሉ::

ሦሥቱ የሥራ ባልደረቦቼ የበገና አውታር መስለው እንደቆሙ ወደ ወፍጮ ቤቱ ያያሉ:: እንደእኛ ለደጅ ጥናት መጥተው መሆን አለበት:: ታሪካችን መናቸፍና መብለጥለጥ የበዛበት ቢሆንም ሳያቸው ደስ የሚል ስሜት ዳሰሰኝ::

"ሙሴ ሰላም ነው?"

"ዮሐንስ እንዴት ነው?"

"ስምዖን ኬፋክ" እያልኩ ሰላምታዬን አዳረስኳቸው:: እነሱ ግን ሠላምታቸውን ገርገብ አደረጉትና ወደ ወፍጮ ቤት ትኩረታቸው ተመለሱ:: አያወሩም ግን ተጠጋግተዋል:: ቆይቶ ሲገባኝ ግን ረድ ሠርዌን ይጌ በመሄዴ ደስ አልተሰኙም ነበር:: ሦስቱንም በሸሙብጭ ክርክሮችና በለበጣ ቅፅል ስሞች መግቢያ ያሳጣቸዋል::

"ሙሴ ፀሊም" ይለዋል:: ሽሙጡን ለእኔ ብቻ ይነግረኛል:: ሙሴ ፀሊም በግብፅ ውስጥ በውንብድና ይኖር የነበረ አባት ነው:: ሙሴ አይት ደፍርሶ ስሞታ ለእኔ ያቀርባል::

"ሙሴ ፀሊም አይበለኝ?"

"መጥፎ ነው እንዴ?" እለዋለሁ::

"እኔ ምን አውቄ ከእፉኝትና ከሠርዌ አፍ መርገዝ እንጂ ሌላ ምን ይገኛል?"

ሙሴ ፀሊም ሰውን ሁሉ በአስቀያሚ እንስሳት የመመሰል ልምድ አለው:: እንዱን አባብ፣ ሌላውን ጊንጥ፣ እስስት፣ አርጃኖ፣ ገበሎ…

@OLDBOOKSPDF

እያለ ሰይሞ ጨርሷል። አንዳንዴ ታዲያ የቆየ መጻሕፍት ላይ የአስፈሪ እንስሳት አዲስ ስም ሲያገኝ ኮተት እያለ መጥቶ ትከሻዬን ይነካኝና ያስነብበኛል።

"መዒዒት ትባላለች አሉ። እንደተኩላና እንደ ነብር ያለች ነጣቂ፣ ጠጉረ ልም ናት ይሏታል አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ። ቁርጥ ስምዖንን። ይሄ መዒዒት!"

ቢሮአችንን መካነ እንስሳት አስመስሎት ነበር። የብዙ አስፈሪና አስቀያሚ እንስሳት መጠለያ።

አንድ ቀን እኔን ማማከሩ ሲበዛብኝ "እኔስ ምንድነኝ?" ስል ጠየኩት።

"አንተ ላጽቂት ነህ"

"እሱ ደግሞ ምንድነው?"

"በእግሩና በልቡ የሚሄድ እንሽላሊት አይነት ይሉታል አለቃ፤ እንደ እፉኝት ጉዳት የለህም። ግን አፈጣጠርህ ለዓይን ያስጠይፋል።"

ሳቅሁ

"ታዲያ ለምን ትፈታተነኛለህ?" ብሎ ተለየኝ።

ረድ ሠርዌ ሦስቱን ባልደረቦቻችንን ያያቸውም አይመስል። ወደ ወፍጮው ቤት አጨንቁሯል። የዶቄት ብናኝ ናኝቷል። ከዓይን ይልቅ ጆሮና አፍንጫ ያለውን ነገሩን ለመረዳት ያገለግላሉ። "እውጡጡውው..." የሚል የሞተር ጩኸት ጆሮን ያውካል። እህል ሳይሆን የተከናነች ነፍስ የሚያሽምድ የገሃነም ወፍጮ ይመስላል። ደግነቱ አፍንጫ ይሄን አይቀበለውም። እህል፣ በርበሬ፣ ሽሮ፣ ቅመም፣ ጌሾ... ተደበላልቆ አጥርቶ ማሽተትን ያደበላልቃል።

ስምዖን በአምድ ወደኛ ሲጠቁም አየሁት። ለረጅም ጊዜ በጋዜጣ ላይ በመቆየቱ ከረድ ሠርዌ የተሰጠው ቅፅል ስም ነው። ሶሪያ ውስጥ በአንድ የድንጋይ አምድ ላይ አርባ ዓመታት የኖሩ አባት ናቸው። "ጋዜጣም የማስቆም የማያስተኛ የድንጋይ አምድ ነው" አለኝ ረድ ሠርዌ። ስምዖን ሽበት የበዛበት ሉጫ ፀጉሩን ልፍጭጭ አድርጎ አስተኝቶታል። ሱሪውን እስከ ጡቱ መዳረሻ ድረስ ከፍ አድርጎ

@OLDBOOKSPDF

ይታጠቃል። ሙሴ ፀሊም ተነጥዷቸው ወደኛ ጥቂት ተጠግቶ በእጁ ጠቀሰኝ።

"ማን ነግሯችሁ መጣችሁ?" አለኝ

"ማንም አልነገረንም"

"እንደ ገበሎ ካብለካብ እየተሹለከለካችሁ ትሰሙን ነበር ታዲያ? እሺ አንተ እንኳን መጣህ እፉኝቱን ለምን ይዘኸው መጣህ?"

"እሱም'ኮ ደምዙን አላገኘም።" በፊትም የሙሴ ፀሊም አፍንጫው እንደዚህ ሹልና ረጅም ነበር እንዴ? እንደግንደ ቆርቁር ከአይኑ አፍንጫው ቀድሞ የሚደርስ ይመስላል።

"ያ-አርጀኖ የሆነ የጋዜጣው ባለቤት እሱን መበቀል ስለሚፈልግ ነው እኛን ሁሉ የሚያጠቃን።ከእሮጌ መጻህፍቱ በሚሰበሰበው ፀረ አህያ ገድል ልቡን አቃጥሎት እንደነበር አታውቅም። አርጀኖው ለኔ ለራሴ ሠርዌን አህያ ምን አደረገች? ብሎኛል"

"ቆይ አንተ ግን "ላዳ" ታክሲ አለኝ ትል የለም እንዴ? ለምንድነው የማትተወው?"

"ቢኖረኝስ? ላጽቂት ብር ሜዳ ላይ ይተዋል?"

ዝም አልኩት

"ደሞ እንደበቆሎ እሸት ከነገለባው ጡብስህ ነው እንዴ ያመጣኸው?" በሰው አፈጣጠር እስከነረም ድረስ ልውጥውጥ አልኩ።

"በዚህ ሰዓት የሚያሳማው መክሳት መጥቆር ሳይሆን እንደ ማድቤት ሴት ማነጥነጥ ነው" አልኩት ግልፍ ብሎኝ።

የሙሴ ፀሊም አፍንጫ እየተመዘዘ ዓይኑ ስር ደረሰ።

"እንዝዝ ነገር ነህ" አለኝ።

"እንዝዝ ምን አይነት እንስሳ ይሆን?"

@OLDBOOKSPDF

እፍንጫው እንደ ጀልባ ሽራ የአቅጣጫ መለዋወጫ መሣሪያው ሳይሆን አይቀርም። ተመናጭሮ ሲዞር በእፍንጫው የተቀዘፈው አየር ሲናወጥ የተሽከመው የዶቄት ብናኝ ተረበሸ።

ወደ ረድ ሠርዌ ስመለስ ወፍጮ ቤቱ ላይ እንዳተከረ ነበር። አውሎ ነፋስ ያግለበለበው የመሰለ ዶቄት ይቦናል። ለፀጉራቸው ብቻ የሚጨነቁ ሴቶች ሻሻቸውን ቆልለው፣ ቡላ ፊታቸውን አስቀድመው ይወጣሉ። ሻኛ የመሰለች የእህል ቋጠሮ ጀርባቸው ላይ አብጣ ትታያለች። ለአንድ ቤተሰብ የአንድ ቀን ፍጆታ ሳይሆን አይቀርም። የመከራ ጊዜው ያለፈ ቢመስልም በየሰዉ ልብ ውስጥ የተወው ቅሪት ዘልአለማዊ ሥጋት ሰንቅሮ ትቷል። ሰው ሥጉ ፍጡር መሆኑን የሚገልፀው እንዲህ ያለ ቀን ነው። የመከራ ጊዜ ፍላጎት አዘቅት ነው። ቆስ ብንከምር፣ ብንቆልል ዓይናችን አይጠግብም። አንዳንድ ሴቶች እነሱ የማይችሉትን አስፈጭተው በሚችለው አሽከመው እየተገላመጡ ይቀድማሉ። ምናልባት ዓይን ውስጥ እንዳይገቡ ይሆናል። ከሽከሙ በጥቂት ምዕራፍ ይርቃሉ። እነዚህ ሴቶች ያልተረዱት ቢኖር ያሽከሙት ሰው ከዘረፋ ውጭ ምንም ተስፋ ከሌላቸው ወገን መሆኑን ነው። ነገሩ ዳግም ካገረሸና የከተማው አቅርቦት ድንጋይ ብቻ ከሆነ ድንጋዩን ጨብጠው እህሉ የገባበትን ቤት የሚከቡ ድሆች ይመጣሉ። አግበስባሾች ያግበሰበሱት መጥፊያቸው ይሆናል።

"እንዴት ዋላችሁ?" አለ ዘግይቶ የመጣው ዮናኤል። ረድ ሠርዌ "አፈትጉሃን" ይለዋል። የጋዜጣችን መዝናኛ አምድ አዘጋጅ ነው።

"እንዴት ዋላችሁ፣

"ደሞዝ ያልተከፈላችሁ፣

"በረሃብ ትሞታላችሁ፣

"ግን

"ዕድቅን ታገኛላችሁ"

ቡልቅ ያለ ሳቅ። "አፈ ትጉሃን" አልኩት ቀደም ባለው ንጉሣውያን ዘመን ቢሆን ከቁመቱ ማጠር ጋር የእንጻ ራስ አጨኔዎች ይሆን ነበር።

"ታለስ ሆይ" አለኝ። አብረን ስለተማርን ግቢ በጠጣልኝ የግሪክ ፈላስፋ ስም ነው የሚጠራኝ።

@OLDBOOKSPDF

"ታለስ ሆይ

"ፍልስፍናህ ከሰማየ ሰማያት ደርሶልሃል

"ምን እንዲደረግልህ ትሻለህ ተብለሃል

"ደቂት ይስፈርልህ?

"ወይስ በተስፋ ትመለሳለህ?

"ካልሆነም ወፍጮ ቤት ትሰራለህ?"

እንደወትሮው ለመሳቅ ብዘጋጅም አልሆነልኝም። ዮናኤል ምስጢር ያውቃል፤ እንደውም የአለቃችንን የህይወት ታሪክ እየጻፈ ነው ተብሏል። በቀልድ መካከል እውነት ያቀብላል። እና ይሄ የወፍጮ ቤት ቁራኛ እኛን የወፍጮ ቤት ሠራተኛ ሊያደርገን ከጅሏል?

ብስጭት እንደቀለጠ መዳብ ከልቤ ወደ አንጀቴ ተንጠባጠበ። ረድ ሠርዌን መለስ ብዬ አየሁት። እንደ ጃክ የተፈጥሮ ብያኔን በፀጥታ የተቀበለ ይመስላል። ስንመጣ የነበረው መደመም አሁን የለም። ትካዜው እንደ መርግ ይጫናል።

በዶቂት ጭጋግ የተዋጠው ዮናኤል ቅንጣቶቹ የእህል ብናኞች የፊቱን ምህዋር የሚሽከረከሩ መሰለኝ።

"ቡ-ጊዜ ለኩሉ" አለ። ለመጀመሪያ ጊዜ ኩልል ያለች ሀዘን በጭጋጋማ ፊቱ ላይ ያየሁ መሰለኝ። አይኑ ሳይሆን መንፈሱ አልቅሷል። አፈትጉሃን ዮናኤልን በዚህ መልኩ የተረዳሁት ዛሬ ስለሆነ ይሆናል። ወይም እኔ ስላዘንኩ መሳቂያ ምክንያትን የሻረው መንፈሱ እውነታውን ገልብጦብኝ ይሆናል። ሰው ጥንቡን በጣለበት፣ መቅሰፍት ይሁን ጥይት በሚያፏጭበት በጦርነት ሲቀልድ እንጂ ሲያዝን ማሰብ አዳጋች ነበር። ዛሬ ግን...

የተጠራራን ይመስል ወፍጮ ቤቱ ደጃፍ ላይ ተሰበሰብን። ሁላችንም ፊት ላይ በከፋ ቀን ባዶ እጅ መቅረታችን የፈጠረብን ሥጋት ይነበባል። ደስ የማይል ስሜት ሰፈነብኝ። የአንዱ መኖር ሌላውን ያወከው ሆኖ ተሰማኝ። ከመኖር ፍላጎት የመነጨ ጠላትነት እንደ ውሃ ከመሬት ፈልቋል። ሳይደራረሱ፣ ሳይነጋገሩ አንዱ ሌላውን ተጭኖታል። የሚያወዳድራቸው ነገር ሳይኖር በንዕዕር ልባቸው ጠፍቷል። መንገድ

@OLDBOOKSPDF

ላይ ሳይበቅሉ እንትፋት የሆኑ ብዙዎች ናቸው። ከሆነብን ይልቅ ሊሆንብን የተዘጋጀው እጅግ ከብዶ አጎበጠኝ።

የቀድሞ የጋዜጣ ባለቤት፣ አሁን የእህል ቤት ጌታ ወጥቶ ሆዱን አሻሸብን። የሚመለከተው ግን ከኛ በስተጀርባ ወዳለው መንገድ ነው። ስዞር ፀሐፊው ስትመጣ አየኋት። ፈርዶበት ይወዳታል። ቤቷ ቅርብ ስለሆነ መሰብሰባችንን ስታይ ባለመታማት የመጣች ሆና ተሰማኝ። በደህናው ጊዜ ረድ ሠርቄ "እግር ወከናፍር" የሚል ያለበት የሸሙጥ ቅኔ መወድስ ያከታትልላት ነበር። ውበቷ ከመልኳ ሳይሆን ከተክለ-ባቷ የመነጨ ነው። አጭር ቀሚስ ለብሳ ከወገብ በታች በዋለ ውበቷ ስትታይ ከበስተኋላዋ የተገኘ ወንድ እርሱ ቀኑ የደረሰ የልብ ድካም ሰለባ ነው። አንድ ቀን እኔና አፈትጉሃን ዮናኤል ይሄ "አደጋ" ደርሶብናል። እጅግ ያስገረመኝ የዮናኤል ሁኔታ ነበር። ጀስሙ እንደሸረሪት ድር ከወገቧ በታች ተቋጥሮበት የተጠመደ ልቡ ሲጎተት እኔ አባተትኩት።

"ምን-አፈትጉሃን?"

እንደምንም ቀልቡን ሰብስቦ "ባልዞርሽ ገድላኝ ነበር" አለ።

ከት ብዬ ሳቅሁ። ባልዞርሽ ከመሽሟቀቅ ጋር ዞራ አየችን። የረድ ሠርቄ "እግርና ከናፍር" ታውሶኝ የበለጠ ሳቅሁ። እግዚአብሔር እንደ ጊዜና እንደ እውነት ሁሉ ውበትንም የተገላቢጦሽ ያደርጋል። ለዓይን የሚቀርበው ፊት ነው ባትግ? ፊትን አከፍቶ እግርን ማሳመሩ ተገልብጣ እግሯን እያሳየች እንድትሄድለት ነበር?

ያም ሆነ ይህ አፈትጉሃን ያወጣላት የሸሙጥ ስም ተዛምቶ ፀናላት "ባልዞርሽ፣ ባልዞርሽ" ትባላለች።

ከዚያች ቅፅበት በኋላ "ባልዞርሽ" እኔና አፈትጉሃንን ጠምዳ ያዘች። አፈትጉሃን ይሄንን ሲሰማ

"ምን ቀረብን ዘወር እንልላታለን፣ ከባቷ እንጂ ከፊቷ ምን አሮንን?" ሲል ደገማት።

የወፍጮ ቤቱ ጌታ ባልዞርሽን በአይኑ፣ በእጁ ሆዱን እያሻሸ፦

"ጊዜው ከፉ ነው! ምን ላድርጋችሁ? ባላስብ ቀርቼ አይደለም። ቢችግረኝ ወንድሜን ለምኜ እዚች ወፍጮ ቤት ውስጥ ቦታ

@OLDBOOKSPDF

እንዲፈልግላችሁ አድርጌአለሁ። ሪፖርተሮች ዶቂት ለደንበኛ አድራሽ፣ ከፍተኛ ሪፖርተሮች አስፈጭ፣ ምክትል አዘጋጆች እህል ነፊ፣ አዘጋጆች በባለቤቱ ረዳትነት፣ የምክትል መዛኝነት ቦታ ተዘጋጅቶላችኋል። ማንኛችሁ ናችሁ በዕድሉ የምትጠቀሙ?

ፀጥ አልን፤ ወፍጮው ብቻ ያገሳል፤ ዱቄቱ ብቻ ይቦናል።

"እኔ" አለ አንድ ድምፅ። ሁሉም ድምፁ ወደመጣበት አቅጣጫ ዞሩ። እኔ ብቻ ድምፁ የማን እንደሆነ አውቄ ወደታች ሰመጥኩ።

የወፍጮው ቤት ጌታ ባልዞርሽን እያየ ተንጠበረረ፤ "ማነው?"

"እኔ"

"ሥርዌ?"

"አቤት"

"ሪፖርተር ነበርክ?"

"አዘጋጅ ነበርኩ ጌታዬ" አለ።

ልቤ የሆነ ረግረግ ውስጥ ስትሰጥም ይታወቀኛል።

"ታዲያ ከእኔ ጋር አንስማማ፣ እንዴት መዛኝ ትሆናለህ? ባይሆን ትንሽ ፈቀቅ ብለህ እህል ታበጥራለህ"

በእጁ ሆዱን፣ በአይኑ "ባልዞርሽን" አሻሸ። ባልዞርሽ የሴት ብሽሽት እንደሸተተው እህያ ከንፈሯን ሸልቅቃ አፍንጫዋን አለበሰች። ሁሉም ነገር አስጠላኝ...።

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፫

፫ ዓለማየሁ ገላጋይ

በወፍጮ ቤት ሆዋ ውስጥ፣ በብናኝ ዓለማት ዑደት፣ በመሳሳብና በመገፋታተር ሥርዓት፣ ቁብ በሌለው አስፈጪ ያልተፈለግን ውጤቶች ነን፡፡ ምድርና የሥርዓት አጋሮቿ ከእነዚያ ህልቆ መሳፍርት ከሌላቸው የብናኝ ቅንጣቶች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የየራሳቸው ንብርብር ያላቸው ቅንጣቶች፣ የአየር ጥንቅር ያላቸው ቅንጣቶች፣ የአየር ንብረት ዞኖች ያላቸው ቅንጣቶች፣ የራሳቸው መንቀጥቀጥና እሳተ ገሞራ ያላቸው ቅንጣቶች፣ የህይወት ክፍፍልና እስረሚጫት ያላቸው ቅንጣቶች... ከነፕላኔታችን ፈረስ አፍንጫ ውስጥ ብንገባ ያስነጥሰው ይሆን? አስፈጪው ግንባር ላይ ስንት ቅንጣቶች በላብ ሟሙ? ስንት ብናኞች የአይኑ ሽፋሽፍት ላይ ሰፈሩ? ከነፕላኔታችን በአስፈጪው ላብ የምንሟሟው መቼ ይሆን? ብናኙ፣ ከብናኙም ቅንጣቱ የዶቂት ቃርሚያ አይደሉምን? እንዴት ያለ አፈታሪክ የቅንጣት ባለቤት ፈጠረ? ምን ያህል ብናንስ ነው ይቺ ቅንጣት ዓለም እንዲህ ገዝፋ የምትታየን?

የናትራ ሲጋራ ቤት ድረስ መጥቶ ነበኘኝ፡፡ ተከትሎ ዝናብ አብሳሪ መብረቅ ባልተገጠመው የደጃፉ ክንፈር አልፎ ወለሉ ላይ ተጥመለመለ፡፡ ከደንባራው ሕውራዶሮ ይልቅ የናትራ ሲጋራ የጊዜ መስፈፊያ መለኪቴ ሆኖ ይሰማኛል፡፡

እኩለ ሌሊት ሆነ

የናትራ ሲጋራ የሚለፍፈው ጊዜን ብቻ አይደለም፡፡ ሥፍራንም ጭምር ነው፡፡ ያለሁት ቅንብኒት እንደሆነ ጥምልምሉ የናትራ ጭስ በአፍንጫዬ ስርጎ ይጠቁመኛል ::

የረድ ሠርዌ ባይጥ (እ፤ሾፋዳ) እንደተንተራሳት ሆና ተጠፍጥፋ ተቀምጣለች፡፡ ምናልባትም ለሃያ አራት ሰዓት ምናምኒት ያልተመስኩ ቢሆንም፤ ያለባለቤቷ ፈቃድ ችምቻሚ መዝገን ነውር ሆኖብኝ ከባይጧ ጋር እየተፋጠጥኩ አለሁ፡፡

@OLDBOOKSPDF

የመብረቁን መብለጭለጭ ተከትሎ ጉብዝና በተሰማው መድፍ፣ እግባብ ጮኸ፤ ነፍሴ ተመነጠቀች፤ ከረሃብ ጋር መኖር ብርቱ ሆኖ... እንኳን ባይጥ እኛ... እንኳን እኛ ፕላኔቷ... እንኳን ፕላኔቷ ህዋውም ያልተፈለገ "የአስፈጭው" ውጤት አይደለምን?

እጀን ሰድጄ ችምቻሚ ዘገንኩ። ባይጡን እንደነበረ ለማስተኛት መጠንቀቄን አስሰራሁ። እጀ ሾልኮ የገባበት ክፍተት በመጠን ጭንቅላቴን አስሰራሁ። እጀ ሾልኮ የገባበት ክፍተት በመጠኑ የአኩፋዳውን ሆድ በአየር ነፍቶታል። በግራ እጀ ጠፍጥፌ እንደነበር አስተኛሁት።ያፈስኩትን ችምቻሚ ወደ አፌ ከማድረጌ በፊት ደጃፌ እየተሽከረመመ ተከፍቶ "ጃክ" ዘባዘቦ ፊቱን ወደውስጥ ሰደደ፤ ገባ፤ ከበሩ ፊቶት ብሎ የፊት እግሮቹ ላይ አገጩን አስደግፎ ተኛ። ጃክን ስመለከት ተፈጥሮ ስመመን ውስጥ ትገባብኛለች። የተፈጥሮ ስመመን እንደልጃገረድ ንውዘት ኃይል እና ውበት ሆኖ አለማወቁ ይቆጫል።

ችምቻሚ ቃምኩ። እንዴት ያለ የመብላት ግፊት ነው ውስጣችን ያለ? በንፍሮና ቆሎ እየተደነቃቀፍኩ ሳኝክ "ጃክ" ቀና ብሎ አየኝ። ከጉዝጓዙ ተነስቼ ፊቱ ላይ ጥቂት ጥሬዎች አኖርኩለት። አሽትቶ ተወው፤ ሳይርበው ቀርቶ ሳይሆን ተፈጥሮዊ ረድፉን ላለመልቀቅ ባለበት የመቆየት ውሳኔው ሆኖ ስለተሰማኝ እራሴን ከእርሱ አሳንሼ ለማየት ተገደድኩ።

ንፋስ የተላቀሰው ካፊያ በሩን መነዝነዝ ጀመረ። ጃክ ከደጃፉ ግድም ፊቶት ብሎ በድብደባ የነተበ ከበሮ የመሰለ ጀርባውን ለእኔ ሰጠኝ። ደጃፉን ከውስጥ ልቀረቅር ሳስብ ናትራ የሲጋራ ጭስ ሽታውን አስቀድማ ገባች። ጃክና ናትራ በቤቱ ላይ የዘናብ ሌሊት ፈቃድ ለራሳቸው ሰጥተዋል። አይበርዳትም?

"እንደ ደሂ ውሻ?" ሁሌም የምትገረምበት ነገር "የውሻ ቤት አደረከው?" የማትዘነጋው አስተያየት፡

በአጭር የሌሊት ልብስ ናት። እግሯ እንደወይን ጠጅ የሰው ልብ ደስ ያሰኛል። ድሆች ድህነታቸውን እንዲረሱ ሲሰጣቸው የታዘዘው ወይን ጠጅ

"እልዬ"

"ወዬ ፈተናዬ"

"ቀን የት ሄድክ?"

@OLDBOOKSPDF

"መስሪያ ቤት" ሥራ ያለኝ ለማስመሰል? ችምቻሚ ቃምኩ::

"ሦስት ሰዎች ፈልገውህ ነበር"

"እነማን?" በችምቻሚ መደነቃቀፌን ገታ አደረኩ::

"አንዱ..." አልፋ አልጋዬ ላይ ተቀመጠች:: የተንጠለጠለ ውብ እግሯ... "አንዱ ፈረንጅ ነው"

'ዶክተር አሮን'

ሁለተኛውስ? እግዜሩስ? እግር ላይ ይሄን ያህል ጊዜ ማጥፋት?

"እያወክ አትጠይቀኝ"

እያወኩ "አላወኩም" አልኳት:: ውበቷ ልጅነቷ

"ያቺ አብራህ የምታስተምር የነበረችው፤ 'መኪና መልክሽ?' ምነው እንኳን መሬቱን ስትረግጥ የምትጠየፈው? ወንድ ፈልጋ የመጣች የማትመስለው..."

"በቃ አውቄአታለሁ" ነፀብራቅ ነች:: ረዳት ፕሮፌሰር ነፀብራቅ:: አብረን ስንማር ተጣልተን፣ አብረን ስናስተምር ታረቅን::

"ምን አለች?" ሲጋራዋ የት አድፍጦ ለአፍንጫዬ ብቅ አለ?

"እሷ ደሞ ምን ትላለች? ፈልጋህ የመጣች ሳይሆን ፈልገሃት የሄድክ ታስመስላለች:: ውይ! ውይ!..."

ልታዘነብባት ሲሆን አቋረጥኳት::

"ሦስተኛው ማነው?" ልቤ በጣም መታ፣ ለምን? እህቶቹ? ቢሆኑስ? እናቴ?. . .

"ሦስተኛዋማ ጉድህን ይዛልህ ከች!" የመብከንከን ሳቅ፤ ምናባቷ ያብከነክናታል?

"የምን ጉድ?" ድንገት ሲፈን አይኔ ላይ ድቅን አለች:: ከአስር አመት በፊት እንደሆነችው ሆና:: አበባ የተነሰነሰበት ቀሚስ ለብሳ፣ አበባ የሆነ ፈገግታ ለግሳ...

@OLDBOOKSPDF

"አላውቅም እንዴትል? የኔ ቢጤ መሰለችኝ:: ልጅ አዝላ ስትንከረፈፍ መጣች:: አልአዛር አላለችም በሌላ ስም ነው የጠራችሁ:: አላውቀውም ስላት እዚህ ቤት ያለው አትለኝም?"

"ማንን አለች" ቾምቻሚውን ለልቤ ያቃምኩት ይመስል ልቤ ተደነቃቀፈብኝ:: ጉዝጓዙ ላይ ተንቆራጠጥኩ:: እስክትነግረኝ እልፍ ዘመናት እየተንቀራፈፉ አለፉ::

"ሊሊ"

እ?

"የለማኝ ሊሊ አለው እንዴ?"

ጠዋት "ታለ" የሚል ጥሪ የሰማሁት ከእሷ ነው? ለማኝ ሆነች? አሁንም ወንድሚን ታዝላለች? ወይስ ልጅ ወልዳለች? ለምንድነው ሀዘን እየተጎተተ የሚከተለኝ? የሠባራ ባቡሯ ሠባራ ዕድል፤

"ኧረ ቆይ መልዕክትም ትታለች" ብላ ወደቤቷ ሄደች:: የሚያምር እግሯ አስጠላኝ:: ብርድ ጠብስቆ በጣላት::

የምን መልዕክት? የምን? የምን?...

...ናትራ መልእክት ያለችውን ይዛ መጣች:: በወጉ የተጣጠፈ ወረቀት ነው:: ናትራ መልእክቷን አድርሳ በዝናብ እንደራሰች አልጋ ላይ ተቀመጠች::

"ይቺ ዕዋ ከእኔ ትለፍ፣ ይቺ መራር ዕዋ"

ወረቀቱ ከባድ ነገር ተጠቅልሎበታል:: ሊሊ ዝርዝር ሳንቲም" አሚልታ በድምሩ አስር ብር በወረቀት ደብዳቤ ጠቅልላ አስቀምጣልኝ ኖሯል:: ደብዳቤውን ሳነበው ሞከርኩ:: ለአረብኛ ዕሁፍ የሚቀርብ የተያያዘ የቀለም ሽንተረር ነው:: እንደ ጅራት ያለ ነገርም አለው:: ከአየር ላይ ፎቶ ግራፍ የተነሳ የአባይ ሸለቆን ይመስላል:: የልቧን ሳይ ውጣ-ውረድ፣ አዘቅት ሽንተረር፣ ተረተርና ሸለቆ ይሆን የሳለችልኝ:: የፅሁፍ ጥበብ ተልዕኮውን ያልተማረችው ሊሊ ከገለፀችልኝ የተሻለ ግብ ይኖረው ይሆን?

@OLDBOOKSPDF

"ይቺ መራር ፅዋ ከእኔ ትለፍ" ስላለ ማን ዕጣፈንታውን ሳያስተናግድ ተሻገረ? የሳንቲም እና የወረቀት ቸንካሮቼን ልቤ ላይ ቀብቅቤ...

* * *

የሊሊ ፅሁፍ ላይ ለሰባ-ሰባተኛ ጊዜ አፈጠጥኩ።እንደካርታ ሽንተረር፣ ተረተር፣ ሰርጥ፣ ስርጓጉጥ፣ ጅረት፣ የተሰበረ መሬት፣ ሸለቆ... የሚመስል ነገር ይታያል። ምን እያሰበች እነዚህን ምስሎች እንዳስፈረች የገባኝ መሰለኝ። እንደጥንታዊ ግብዖች፣ ሱሜሪያን፣ አሻንቲዎች... ስሜቷን ያለወካይ ፊደል በጥሬው ያስፈረችው መሰለኝ። ሽንተረርና ተረተር የልቧ ነው! ሰርጥ ስርጓጉጡ ህይወቷ ነው! እንደሸለቆ ውኃ በማይገኝ አጣብቂኝ ውስጥ የሚፈሰው ዕጣፈንታዋ ነው....

...ደጃፌ ተቆርቆረ። በሩን እንደዘጋ ልበኛ ተነስቼ ከፈትኩ። እነ እማሪት ሦስት የረገቡ የበገና አውታሮች መስለው መስመራቸውን ሳይጠብቁ ገቡ። ቀዳሚው ሙሴ ጸሊም ሲሆን ተከታዩ ስምዖን ዘእምድ ነው። ዮሐንስ ሐዊር እገጩን ታስሮ የተንተተ መስሎ ገባ።

"ዛሬ የት ተገኛችሁ?" ወደጉዝጓዜ ተመልሼ። የረድ ሠርዊን የውርደት አዘቅት መውረጃ ሠልስት ለመድረስ የመጡ ሆኖ ተሰማኝ።

ሙሴ ጸሊም የያዛትን አነስተኛ መጽሐፍ ግራ እጁ ላይ እየፀፉ "ምን እባክህ ኢምባሲዎች ጋዜጠኛ ይረዳሉ ብለውን በከንቱ ለፍተን መምጣታችን ነው።"

ዮሐንስ ሐዊር እና ስምዖን ዘእምድ መንገር ያልፈለጉት ምስጢራቸው ስለነበር የተሽማቀቁ መሰለኝ።

"ቁጭ በሉእ" ብዬ አልጋውን አመለከትኩ። ሙሴ ፀሊም አኩፋዳውን በትዝብት አይቶ ወዲያ አለውና ተቀመጠ። ተጠጋግተው ተቀመጡ። ዮሐንስ ሐዊር እንደውሻ ሲቀመጥ ይረዝማል መሰል እማሪት ትክክል የተቃኘ የበገና አውታሮች ሆኑ። ስምእን ዘእምድ የሱሪ ኪሱን ለመፈተሽ ቀኝ እግሩን ሲዘረጋ የጫማው ሶል ፊቴ ላይ ተደቀነ። ሶሉ ፈንጣጣ የወጋው ይመስላል። እንደ ረድ ሠርዊ ቸምቻሚ በሚያደነቃቅፍ ኮረኮንች ላይ ሲሄድ እንደኖረ ይመስክራል።

ስምዖን አንድ ወደጎን የረዘመ ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ ሰጠኝ።

@OLDBOOKSPDF

"ምንድነው?" እየተቀበልኩ

"ጥቅስ ነው" ስምንን ዘአምድ የሚታማበት አንዱ ጉዳይ የጥቅስ መጽሐፍ እንጂ ሌላ አለማንበቡ ነው:: የሚፅፈው መጣጥፍ በጥቅስ የተሞላ ነው:: አነበብኩት:: "I hope for nothing, I fear noting, I am free" ይላል::

"ምንድነው?"

"የታላቅ አምላክ - የለሽ ሰው ጥቅስ ነው:: መቃብሩ ላይ የሰፈረለት ግሪካዊ ደራሲ ነው:: ስሙ ጥቅሱ ሥር አለ፤ እየው::

"Nikos kazantazakis"

አዎ ስሙ ስለማይያዝልኝ ነው፤ ከሞት ባሻገር ተስፋ መጣልና በፍርሃት መርበድበድ ነፃ እንዳንወጣ አደረጉን::" አንዳንዱ ጥቅስ ብቻ ስለሚያነብ ተናጋሪውን ወንዱን ሴት አድርጎ ይጠቅሳል:: አልነገርኩትም እንጂ ደራሲውን አውቀዋለሁ:: አምላክ የለሽ አይደለም:: እንደውም ገዳም ገብቶ እንደነበር አንድ ቦታ አንብቤያለሁ:: ይሄንን ብነግረው ስምዖን ዘአምድ ይከፋዋል:: እሱ የሚፈልገው ሰው ያላገኘው ጥቅሱ እሱ ዘንድ እንዳለ እንዲመሰከርለት::

"ይገርማል" አልኩና ጥቅሱን አቀበልኩት

በደስታ ቆነጥነጥ ብሎ "ወረቀት ስጠኝ ልገልብጥልህ" አለኝ

"በኋላ"

"እየሀ ተስፋ ማድረግና በፍርሃት መሸበር በሰው አቅም የማይዘለሉ የህይወትና የሞት ዙሪያ ሽምጥ አጥሮች ናቸው"

ምን ማለቱ ይሆን?

"...ሰው ሆኖ የተፈጠረ ከእነዚህ አያመልጥም:: አምላክ የለሽም ቢሆን...."

"የመዒዒት ጥቅስ"

"መዒዒት አትበለኝ ብዬሃለሁ"

@OLDBOOKSPDF

በፀብ አማሪት ሲፈርስ ነው። ሥስቱ የበገና አውታሮች ቃኝታቸውን ሲስቱ?

"የያዝከው መጽሐፍ ምንድነው?" ስል ሙሴ ፀሲምን ጠየኩት።

"አንተ ያዋስከኝ ነው። "The plague" የአልበር ካሚዩ በጣም ወድጀዋለሁ። ብታምንም ባታምንም ለአራተኛ ጊዜ እየደገምኩት ነው።

እኔ ደግሞ አስጠይፎኝ አልጨረስኩትም። የአይጥ መአት ከተማ ሲወር፤ የአይጥ ደራሽ የሰውን ልጅ ሲያጥለቀልቅ፤ ተስቦ ሲናኝ። ትክ ብዩ አየሁት። በእባብ ተከበብኩ፤ ጊንጥ መሀል ቆምኩ ብሎ የማማረሩን ያህል ንቁ እና እራሱን ጠባቂ መንፈስ የለውም። ይሁንና ያንቀላፉ ሩሁ ሲባትት የእባቡንና የጊንጡን ሥራ የሚያቀላጥፈው እራሱ ነው።

"በትክክል የመጣችሁት ለምንድነው?" ምን አበሳጨኝ? ተያዩ:-

"በእርግጥ የመጣነው ኢምባሲዎችን እንዲረዱን ጠይቀን ስንመለስ ነው። ለዚህ ያዘጋጀነው በጀት የለንም አሉ።" ብዙም ንግግር የማያበዛው የዮሐንስ ሐኪር ነበር።

"እና?" የሀገር ጭምር ውርደት መስሎ ታየኝ።

"እ-ና ዶክተር አሮን እንዲያናግርልን ከጋዜጠኛው ተወክለን ነው።"

"አንተ አውቶብስተራ "ላዳ" ታክሲ አለኝ ምናምን ትል የለም?"

"ቢኖረኝስ? ላጽቂት! ያ ሌላ፣ ይሄ ሌላ..."

ፀጥታ ሰፈነ። ፀጥታ ስድ ድምፅን ከማላጣት ውጭ እራሱን የሚገልፅበት ተጨባጭ ህልውና እንደሌለው የገባኝ መሰለኝ። የሙሴ ፀሲም አፍንጫ እየተመዘዘ አይኔ ስር የተደቀነ መሰለ። ግንደ ቆርቋር ነገር።

"ሴሽ አላችሁ?" 'ቴፕ አላችሁ?' ትላለች መሰሎኝ። ድንገት ቤቱ በሮዝ ቀለም ተሞላ። የሙሴ ፀሲም አፍንጫ ወደ አፎቱ ገብቶ ዓይኖቹ ተመዘዙ።

"አሴ፣ ከማታው ብር፣ ከዛ እንኳን..."

@OLDBOOKSPDF

"ውሰጅ" አልኳት ከማውራቷ በፊት።

ወደሼልፉ አምርታ ከተቀመጠበት ከነወረቀቱ አነሳችው "ወረቀቱን አስቀምጪው" አልኳት።

ሦስቱ የበገና አውታሮች በተመሳሳይ የያሬድ ዝማሜ ላይ ያሉ መሰሉ። የናትራ አጭር የሌሊት ልብስ እንኳን አጎንብሳ...

"ትንሽ አትቆይም?" ሙሴ ፀሊም ደፍሮ ናትራን ጋበዘ። ሳትግደረደር

"እሺ!" ጉዝጓዙን ተጋራችኝ ስድስት ዓይኖች ተዘረገፉባት። ሰብሳቢ ያጣ ጭኗን...

"አንተም ጋዜጠኛ ነህ?"
"አዎ"
"አንተም?"
"አዎ ግን የምተዳደርበት "ላዳ" ታክሲ አለኝ።"
(እቤት! ይሄ "ላዳ" እዳው)
"አንተም?"
"አዎ"

ሦስት "አዎ" ሰብስባ ምን ልታደርገው ነው? ግራ ጎኔን ሞቀኝ። ተራቁታም ትሞቃለች።

"እኔ ናትራ እባላለሁ! አንተስ? አንተስ? አንተስ?"
ሦስት ስም ሰብስባ...
"የአልዩ ባለቤት ነኝ" አለች ጎኔ ተሸጉጣ።
አይናቸው እንደ ዒሊ ወደ ድንጋዩ ተሳበ።

"ውሽቱን ነው እኔ የማፈቅረው አለኝ፣ ጨረቃን እና ብዙዬን አስታቅፎ 'ጥፊ' ያለኝ።" ዘወር ብዬ አየኋት። ብሮቹን ወደ ያዘችበት እጇ አቀረቀረች ሲያዝን ደስ የሚል ሰው አለ? ፊቷን ማዘን ነበር የጎደለው?

"አንድ ትምህርት ቤት መሆን አንችልም ትምህርትሽን አቋርጪ ወይ እኔ ማስተማር ላቋርጥ አለ። እኔ አቋርጣለሁ አልኩት"

@OLDBOOKSPDF

እኔም እስከዛሬ ያልሰማሁት ታሪክ ሆነብኝ።

"እማረብሽ ሲሉ እንዳልሰማ! እስከመለስ ድረስ አሉ። ፍቅር በዛብኝ ይላል፣ በዚሁ ከቀጠልኩ እሞታለሁ ይላል!"

ዛር ነው'ዴ ያፈቀረችውጥሩ ነገር ስታገኝ የማያስወድደው?

"እኔና አልአዛር! ሁለት በፍቅር የተጎዳን፣ ጎን ለጎን ጎጇችን ውስጥ ከፍቅር ለማገገም የምንጥር ወፎች ነን። አይደል?"

ይሄ የእሷ ውልድ ሀሳብ አይደለም። ያየ፣ ያሰላሰለና ያነባበረ እንዲሁም በዚህ መልክ የገለፀ ሌላ ነፍስ ነው።

ናትራ ከጉዝጓዙ ተነስታ እጇ ላይ ታንቀረቅብ ከነበረው ገንዘብ የሆነ ያህሉን የሊሊ ደብዳቤ ላይ ቀንሳ ወጣች "የሮዝ ቀሚሷ ቅሪት ቀስ በቀስ ከቤት ውስጥ ወጥቶ ሄደ።

"ናትራ! ናትራ! ናትራ!" የሚል ድምፅ ከወደውጭ ሰማሁ።

ሦስቱ አውታሮች ከርግበት አለም ባትተው ተመለሱ።

"ይኸው ዶክተር አሮን መጣ" ሙሴ ፀሊም ተቁነጠነጠ። ለሌሎቹ ምን አገባን? ለኛ ይጠይቅልን፣ ለሦስታችን።" ወደ እኔ ዞረ "አልአዛር ላጽቂት፣ አንተ ትፈልጋለህ?

"አልፈልግም፣ ሙሴ ፀሊም"

"እፉኝቱ ባወጣልኝ ሥም አትጥራኝ፣ ስትፈልግ የራስህን ስም ስጠኝ።"

"ቤቶች?" አሮን

"ደጆች" ይባላል ብሎኛል "ደጆች"

"ቤት ለእንቦሳ"

"እሰሩ እንቦሳ" ገባ "ለመጀመሪያ ጊዜ የሚገቡበት ቤት ነው 'ቤት ለእንቦሳ' የሚባለው።"

"ጥሩ ምኞት ነው፣ ምናለ ሁሌስ ቢባል? ለመሆኑ እንቦሳ ምንድነው?" ሲል ጠየቀ

@OLDBOOKSPDF

"ጥጃ ነኝ"

ከት ብሎ ሳቀና "አይደለም፣ እንደሱማ ቢሆን አንተን ከቤት እርባ እያልኩህ ነው::"

"ታዲያ?"

"እንቦሳ ልጅ ነው:: ይሄ ቤት ልጅ ይወለድበት የሚል ምኞቱን እየገለፀ ነው:: ጤና ይስጥልኝ" አለ ወደ ሦስቱ አውታሮች ዞሮ

"ሠላም፣ ሃይ፣ ጤና ይስጥልኝ" አሉት::

"ክብሩ ይስፋ" እያለ መቀመጫ ቦታ ፈለገ:: ስምምን ዘለምድና ዮሐንስ ሐዲር ተነስና እኔ ጎን ተቀመጡ የበገናው አውታር ፈረሰ::

"እግዚሀር ይስጥልኝ" ተቀመጠ:: "ሙሴ ደህና ነህ? እናንተስ እንዴት ናችሁ?..."

እኔና እርን የምንጨባበጠው በእጅ ሳይሆን በተፍተለተለ ነገር ነው:: ፀጉሩን ከግራ ወደ ቀኝ አስተኝቶ መራቶት የጀመረ እናቱን አለበስ፣ በተንጮለጮለች አይኑ ከመነፅሩ ባሻገር አትኩሮ

"ሥራህ ከምን ደረሰ?"

እኔ ቤት ሰው ሲያይ ሆነ ብሎ ስለሥራ ይጠይቀኛል:: የእኔን ቤት እንዳይለምዱ በሥራ ስም እግራቸውን እንዳስይዝ እድል ሲሰጠኝ ነው::

"የቱ ሥራ?" አውቄ፣ ለምን? እንጃ!

"የኢትዮጵያን ነባር ሰውቶች በአውሮፓው የፍልስፍና አውድ አንፃር ለማጥናት የተነጋገርነው::"

"ብርሃን ሁን ሲል የሆነለት እግዚአብሔር ብቻ ነው::" አልኩት፤ የእውነት ተስፋ መቁረጥ ተሰምቶኝ::

"በገባእን ዐሐይን ያቆመም" አለ:: እኛ የተፈጠርነው ጥረን፣ ግረን ለዋዊ ተአምራትን እንድናደርግ ነው::" ጨረር የሚተፋ ጨለልጨል ዓይኖቹን ፈራኋቸው::

@OLDBOOKSPDF

"ለጥናቱ ፈንድ አስፈቅጄ ነው የመጣሁት:: ትንሽ የድምፅ መቅረጫም አምጥቼልሃለሁ:: ጥናቱን ብቻ እንድትሰራ፤ ጋዜጠኝነት ያንተ ቦታ አይደለም::"

በኢትዮጵያና በሕዝቦቿ ስም የተለመነ፣ የፎቅ ጫካ ውስጥ፤ በልመና ሀፍረት አቀርቅሮ የቆመ ሰው::

"ፈንድ አያስፈልገኝም፣" ሙሴ ፀሊም ጣልቃ ገባ::

"እሱ ካልፈለገ እኔና አንተ ሆነን..."

"ይሄ ያንተና የእኔ ሥራ አይደለም፤ የእሱ ብቻ ነው::"

ሙሴ ፀሊም አልተሸማቀቀም እንደውም አፍንጫውን መዝዞ ወደ አሮን አዞረ::

"የትኛው ሀበሻ ነው እንደዚህ አይነት ትልቅ ጥናት የሰራው?" አሽሟጠጠ፣ ሲያሽሟጥጥ አፍንጫው ተቀልብሶ አፉ ውስጥ ሲገባ የፈለገ መሰለ::

"ስለእኛ ፍልስፍና፣ ሥነፅሁፍ፣ ታሪክ፣ በል ሥነ ሰብ... በሙሉ ጥናቱ የባዕዳን አይደለም? በፍልስፍና እንኳን ዶክተር ሳምነር ለ"Ethiopan phylosopy" ባያጠናቅሩ ኖሮ..."

እኔና አሮን ላይ ቀጥተኛ ጦርነት የከፈተ ሆኖ ተሰማኝ፤ አሮን ቀጥል በሚል አኳኋን ያዳምጠዋል::

"መዝገበ ቃላቱን ቢሰራ ሉዶልፍ ባዳው፣ ሥነ ፅሁፍን ቢተነትን ገሬርድ፣ ኬን... ሥነ ሰብ ላይ አዝረክርከን የተውነው ቢሰራ ማነው ያ፣ አምጡልኝ..." አፍንጫውን ወደ ስምዖን ዘአምድ ጠቆመ::

"ሞልቬየር" አለለት

"አፉ ቁርጥ ይበል መዔዒት"

"መዔዒት አትበለኝ ብዬሃለሁ" እንተመተመ::

ላሳፍረው ፈልጌ "ሞልቪየር ስለአማርኛ ደራሲዎች "Black Lion" የሚል መጽሐፍ ነው የጻፈው:: እንዴት ሥነ ሰብ ውስጥ ገባ?" ስል አፋጠጥኩት::

@OLDBOOKSPDF

"ተወው ላጽቂት ሞልቪየር ሌላም መጽሐፍ አለው:: 'Tradition and change in Ethiopia' የሚል:: እሱን ሳያነቡ ማስተማር ቀርቶ መማር የሚከብድ ይመስለኛል::

ጥርሴን ነክሼ ዝም አልኩ::

"አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከማለት ኦብሳላ ዩኒቨርሲቲ ቢባል ብድር መመለስ ይሆን ነበር:: እንዳለ በእኛ ላይ ያጠኑት የካናዳ ጄስዊቶች አይደሉም እንዴ? ፈረንጅ የማንጠቅስበት በእኛ ላይ የተሰራ ጥናት አለ? የለም!"

ናትራን ጠርቼ አይኑን ካላስጎለጎልኩት የሚያቆም አይመስልም:: እኔ የማውቀው ጉዳይ ሆኖ ሙሴ ፀሊም ሲያነሳው ለምን ተናደድኩ? ምንም ነገር ቢሆን እሱ ካነሳው ለመጉዳትነት ስለሚጠቀምበት?

"ሌላው ቀርቶ የጥበብ ሥራዎቻችን ባዕዶቹ ባይደባለቁበት የሚሰምር አልነበረም እያልኩ አስባለሁ:: ደራሲዎቻችን፣ ገጣሚዎቻችን፣ ጋዜጠኞቻችን... ሁሉ በደም ግማሽ ባዕዶች ናቸው:: በዓሉ፣ ከበደ ሚካኤል፣ ጳውሎስ፣ መስፍን፣ ተስፋዬ፣ ኃይሌ..." ሙሴ ፀሊም እንደ እባብ መንደፍ፣ እንደጊንጥ መመረዝ፣ እንደ አይጥ ሰው የሚወደውን ማበላሸት እንደ እንቁራሪት ማስፀየፍ... በህይወት ለመቆየት አስፈላጊው ይሆን?

"እንተንም መጥቀስ ይቻላል" ብሎት አረፈው:: እንደጥንብ አንሳ የዞረው፣ እንደ እባብ በደረቱ የተሳበው፣ እንደ አይጥ የተሽሎከለከው እዚችጋ ለመድረስ ነበር?

የምለው ጠፋኝ ፀጥታ!

"ምሳ በልታችኋል፣ እኔ እርቦኛል..." እርግን ላይርበውም ይችላል:: ግን ሲጋብዝ እንኳን እንዳይሰማ አድርጎ ነዋ! የተሰማውን ለማጠን ዕድል ሳላገኝ ቀረሁ::

"ጥቅሱን ልገልብጥልሃ" አለኝ ስምዖን ዘአምድ

"ጥቅሳም! ጥቅስ ብቻ!" አልኩት በአይኔ::

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፯

...ከዚያ እስከዚህ ድረስ እቡይ ዘመን ተደንብቶብናል። እስማታዊ ዓለም ውስጥ፣ ተሳትፏችን እንደባህር ትል፣ ፈልቶ በቀዘቀዘ የድንጋይ ኩርፍርፍ ውስጥ፣ ፈሪልቡና እያስታመምን ሌላ ዘመን መጠበቅ ሆነ። ባለብዙ ደጃፍ ጉሮኖ በመፍጠር እራስን መታደጊያ የእይጥ ደመነፍስ እንኳ የለንም...

...መነሻ ትናንታችንና መድረሻ ነገአችን እንደ እትብታችን የተቀበረበት ጠፍቶን ዛሬአችን ላይ መተራመስ የማይለወጥ ዕጣፈንታችን ሆኗል።

...የተበጠሰ ጣት እንደ እንሽላሊት መሽሽጊያ ሲያስስ የመመልከት ያህል ህልውና ተአምር ናት። እንደገና ሌላ ጣት... ከጣት ላይ ሌላ ጣት፣...ጣት፣ ጣት፣ ጣት... ከምንጩ የተጨለፈ ሌላ ምንጭ... ነባሩን ምንጭ ያድበሰበሰ ሐሰተኛ ምንጭ በተተኪው ሌላ ምንጭ ይረሳሳል።

በሀሳብ ከየት ተነስቼ ምን ላይ እንደደረስኩ ጠፋኝ። ከቤቴ ወጣሁ፤ እንደ ዳዊት መዝሙር ትንቢት፣ ተግሣጽ፣ ተማፅኖን... የሚዘከረውን የቅንብቢት መንገድ ተያያዝኩት። የከሰረ ቁጠማ ሻጭ አገረከርኮ የተወው ጉዝጓዝ በዝናብና በነፋስ ተጠርጎ አላለቀም። ጠጅሳር፣ እርቲ፣ ከሴ፣ አደስ... ይሸታል። ለተማጸኖ የተጠራች ነፍስ በሽታው ማልላ ለጽድቅ ሳይመስላት አይቀርም። የአቶቡቱ ሁለተኛ ምዕራፍ ከጠንቋይ ማረፊያ አግበስብሶ ያመጣውን የባህር ዛፍ ዝንጣፊ ብቅ እንቅ ላይ ረብርቦታል። ጠንቋይ ማረፊያ ላይ አውሊያውን መዘየሪያ የሚያስተምጡት ሳንቲም የሌላቸው የባህር ዛፍ ዝንጣፊ በትነው ስለሚያልፉ እሳቱ ገዘየራው ለብቅ እንቅም ይተርፋል። አንዳንዴ ልጆች የአውሊያውን እስራት ብቅ እንቅ ላይ ይፈልጋሉ። በርጥበት በስብሶ የተጣበቀ የብር ኖት በደለል ተቀብሮ ያገኛሉ።በአይኔ እያሰስኩ ብቅ እንቅን አለፍኩ።

@OLDBOOKSPDF

"ሠላም ለኪ ቅንብቢት፣ ሠላም ለኪ ለመምጎፃን ቅንብቢት!"

ሲሲ አይነህሲናዬ ላይ ተደቀነች። ስለምን ቅንብቢትን መጥኝ አለች? እመፅተሰራባት እንጂ መች አመፀች? ወንጀል ተሰራባት እንጂ መች ተወነጀለች? ልጅነቷን ተቀማች እንጂ ማንን ነጠቀች?... በደልኩ፣ ማረኝ የምትለው ለየትኛው ጥፋትዋ ነው?...

ድሬን አልፌ የልደታን አፀድ ታክኬ ቁልቁል አዲስ አበባን ለመመልከት ሞከርኩ። እይታው አይኔን አልጠቀመውም። ወደጠንቋይ ማረፊያ እቀብቱን ተያያዝኩት። ጉልበቴ ብርክ-ብርክ ማለት ጀምሯል። ሁሉም ነገር ዕዋፈንታ ነው። ለራስህም ቢሆን የሰጠኸውን ያህል ነው የምትጠይቀው። ሆድን በእፍኝ ችምቻሚ ከደለሉት ጉልበት ዳገት ላይ መለገሙ ይቀራል?

ወሎ ሰፈር ከሩቅ ትታያለች። ማን እዚያ ደርሶ? ቢደረስስ ጠላው ያለዋጋ ይገኛል? በብላሽ ደጃፍ ቁጭ ተብሎ የአዝማሪ ግጥም ይደመጣል? የሰጠኸውን ያህል ነው የምትጠይቀው። መምህር ሳለሁ ይሄን ቦታ አዘወትረው ነበር። አንዳንዴ ለሃሳብ ማዳበሪያ የሚሆኑ ግጥሞችን ከአዝማሪዎቹ አገኝ ነበር።

"ሆዴን ሳማክረው

ልቤ ይላል ፈንጠር፣

እራሴን በራሴ

ጀመርኩኝ መጠርጠር!

ጥርሴ ለምላሴ

ቀና መልስ አይሰጠው፣

ጊዜው ነው እየሩ

የሚለዋወጠው?"

የህይወትን ወለፈንዲነት (Absurdity of life) ለማስተንተን ግጥሙ ልክክ ያለ ምሳሌ ነበር። በአንድ ጣላ ጠላ የገዛሁት ነገር ዕውቀት። ዶክተር እርገን እንድሰራ ለሚፈልገው ጥናት አንዱ የሚተነተነው ይሄ ግጥም ነው። ለመሆኑ ጥናቱን እሰራዋለሁ?

@OLDBOOKSPDF

ሙሴ ፀሊም ዘአምድንና ሐዒርን አስከትሎ በመጣ ማግስት ደጃፌን ቆፈቆፈ:: ስወጣ በክላሰር የተከተተ ወረቀት እያሳየኝ

"አልአዛር ላጽቂት"

"እነሆ ሙሴ ፀሊም" አልኩት ደጃፉን ይገፎ ሀሳቡን አደናቅፎ ሲመለከተኝ ቆይቶ፡-

"ጥናቱን ጀምሬዋለሁ፤ ለዶክተር አሮን ልሰጠው"

"መች ሥራው ተባልክ? ተብለሃል እንዴ?" ለዶክተር አሮን ቅፅል ሥም ሳያወጣ መቅረቱ እየገረመኝ::

"ጀምሬዋለሁ፣ ጀምሬዋለሁ"

"እሱ ያንተ ጉዳይ ነው"

"እስኪ እኔ ለፍቼ ፈንዱን እሱ ይበላው እንደሁ አየዋለሁ" አፍንጫው አስግጎ አይኔ ውስጥ ሲገባ ይጣጣር ጀመር::

"ጉዞውን ነው የማደናቅፍበት፣ ይሄ ሲላ"

"አሁን ሂድ ከዚህ"

"እከሳለሁ፣ እከሳለሁ:: የቅጂ መብቴንም አስከብራለሁ:: አንተ ብትሆንም አትሰራውም::"

እንደ አይጥ የሰው ወዝ የነካካው ነገር እየፈለገ የሚቀረጣጥፍ ነፍስ አለው::

የጠንቋይ ማረፊያ ደረቅ ዛፍ በቅርበት ይታየኛል:: ከመድረቁ የመንጣቱ ነገር መንፈሳዊ መልእክት ያለው ለመሆኑ በምስክርነት ይቆማል:: ወሎ ሠፈር ጠላዬን ገርገጭ እያደረኩ ስለዛፉ ጠይቄ ነበር::

"መብረቅ ነው አስደንግጦት እንዲህ ሆኖ የቀረው:: ቢመታውማ ይተረተር ነበር:: አንዴ ሀይ! ሲለው ጊዜና እንደልብ በድንጋጤ ቀጥ ብሎ ቀረ::"

የሚደነግጥ ዛፍ?

@OLDBOOKSPDF

"እይደለም" አለ ሌላ ጠላጠጪ ገፌቱን ከምላሱ ላይ እያፌናጠረ።

የመጀመሪያው ሰው እውነቱ ሊስተባበልበት ሲሆን ጊዜ ተቆጥቶ "ታዲያ?" ብሎ አፈጠጠ።

"የአውሊያውን አስራት እያነሱ ቢያስቸግሩት በንዴት እንዲህ ሆኖ ቀረ። ብንለማመን፣ ብንለማመን አልመለስ አለ።"

የሚናደድ ዛፍ?

ጠላው አሁን-አሁን ሲለኝ ገፌቱን በምላሴ አፈናጠርኩ።

ከላይ ሆኜ ሳያት አዲስ አበባ ላይ ሰለጠንኩ። ከተማው ለመታየት ከሚንጠራራው ይልቅ ለመደበቅ የሚሞክረው ሳይልቅ አይቀርም። እንደ እኔ የሰርንጉጥ ውስጥ አይጥ... ሩቅ የጣልኩትን ዓይኔን ሰበሰብኩ። ጠንቋይ ማረፊያ በመናፍስት ህብረት ክብሩን የጠበቀና ፀጥታውን ያሰከነ የአትክልቶች ዙሪያ እቅፍ፤ ሞት እንደዚህ ፀጥታውን ያስከበረ የተከሉች ዘላለማዊ ሥፍራ እንደሆነ ተገዝተው ቢነግሩኝ የሞትን ፅዋ እንስቼ ለመጨለጥ ወደኋላ የምል አይመስለኝም።

"እንደምን ዋላችሁ?

ደምዝ ያልተከፈላችሁ!

ለክልክሉሳ ነገራችሁ?

ለጠቋር አለቀላችሁ?

ወይስ ደምቀለቡን ዳኛኝ አላችሁ?"

አይኔን ጨፈንኩ። ብቸኝነቴን ፈልጌው አልነበር ወደ ጠንቋይ ማረፊያ ያሻቀብኩት? እና አፈትጉሣን ዮናኤል ሲመጣ ለምን ከእስር የተለቀቅሁ መሰለኝ? አይኔን እንደጨፈንኩ ቃል ሳልተነፍስ አፈትጉሣን ነገር እስኪያክል ጠበኩ።

"አውሊያ ልትለማመን መስሉን በፀጥታ ተከተልንህ" አለ። ዶክተር አሮን ነው።

ሦስተኛ ሰው ይኖራል? ማን? አሰብኩ፤ ምናልባት ናትራ... አሁንም አይኖቼን ሳልገልጥ

@OLDBOOKSPDF

"የደኑ ግርማ ሞገስ ብቻ ለአምልኮ ይጋብዛል:: መቼም መናፍስቱ እዚህ ላይ የተሰቀሉት ለተፈጥሮ ውበት ልዩ ፍቅር ቢኖራቸው ይመስላል:: በዚህ የተፈጥሮ ትንግርት ይዘን ብናምላቸው አይማለዱን ይሆን?"

እጆን ብቻ ለዳበሳ ሰድጄ ሌጣው አፈር ላይ ቁጭ አልኩ:: ዶክተር አሮንን ማዳመጥ እንዲህ ዓይንን ጨፍኖ ነው::

"ጠቋር፣ ባዶስ፣ ብር አሮንጋ፣ ወርቁ፣ ዋስ አጋች፣ ጌታ ይቅጨው፣ ጢሞቲዎስ..."

"ይሄ ሁሉ ምንድነው?" አሮን ጠየቀ

"የዛር መንፈስ፣ ህብረት ያለው መንግሥት ስለመሰረቱ እንጂ የጥቅም ፍጅት ውስጥ መግባታቸውማ አይቀርም ነበር:: አይ ሰው! ከዛር ይነስ?" አጠገቤ ሲቀመጥ "እክክክክ..." አለ::

"ዮናኤል ስሞቼው የማላውቅ ሥም ነው፣ ቅዱስ ነው፣ ሰማዕት ውስጥ ይካተታል? ወይስ እዚህ ግድም ከመናፍስቱ ጋር እሱም እርስት አለው?..." ስል ዶክተር አሮን ከትብሎ ሳቀ::

"ስም የመጨረሻው "ኤል" ከሆነ ከመላእክቱ ወገን መሆኑ ይታወቃል" አለ ዮናኤል:: በክርክሩ የበላይነት እየተሰማው::

"እንደ ሳጥናኤል?" አልኩት

"አዎ፣ እሱም ወደቀ እንጂ መልአክ ነበረ፤ ያውም ሊቀ መላእክት" ድምፁን አክሳትሮ ወጉን ቀጠለ፦

"አባቴ በህልማቸው ወንድ ልጅ ትወልዳለህ፣ ስሙንም ዮናኤል ትለዋለህ የሚል መልእክት ይደርሳቸዋል:: አባቴ ሊቅ ቢሆኑም የሥሙን ፍቺ እስካሁን አልደረሱበትም:: አንዳንዴ እመሌ ግራ ሆኖ ሲያስቸግራቸው 'ያ በህልሜ ያየሁት ሰው ሳጥናኤል ይሆን እንዴ?' ይላሉ::

"እኛም እንጠራጠራለን" ዛሬ በነገር ሰነፈልኝ:: ዶክተር አሮን ዝም ብሎ ፀጉሩን ወደኋን እያስተኛ ይስቃል::

"ይልቅ እጣ ክፍልህ የሆነውን ዛር ለይተህ ነው እዚህ የመጣኸው?" ሲል ጠየቀኝ::

@OLDBOOKSPDF

"የምን ዕጣ ክፍል?"

"የዛሬን ሁሉ ሥም ፃፍና ዕጣ አውጣ። ያለ ዕጣ ክፍልህ ሄደህ እንዳየጣፋህ። እለነገርማ ካልጠፋ ቦታ ዛሮቹን አልተጎራበትክም።"

የረድ ሠርዌ ሀሰተኛ ኑብይ ትዝ አለኝ። የቱጋ ይሆን የጠርቅ ድንኳኑን የሚጥለው? ለረጅም ሰዓት ዝም ተባባልን። አርምሞ አላዛር ዘአርምሞ፤ ረድ ሠርዌ። እንደ ዮሴፍ ለጠፍጮ ቤት ባርነት ሽጬው የመጣሁ ያህል እየተሰማኝ ነው። ከሱ የተሻለ ክብርና አማራጭ ያለኝ ይመስል ለሰምን በኩሊነት ሳልቀጠር ቀረሁ? ቁጭት እንደሻህላ ልቤን በላው።

"እንዴት አርቦኛል" አለ ዶክተር አሮን።

መጋበዝ ፈልጎል ማለት ነው። ትዝ ሲለኝ ልቤ ወደ ወሎ ሠፈር ተነጠቀ።

"ከጠላ ጋር ክክ ወጥ የሚሸጥበት፣ እዚያ መንገዱን ተከትሎ የተመሰረቱ ቤቶች ውስጥ አለ። ወሎ ሠፈር ይባላል..." ተናግሬ የጨረስኩ አልመሰል አለኝ።

"ጥሩ እንሂድ፤ ቁዘማው በቂያችን ነው። አርምሞ ሲለመድ ሱሱ ከጋይ ይጠነክራል።" አለ። መልኩና ንግግሩ አልገጥም ስላለኝ አይኔን ጨፍኜ አደመጥኩት።

"የእነ እንቶኔ በረከት ያለበት ሳይሆን አይቀርም" ብሎ ዮናኤል ቀደመ። ከቁመቱ ማጠር ጋር ዓይነሥውር የሚመራ ሕፃን ልጅ መሰለ። አረማመዱ እግሩን በረጅሙ ይለቅና በተረከዙ መሬት ወግቶ በመቀጠል መዳፉን ያሳርፋል። ምድር ክበሮ ብትሆን ዮናኤል እንዴ ሲራመድ ሁሉቱ ትጮህ ነበር ስል አሰብኩ። በተረከዙ እየጠቆመ በመዳፉ ይፀፋታል። ቋ-ድም፣ ቋ-ድም፣ ቋ-ድም....

"ይኸውልህ፣ ዮናኤል አንድ ለአማርኛ ሥነ ሰሁፍ እንግዳ የሆነ ልቦለድ ፅፎ አስነበበኝ። ከፍፃሜ ወደ ጅምር የኋልዮሽ የሚተርክ። ልብ ሰቀላውን ገድሎ በምናውቀው አዕመታሪክ ውስጥ ሲተርክ ማቋረጥ የማይቻል መሆኑ አስደምሞኛል። ላይ ላዩን ለሚጋልብ እንባቢ ማቅ፣ ሥላቅ ይመስላል። እንዴት ስስ የታሪክ ልባስ መገሸለጥ ለቻለ እዚያ ውስጥ እንደበረዶ ቅዝቃዜ ያስተኛው መፍሰስ የተሳነው ሀዘን አለ።

@OLDBOOKSPDF

እሱ አንተ እንድታነብለት ፈልጎ ነበር። እኔ ግን አሁን ትልቅ ሥራ አለበት፣ ከታተመ በኋላ ያነበዋል አልኩት፤ ትክክል ነኝ?"

ጎን-ለጎን የማያኳኋን ቀጭን የእግር መንገድ ይዘን እየተጓዝን... እንደ አይነ ሥውር በዮናኤል እየተመራን፡፡

"ሙሴ ፀሊም እየሰራሁ ነው ብሎ የሆኑ ወረቀቶች ይዞ መጥቶ ነበር" ምን እንደተሰማው ለማወቅ ዘወር ብዬ እየሁት ባዕድ መልኩ በንዴት አልተለዋወጠም፡፡ በባህር ጥልቀት ላይ መሰረቱን የጣለ ሰብዕና በሚገነፍል ደራሽ ወንዝ ይደፈርሳል?

"ተገናኝተናል፣ ጨርሰናል"

ተለማመጠው? በገንዘብ ደለለው? ወይስ...? እኔ እንደ ዶክተር አሮን ጥልቀት ያለው መሠረት ላይ አልቆምኩም፤ ትንሽ ሲነኩኝ ቢል እላለሁ፡፡

"በእሱ ሰውዬ ስንቴ እንደተሸማቀቅሁ፤ ሁለተኛ አትምጣ እለዋለሁ ግን..."

"የልቦለድ ደራሲ ነህ፤ ፀባይ ለፀባይ የማትግባባውንም ማጤን ግድህ ነው፡፡ እንኳን ቤትህ ድረስ መጥቶ ቀርቶ ያለበት ድረስ ሄደህ ማግኘት ይገባሃል፡፡ ደግሞምኮ የትኛውም ሰው እሱነቱን የሚቀበለው ወድዶ አይደለም፡፡ አንዳንዱ እስኪሰበር ድረስ ተጠምዝዞ የሆነውን እንዲሆን ይገደዳል፡፡ ማንኛችንም እናብዛው እንጂ መምጣታችን ጠቀሜታ አለው፡፡"

ከኋላ የሚከተል መምህር፣ ከፊት የሚቀድም ደቀመዝሙር፤ ሁኔታው ሁሉ የተምታታ ሆኖ ተሰማኝ፡፡ በፀጥታ ውስጥ ወፎች ይዘምራሉ፡፡ ነፋስ እንደጫጩቶቻቸው ከአፋቸው እየተመገበ ዝማሬአቸውን ለአዲስ አበቤዎች አቆልቁሎ ይበትነዋል፡፡ ነፋሱ ሲላም ተሸክሟል የክክ ወጥና የዘመራ ሰጋ ሽታ...

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፯

ሐሰተኛፀሑም

ዮናኤል መጽሐፍ መደርደሪያው ሥር ቁጭ ብሎ ያነሳል . መልሶ ይከታል። አንዳንዱን መጽሐፍ በእጁ መዝኖ የማያስቀምጠው ያህል ይፈጥንበታል። አንዳንዱ ላይ ደግሞ የጀርባውን ዕሑፍ፣ መግቢያውን፣ ማውጫውንና የኋላ ገፅ ማመላከቻውን ሁሉ ያነብና አጠገቡ ያስቀምጣል።

ዶክተር አሮን ብዙ ብር አውጥቶ እየደለደለ ለናትራ ይሰጣታል። "ፓስታ፣ ሽንኩርት፣ ኮንሰርቫ"

"ኮንሰርቫ ምንድነው?" ለመጀመሪያ ጊዜ ሽቱ ለብሳ ማየቱ ነው። የሽቲውን ጎንና ጎን የውስጥ ሱሪዋ ውስጥ ከትታ ቀልጠፍ ያለ አለባበስ እንዲሆን አድርጋዋለች፤ እግሯ...

"የቆርቆሮ ቲማትም"

"ቲማቲም አረክሷል፣ ገዝቼ እከትፈዋለሁ"

"ጥሩ፣ ዘይት..."

"ዘይት በዚህ ሁሉ ብር?"

"አዎ፣ ለሌላ ጊዜም ይሆናችኋል፣ ዳቦ፣ ሙዝ፣ ሲጋራ ደሞ በዚህ። ጫቱን እኛ እንገዛለን"

እንዲህ ያለ እውን ቀርቶ ህልም ካየሁ ቆይቻለሁ። ናትራ ህልሜን ለማሟላት ወጥታ ሄደች። ዶክተር አሮንም አውልቆ አል.ጋ ላይ የጣለውን ጃኬት ለብሶ "መጣሁ" አለ።

"የት?" ደግሶ ሊጠፋ መሰለኝ

@OLDBOOKSPDF

"እዚች ቅርብ! ሞት የሌለበት" እያለ አሮጌ ቀልድ ቀልዶ ወጣ:: ዮናኤልን መሬበሽ ስላላሰኘኝ እኔም ከደጃፉ ፊቀት ብዬ ቆምኩ::

"የግራዝማች ዋለሉ ያለህ! አንተ ቱሊያም ያንተን ምናምን ጠራጊ አደረከኝ?" ጥፍጥሬ በተቀበቀበበት አፍንጫ ተነጫነጩ::

"እማማ ድንቂ-እ-ብርቂ---ስንቂ---" ሁሌም ስማቸው አይያዝልኝም::

"ምነው?" አሉ ቆጣ ብለው ምስር ቀቅሉ የምላቸው መስኗቸው ይሆን? ጥፍጥሬያቸውን ሊያፈናጥሩ ተዘጋጁ? መፍተላቸውን ገታ አደረጉ::

"ጃክ ጌታ አለው? ማለቱ ነበረው?"

"ነበረው እንጂ፣ እንዴት ያለ ከጌታም ጌታ:: ጥልያን ነበር:: ጥልያኑ አባቱን ደጅ ሊጠና ሲመጣ ጃክ መኪና ውስጥ ከኋላ ጉብ ብሎ የሰው ልጅ ይመስል ነበር:: በኋላ ነገር ተገለበጠና አባቱ የጥልያኑ ደጅ ጠኝ ሆኑ:: ጥልያኑ መቼም ስሙ ነው ጥልያን:: ቁርጥ አበሻ:: ሲተርት፣ ለአዝማሪ ግጥም ሲሰጥ፣ የዘወትር ፀሎት ሲደግም... ምኑ ቅጡ:: እንዲህ እንዳተ ኳደኛ!

"ግራዝማች ዋለሉ ይቺን ልጅዎን..."

"ምንትሆን?" አባቱ ያፈጣሉ

"ባላገባ ኖሮ ሽማግሌ እልክቦት ነበር"

"ድመት መንኩሳ አመሏን አትረሳ አሉ፤ ለአባት እንዲህ ይባላል? ፈረንጅነትህ አለቅ ብሎህ እንጂ--- እሆሆይ!"

"ያኔም ጥፍጥሬ ነበርዎት? ማለቱ ጥጥ ይፈትሉ ነበር?" ምን እያሰብኩ ዘባረኩ?

"ያኔማ እመቤት ነኝ፤ ይልቅ ጨዋታውን ልጨርስልህ" እንዝርታቸውን አገልግላቸው ላይ ጣል አደረጉና ቀጠሉ:-

"ያን ጥሊያን አድዋ ላይ አባቱ ነበሩ የማረኩት! አጤ ምኒልክ ፊት እጁን ይዘው ቀርበው ምህረት አሰጡት:: ኖረ፣ ኖረና ማይጨው

@OLDBOOKSPDF

ላይ ደሞ እሱ አባቴን ማረካቸው። ጄነራል ናዚ ፊት አቅርቦ በተራው ለአባቴ ምህረት አሰጣቸው።

"የጣሊያኑን ሥም ያስታውሳሉ?"

"የግራዝማች ዋለሉ ያለህ! ሙሴ ቀስተኛ ነዋ። በኋላ ድልም አድርገው አላርፍ አለ። መኳንንቱን ሁሉ ከየተደበቀበት እየጠቆመ ያስለቅም ጀመር። አባቴ 'ምነው ይሄን ከማይ ሞቼ ባረፍኩ ኖሮ!' እያሉ ሲቆጩ፣ አንድ ቀን እድል ገጠማቸው።"

"እንዴት ያለ እድል?"

"በጠዋት እቤት መጥቶ እኔን ካሸኮረመመኝ በኋላ አባቴን ደጃፍ አስጠርቶ 'ግራዝማች ዋለሉ ታላቁ የኢጣሊያ መንግሥት ላንተ ምህረት ሲያደርግ በአፀፋው ደግሞ አንዳንድ...

"ምንድነው?" አሉ አባቴ ታክተው

"ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ለኢታሊያ መንግሥት እንዲገባ ለማግባባት እኔ ተመርጫለሁና እንድታገናኘኝ። ለወትሮው 'አንቱ' ነገር የሚላቸው።

"ምን ገዶኝ፣ ያለበት ከታወቀ ይገኝ እሄዳለሁ።

"ቅድሚያ አንተ ሄደህ አመቻች"

"ጥሩ"

"ሄዱና ቁጭታቸውን የሚወጡበትን ለደጃዝማች ገረሁ መካከሩና ይዘውት ሊሄዱ መጡ። ማታ ስንቁ ካልመጣሁ አንቺ ወደቡልጋ ሂጂ። እህትሽን ጨምረሽ እንዳሉትም ሙሴ ቀስተኛን በገረሱ ዱኪ አሰቅለው አርበኞችን ተቀላቀሉ። ታዲያ ጥሊያኑ ሊሰቀል ሲል ይሄን ውሻ አደራ አለ። 'ሰሙ እንዳይቀየርብኝ' ማለቱን እንደሙት ቃል ይዘው ለእኔ አስተላለፉ።"

"እንዴ ሻክ ታዲያ ስንት አመቱ ነው?"

"ብዙ ነው" @OLDBOOKSPDF

"ውሻኮ ቢበዛ ሃያ አምስት አመት ቢኖር ነው" እንደ ሆሜር ትርክት እንደ ኦዲሴ ውሻ ጃከም የማይሰፈር ዕድሜ ሰጥቶት ይሆናል።

"አሃ-አሃ-አሃ... ይሄ ቱሊያሙ የዋናው ጃክ ልጅ ነው። ግዝት ሆኖብኝ እሱንም ጃክ አልኩት።"

"ዳግማዊ ጃክ መሆኑ ነው። ፍዝዝ ቅዝዝ እንዳለ በብሱዝ አዘፋፈን ስልት ሊነግረኝ ይፈልግ የነበረው ታሪኩ ይሄ ይሆን? አከራዬ ከወደ "ብቅ እንቅ" ሲመጡ አየኋቸው። ፊቴን እንዳያሚልሉብኝ ተሸቀዳድሜ ወደ ውስጥ ስገባ...

"የውሻ መዋዕለ ዜና ልትፅፍ ነው?" አለ አፈትጉሃን ዮናኤል ከሚያገላብጣቸው መጻሕፍት ላይ ቀና ሳይል።

"አይሻልም?"

"ከምን?"

...ዝም...

ሣቀ። "በወፍጮ ቤት ተጀምሮ በወፍጮ ቤት የተጠናቀቀ ገድል ልፅፍ እንደሆን አንተም ሰማህ? እናም አመንካቸው?" መጽሐፍቱን አገላበጠ፣ አገላበጠ፣ አገላበጠ - እና

"ውሸት ነው። ልቦለድ እየፃፍኩ ነው ላለማለት የነገርኳቸውን ይዘው ነው።" መጫሚያው በፊትም እንዲህ ትልቅ ነበር? ወይስ እኔም እንደአከራዬ ነገሮችን አሟልዬ ማየት ጀመርኩ?

"በኢየሱስ ላይ የሆነ ነገር ለመፃፍ ያሰብክ ትመስላለህ" አለኝና አጠገቡ ያነባበራቸውን መጻሕፍት ዳሰሰ።

"እንዴት?" አልኩ ጉዝጓዜ ላይ እየተቀመጥኩ

"የመጽሐፍ ስብስቦች ውስጥ ከኢየሱስ ጋር የተያያዙ ጥናቶች ይበዛሉ።" እግሩን በተረከዙ ተከሎ የጫማውን አፍንጫ ወደጣሪያ ስለጠቆመበት የመጫሚያው ቁመት ከትከሻው ጋር ተነፃፃሪ ሆኖ ታየኝ።

"ኢየሱስ አንድ ተመራጭ የንባብ ዘርፍ እኮ ነው። ከእምነት ባሻገር።"

@OLDBOOKSPDF

"እንዴት?"

ሰዎች ለእኔ ሲያብራሩ እንጂ እኔ ለእነሱ መግለጫ ስሰጥ ደስ የማይል ስሜት ይቆነጥጠኛል።

"በማኅበራዊ ጥናት፣ በሥነ ልቦና፣ በታሪክ፣ በሥነ ሰብ፣ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ... በሁሉም ዘርፍ ያሉ ምሁራን ኢየሱስን መነሻ አድርገው የሚሉት አንድ ትልቅ ነገር አላጡም። ኢየሱስ አምላክነቱ የሚታየኝ ሞቶ በመነሳቱ ሳይሆን ለሁሉም ዲሲፕሊን የሁልጊዜም ጭብጥ መሆን መቻሉን ስመለከት ነው።"

"ለምሳሌ?" ትክሻ ለትክሻ የገጠመ የእግሩን መዳፍ ወደመሬት አወረደና ወደእኔ ዞረ።

"ለምሳሌ" ሲባል ሻምበል ጠናጋሻው ትዝ ይለኛል። መምህርነቱ ተዕፅኖ አድርጎብኝ ለምሳሌ ስል እገኛለሁ ይል ነበር።

"እሱ መካከል ላይ ያለው መጽሐፍ፣ አ-አዎ፣ ከፍ እሱ፣ "Jesus in contemporary scholarship" ይላል። ከአርባ በላይ ምሁራን፣ በተለያየ ዲስፕሊን፣ ኢየሱስን ርዕስ አድርገው ዕፈዋል። የቅርብ አስተምህሮዎች ሳይቀሩ እንደ ሥነ-ልቡና ዘርፎች እንደ የገረመኝን ልንገርህ።"

"ጥሩ" እንደጠናጋሻው፤ አጋጣሚ ይሆን?

"በኢየሱስ ዘመን ማህበራዊ ተዋረዱ ሦስት ክፍሎች ላይ መሠረት ያደረገ ነበር። የመጀመሪያው የገዢው መደብ አባሎችን ሮማውያንን የበላይ አድርጎ ይነሳል። ቀጥሎ ከእስራኤላውያን የተመረጡ እንደ እምነት አባቶችና ቀራጮች ያሉ ቦታ ይሰጣቸዋል። እንጡራው ግብር ከፋይ በሥነ-ልቡና ተቀይዶ፤ የበታችነቱን አምኖ እንዲቀመጥ የተደረገው ነው። "አባት" የሚባሉት እነዚህ የእምነት አባቶችና ቀራጮች ናቸው።

"ስለዚህ..." ናትራ በር ላይ ከወዲያ ወዲህ ትላለች። የሹቲዋ ወጋገን የቤቱ ብርሃን ላይ ተፅዕኖውን ያሳርፍና መልሶ ይጠፋል። ቀልቤን ንግግሬ ላይ አድርጌ ቀጠልኩ።

"ስለዚህ ኢየሱስ ያሰበውን ለውጥ ለማምጣት የታችኛውን ማህበረሰብ ከሥነ-ልቡና ዝቅጠት ማውጣት ነበረበት። ስለዚህ፣ በብዙ

@OLDBOOKSPDF

ሏና አንገቱን የደፋውን አንጠራራ ይሁዲ ከእስራኤል ጨቋኞች ብቻ ሳይሆን ከገዢዎቹ ሮማውያን በላይ ነኝ እንዲል የሚያሰኘውን እንዳች ቀስትና መስጠት ነበረበት ስለዚህ..." ሳስተምርም "ስለዚህ" የሚል ቃል አበዛ ይሆን?

"ቀጥል"

"ስለዚህ" (ወይዛሪ) "ኢየሱስ አንድ ዘዴ ተግባር ላይ አዋለ:: እሱም ጥምቀት ነው:: አንድ ይሁዲ ሲጠመቅ ቀጥታ ከአባቶች እና ከሮማ ገገርዎች አልፎ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚወርስ ቀጥተኛ ተጠሪ ይሆናል:: አንጠራራው ይሁዲ ከካህናት አለቆችና ከአይሁድ ታላላቅ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ከመጨረሻ የበላዮቹ ሮማውያንም በሥነልቡና ደርጅቶ ይገኛል:: በዚህም ላይ "ከሰማይ አባታችሁ በቀር ማንንም 'አባት' አትበሉ" ሲል የሥነልቡና ውጤታቸው በምድር ተግባር ላይ የሚውልበትን የአመፅ መነሻ ሰጥቷቸዋል::"

"ጥሩ፤ እኔ ደግሞ ያነበብኩት ሮማውያን ለራሳቸው የገገርነት ሥነልቦና ኢየሱስን በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በኩል እንዴት እንደተጠቀሙበት ነው:: ያም ሆነ ይህ እንዳልከው ኢየሱስ ከብዙ አቅጣጫ ሲታይ ትክክል የሚሆን አስደናቂነት አለው::"

ናትራ ገባች:: ሦስት ዱካዎችን ይዛለች:: ቦታ እያየች ደረደረች:: ዶክተር አሮንና ናትራ መንደርተኛውን ሁሉ የሚያስጠራ ዝግጅት ላይ ያሉ መሰለኝ:: የመጀመሪያው የፓስታ ድግስ ሳይሆን አይቀርም:: አፈትጉሃን ዮናኤል አንዱን ዱካ ስቦ በመቀመጥ የመጽሐፍ ምርመራውን ቀጠለበት::

እኔ በናትራ ወጋገን ውስጥ እየዋኘሁ እግሯን እንደወቅት ሲመጣና ሲሄድ የተለያየ ስሜት እየፈጠረብኝ ጉዝጓዜ ላይ ቆየሁ::

ዶክተር አሮን የጫት ነዶ አሸክሞ መጣ::

"አልጋው ላይ አድርገው" አለ:: የረድ ሠርዊ ባይጥ ትቷት እንደሄደ አስመስዬ እራስን አስተኝቻታለሁ:: የጫቱ ቀንበጥ በክፉል ሽፍኗት እያጮለቀች የምትመለከት መሰለች:: ከባይጧ ጋር ምስጢር አለኝና! ሰው የመሆን ድክመት የተገለጠበት ምስጢር::

"እስኪ ጥምቀትን ከእኛ አንፃር እየው? የበላይነትን የምናረጋግጥበት ነው? ወይስ?..."

@OLDBOOKSPDF

ዶክተር አሮን ከደረሰበት ጨዋታ ለመቋደስ ጆሮውን እንደ እጅ ሰደደ:: ጮልጯላ አይኑን አስከተለ::

ገዛም፤ ፀጥ ተባለ::

"ስለምን እየተጨዋወታችሁ ነበር?" አንዷን ዱካ ስቦ ተቀመጠ::

"ስለ ኢየሱስ"

"ምን አላችሁ ብዬ አላስደግማችሁም:: ግን ሁሌም የሚገርመኝን ልንገራችሁ:: የእኛ ኢየሱስ ዓለም ከሚያውቀው ኢየሱስ ሁሉ የሚለይ ይመስለኛል:: አዲስኪዳን ላይ ያለው ኢየሱስ አምላክነቱ እንዳይገለጥበት የሚሸኮረመም ነው:: የእኛ ግን ከልጅነቱ ጀምሮ ብዙ ተአምራትን እያደረገ መለኮታዊ ኃይሉን እየገለጠ የኖረ ነው:: የእስራኤል ልጆች አምላክነቱን እንዲቀበሉ አብርሃምን፣ ሙሴን፣ ይስሃቅን... ሁሉ አስነስቶ ለምስክርነት የሚያስቀርብ ነው::"

ቆም አድርጎ በመደመም ቆየና...

"በተለይ ልጅ ሆኖ የሚያሳየው የጨዋታ ዝንባሌ የእኛን ኢየሱስ ያሟላዋል:: በፀሐይ ጨረር ላይ ሸረር እያለ በመንሸራተት ይጫወታል፣ ጭቃ አቡክቶ የወፍ ቅርፅ ይሰጠውና እፍ ሲልበት ነፍስ ዘርቶ ይበራል:: እናቱን እንጨት በመልቀም ይረዳል:: ለእናቱ ስሞታ ይመጣበታል:: አንዳንዴም የጓደኞቹ እናቶች ይመቱታል:: የአዲስኪዳኑ ኢየሱስ ልጅነትን አያውቃትም:: ያሳዝነኛል:: የትልቅ ሰው ተልዕኮ የተሸከመ፣ እንደ ዕድሜው እንዳይሆን የተከለከለ አይነት ነው::"

ጥቃቅን አይኑን ከሰደደበት እየመለሰ

"በተለይ የሥነ ፅሁፍ ሰው ተአምረ ኢየሱስን ጨምሮ ሌሎች ገድሎችን ማንበብ ግዴታው መሆን አለበት::"

ዛሬ ፊቱና ንግግሬ እጅግም ሳይራራቁብኝ ቀሩ:: ፀሐይ ስለመታው ይሆን? አይኑ ሥር ያለው ቆዳው ፍም መስሎ ቀልቷል::

ናትራ ተጨማሪ ዱካዎችን ይዛ መጣች::

"ናትራ ይሄ ቤት የሴት ሽርጉድ ይጎድለው ነበር:: ምናለ ለሁልጊዜው እዚህ ቁጭ ብለሽ ቤታችንን ብታሟሙቂ?" ብሎ ፀጉሩን ወደእናቱ መልስ አለ፡፡

@OLDBOOKSPDF

ፈገግ ብላ ወጣች:: የውስጥ ሱሪዋ ውስጥ የተወተፈው ሽቲዋ ሌላም ተልዕኮ እንዳለው ደጃፍ ላይ ስትደርስ የገባኝ መሰለኝ::ምን?...

ዮናኤል አፈትጉሣን "The last temptation of christ" የሚል መጽሐፍ ይዞ ፊቱን ሙሉ ለሙሉ ወደኛ መለሰ::

ናትራ ፓስታውን አቀረበች:: ማባያው የበሰለ አትክልት መሆኑ ልዩ አድርጎታል:: በፀጥታ ተመገብን:: ስናበቃ ዶክተር አሮን አጭር ንግግር አደረገ::

"ለረጅም ጊዜ ሳስብበት ቆይቻለሁ"

"ፓስታ ድግሱን?" ስል አሰብኩ::

"የጥበብ ሥራዎች በጥበበኛው ቀስትና ማጣት ቀገርቃ ሆነዋል:: በተለይ ግጥም እንደውዳቂ ነገር ለመታየት በማዘቅዘቅ ላይ ይገኛል:: ልቦለድ ተረካቢ የማጣት አደጋ ላይ ነው:: አጭር ልቦለድ በወግ እየተተካ ጨርሶ ጠፍቷል ማለት ይቻላል:: ስለዚህ አንድ የጥበብ ማዕከል የሚሆን መሰባሰቢያ ቤጤ እንደሚያስፈልገን ዘወትር ከሐሳቤ ሳላጠፋው ቆይቻለሁ:: አሁን ጊዜው የደረሰ ይመስለኛል:: ከቻልን በቅርብ ጊዜ ውስጥ አንድ ትልቅ ቤት ገዝተን ሰርቪስ ቤቶች ያሉት:: ተጨማሪ ክፍሎች እንገነባና ትልቁ ቤት ይከራያል:: ኪራዩ እዚያ ለሚቀመጡ የጥበብ ሰዎች አንዳንድ ወጪ ይውላል:: ስንፈልግ ብቻ ውይይት እናደርጋለን:: በተረፈ ሌላ የኑሮ ግዴታዎቻችን ብዙም ሳይጫጫኑን ለጥበብ ብቻ የምንኖርበት ማዕከል ይሆናል ብዬ አስባለሁ:: ወደ እንግሊዝ ደርሼ ስመለስ ይሄንን የመፈፀም ህልም አለኝ::"

ፀጥ፤ በእርግጥም ፀጥታ በባለጌ ድምፆች አለመኖር ህልዉን እውን ያደርጋል::

ናትራ የተበላበትን ሰብስባ የተፈላ ቡና ማቀራረብ ስትጀምር ጠቀስኳት:: ወደ ጉዝጓዜ ቀርባ ጆሮዋን ሰጠችኝ::

"ትንሽ የተረፈ ብር አለ?"

"አለ፣ ምነው?"

"ለጃኪ ቅንጥብጣቢ ሥጋ..."

"ለጃኪ?"

@OLDBOOKSPDF

"አዎ"

"ጣሊያኑ ጃክ'ኮ ፓስታ ይበላል! እሰጠዋለሁ" ሄደች።

ጃክ ፓስታ በሹካና በማንኪያ እየጠቀለለ ሲበላ አስቤ ፈገግ አልኩ። ከጨምዳዳ ፊቱ በተጨማሪ በሹካው ሠላምታ እየሰጠኝ።

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፰

ጫት ከቃምኩ ስለቆየሁ ምርቃናውን የማልችለው ሆነ፡፡ ሙቀት ብቻ ሳይሆን ውዝግቡና ንውዘቱ የማይጨበጥ ዓለም ውስጥ ወርውሮኝ አደርኩ፡፡ እንቅልፍ ሽለብም ሳያደርገኝ ብርሃን ተበሰረ፡፡ ደጃፌ ሲቆረቆር ከንውዘት ሳልወጣ ያለሁበትን ለማጣራት ሞከርኩ፡፡ የጫት ገራባ ተከምሯል፤ የረድ ሠርዌ ባይጥ አድፍጧል፡፡

ቅንብቢት…

…ዳግም ደጃፌ ተቆረቆረ፤

"ይግቡ"

"ክፈተዋ" ናትራ ናት

ምን ሆኜ ደጃፌን ከውስጥ ሸጎርኩት? ለመነሳት ተፍጨረጨርኩ፡፡ ሰውነቴ በሙቀት ነውጥ ውስጥ ነው፡፡ ልቤ ግን ዝሏል፡፡ እንደምንም ተነሳሁ፡፡ ትናንት የተቃመ ጫት ገረባ ተዝረከርኳል፡፡

"በርሽን ስትቀረቅሪ ያቺ ወንድ ፈልጋ የመጣች የማትመስለው፣ እሷ መጥታ መስሎኝ ነበር፡፡"

ዝም! የሌሊት ልብሷን አቅብጣ እንደለበሰች ነው፡፡ እግሯ…

"እንተ፣ ለጃክ ፓስታ ሰጪው አላልከኝም? ፓስታውን ውጦ ውጦ ምን ቢያደርግ ጥሩ ነው? የጣሊያን ነገር"

"ምን አደረገ?"

"ሴት ተከትሉ ወደ ብቅ እንቅ፡፡ ከወንዶቹ ጋር እየተደባደበ ነው አሉ፡፡ ወይ ጥጋብ! ወይ ጥጋብ! ብቻ ወንዶቹ እንዳይገድሉት፡፡ የሱ

@OLDBOOKSPDF

ሲገርመኝ አንተም በርህን ከውስጥ አልቆለፍክም? ኧረረረረረ... አልኩና።"

ቀና ብዬ አየኋት። እግሯ ከሚለቅብኝ ሽብር ይሻላል።

"ሲጋራ ተውሽ?"

"ዛሬ ሌሊት ጨረቃ አልነበረችም። አንተጋ ልገባ ስሞክር በሩ ተቀርቅሯል። ጨረቃ ስለሌለች አቅፍ አድርጌህ እተኛ ነበር።"

"እንደጃክ አንቺም ፓስታ በላሽ?" ካልኩ በኋላ ቀልዱ መራር እንደሆነ ገባኝ። የፊቷን ባላውቅም እግሮቿ አኩርፈዋል።

ናትራ... ይቅርታ... ናትራ... ይቅርታ... ልቤ ተንደፋደፈ። ረድ ሠርዌ ይሄንን ይሆን ጥጋብ ጸጋ እግዚአብሔርን ይገፋል ያለው?

"ይቅርታ" አልኩ፤ በልቤ የሞላውን በአፌ ቀነስኩ።

ምላሽ ሳትሰጠኝ አልፋ አልጋው ላይ ተቀመጠች። የበለጠ ያኮረፉ እግሮቿ በፊቴ ትይዩ ዋሉ፤ እግር ያኮርፋል?

"መምህሬ ነበር፤፤ ስለኮከቦች ብዙ ነገሮች ይነግረን ነበር። እንደውም እንኳን ስለአንዷት ኢትዮጵያዊ፣ ኮከብ የሆነች ተርኮልናል።"

"አንድሮሜዳ?"

"አዎ፣ መሰለኝ ስሟ እንደሱ ነገር ነው። ተቀራረብን፣ ከትምህርት ቤት ውጭም እንገናኝ ነበር። እየወደድኩት ስሄድ ችግሬን ነገርኩት።"

"ምን ነበር ችግርሽ?" የቸኮልኩ መሰለኝ።

ዝም አለች፤ እኔም የማልችለው እግሯን ተጋፍጬ ዝም አልኩ።

"ሽንቴ ድንገት ያመልጠኝ ነበር። ሌሊት ተኝቼ አንዳንዴ በቀን የተቀመጥኩበት።እና ስነግረው ከጨረቃ ጋር እንደሚገናኝ ተረከልኝ። ከመጽሐፍ ላይ አሳየኝ። በጣም ትልቅ መጽሐፍ ነው። ጨረቃ ይልና ሽንትን ጭርት፣ ጭርት ማድረግ ወይም እንደ ጨረቃ መድመቅ፣ በአይኔ አንብቤአለሁ። ከዚያ ለጨረቃ ንገሪያት። ሙሉ ስትሆን፣ ይቆምልሻል አለኝ።

@OLDBOOKSPDF

"እሺ' አልኩት"

"እንደውም የመጀመሪያውን ሥነ-ሥርዓት አብረን እናደርገዋለን" አለኝ።

"ብጣም የተቸገርኩበት ነገር ስለነበር አላንገራገርኩም። የመጀመሪያ ቀን ከአዲስ አበባ ይዞኝ መጥቶ አልጋ የተከራየንበት ፊት ለፊት ውቅያኖስ አጠገብ..."

"ውቅያኖስ?"

"አዎ"

"ሐይቅ ማለትሽ ነው?"

"ሁለቱም ውኃ አይደለም? እና ጨረቃን እያየን፣ እሱ ሲጋራ እያጨሰ ችግሬን እራሴ እንድነግራት አደረገ። የዛን ቀን ሌሊት ሳልሸና ቀረሁ። ደገምን፤ እንዴት እንደሆን እንጃ የዛን ሌሊት ሽንቴ ሲያመልጠኝ ነቃሁ።

"ለጨረቃ ከልብሽ ስላልነገርሻት ነው አለኝ። በሽንት የራሰ ጭኔን ሳመልኝ። ሦስተኛው ቀን ላይ ለጨረቃ እያለቀስኩ ነገርኳት። ቆመ፣ ቆመ፣ ቆመ። ወደአዲስ አበባ ተመለስን። በወሩ ማርገዜን አወቅሁ።"

ልብን ዘጭ የሚያደርግ ድንገተኛ ሆነብኝ።

"ጨረቃን አስታቅፎ ጥፎ አለኝ። ችክ ስልበት ችግርሽ የሥነ-ልቦና ነበር። በጨረቃ ሰበብ ድነሻል። እኔን ተይኝ፣ ካልሆነ እኔ ማስተማሬን ትቼ እጠፋለሁ አለኝ። ባላገኘውም ወደማላውቀው አካባቢ ከሚጠፋብኝ፣ እዚያው አለ ለማለት እኔ መማሬን አቆምኩ።"

"ልጅሽስ?"

"አልወለድኩትም"

ቀና ብዬ አየኋት። በተራዋ እግሮቼን አየች።

"ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት ብቻ ከአዳኜ ጋር ነበርኩ። ዘልአለም መመለክ ሲያንሰው አይደል? አቤት የነበረብኝ ሀፍረት? እንዴት ነበር የምሸማቀቀው?... እንኳን ያልወለድኩትን የወለድኩትንስ ብለዋለት?..."

@OLDBOOKSPDF

ደነገጥኩ!

"ልጃቸውን የሚሰጡ ነበሩ አይደል?"

"አዎ" የሞት ሞቴን፡፡ "ሞሎክ የሚባል ጣዖት ነበር፡፡ ሆዱ ምድጃ ነው! ሀብት ለማግኘት የበኩር ልጅ ምድጃው ላይ ይጣላል" ወደየት ሄድን? እንዴት የሚያስጠላ ርዕሰ ጉዳይ ውስጥ ገባን?

"ወደ ጨረቃ የሚኬደው እንዴት ነው?"

"ምነው?"

"ብሄድና ሰንደል አጭሼላት፣ ሴሽ ለኩሼላት ብመጣ እያልኩ አስባለሁ፡፡"

ደሞ ልታስቀኝ?

ናትራ ተነስታ ገረባዎቹን መሰብሰብ ጀመረች፡፡ አጭር የሌሊት ልብሷ ወለላ ማር የመሰለ ጭኗን ለጉብኝት ያቀርባል፡፡ እንደወትሮው ደስ አላሰኘኝም፡፡ ፍላጎታችን ያለው ምናችን ላይ ነው? የምታስበውን ስለነገረችኝ ለምን ዝግትግት አልኩ? ሽንገላ እፈልግ ነበር?

የፍቅር ሾተላይ አለብኝ፡፡ ፍቅር ሲታሰብ የሚያጨነግፍ ሥራይ፡፡ በዚህ ሰዓት ከናትራ ጋር መሆን ለሁለታችንም የነፍስ ህመም መድህን አልነበረም? የታፈነ መሰልቸት ውስጥ እራስንና አምላክን እየወቀሱ፣ የሚሆን የማይሆነውን እያሰቡ፣ እጅ እግርን ታስሮ እየሟሙ ማለቅ ዕጣፈንታዬ ይሆን? ለእራሴ መሆን ተስኖኝ በአይነ ጥላ እየዋለልኩ በከንቱነት የህይወት መንገድ ዳር መቅረት የተፈጠርኩበት ግብ ይሆን? የምበላው ማጣት ነበረብኝ? መጠለያዬን መመፅወት የነፍስ ደዌ አይደለም?

ናትራ ገረባውን ሰብስባ ወጣች፡፡ ሽርጉዷን ጠላሁት፡፡ ሴቶች የእኔ የመሆናቸው እድል እየሰፋ ሲሄድ፣ ለእነሱ ያለኝ ስሜት እየጠበበ ይመጣል? ይሄንን ደዌ እንደ ናትራ ጨረቃ በማምለክ እወጣው ይሆን? ለጨረቃ ሲጋራ በማጨስ...

ናትራ ቤቱን በሮዝ ቀለም ሞላችው፡፡ በር ላይ ቆማለች፡፡ ባለችበት ስትቆይ ቀና ብዬ አየኋት፡፡ ከንፈሯን የጣለችው መሰለኝ፡፡ ሌላ ቀለም

@OLDBOOKSPDF

ከበስተኋላዋ ተደረበ:: የመጣችውን አፍንጫዬ አውቋታል:: ናትራ የንጥር ሽቶውን ስም ይዛዋለች:: ነፀብራቅ ተነክራዋለች::

ናትራ ገሸሽ ብላ ደጃፉን ለቀቀችላት:: ሌላ ቀለም ተተካ:: ደማቅ ሠማያዊ ቤቴን ሞላው:: በቀለም ብቻ ሳይሆን በውበት፣ በሽቱ፣ በሴትነት ለዛ፣ በአለባበስ ጥንቃቄ... ናትራን ጋረደቻት:: አፍንጫዋን ለቅላ ደስ የማይል ጠረን እንደደረሳት አሳወቀች:: ዓይኖቿ መካከል ቋጥራ የሚታየው ሁሉ ትክክል አለመሆኑን ጠቆመች::

"በልደትዬ እንውጣ፣ እንሂድ" አለችኝ::

"የት?" እያወቅሁ

"እኔ ቤት፣ የምትሠራልኝ አንተን የሚመለከት የጥናት ማመሳከቻ አለ::"

"የምን ጥናት ማመሳከቻ?" ከስር ሆኜ ወደላይ ስመለከታት የግሪክ ከተሞች መግቢያ በራቸው ላይ የሚያቆሙትን የአምላክ ሐውልት መስላ ገዘፈችብኝ:: ባህሪዋም የቁጡ አምላክ ነው::

"ፍትህ ሚኒስቴር ለሲምፖዚየም የሚሆን ጥናት እንዲሰራለት በጀት መድቦ ወደኛ ላከ:: ልደትዬን አንዱ ርዕስ አንተ ልትሰራው የምትችለው ስለሆነ እኔ ተቀበልኩት::"

ነፀብራቅን ትቼ ገሸሽ እንዳለች የቀረችውን ናትራን አየኋት:: ነፀብራቅ ዘወር ብላ ከላይ እስከታች እንደመውዝ ልጣ:-

"እንዴ፣ ትንሽ ደቂቃ፣ የሥራ ጉዳይ ስላለን... ትወጪልን?" ድምፀቷ ግን ትህትናን አልተላበሰም::

የናትራ ሮዝ ቀለም ጨርሶ ከቤቱ ተወገደ:: በእኔና በነፀብራቅ መካከል ያለው ግንኙነት እንደ 'ሥራ ጉዳይ' የሚቆጠር አይነት ነው:: አንድ ቀን እኔን እንደምትፈልግ ነግራኝ አታውቅም:: የሌለ ፕሮጀክት ነድፋ፣ እኔ የምሰራው አስመስላ ወደቤቷ ትወስደኛለች:: ሥራውን ስጠይቅ "ይደርሳል" እያለች ታቆየኛለች:: የሆነች ዘመናዊ ሴት ባላባት ነገር ትሆንብኛለች:: በሚበላ፣ በሚጠጣ... አንዳንዴ በሚለበስ ወደእሷ ደረጃ ከፍ ያደረገችኝ ይመስላታል:: የበቃት ሲመስላት በፊት እንደማይመጥነኝ ወደነገረችኝ ህይወቴ መልሳኝ ትሄዳለች:: በተለይ

@OLDBOOKSPDF

ማስተማሬን ካቆምኩ ወዲህ እንዲሁ ሲሆን ነው የቆየው። የባላባቷ የጭን ገረድ(አሽከር ይባላል?) ሆኛለሁ መሰል...

"በልደትዬ ከዚህ ቤት እንውጣ፤ የማትሰራውም ከሆነ እመልስሃለሁ።" ብላ ወደአልጋዬ አይኗ ተሰክቶ ቀረ። አኩፋዳውን እንዳየች ገብቶኛል።

"መሰመን ጀመርክ እንዴ?" ዝም አልኳት። ስድቧን ለመርሳት የሥራው ማስተዋወቂያ ፕሮፖዛል አይነህሲናዬ ላይ ደቀንኩት

- የሥራው አይነት "ፍቅር መሰል"

- ሥራው የሚያካትታቸው ግብአቶች መብላት፣ መጠጣት፣ መጻሕፍት ማገላበጥ፣ የሀሳብ ውይይት ማካሄድ፣ መካከል ላይ ጥንቃቄ የበዛበት መሳሳም፣ ወሲብ መፈፀም።

- ሥራው የማያካትታቸው ነገሮች፤ አብሮ ማደር፣ ጠዋት የፍቅረኛ መልክ ማሳየት፣ የፍቅር አፈፃፀም አንስቶ መቀላለድ፣ ጓደኞቿ ሲመጡ ድምፅ ማሰማት፣ መኖርን መግለፅ።

"አልወጣም" አልኳት። አስቂኝ መንቆራጠጥ እየሁባት። መንቆራጠጡ ውስጥ አይኗና ከንፈሯ አሉበት። ከንዴት ይልቅ መገረም ያዘነበለበት። ቆይታ መገረሟን ንዴት እየተካው ሲሄድ በግልፅ አየሁ።

"ለምን በልደትዬ? ላንተ አስቤ፣ ማለቴ ባንተ ተማምኜ ጥናቱን ስለተቀበልኩ እኔን ጉድ ልታደርገኝ? ልታሳፍረኝ? እንዲህማ አታደርግም" የቤቱን ዙሪያ በፍጥነት ስትቃኝ የሚወረወር ዕቃ የምትፈልግ መሰለኝ። ንዴት፣ ሰማያዊ ልብሷን ሆነች።

"የጀመርኩት ሥራ አለ፣ አልሄድም" ንዴቷ ሲቀጥል ማየት ፈለኩ። ቀጥሎ፣ ቀጥሎ... እንደ ደረቅ ቁጥቋጦ በፀሐይ ቃጠሎ ቢል ብሎ እንደሚነደው ትሆናለች? ከዚያ የንዴት እሳቷን እዚህ ቤት ተቀብሎ የሚነድ ነገር አለ? እኔ...

"ገባኝ! ልደትዬን ገባኝ" የምትፀየፈው አልጋዬ ጫፍ ተቀመጠች፣ ተነሳች...

@OLDBOOKSPDF

"ምንድነው የገባሽ?" እንዲህ እንኳ ስሜት የታከለበት ፀብ አካሄደን አናውቅም:: እሷ ለማጥቃት ይሉኝታ የላትም፤ እኔ አፀፋ ለመመለስ ወኔ የለኝም:: እንዲሁ ፊትና ኋላ ስንሄድ ስንት አመት ሆነን?

"በጥናት አታሳብ፤ እንደ አይጥ ጉሮኖ ውስጥ ተቀምጠህ የትናንሽ ሴቶችን ህይወት መቅኖ ትነሳለህ:: እሱ ነው ያንተ ጥናት!!"

ዝም አልኩ፤ ከማላውቀው "እውነቴ" ጋር የተጋፈጥኩ መሰልኩ::

"ልደትዬን፣ ብታውቀው የሚያሳፍር ነው::"

ያፈርኩ መሰልኩ:: ደማቅ ሰማያዊ ቀለም የምን ምልክት ነው? የእውነት? የወቀሳ? የመግዛት? የባላባት?... የምን? ሮዝ ቀለም በየግድግዳው ሽንቁር ያጮልቃል::

"ልትወነጅይኝ ነው? ይሄ የታየሽ እንቢ ስል ነው?" የግሪክ አምላክ ቁመናዋ የተጋነነው እረጅም ሰማያዊ ጥልፍልፍ ጫማ ስላደረገች መሆኑን ልብ አልኩ::

"በልደትዬ" አልጋ ላይ ቁጭ አለች፣ ተነሳች "መንገድ ዘግቼ ነው መኪና ያቆምኩት፣ አትቀልድ" እንዴ ተከሳትሮ ከድንጋይ የተቀረፀ አምላክ ይለማመጣል? እንደዛ ተአምር"

"ተናገርኩ"

"ትለምነኛለች ብለህ ከሆነ..."

"አይደለም፣ አለመፈለግ ነው" የሆነ ነገር ሲፈርስ ያየሁ መሰለኝ:: የጣዖት አምላያነቷ ይሆን?

"ምን አገኘህ፣ በልደትዬ?"

"ምን ስላጣሁ ነበር ስትጎትቺኝ አጎቱት የነበረው? ማብላት ማጠጣትሽን፣ ሽሽገሽ ማስቀመጥሽን ለኔ እንደዋልሽው ውለታ ቆጥረሽ ነው? ያ- እንዳንዴ..."

"በቃ፣ በልደታ"

"በጭን ገረድነቱ ኩራት የሚሰማኝ ይመስልሻል?"

@OLDBOOKSPDF

ዓይኗም፣ ከንፈሯም መንቀዥቀዡን ለደቂቃዎች ገታ። ንግግርም ማረፊያ ስስ ብልት አለው። ለማንኳረፍና ለመንደፋደፍ እድል የማይሰጥ። እንዲህ ያሉ ንግግሮች ንትርክ ያሳጥራሉ፣ ነገሮች መሆን ወደሚገባቸው በፍጥነት እንዲያመሩ ያደርጋሉ። እርግጥ ቅስም ይሰብራሉ።

"በሰው ድክመት መጠቀም እንዳንቺ ካለ ሰው የሚጠበቅ አይደለም። በጥናት አታሳቢ፣ እንደ ፒኮክ የተብረቀረቀ ነገር እያሳየሽ የድሆችን ተስፋ መቅኖ መንሳት አይሰለችም?" ሆን ብዬ የእራሷን ስልት ተጠቀምኩ። ነገር ሲበዛባት ምን አንስታ ትወረውርብኝ ይሆን? መጽሐፍ? ይሁን፣ አኩፋዳ? ይሁን፣ ዱካ? ኧኸኸ...

ነፋስ እንደበዛባት ደመና የናኘችው ቀለም ከቤት ውስጥ ሲገፈፍ ታየኝ። ምናልባት መኪና ያቆመችበትን ትታ ወደብቅ እንቅ ትሄድ ይሆናል፤ ድሬን አልፋ፣ ልደታን ሳትሳለም ጠንቋይ ማረፊያ ስትደርስ የባለአውሊያዎች ድቤ ያነቃት ይሆናል።ለመሆኑ ስንት ሴቶች በእንዲህ ያለ ተስፋ መቁረጥ ቤቴንና ህይወቴን ለቅቀው ሄዱ? ቤቴንና ህይወቴን ባዶ አድርጎ ለማቆየት የስንት ሴት እንባ ጭዳ ሆኖ ፈሰሰ?

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፱

"ሠላም ለአልአዛር ከሞት ለተነሣው፤ በጭማሪ ህይወት አርባ አመት ለኖረው"

"አልአዛር ከሞት በኋላ አርባ ዓመት ኖሯል?"

"ታዲያስ፣ ያውም በምድር በረከት፣ በቤተክነት ሹመት፣ በኢጲስቆጶስነት..."

ዓይኖቹ ጎድጉደዋል፤ ቹንቹ ፈጧል፣ ከላይ እስከታች ዶቂት ለብሷል። ከይብሳ ህንጻ አንስቶ እስከ ቅንብቢት የወፍጮ ቤቱን መለያ ገዋን ለብሷል።

"ዓይቹህ ልሂድ ብዬ መጣሁ"

ማን ነበር መጠየቅ ያለበት? እርሱ? እኔ? በዶቂት ተወርሶ ከካኪ ጨርቅ የተሰፋ አሻንጉሊት መስሏል። ከፉ ቀን በመሸሸ የተሸሸጉ ዓይኖቹ ጭራቸውን የዶቂት ብናኝ ወርሷቸዋል።

"እረ ባይጤም ለካ አለች" ከራስጌ አንስቶ ውስጧን ፈተሸና ትምቻሚ ዘገነ።

ሰው የመሆን ሀፍረት ነካካኝ። መዝገኔን፣ መቃሚን፣ ባይጧን መልሼ አየር የሞላው ሆዷን ማስተንፈሴን እንዴት መናዘዝ ይቻል ይሆን? ከነ ኃጢያቱ ቤተመቅደስ የገባሁ ያህል ተሰማኝ። ኑዛዜ ሸክም መሆኑን ተረዳሁ።

"ይኸውልህ ጌታ ያለቀሰ አንድ ጊዜ ብቻ ነው። እርሱም አልአዛርን ይወደው ስለነበር መሞቱን ሲሰማ አለቀሰ። ይኸውልህ ሞት ሲታሰበኝ የጌታ የትንሳኤ መሸጋገሪያ መሆኑ አያፅናናኝም። ጌታ በማልቀሱ እንዳች ጥርጣሬ ልቤ ላይ ይቀበቀባል። ሞት ምን ቢመስል ነው ጌታ ስለወዳጁ ሞት ማልቀሱ? እላለሁ።"

@OLDBOOKSPDF

ጥሬ ያፈሰ እጄን ከእምብርቱ አንግር ብዙም ሳያርቅ አንዳንድ ፍሬ በተመሳሳይ ፍጥነት ወደአፉ ይወረውራል። ከመዳፉ ልሳን የሚወረወሩት ፍሬዎች እንደ አመሻሽ አሞሮች ተስልፈው ወደአፉ ይገባሉ። አንዷ እንኳ ከቾንቹ ጋር ተጋጭታ አትወድቅም።

"መቃናጣት ነው እንጂ ትምቻሚ ዝም ብሎ መቸርፈስ ነው ወጉ። በገፍ ይቀርባል በገፍ ይቸረፈሳል።"

ረድ ሠርዌ ከእንግዲህ መቼም ቸርፍሶ እንደማይበላ የሆነ ነገር ነገረኝ። አንድ ቀን ጠኔ እስኪጥለው ድረስ ከእህል ጋር እንደተናናቀ ለመቀጠል ሳይወሰን አልቀረም።

"ከሀዲስ ኪዳን ላይ ተቆርጠው የወጡ፣ የሙት ባህር ጥቅልል መዛግብቶች ውስጥ የተገኘ ተብሎ ማንበቤ ትዝ ይለኛል።"

"ምኑን" ጠደ አፉ ተከታትለው የሚበሩ ድንቢጦች የሚመስሉ ጥሬዎች ቆም አሉ።

"አንዱ የአላዛር ጉዳይ ነው። ከሙታን ለይቶ ካስነሳው በኋላ አልአዛር እጅግም ደስተኛ አልነበረም አሉ። አንድ ቀን ኢየሱስ በጋለሞቶች ደጅ ሲያልፍ አልአዛር ወይንጠጅ ጠግቦ ከዚያ ሲወጣ አገኘው።

"አልአዛር ሆይ በመጨረሻው ሰዓት ለአህዛብ ሁሉ መሆናከያ ምክንያታቸው ትሆን ዘንድ ወደድክን? ስለምን እንዲህ አደረክ?" ሲል ኢየሱስ ይጠይቀዋል።

አልአዛርም በስካር ንውዘት ውስጥ ሆኖ እንዲህ አለው

"ለረጅም ዘመን ህግን ጠብቄ ባንተ ተወዳጅ እስከመሆን ደርሼ ነበር። በኃጥአን ከመከበብ የሚመጡ ግፊቶችን ለመቋቋም ጥርሴን ነክሼ ቆይቻለሁ። አሁን ግን በደህና ያለፍኩትን የህይወት ጉዞ በትንሣኤ መልሰህ ጨመርክብኝ። አልቻልኩም፣ ተሸነፍኩ። መሸነፌንም በፀጋ ተቀበልኩ። ከዚህ በኋላ ባንተ መንገድ ላይ እኔ አልገኝምና አትፈልገኝ።"

"ኢየሱስ የሚለው ስላጣ ወደ ተራራ ወጥቶ ወደአባቱ ፀለየ።" ይላል የሙትባህሩ ሰነድ።

@OLDBOOKSPDF

ፀጥታ፣ ባለጌ ድምፅ መልሶ እስኪናኝ በጊዜአዊነት ሥልጣኑን ተቆጣጠረ:: ረድ ሠርዌ የመዳፉን ትምቻማ እንድ ሁለቱን ጥሬ ለቅቆ አፉ ውስጥ ከከተተ በኋላ የቀረውን ወደባይሟ መለሰ::

"የውኸርንብር ዘመን ነው:: የዕምነት ደላላው በዝቷል:: እርኩርሲምቶን በዋሸ ወርቅ የሚለውጥበትን ዘመን:: የኀብረወርቅ ድንጊያው የቱ ነው? የእኛ ወይስ የእነሱ? አለየም:: የገበያ ቱምታ ላይ ነን:: የሚለየው ሁሉም የያዘውን ይዞ ቤቱ ሲገባ ነው::"

ፀጥታ... ባይጡን በጣቱ እየከረከረ ተከዘ::

"መንታ ወንድም እንደነበረኝ ነግሬህ ነበር?"

"ትዝ አይለኝም፣ ብቻ አንድ ጊዜ እናት እንዳለህና አባትህ..."

"እዎ፣ እናቴ እሱን ነጥላ ይዛው ሄዳ ነበር:: ከትናንት በስትዚያ ወፍጮቤት መጣ"

"ወንድምህ? እሰይ!"

"ልነግርህ አይደል:: የእኔ አምሳያ ነው:: አብሮት የነበረው ሰው ያ ባለፈ ጊዜ የነገርኩህ?"

"የቱ?" ልቤ መታ

"ትንቢት ይቀደሞ ለነገር እንዳለ ትንቢቱ እየተፈፀመ ነው:: ሰውየው ጭንቅላተ ሞላላ፣ አንገተ ሰላላ፣ ቁመተ መሳላ፣ አንድ አይኑ የከሰመች፣ ሌላይቱ አይኑ የተቅላላች ናት:: ቁርጥ ሐሰተኛ መሲሁን:: ስደነግጥ በግዕዝ ተናገረኝ::"

"ምን ብሎ?"

"ቦ እለ ተሐርዩ እመ ኮርሠ እሞሙ"

"ምን ማለቱ ነው?"

"አንተ ግን ምናለ ግዕዝ ብትማር? አማርኛ ለግዕዝ ማመሳከሪያነት ይሰንፋል:: 'በእናታቸው ማህፀን ጀምሮ የተመረጡ አሉ' ነው ያለው::"

@OLDBOOKSPDF

"ክዚያስ?" ለምን ደነገጥኩ?

"ቀለበቱን እንድሳለም ግራ እጁን ሰደደልኝ። ኤጲስቆጶስ መሆኑ ነው። አሻፈረኝ አልኩ። ወንድሜ ጣልቃ ገባ፤ ምን ሲታሰብ አልኩ። በመጨረሻ ከእርሱ ልሰማው ብዬ 'ለመሆኑ እንቱማነዎት? ስምዎስ ማን ይባላል?' ስል ጠየኩ።

"'ኖላዊ' አለኝ። ከትብዬ ሳቅሁ፤ የማስበውን የመረዳት ኃይል ሳይኖረው አልቀረም" በዛች በተቅላላች አንድ አይኑ የሽሙጥ መልስ ሳቀ።

"ተግባባን፤ ከእኔ ይቅር ብዬ አልተውኩትም ነገርኩት። 'እቀትሎ ለኖላዊ ወይዝረው አባግዒሁ' ይልብዎታል። ትንቢት ነው። ድርጊትን ትንቢት ይቀድመዋል።"

ግዕዝ ማስተርጎሜ እየከበደኝ ግን ደግሞ ዝም ማለት እያቃተኝ ጠየቅሁት በዓይኑ ብቻ ገስፆኝ።

"'እረኛውን እገድለዋለሁ፣ በጎቹም ይበተናሉ' ለማለት ነው። ኖላዊ የሚል ሥም ይዞ የመጣው ኢየሱስ እንደ እረኛ ስለሚቆጠር 'እረኛ ነኝ' ለማለት ነበር። እኔ ግን ስሙን ወደፍካሬ ኢየሱስ መራሁበት"

"በመጨረሻ እንዴት ተለያያችሁ?"

"በመጨረሻማ፤ 'አንተ የተወለድከው ለእኔ፣ እኔ የመጣሁት ላንተ ነው' አለኝ። 'ቦ እለ ተሐርዩ እመ ከርሠ እሞሙ፤ ቦ እለ ተሐርዩ... ቦ እለ...' እያለ ወንድሜን አስከትሎ ሄደ። አልባሌ መስለዋል። አባቱ ወደ ብሔረ ብፁአን የሸሹት፣ እኔ የመታጎቻቸው ሁሉ የመጨረሻው መግቢያ ነው። የመጨረሻው፣ የመጨረሻው፣ የመጨረሻው..."

ቃላት ሲደጋገሙና ሲነባበሩ ስለምን ኃይል ነጥሮ ይወጣል? ረድ ሠርዊ አመድ በጋረደው ጠርሙስ ውስጥ የተቀመጠ መሰለኝ። ምንድነው ቤቱ ድረስ ይዞብኝ የመጣው ሽብር? ስል እራሴን ጠየኩ። በእርግጥ ይቺ ብናኝ ዓለም ገዝና ባለቤት አላት? የብናኟ ኢምንት ቅንጣት እኛ፣ ከተሽንጥንበት የድንጋይ ኮርፍርፍ ድረስ መጥቶ ሰብሮ የሚያወጣን፣ አውጥቶ የሚቆጥረን ፈጣሪ አሮን? እኛን ከቁብ ቆጥሮ

@OLDBOOKSPDF

አንተ ገሃነም ግባ፣ አንተ ገነት እያለ የሚደለድል ከሆነ በእርግጥ እርሱ ታላቅ ነው?

"...የመጨረሻው፣ የመጨረሻው፣ የመጨረሻው፣ የመጨረሻው... ስለምን እኔን? ስለምን እኔን አሳልፈህ ሰጠህ? ስለምንስ ዕጣፈንታዬን ከእዚህ ጋር አስተሳሰርህ? እስትንፋስህ በእኔ አልሰረፀምን? እናቱን ስለእናትነህ አይተህ ልትምረኝ አይገባምን?..." ተነሣ፣ እንደመንፈስ ሰተተተተ... እያለ ከቤት ሲወጣ እንዲህ እያለ ነበር።

"ልበ ንጹህ ፍጥር ሊተ እግዚእ

መንፈስ ርቱዕ ሐድስ ውስተ ከርስየ

አትግድፈኒ እመቅደመ ገጽከ

አልኩ። ክፉው ትንቢት ከፀሎቱ በላይ አይደለምን? ማንድከም አለኝ? ትንቢትን ድርጊት እንጂ ምህረት ይከተለዋል? ከኖረ፣ ከተብላላ ትንቢት ይልቅ ድንገት የገነፈለ ቁጣ አይሻልምን? ትንቢትህን በቁጣ ቀይርልኝ" ግትር ብሎ ቆመ። ያልበሰለ የሲሚንቶ ሀውልት ይመስላል። ፀሎቱን በአማርኛ ቀጠለው።

"አቤቱ ንጹህ ልብን ፍጠርልኝ፣

"የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ

"ከፊትህ አትጣለኝ፣ ከፊትህ አትጣለኝ፣ ከፊትህ አትጣለኝ፣ ከፊትህ፣ ከፊትህ..." ወጣ። አከታትሎ ውሻ ጮኸ። 'ጃክ?' በዱላ እንደተጠለዘ ምንጣፍ ቡን የሚል ድምጽ አሰማ። እውነትም የአገሩን ፓስታ መብላቱ አወበራው? ወይስ ረድ ሠርዊን የተከተለው ለሱ ብቻ ታየው?...

...እኔም 'ከፊትህ አትጣለኝ' ማለት አሰኘኝ።

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፲

ልቤ በሀሳብ ስፌት ደግግሞሽ የክር ትብትብ ኳስ ሳይመስል አይቀርም። የሚገላግለኝ ፍለጋ ነፍሴ ኡኡኡ... ብላ ጮኸች። ፈጣሪ ካለ የተፈጣሪ ዕጣ-ፈንታ ከሸክላ ሥራ አንድ መሆን ነበረበት? ከንጉስ ፊት በክብር ተሸልሞ የሚቀመጥ ዕዋ ሆነ፣ ለወጥ መቀቀያ እሳት ላይ የሚወዘት ቶፋነት የሸክላ ሠሪው ውሳኔ እንደሆነ፤ እንዲሁ ታላቅ በተባለው ፈጣሪ ዘንድ መተግበር ነበረበት? እዚህ ውስጥ ምን ታላቅነት አለ?...

ኡ! ኡ! ኡ!....

...እኛ እርሱን በመፍጠራችን ልንፀፀት ይገባል። ከዚህ የተሻለ፣ ያስቀመጥንበትን ቦታ የሚመጥን እግዚአብሔር መፍጠር ይገባን ነበር። የአጥቢያ ዳኛ ይመስል የሐጢያት መዝገብ አገላብጦ 'አንተ ለእሳት'፣ 'አንተኛው ለገነት' ብሎ መፍረድን እንኳን ታላቁ ፈጣሪን እኔንስ ይመጥናል? ይሄንን ታላቅነት እኔ እፈልገዋለሁ?...

ኡ! ኡ! ኡ!...

...እንደተባለው እግዚአብሔር የለም! ወይንም እግዚአብሔር ሞቷል! የእኛ የመፍጠር አቅም ሆነ የማሰብ አድማስ ትክክለኛውን ፈጣሪ አይሸከመውም። መፍጠር ህልውናው የሆነ አምላክ ቁጭ ብሎ ጥንት በፈጠራቸው ላይ ለመፍረድ መከዳ አያሞቅም። ሌላ ይፈጥራል... ሌላ... ሌላ... እንዴ ከፈጠራቸው ጋር ጉዳይ የለውም። ምስጋና ለማትረፍ የሚፈጥር የፈጣሪነት ሚና ሊኖረው አይችልም።

ኡ! ኡ! ኡ!...

...አሁን የጮኸው ነፍሴ ሳይሆን ደጃፌ ነው። ማን ከፈተው? ዘወር ብዬ አየሁ። ጃክ ነበር፡ የዘነበ መስሎኝ ከቀልቤ ለመሆን ሞከርኩ። አልዘነበም። ጃክ መቀናጣት ጀምሯል። ለዝናብ የፈቀድኩለትን መብት

@OLDBOOKSPDF

ወደ ቋሚ ደባልነት ለመቀየር ያሰበ ይመስላል:: የፊት እግሩን አንጥፎ ዘባዘቦ ፊቱን አሳረፈ:: የሚዘንብ ፊት፣ ዓይኖቹ ባዘበዘበ ቅንድቡ እየተሸፈኑ ነው:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሞት ይቅርታ ካላደረገለት ዓይኖቹ በቅንድቦቹ ተጋርደው ምርኩዝ እየጠቆመ መሄዱ አይቀርም::

...ደጃፌ ኡኡታውን ሲያሰማ ናትራ መስላኝ ነበር:: ዛሬ ቀን ናትራን ለመንኳት፣ እኔጋ እደሪ አልኳት::

"ጨረቃ ሙሉ ናት" አለችኝ::

ናትራን ሙጥኝ አልኩ:: ትናንሽ ጉዳዮች ላይ ማሰብ ናፈቀኝ:: የሚያስጨንቅ በስሜት የተሞላ፣ በአንዱ ንግግሯ በቀደደችው መንገድ ልታመልጥ ስትል ቀድሜ መሸጋገሪያ ድልድይዋን መስበር::

"በእናትሽ" ብዬ አውቅ ነበር? እንጃ! ግን አልኩ::

"እንቢ"

"በቃ?"

"በቃ!"

አበቃ፣ ከማያልቅ እግዚአብሔር ጋር መጨረሻ የሌለው የሀሳብ ህዋ ውስጥ ድብብቆሽ ሲጫወቱ ጭንቅላት ማፈንዳት ዕጣ-ፈንታዬ መሆኑን አረጋገጥኩ::

ለመጀመሪያ ጊዜ የቤቱን መብራት አጠፋሁ:: ጨለማ የህዋ አምሳያ ወንድም ነው:: እንደብርሃን ቀሊል አይደለም:: ናትራ በእንቢታዋ የፀናችው እንደጭለማ ግርማ ሞገሴ ሳይገለጥ በመቆየቱ ነበር:: በመጨረሻ እንደብርሃን ቀሊል፣ ፍላጎት የማልሸሽግ ሆኜ ተገኘሁ:: የትኛውን ምስጢር ለማሰስ ከእኔ ጋር ትደር? እምቢ ስባል እግር ላይ ተደፍቼ ለመለመን ወደኋላ አልልም::

"እውነትም የስርቻ ውስጥ አይጥ ነኝ:: የትናንሽ ሴቶችን ህይወት መቅኖ ለመንሳት የተፈጠርኩ"

"ነኝ?"

"አዎ!"

@OLDBOOKSPDF

"ነኝ?"

"አዎ!"

"ምናገባኝ"

"እንዴት?"

"እንዲህ አድርጎ የፈጠረኝ ይዘንበት"

ላብድ ይሆን እንዴ? የሌለ ድምፅ ከየት መጣ? ለንትርኩ ምላሽ ስሰጥ ድምፅ አውጥቼ ይሆን? እንዲያ ከሆነማ...

...እንቅልፍ መሰል መናወዝ እንዴት ጣለኝ? ደጃፌ ሲከፈት ማስካካት የጀመረው ከየትኛዋ ጋለሞታ ተምሮት ነው? ከጃክ ቀድሞ ደጃፌ ሲያረጅ? የተኛሁበት አይኔን ሳልገልጥ የሚገባውን ወይም አድሮ የሚወጣውን ጃክ ለማወቅ ጣርኩ:: ቤቱን የገነነ የሴት ጠረን የሞላው መሰለኝ:: በናትራ ላይ የጀመርኩት መቃበዝ የፈጠረው መናወዝ መስሎኝ አደፈጥኩ::

"መብራቱን አብራ እስኪ" የሴት ድምፅ:: ከማበዴ በፊት ለይስሃቅ መድህን የተላከው ነጭ በግ:: ይሄን ካደረገማ አምላኬ አለ ማለት ነው? መከዳ እያሞቀ ለእያንዳንዷ ነፍስ መቃበዝ ማመልከቻዋ ላይ ይመራል:: በጠየቁት መሰረት ይፈፀምላቸዋል (አንቱ ሲለኝ?)

መብራት አበራሁ:: ነፀብራቅ ማንፀባረቋን ትታ እንደደበዘዘች ለዘብተኛ ብርሃን ትረጫለች:: ንጥር ሽቶዋን ምን ዋጠው? ከመልመጼ ብዛት ነፀብራቅ ንጥርሽቶዋን የምትቀባው ሳይሆን ከላይ ጋር የምታመነጨው እስኪመስለኝ ደርሶ አልነበር? ይሰበር ይመስል የነበረው ግትርነት የትገባ?

"ለምን የመጣሁ ይመስልሃል?"

ዝም፣ ስክራለች? ~

"ለምን የጠጣሁ ይመስልሃል?"

ዝም፣ አዎ ስክራለች

@OLDBOOKSPDF
"አንተ ያሰብከኝን አይነት ሰው እንዳልሆንኩ እንድታውቅ::"

"እንዴት መጣሽ? ማለቴ መኪናሽስ? እእ ከማን ጋር መጣሽ?"

"ከጓደኞቼ ጋር፣ መኪናዋን ይዘው ተመለሱ"

"የት እንደምትሄጂ አውቀዋል?"

"ነገርኳቸው ልደትዬን ነገርኳቸው"

"ምን ብለሽ?"

"ታለን ታውቂታላችሁ? ግቢ እያለን የተጣላነው? እሱጋ ነው የምሄደው"

"ነዒ?"

"እውነት ስላቸው ወይኔ ጉዷ እያሉ አሾካኩ፡፡ "ዞረሽ፣ ዞረሽ እዚያው?" አሉ፡፡ በልደትዬ አቤት የተሰማኝ ማነስ?

"ማነስ ከተሰማሽ መቅረት"

የጠገበ ቦርሳዋን ወረወረች፡፡ ያልበላ ሆዴ ላይ አረፈ፡፡ ሊያስቃስተኝ?

"ጓደኞችሽ ከሄዱ ታዲያ..."

"እዚህ አድራለሁ፡፡ ልደትዬን እድሌ ጥሩ ነው፡፡ ሌላ ሴት ውሻ ትኖራለች ብዬ ነበር፤ ብትኖርስ? እኔ እዚያ ከለማኝ አቁማዳህ ጋር እተኛ ነበራ፤ አንተ ከውሻህ ጋር፡፡"

ዞራ ጃከን አየችው፡፡ ቀልቧን አልወደደውም መሰል እንደቅጠል የከሸለለ ጆሮውን ለማቆም ያልወሰውሳል፡፡

"ና-ውጣ!" በሩን ከፍታ፡፡

(እ! እ! የዛሬዋ ደም) የሚል ይመስላል ወገቡን እያጥመለመለ፡፡

"ና ውጣ'ኮ"

(ቀስ በያ፣ ወገቤ መያዙን አታይም?) ከመውጣቱ በፊት እኔን ባዘበዘበ ፊቱ አየኝ፡፡ የትዝብት አመለካከት የላከብኝ ይመስላል፡፡ "ፍቅር

@OLDBOOKSPDF

ያዘኝ ብለህ ከቤት ልታስባርር? እኔም ትናንትና እንዲህ አድርጎኝ ነበር የሚል።

ምንም አላልኩለትም።

"የምን ጉድ ነህ ግን! ለራስህ የሚገባህን ክብር ለምን አትሰጥም?"

"በዛሬ ሁኔታችን መመከር ያለብሽ አንቺ ነሽ።" የደበዘዘ ኮትና አጭር ቀሚስ ለብሳለች ልብሷን ሳይ ቡና በወተት አማረኝ። ከጠጣሁ ስንት ጊዜ?

"እውነቱን እኮ ነው። ከማንም የተሻለ ዕውቀት አለህ፣ ከማንም የሚበልጥ! ዛሬ ልመስክርልህ... ግን...

ዝም፣ ብቃረናት ልትቧጭረኝ፣ ልትነካክሰኝ ለንደኛ ምላ የመጣች ይመስላል። ከወገቧ በታች ጠንካራና የተስተካከለ ቁመና አላት። ስታወራ የምታንቆለጳጵሳቸው ክንፈሮቿ ምን ውስጥ ተወሸቁ?

"መለመን ጀመርክ?" ወደ አልጋው ተጠግታ ባይጧን በንቀት እያየች:

"አስቤ፣ ተዘጋጅቼ ነበር"

"እና?"

"እንደ እውርአሞራ ቤቴ ድረስ እያመጣልኝ እያየሽ?"

"ምን ለማለት ነው?" ድርቅርቅ ያለ ቁጣዋ የት ሄደ? "እኔን ቤትህ ድረስ አመጣልህ?"

ዝም-ፀጧ ባያስፈራም፤

"እስኪ በልደትዬ ይሁንብህ ይሄንን ህይወት ለመምረጥ ያስቻለህ ምንድነው? ምክንያት አለህ?" አልጋ ላይ ቁጭ አለች።

"እስኪ አንቺ የምትኖሪውን በምን ምክንያት እንደመረጥሽ መጀመሪያ ንገሪኝ።"

"Sociatic Dialogue በሎጂክ ልትከራከረኝ ነው? እሱን እዚህ ላይ እርሳውና..." @OLDBOOKSPDF ቆየች "ምን ነበር እናወራ የነበረው?"

"እኔ እንጃ" አልኳት በትከሻዬ:: የእግሯን አውራጣት ተረከዟ ላይ እያስደገፈች ጫማዋን እስፈንጥራ አወለቀች::

"ወይ ልደትዬ ምን ነበር በእናትህ?"

ኧረ ነፀብራቅ! ዛሬ ቁጭ አህቴን፤ ረቂቅን::

"በቃ ተኚ፣ ነገ እናወራለን"

"አንተ አትተኛም? በልደትዬ"

"እተኛለሁ፣ ብቻ አንቺ..."

"ይሄንን ተንተርሺ? የስራ briefcase? ጠዋት ስራ ስትሄድ ጭንቅላቴን አመናጭቀህ..."

አለመጠጣት ነበር የሚጎድላት? ሰው እንዳትሆን ያገዳት? ቆይ ጨዋታ ልጨምርላት...

"አንድ ነገር ልንገርሽ?" አልኳት::

"በልደትዬ፣ ንገረኝ፣ ንገረኝ..."

"በፊት ሥጋ፣ አጥንት፣ ደም ያለሽ አይመስለኝም ነበር::"

"What does it mean? ማለቴ..."

"በቃ Mechanical woman አይነት:: ብሎ ብሎን፣ የተወታተበ ኬብል፣ ጀርባሽ ላይ RS Number 2348 የሚል ነገር የተፃፈብሽ::"

"እንዴ፣ ኧረ ቆይ... እኔ..."

"አዎ Imput — output — COHRKC 010272 ሴሪያል፣ ሞድ፣ DC 48V... ምናምን"

ሳቀች፣ ያልተቆጠበ ሳቅ:: ስትጨርስ ኢንፑቱ የት ነው?"

በአይኔ አቅጣጫውን ጠቆምኳት

"እናትን፣ አውትፑቱስ?"

@OLDBOOKSPDF

ጠቆምኳት "አሳመምከኝ" እያለች ሳቀች "ይሄን ያህል?" ሳቅኩ።

"ግን እኮ ሰው ሁሉ Mechanical ነው።"

"በ Mechanicla philosophy ማለትሽ ነው?"

"አዎ፣ በእርግጥም" ደሞ ይመስላል። የተወታተበውን ከብል በደም ሥር መስለው፣ ልብ ደሞ ዲናሞ መሆኑ ነው። የመረጃ ቋቱን በአእምሮ፣ ደምን በኃይል..."

"ልደትዬን እንዳትጨምሪበት"

ሳቀች፤

"እያስረገጥሽ ያለሽውኮ በቁስ አካል የሚያምኑ ፍልስፍናን ነው። ነፍስ፣ መንፈስ፣ ፈጣሪ፣ ተፈጣሪ፣ ኃይማኖት... ምናምን የሚባል ነገር የለም የሚሉ። ሰው እንደመኪና አንድ ጥግ እንደቆመ ዝጎ ግብአተመሬቱን እንደሚፈፀም አይነት የሞተሮች መገጣጠም ውጤት ነው የሚሉ። አንቺ በዚህ ታምኛለሽ?"

"በፍፁም፤ የሰው ልጅ ከፍፁማዊው እውነት ሲርቅ የራሱን መጫወቻ ሃሳቦች እየገጣጠመ ለጊዜውም ቢሆን መፅናኛውን ያገኛል።"

"ፍፁማዊው እውነት ምንድነው?"

"ፍፁማዊው እውነትማ ፍፁማዊ ካልሆነው እውነት ባሻገር ያለ፣ የሁሉም ነገር ምንጭ፣ ጠፍቶህ ነው የምትጠይቀኝ በልደታ?"

"በነገራችን ላይ፣ እንደዛ ማሰብህ አይሚን "Mechanical woman የመሰልኩህ ህልምህ ቲፕ ስለሆነ ይሆናል፤ ደሞ እታያ" አያንጓህም። ይሁንና ሰው ተመኝተህ አታውቅም። ለቤትህ ሰው እርካሽ ነው። ገባህ? በቃ፣ ቆንጆ ሴት አስቀምጠህ ስለኢንቲት አውትፑት ታወራለህ? ና ወይም ልምጣ?"

ይሄን ነበር የተመኘሁት? እንኳኳሁ ተከፈተልኝ፣ በመሻቴ አገኘሁ... ከዚህ በኋላ ያለው ትርፍ ጉዳይ ነው። ወደግድግዳ መግፋት ስላልቻልኩ አልፈያት ጥግ ያዝኩ። በእንቅልፍ ልብ በሚመስል መንፈስ ዞራ አቅፋኝ።

@OLDBOOKSPDF

"ዓለም ገፍቶሃል፣ የሚገባህ ቦታ ላይ አይደለህም፤ ሁልጊዜም ስላንተ ሳስብ ልቤ ይደማል፡፡ እኔ ወዳለሁበት ልወስድህ አስባለሁ፤ ልደትዬን ግን አንተን የሚያፅናናህ ወዳለህበት ወርጄ እንደምትሆን ሆኜ መገኘቴ ሆነ፡፡ በእኔ ሰበብ እኔ ወዳለሁበት 'ፕሮፐር ላይፍ' ካልመጣህ ለዘንተ ዓለም እዚሁ መቅረትህ ነው፡፡"

ወደ ጡቷ አስጠግታ እናቴን ሳመችኝ፡፡ የፀጉሬ ጫፍ የነርቬ ማጣቀሻ እንደሆነ ሁሉ መላ አካላቴ በስሜት ረብሻ ውስጥ ሆነ፡፡ ማወናበጃ የሌለበት የሴት ጠረን ማግሁ፡፡

* * *

ጨለማ ያድበሰበሰውን ብርሃን ይገልፀዋል፡፡ የነፀብራቅን ሁኔታ አስካረጋግጥ በፀጥታ በጆርባዬ ተንጋለልኩ፡፡

"Bathroom አለ?"

ዝም

"restroom? በልደትዬ"

ዝም፣ ተጀመረ፤ የሌለ እያወቁ መጠየቅ?

"ከነ ቅንቅኔ ወደቤቴ እንድሄድልህ ነው እዚህ እንዳድር የፈለከው?"

ዝም፤ ሁሉም ነገር ዋጋ አለው፡፡ ማታ ከተደሰትኩ ጠዋት አፀፋውን ቆጥሬ መቀበል ይኖርብኛል፡፡

እጇን ወደጎኳ ሰድዳ እጄን ፈለገች፡፡ Bathroom እና Restroom ስለሌለ ልትቆነጥጠኝ? እንደተፈራው አይደለም፤ እጄን ስባ በወገቧ በኩል አሳልፋ እንዳቅፋት አደረገች፡፡

"እንዴት ይሄን ያህል ዝቅ ማለት ይቻላል? እንዴት ሁሉን ነገር ትቶ ህይወትን ባዶ በማድረግ ኑሮን መምራት ምርጫ ይሆናል? ቤትን ከፍቶ ትቶ እርኩሱን፣ ቅዱሱን ሳይመርጡ መጋበዝ ለሰው ልጅ ይቻላል?..."

@OLDBOOKSPDF

እሷ ባየችኝ መንገድ እራሴን ከተቀበልኩ ለራሴ ገድል መዓፈ የማይቀር ነው:: "ዜና ህይወቱ ወተጋድሎቱ አባ አልአዛር በእርምጃው" ሳቅሁ::

"እየሳቅህ ነው በልደትዬ" እጇን አመናጨቀች::

"ሳይሆን..."

"ሳይሆን ምን?"

"በቃ ሥራ ቆመ፣ ገቢ ታጣ፣ ድህነት ሰተት ብሎ ገባ:: ከዚህ ውጪ ኑሮዬን በሌላ መንገድ ማየት የሚቻል አይመስለኝም::"

"የመረጥከውን እንጂ ያልመረጥከውን ህይወት እየኖርክ አይደለም"

"እንዴት?" እጇን ወደነበረበት ለመመለስ

"መጀመሪያ ጋዜጠኝነት ያንተ ቦታ አልነበረም:: ጭንቅላትህ ከዚያ በላይ ሊያሰራ የሚችል ነው:: ሁለተኛ ቋሚ መምህርነት ተወዳድረህ መግባት ስትችል በኮንትራት የውርደት መምህርነትን መረጥክ:: እሺ ይሁን፤ ለምን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ በደህና ደሞዝ አትቀጠርም? እኔም ብሆን ላገኝልህ እችላለሁ::"

"እሱ የእኔ ቦታ አይደለም::"

"ለምን እንዳልሆነ አውቃለሁ ልደትዬን"

"ለምንድነው?"

"ፕሮቶኮል ግድ ስለሚል፣ ይሄንን ዝቅታው የተረጋገጠ አኗኗር ስለማይፈቅድ"

ዝም፣ እውነትም ሊሆን ይችላል:: ሱፍ ለብሼ፣ ከረቫት አስሬ፣ ሽቶ ተርከፍክፌ፣ የብብት ጠረን ማጥፊያ ነፍቼ... በየቀኑ...::

"አይደል?"

"እየተጨቃጨቅን ነው? በፍፁማዊ እውነት ይገርሻለሁ ይሄን ነገር ተይው::"

@OLDBOOKSPDF

"የምን ፍፁማዊ እውነት?"

"ፍፁማዊ ካልሆነው እውነት ባሻገር ባለው ነዋ"

"መሸፋ ነው? አሹፍ፣ ልደትዬን አሹፍ" ከአልጋው ላይ እግሯን አውርዳ ጀርባዋን ሰጠችኝ፡፡ መሄዷን እኔም ፈቅጄዋለሁ፡፡

"ኡሁሁሁ፣ የሚበላ ነገር የለም?"

"አለ፣ አኩፋዳው ውስጥ፣ ችምቻሚ ይባላል" ለሌላ ጭቅጭቅ እራሴን አሳልፌ መስጠቴ ገባኝ፡፡ ቶሎ ብዬ አፏን ያዝኩት፡፡

"በቃ! በቃ! በቃ!..." አፏን አስለቅቃ

"ለምን ያቺ ልጅ ቁርስ አትሰራልንም?"

ዝም

"እንቁላል መጥበስ አትችል ይሆን?"

ዝም፤ የእህቶቼ ወንድም ነኝ፡፡ የዚህ ትርጉም አይጠፋኝም፡፡ ነፀብራቅ ናትራን በእኔ ጠርጥራታለች፤ ደረጃዋን ዝቅ ማድረግ ፈልጋለች፤

"እንዳትንገላታብህ ነው?"

"እዚህ ምንም አይነት ምግብ ማብሰል አይቻልም፡፡ ዕቃም ማብሰያም የለም፡፡ ስትሄጂ እውጭ ትበያለሽ"

በፀጥታ ልብሷን ለባበሰች፡፡ አለባበሷ ላይ ኩርፊያ አለበት፡፡ ከቧንቧ በጠርሙስ የፊት መታጠቢያ ይገፍላት መጣሁ፡፡ ሁኔታዋ ከኩርፊያ ወደ ሽሙጥ ተሸጋገረ፡፡ ለጥቂት ጊዜ ከቤት ወጥቼ ደጃፍ ላይ ቆምኩላት፡፡ ናትራም ጃክም አለመኖራቸው አስደሰተኝ፡፡ ቦርሳዋን ይዛ ወጣች ፤ በመጠኑ ተኳኩላለች

"ልሸኝሽ? ትፈልጊያለሽ?" አብሬአት እንዲት ምዕራፍ ተጉዤ እንደማላውቅ ትዝ አለኝ፡፡

"እሺ" ትልቅ ለውጥ፣ በብርሃን ያልጠበኩት ለውጥ፤ ቦርሳዋን ስትፈትሽ የሀፍረት መሸፈኛ መስሎኝ ነበር፡፡

@OLDBOOKSPDF

"መኪናዬን እምጥታችሁ ትምህርት ቤቱ ጋ አቁሙልኝ ብዬ ነበር"

"ቁልፉስ?"

"ትርፍ አለኝ፣ ከቤት ይገኙ ወጥቻለሁ።"

በሽሙጥ ፈገግ ስል

"አዎ፣ ከቀን ጀምሮ ተዘጋጅቼበት ነው የወጣሁት፣ ጉረኛ! ልደትዬን ጉረኛ ነህ። የምትሄድበት ካለህ ላድርስህ" አሰብኩበት፣ አዎ...

"ይብሳ ህንፃ አድርሺኝ"

"የት ነው?"

"አሳይሻለሁ"

አሳየኋት፣ ልወርድ ስል ሸሚዜን ጎተት አድርጋ ጥቂት ብሮች ኪሴ ውስጥ ወሸቀችልኝና

"ሌላ ብር የለማኝ ኮሮጆህ ውስጥ ከትቼልሃለሁ። ከቻልክ፣ በእናትህ ቻል፣ ልብስ ግዛ፣ ጥሩ፣ ጥሩ... ወደድከም ጠላህም አንድ የማውቀው ግብረ ሠናይ ድርጅት አለ፣ እዛ ሄደን ሥራ ትጀምራለህ። እወድሃለሁ፣ በጣም!" ፊቷን መለሰች። አይኖቿ እንባ ያቀረሩ መሰለኝ።

ረድ ሠርዌ ስለአባቱ እንዳለው ነው። ማሽነፍ ውስጥ መሸነፍ፣ መሸነፍ ውስጥ ማሸነፍ እንዳለ እኔም ገባኝ። የትኛውም የድል በአል ጀርባው የሽንፈት ንክኪ አለው።

መኪናዋን በአይኔ ሸኘቼ ወደ ወፍጮ ቤት አመራሁ። ዛሬ ጭንቅላቴ ውስጥ የምከተው ትዕይንት ለዘልአለሙ አብሮኝ መዝለቅ እንደሚችል ሳስብ ፈራሁ። ረድ ሠርዌ ጾቂት ተሸክሞ፣ ወይ በሰራ ወንፊት እህል እየነፋ፣ ወይም እየፈጨ...

...ረድ ሠርዌ ወፍጮ ቤቱ ደጃፍ ላይ ሆኖ በትልቅ የፕላስቲክ ሳፋ የሆነ ነገር እያጠበ ነበር። ሲያየኝ በድግ ብሎ የእጁን አረፋ ወደ ሳፋው አጋባ።

@OLDBOOKSPDF

"ወውእቱ ገብረ በህላዌሁ በዘያነጽህ ኃጢአተነ" የሚል ሲሰርፅብኝ፣ አንተ ስትመጣ አንድ ሆነ። ልዑል እግዚአብሔር በኃጢአታችን በውኃ ጥምቀት እንዳነፃን የተነገረ ነው። እኔም እዚች ሳፋ ላይ ያለውን የውኃ ክንውን እንደመዳኛዬ አየሁት።"

"እንዴት?"

"እንዴት ማለት ጥሩ፤ እንዴትማ..." ሲል የወፍጮ ቤቱ አለቃ ሆዱን እያሻሸ ወጣ።

"ቶሎ በል እንጂ፣ መለወጫ ካልሲ የለኝም ስልህ? እሺ ማለት ብቻውን ምን ይሰራል? ሠርቶ ማጥገብ አትችልምና" አለ። እኔን ድንገት ያየ መስሎ ነገር አከለ።

"አልአዛር፣ የወፍጮ ቤቱ ደንብ ነው። "ልጆቹ" በየተራ የእኔ የሆኑ ነገሮችን ያጥቡልኛል። ዛሬ ሠርዌ ተረኛ ነው።"

ነገር እጅ እጅ እንዳለ ምግብ ወደላይ ይላል? እኔን አለኝ። የረድ ሠርዌ ውርደቱ በዛ። ወደ ጥግ ሄጄ ለማስመለስ ሞከርኩ። ነገር እንጂ ሌላ ሆዴ ባለመኖሩ ልቤን ከፋኛ ለበቀኝ። ልቤን በጉሮሮዬ አስጎትቱ ሲበቃኝ ረድ ሠርዌን መለስ ብዬ ሳላይ ወደ መንገድ ገባሁ።

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፲፩

ሰው ከአቶንት፣ ሰው ከጊንጥ፣ ሰው ከጥንብአንሳ፣ ሰው ከመናጢት፣ ሰው ከዝሆ፣ ሰው ከአርጃኖ፣ ሰው ከአንዝዝ፣ ሰው ከአጽዋት... የሚለይበት የተፈጥሮ መድልኦ አለው? ከአይጥና ከጉርጥ የተሻለ ሐልዮት ለሰው ልጅ ስለተሰጠ በተፈጥሮ ዘንድ ልዩ ሥፍራ ተዘጋጅቶለታል ለማለት ያስችላል? የግሪኩ አምላክ ፕሮሚቲየስ ለሌሎቹ እንስሳት፣ ጥፍር፣ ቀንድ፣ ኩምቢ፣ ጥርስ፣ መንደፊያ፣ መርዝ፣ ጠጉሬ ሸሆና በመታደሉ ተቆጭቶ አይደለም ለሰው ልጅ እሳትና የእሳት መጠቀሚያ ሐልዮት የሰጠው? የሰው ልጅ ሐልዮት እራሱን ከመከላከያ ቀንድ እና ከንድ በምን ይለያል? ተፈጥሮ የሰው ልጅ እራሱን ከአጥፊዎች እየተከላከለ ዘሩን ከማስቀጠል ውጭ የምትፈልግበት ነገር አለ?...

...ለመሆኑ 'ክብር' የሚባለው ነገር የሰው ልጅ ጣጣ ከመሆን ያልፋል? የተከበረ ለመሆን አጠቃላይ የሰው ልጅ ጣጣ ከመሆን ያልፋል? የተከበረ ለመሆን አጠቃላይ የሰው ልጅ በልዕለ-ተፈጥሮ ካልተቀባ ክብሩ እምጥቶ አስኬማ ደፋ? 'ለክብር ተፈጠርህ፣ ወድቀህ ተገኘህ' ማለት አለማዊ ረድፍን ከማሳመር ውጭ ለተፈጥሮ ምኗ ነው? ሥነ-ምግባር፣ ትህትና፣ ግብረገብ፣ ሆደ ሠፊነት፣ ፍቅር፣ ታማኝነት... ሰውን በሰው ከማሸለም ውጭ ለተፈጥሮ ቁብ ይሰጣታል? የመኖር ግባችን ከመብላትና ከመብዳት አልፎ ይዝላል? ዘርን መተካት፤ በሁሉም እንስሳት እትክልትም ጭምር የሚታይ ደመነፍሳዊ መፍጨርጨር አይደለም?...

...ንጉስ ዳዊት "ህግህም በልቤ ውስጥ ነው" ማለቱን መዝሙር ላይ ለፍሮ ስመለከት ቀጥታ ከሰው ልጅ ዕጣ ፈንታ ጋር መላተሜን እስታውሳለሁ:: እግዚአብሔር ተራ ክልኖን በስተቀር ህጉን በማያስተማምን የሰው ልጅ አፍ እና ዕህፈት ላይ አያደርግም:: ከተፈጥሮዬ ጋር ተላውሶ፣ ከደምና ከሥጋዬ ጋር የተነበረ ህግ አለ፤ ስንፈልግ ህጉ-ልቡና [illegible]:: እንደሁኔታው እየተለዋወጠ የሚጠብቅና የሚላላ መተዳደሪያ ልቤ ላይ ተደርጎልኛል:: እርሱም

@OLDBOOKSPDF

በድንጋይ ዕላት ላይ ከሰፈረው ህግ በላይ ለሰው ልጅ በምድር መገኘት አስፈላጊ ነው።

ባይጥ ውስጥ ቸምቻሚ አድሮ እኔ በታማኝነት ብሞት ለተፈጥሮ ትርፏ ምንድርነው? በእርምሞ ቤቴን ዘግቼ ሴት ሳላስደርስ በብህትውና እና በድንግልና ባልፍ ለተፈጥሮ ኪሳራ ማስቀጠር አይሆንም? ከእኔ መብላት ሆነ ፍትወት ውጭ ተፈጥሮ እኔጋ ምን ተፈጥሯዊ ህግ አላት? ሲበዛብኝ፤ ኡ! ኡ! ኡ!... ማለት አሰኘኝ።

ግን ሰው ወደ አያስብም፤ ምንም እንኳን ግዳጁ ከምን እንደመነጨ ባይገባውም ማንቁርቱን ታንቆ ያስባል። የሚያስበው ነገር የመውረድና የመውጣት ለውጥ የለውም። ስለሚማ አሰበ ስለፈጣሪ ሀልውና አውጠንጠን ልዩነት አያመጣም። ግን ማሰብ የሰው ልጅ ሰው የመሆኑ ግዳጅ ነው።

መነሻዬ የረድ ሠርዌ ከክብር ወድቆ መገኘት ነው። የክብርን ጉዳይ ፈረንጅ እያጣቀሱኩ ክፍል ውስጥ ብዙ ጊዜ አነብንቤዋለሁ። ረድ ሠርዌ የእግር ሹራብ ሲያጥብ በማግኘቴ የተሰማኝን ያህል ክብር ተፈጥሮዬ ሆኗል ብዬ አስቤ አላውቅም። ለራሴም የክብር ልኬት ስላላስቀመጥኩ ይሆናል፤ አንድ ነገር ክብሬ ተነካ በሚል አተካራ ገጥሜ አላውቅም። ለእኔ የክብር መለኪያዬ ከረድ ሠርዌ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስላለው ይሆናል። ሁለት ጊዜም ክብሬ የተነካ የመሰለኝ ረድ ሠርዌ የተዋረደ ሲመስለኝ ነው።

የክብር ጉዳይ አዲስ ምርምርና አዲስ መዳረሻ ሳያስፈልገው አይቀርም። የወፍጮ ቤቱ ጌታ የረድ ሠርዌን የእግር ሹራብ ቢያጥብስ? የዓለም መጨረሻ የደረሰ የሚመስላቸው ሰዎች የሉም? ጀርመናዊው ፈላስፋ ካንት እንዳለው ሳይሆን አይቀርም። ክብር ግለሰቡ ለራሱ ከሚሰጠው ውስጣዊ ግምት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ነገር ነው። ይሁንና ዘወትር ክብርን እያሰቡ መንቀሳቀስ በተለይ እራስን በሚፈልጉት አቅጣጫ ለመምራት የማያስችል እንቅፋት ነው ይላል ካንት።የክብር አድማስ እየሰፋ ሲሄድ መንቀሳቀሻ መስክ እየጠበበ መሄዱ እውነትነት ይኖረው ይሆን?

"እንደምን ዋላችሁ፤

ለጠንቋይ ያስቀላችሁ፤

እንባችሁ ከወፍጮ ቤት ይረሰላችሁ።

@OLDBOOKSPDF

ሀቅህን ውሰድና ገላግለን፣

ጠቋር ስንት ቀን እንቅልፍ ነሳን፤

ተብለሃል!!"

ያሰሁበትን ገረመምኩ፣ እቤቴ አልነበርኩ? ጠንቋይ ማረፊያ እንዴት ደረስኩ? አዲስ አበባ በሦስቱም አቅጣጫ ምንጭሯን ጥላለች:: የከፋት ነገር ያለ ይመስላል:: የአፈትጉሃንን የድምፅ ቅላፄ ስሰማ ረድ ሠርዌን ያጣቅስልኛል:: የምፅፈው የህይወት ገጠመኜን ባይሆንና ልቦለድ የምደርስ ቢሆን ኖሮ ረድ ሠርዌንና አፈትጉሃን ዮናኤልን እንደ መጽሐፍ ውስጥ አንድ ላይ ማካተት ብክነት እና ማደናገር ይሆን ነበር:: ህይወት ግን አትመርጥም:: እንደውም ተመሳሳይነት ያላቸውን ሰዎች በተመሳሳይ ቦታ በማካተት ትታወቃለች::

አፈትጉሃን አጠገቤ ያለ ደንጋይ ላይ ተቀመጠ ባለፈው ያዋስኩትን መጽሐፍ ይዟል:: ገፁን በአውራጣቱ እያበጠረ ወደ አዲስ አበባ ገፅታ ቁልቁል አተኮረ::

"እንዳንዴ ምንጣፍ ይዞ መጥቶ እዚህ ማደር አ-ቤ-ት አቡነ ዘርአብሩክ!:: ዘልአለም እንዲህ ቁልቁል መመልከት የአምላክነት መታበይ ውስጥ ይከታል:: ሊቀ መላእክት ሆኖ ቁልቁል እንዲህ ሲመለከት ሳይሆን አይቀርም እኔ ፈጣሪያችሁ ነኝ ያለው - ያ አህያ!"

የመጽሐፉ ርዕስ በጉልህ ታየኝ "The Last temptation of Christ" ይላል:: Kazantzakis ደራሲው ነው::

"መጽሐፉ እንዴት ነው?"

"ሸጋ ነው"

"ስለደራሲው በጣም የተሰማኝን አንድ ነገር ላጫውትህ?"

"ሸጋ"

አዲስ አበባን በአንድ እይታ ውስጥ ጠቅልዬ ለመጉረስ እየጣርኩ፡

"Kazantzakis [illegible] አልጋ ላይ በፅኑ ህመም ተይዞ ነው አሉ:: እግዚአብሔር ፊቱ የቆመ ያህል አይኑን እያንከራተተ ይለምን

@OLDBOOKSPDF

ነበር። 'አስር አመት ብቻ! አስር ዓመት ስጠኝና ውስጡ ያለውን ከሁሉ የላቀ መጽሐፍ ልገላገል። አስር ዓመት' እያለ ይመፀን ነበር።"

"እና የጠየቀውን ሰጠው?"

"ልነግርህ አይደል፣ ሚስቱ ሔለን ካዛንትኪስ በጥሩ አገላለፅ ገለፀችው። ባለቤቷ ውስጡ ካከማቸው ዕውቀት ውጭ ከታሰበ አጥንት በጆንያ ተሞልቶ ብቻ ነው። መልአከ ሞት ደግሞ ያንን ጆንያ መረከብ አልፈለገም። ሲሰራ ካሰበው ሥራ ጋር ወሰደው።"

"ያሳዝናል"

"እኛ እንጂ የምናሳዝነው" ተበሳጨሁ እንዴ? "እስኪ የፃፋቸውን መጻሕፍት አስባቸው? Zobra the Greek? Freedom or Death? Report to Greco?... ከእነዚህ ሁሉ የሚበልጥ መጽሐፍ ውስጡ አለ እያለ ነበር'ኮ። እሱ በፃፋቸው ምን ተጠቅሞ ነው ባልፃፋቸው የሚጎዳው? ተፈጥሮ በመክሊታቸው ያተረፉና መክሊቶቻቸውን የቀበሩ እያለች የተለያየ የሞት ክፍሎች የምታዘጋጅ ይመስልሃል? የሰው ልጅ ሥራ ምድር ላይ የሚካተት የምድር ላይ ጣጣ ብቻ ነው። የምድር ሥራ የሚለፍርበት የሰማይ ቤት መዝገብ የለም። አፈራችን በንኖ እንዳልሆንን የምንሆን ቁራሽ የትቢያ ጥቢኛ ነን።"

ዘወር ብሎ አየኝ። ግራ መጋባት ፊቱ ላይ ይነበባል። የራሱን ችግር እግር ተወርች አስሮ የሚይዝ አይነት ሰው ስለሆነ አብሮት ያለ ድንገት ሆድ ሲብሰው እና ሲገነፍል ይደናገጣል። አይታዬን መቋቋም ተስኖት ወደዚያ ትልቅ ጫማው ዓይኖቹን መለሰ።

"የሰው ልጅ ክፋት መጠን እንደሌለው የምትረዳው እግዚአብሔርን እንዴት አድርጎ እንደፈጠረው ስታስብ ነው። ሰማይ መቀመጫው፣ ምድር መረገጫው፤ ከዛስ? ኢምንት ጉዳዮችን ለማንም ሳይተው ኩሳሊት እና ልብ የሚመረምር። ግዙፍ እንደጠፈር፣ ረቂቅ እንደ ጨረር... የት እንሂድ?"

አፌትጉሃን ለቅሶ ደራሽ መሠለ። ወደጎን የተንጣለለች አዲስ አበባን እንደ አስከሬን ዘርግተን የፍትሃት ለዛ ባለው ፅሞና ተሞላን። ቀልዱን፣ ሳቁን፣ ለዛውን... መንጠቁ እንዳች ፀፀት ልቤ ላይ ተከለ።

"ኤሪክ ፍሮም ይመስለኛል፣ ጀርመናዊው የሥነ ልቡና ምሁር።" እለና ጥቂት አዘቅዝቃ ቆየ፤ ሀዘኔን ሳላጋባበት አልቀረሁም፤ "In the @OLDBOOKSPDF

nineteenth... እ... Century the problem is... እ... ኖ... the problem was that God is dead ይልና... In the twentieth century the problem is that man is dead." አየህ አሁን እንዳልከው ነው:: የፈጠረህ ለመኖር የሚያስችልህን አሟልቶ ከሆነ፣ ፈጣሪው ቢሞት ተፈጣሪ ላይ ምንም የሚደርስ ሳንካ የለም:: ነገር ግን ተፈጣሪ ቢሞት ወዲያውኑ የፈጣሪ ህልውና ይናጋል:: እግዚአብሔር የተፈጠረበት ምክንያት ነበረው:: ግን በሰዎች ቢፈጠር እንኳ የሰዎች መኖራችን ምክንያት አልባ ይሆንና የእግዚአብሔር ሞት ስናውጅ ሙሉ በሙሉ በጠላትነት እንዘራለን:: አሁን አንተ በነገርከኝ ላይ ወደራሳችን ተመስርቼ ላስብ የመጣልኝ ነው:: ፍሬደሪክ ኒቼ 'እግዚአብሔር ሞቷል' ብሎ ሲያውጅ ከ Existentialism አንፃር ሌላ ፍቺ ይኖረው ይሆናል፤ የኔ ጉዳይ አይደለም::"

ሞቶ ያልሞተ የጠንቋይ ማረፊያ ዝግባ የራሱ መቃብር ሆኖ ለዘልአለም በሚመስል መንገድ ተገትሯል:: መናፍስቱ እስሩ ያሽበሽቡ ይሆን? ከእግዚአብሔር የተሻለ በአወሊያዎቹ ህልውና ለምን እርግጠኝነት ይሰማኛል? ልጅ ሆኜ እናቴ ይዛኝ በመሄዷና በመዘየሯ? እናቴ አሁንም እዚያው ጠንቋዮቹ ሥር ስላለች? ወይስ?...

"ዛሬ ወፍጮ ቤት ሄጄ ነበር" አለኝ:: ድምፁ ከአጭር ቁመት ከጠባብ ደረት የወጣ አይመስልም::

"ለህይወት ታሪክ ነው?" ሆን ብዬ ከከተትኩት ሀዘን የተላቀቀ አይመስልም:: አየት አድርጎኝ

"ረድ ሠርዌን አይቼዋለሁ:: ሳናወራ ተግባብተናል:: እንደሱ በጥልቀት ባይሆንም የአባቶችን አስተምህሮ በጥቂቱ አውቀዋለሁ:: አካላቸውን ለመንፈሳቸው ለማስገዛት ሥጋቸውን እንደ አባያ በሬ ይቀጠቅጡታል:: በፆምና በፀሎት ብቻ ሳይሆን ክብር በመንሳት ጭምር ሥጋቸውን ያበሳቁሉታል::"

ዘወር ብዬ አየሁት

"እም፣ ሥጋ የሚፈልገው እህል ውኃ ብቻ አይደለም:: እንክ-እንክ መባልን የሥጋ ህይወት ከእህል ውኃ በላይ ይፈልገዋል::እፁብ፣ እፁብ መባል የኃጢያት ሁሉ ምንጭ ነው:: ስለዚህ ፃድቃን አባቶች ማኅበራዊ ሥፍራቸውን ለመግሰስ ብዙ የውርደት ነገር ይሰራሉ:: የነሆለሉ፣ ያበዱ [illegible] አራቂታቸውን አደባባይ ይወጣሉ::"

@OLDBOOKSPDF

በረጅም መጫሚያው አፈር እየማሰ ጥቂት ቆይቶ ቀጠለ

"አባቶች የሚያዋርዷቸው ሰው ካገኙ እንደ ዕድት ይቆጥሩታል:: መጀመሪያ ሲያዋርዷቸው መጥፎ ስሜት እንዳይሰማቸው ማድረግ ነው:: ሁለተኛ ደረጃ ክፍ ሲሉ ደግሞ፣ አዋራጁ ላይ የጠላት ስሜት እንዳይኖራቸው ማድረግ ነው:: ሦስተኛው ለአዋራጁ ማዘንና መፀለይ:: አራቱ ተገኝቼ አለናከልኩት ስለዚህ ይቅር በለው እያሉ እንባን ማፍሰስ::"

"ይሄማ" አልኩ ለመትከንከን እየከጀለኝ "ይሄማ የሥነ ልቡና ጣጣ ነው:: Masochism እራስን ለስቃይ አሳልፎ መስጠት..."

"ይሆናል፣ ይህን የምትለው አንተ እንዲሁም መሰሎችህ ናቸው:: ለእናንተ ልዩ የማሰቢያና የማሰላሰያ ቦታ መተው ተገቢነት አለው:: ግን እንዳንተ ለማያስቡትስ?..." ፈገግ አለና አካላቱን የማይመጥን መጫሚያ ለማየት ጭንቅላቱን ደፋ:: በአውራጣቱ የሚያበጥረው የመጽሐፉ ገፆች እንደ ድንቢጥ ክንፍ አየር ሲቀዝፉ ይሰማል::

"አንድ ጊዜ ቮልቴር 'እግዚአብሔር አለ?' ተብሎ ተጠየቀ:: ወደጠያቂው ጆሮ ጠጋ ብሎ 'የለም' ሲል መለሰ:: 'ግን ይሄንን አገልጋዬ እንዳትሰማ' ትናንሽ ቦታ ያሉ ትናንሽ ሰዎች የፈጣሪን አለመኖር ለራሳቸው ሲያውጁ ገሃነምን በመፍራት የታቀቡበትን መጥፎ ነገር ሁሉ ማድረግ ይጀምራሉ:: እንደ ቮልቴር የእግዚአብሔርን አለመኖር በማውጠንጠን ብቻ አካክሰው አይመለሱም:: ማህበራዊ ቀውስ! ምናልባትም የሰው ልጅ በምድር ላይ መኖር ያበቃ ይሆናል::"

ዝም፣ ፀጥ፤ የዛፍ ሽውሽውታ እና ሽታ ብቻ አካባቢው ላይ ናኙ:: በዛፎች መካከል አንዳንድ ነጠላ ያጣፉ ሴቶችና ጋቢ የደረቡ ወንዶች አቀበቱን ለማቆራረጥ እኛ ወዳለንበት መምጣት ጀመሩ:: ዛሬ የተክልዬ የንግሥ ዋዜማ መሆኑ ነው:: ቤተክርስቲያን ሲያስቀድሱ ለማደር እንጋሽቱን እያስቆመ እግዚአብሔር የለም ወደየቤታችሁ ተመለሱ ቢባል?...

"በወፍጮ ቤቱ ባለቤት ምሳሌ ልስጥህ፣ዛሬ ወፍጮ ቤቱ በር ላይ አግኝቶኝ ስላንተ አነሳብኝ:: አቤትህ መጥቼ እንዳጣሁህ ነገርኩት::

"የት ሄደ? ሲል ጠየቀኝ

@OLDBOOKSPDF

"ሕሱ መች ቤቱ ያድራል? ውሎና አዳሩ ጠንቋይ ቤት ነው" ደነገጠ! ወፍጮ ቤት ገባ፣ ተመልሶ ወጣ:: 'እንዲህ አይነት ሰው አይመስልም' አለ::

"አዎ፣ ብቻ እንዲታወቅበት አይፈልግም::እኛ ሁሉ ተስማምጠን ነው፣ ከሱ ጋር ፀብ የሚገጥም የለም::' አልኩት:: በኋላ 'ደሞዙን መጥቶ እንዲወስድ ንገረው' አለኝ:: ለዚህ ሰው የእግዚአብሔርንና የእርኩስ መንፈስ አለመኖር ሲታወጅ አሰበው..."

ዝም፣ ፀጥ...

"ለአንዳንድ ነገር ይሆንሃል...::

"አልፈልግም፣ በፊትም እሄድ የነበረው በሠርዌ ግፊት ነበር:: የረድ ሠርዌን ሥም ማንሳት አፌን ይከብደው ጀምሯል:: እራሱን ሳይሆን እኔን ያዋረደኝ ሆኖ እየተሰማኝ ይሆን?

የሚያበጥረውን መጽሐፍ አቀበለኝና ሳር መቀነጣጠብ ጀመረ:: የምዕመኑ ቁጥር እየጨመረ ስለመጣ ቦታው ጭርታውን እየተነፈገ ሄደ::

"እንሂድ" አልኩ እየተነሳሁ:: ቁመቱ ከክንዴ በመጠኑ ከፍ ይላል:: ምድርን በተረከዙ እየወጋ፣ በመዳፉ እየፀፋ ይጓዛል:: አንዴ ሲራመድ ምድር ሁለቴ ትጮሃለች:: ፀጉሩ ጎንባሳ ነው:: ለአፍሮ የፀጉር አቆራረጥ የሚመች አይመስልም::

ተዳፋቱን ጨርሰን ብቅ እንቅ ስንደርስ ሥሜ ሲጠራ ሰማሁ::

"ታለ? ታለ? ታለ?..."

ቆም ብዬ አፈትጉሃን ዮናኤልን አየሁት:: እሱም ሰምቷል፤ ትገርት መሰል ህይወት እንጂ እንደጠረጠርኩት ህልም አይደለም:: ለተክልዬ ንግሥ ገና በዋዜማው ወደተሰደሩት የኔብጤዎች መሰስብዬ አየሁ:: እጅ አልተውለበለበልኝም:: ድፍርስ ጎርፍ እንደተከናነበ ድንጋይ እድፍ ያሰመጣቸው የኔቢጤዎች ተሰድረዋል:: እዚያ መካከል ልጅ ያዘለች እንዲት የሚጨች ሴት አድፍጣ አየሁ:: ቀጥታ ወደሷ ሳመራ የየኔቢጤዎቹ ተማፅኖ ጨመረ::

@OLDBOOKSPDF

"ሊሊ?" ብድግ አለች፣ ቁጭ አለች:: "ነይ" አደፈጠች "ሊሊ? ነይ" ተነሣች:: ሁለት ጭንቅላት ክንብንብ ደባልቆት መንታ የግመል ሻኛ መስሏል::

"ነይ"

"ቦታዬስ?" የተነፈሰ ድምፅ፣ ቃለ እያለች ስትጣራ የነበረው ንቃት የለም::

"ትመለሳለች፣ ጠብቂላት"

"የት ትወስዳት?" የትም ቦታ የለብአዊ መብት ጥበቃ አለ::

"ትመጣለች" እጇን ከተሸሸገበት ጋቢ ውስጥ ፈልፍዬ ያዝኩት:: እስካሁን ቀና ብላ አላየችኝም:: አፈር-አፈር ትሸታለች::

ዩናኤል በትንግርት ያየኛል:: እያጣደፍኩ ቁልቁለቱን ሳንደረድራት መሞትና መኖሩ የማይለይ ወንድሟ ጭንቅላቱን ከጭንቅላቷ ሳያጋጭ አይቀርም:: ዮናኤል እርምጃውን ከኛ ጋር እያመጣጠነ ይከተለናል::

"ለምን? ለምን? ልመና ጀመርሽ?" ዝም አለች:: ምን እንድትለኝ ፈልጌ ነው? ህይወቴን ሐዘን ታክቷታል:: ኑሮዬን የሞላው የሰው ልጅ ውድቀት ነው:: ብዙ የውድቀት ታሪኮች የእባጭ ክሬብታ ሠርተው የነፍሴን ጫንቃ ተጭነውታል:: ሊሊ ከዚህ ውጭ ሌላ አማራጭ ነበራት? እስካሁን መልኳን አላየሁትም:: የአሁን ቅርጿን ካለፈው ሁኔታዋ ጋር እያያያዝኩ ነዳይዋ እሷ መሆኗን አመንኩ::

ተረክ ጀመረች፤ በሚንዘለዘለጥ ድምፅ::

"በወር ሦስቴ እለምናለሁ:: ልደትዬን፣ ከዛ ኪዳዬን፣ ቀጥሎ ትክልዬን:: እናቴ ስለምን የሰፈር ሰው እንዳያየኝ እዚህ አመጣችኝ::"

ይቺ ፅዋ ከእኔ ትለፍ፤ አልኩ:: ዝርዝር አሟልታ በወረቀት ግራ የገባው ደብዳቤ ጠቅልላ ያኖረችልኝን መልዕክት:: በቀለም የነጠበ ሸንተረር፣ ጅረት፣ ጉድባ፣ሰርጥ... አሁን የምትነግረኝን እያሰበች የሄፈችልኝ የልብ ስሜት::

ይቺ ፅዋ ከእኔ ትለፍ::

@OLDBOOKSPDF

የለም ያልኩት አምላክ ለጊዜው ተከስቶ መፍትሄውን በልቤ እንዲያኖር ተማፀንኩ። አለቀስኩ? እንጃ!

"ወደ ሠባራ ባቡር ስመለስ የምለብሰውን ለውጬ እንዴት እንደሚያምርብኝ። ቦብሊን ገበር ያለው ኪሮሽ ቅድ፣ አበባ ያለው ቀሚስ፤ አንድ ቀን እንደሱ ለብሼ አንተ ጋ እመጣለሁ።" የሚንዘጠዘጥ ድምፅ።

መፍትሔው ተገኘ። ልደትዬ፣ ነፀብራቅ ያኖረችልኝ ብር አኩፋዳ ውስጥ...

...መለስ ብዬ አፈትጉሃንን አየሁት። ቃል አልተነፈሰም እንጂ ቢያወራ የእሱም ድምፅ እንደ ሊሊ ሳይንዘጠዘጥ አይቀርም።

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፲፪

በረሃቡ ዘመን እጤ ምኒልክ ፊት አንዲት ጭርንቁስ ሴት ቀረበች::

"ምን አደረገች?" ሲሉ ጃንሆይ ጠየቁ:: ከሳሾች አቤቱታቸውን አሰሙ::

"የእራሷን አስቀምጣ የእኛን ሰባት ልጆች በላች"

እጤው ሴትዮዋን ሲመለከቷት እንኳን ሰባት ልጆች ምናምኒት የቀመሰች አትመስልም::

"ህዝቡ እንዴት ተበድሏል?" አሉ እጤው:: "ለእኔ ስትሉ ማሩልኝ"

ሰው መሆናችን፤ ተፈጥሯችን ነው የተበደለው:: እግዚአብሔር ከመፍጠር እሽክርክሪት እራሱን ለመገላገል ሲል መብላትና ፍትወትን በአፈጣጠራችን ላይ አተመ:: ዕዳውን እኛ ላይ ጣለ:: ምድርን እራሷን በራሷ እዙሪት ውስጥ በመክተቱ ከዕለት ዕለት፤ ብርሃንና ጨለማን ከማፈራረቅ እሽክርክሪት እራሱን ነፃ አወጣ:: መለኮታዊ የውኃ ክፍል ሆኖ በውኃ እጦት ተፈጥሮ ከምታቀርብበት ሮሮ አሁንም እራሱን ነፃ አወጣ:: የአውቶማቲክ ዓለም ፈጣሪ ከተፈጣሪው ጋር ሊኖር አይችልም:: እራሳችንን ለራሳችን ለመተው ሲል ብዙ ተጠቧል፤ ከዚያ በኋላ መከዳ ላይ ተቀምጦ እኛን የሚቆጣጠርበት ምንም ፍላጎት ሊኖረው አይችልም::

"ህዝቤ እንዴት ተበድሏል? ለእኔ ስትል ማርልኝ" የሚባል ከሳሽ ማጣት የሰው ልጅን ዕጣ ፈንታ ያከፋዋል::

ናትራ ገባች:: ጀበናና ማቶት ይዛለች:: አስቀምጣ ወጣች:: የኒጋ አልመሰለኝም ነበር:: ማን ቡና እፍይ አላት? ዳግም መጥታ ስኒ ከነረከቡቱ አኖረች:: @OLDBOOKSPDF [illegible] ቀርቶ አታየኝም፤ ወጣች:: ስኒዎቹን

መቁጠር ጀመርኩ። ድርድሩ አደናጋሪ ነው። ወደላይ አፋቸውን የከፈቱ ስኒዎች። እፍ አከፋፈታቸው ለቁጥር ያደናግራል።

ናትራ ማንደጃ ይዛ መጣች። ፍሙ ፊቷን ስለገላመጠው ወደኋላ ለጠጥ ብላ! እጇን አስረዝማ አኖረችው።

"ምንድነው ጉዱ?" ነፀብራቅ መጥታ ካደረች በኋላ ናትራ የድሮዋን አይደለችም።

"ያኛው፤ የቆሎ መምህሩ..."

"ሠርዌ?"

"አ-ይ ያኛው የቆሎ መምህር፤ እሱ ቡና ጣጂና ጠብቂኝ ብሎ ብር ሰጥቶኝ ሄደ። ትንሽ ጫት ገዝቶ አስቀምጧል።"

ያኛው የቆሎ መምህር አፈትጉሃን ዮናኤል መሆን አለበት። ዶክተር አሮን መስሎኝ ነበር። እንኳን ምሣ፤ ቁርስ ሳይበላ ቡናና ጫት ምን አስፈለገው? ብረት ምጣድ አምጥታ የማንደጃው እሳት ላይ ጣደች። ውኃ ጨምራ ቡናውን እዚያው ላይ አጠበች።

እንደስኒዎቹ አንጋጥጬ አፌን ወደ ላይ የከፈትኩ ሆኖ ተሰማኝ። ሁሉም ነገር ከላይ ይወርዳል። እኔ እንደሚጨነቅ በመዋጥ ብቻ እተባበራለሁ። እውነት ምንድነኝ? ይሄንን ህይወት ያልፈለኩት ነው ብዬ ማማረር እችላለሁ? ምህረት መጠየቅ ያለብኝ ከራሴ ለራሴ ነው።

ቤቱ ተሟሟቀ። ቡናው ተጫጫሰ። ናትራ ቡናውን በር ላይ ስትወቅጥ ሰዎች መጡ። የቀደመው አፈትጉሃን ነበር፤ ያስወትሮ በር ላይ ጫማውን አውልቆ እንደገባ ጠቀሰኝ። የተከተሉትን ስመለከት ለምን እንደጠቀሰኝ ገባኝ። የወፍጮ ቤቱ ባለቤት የጭን ገረዱን አስከትሎ ጫማውን አውልቆ ገባ። ባልዞርሽ በካኪ ወረቀት የተጠቀለለ ነገር ይዛለች። ፊቷን ሲያዩት፤ ያውም ከድንጋጤ ጋር ፈገግ ብላ። አህያ ስለመሰለች ይሆን የወፍጮ ቤቱ ባለቤት የወደዳት? ጥቅልሉን ለእኔ ልትሰጥ ስትል አፈትጉሃን ከግሳፂ ጋር ተቀብሎ ለናትራ ሰጣት።

የሆነ ነገር የገባኝ መሰለኝ።

"አባቴ ይቅር በለኝ፤ ሳላውቅ ተጋጨሁህ" አለ ሆዱን ማሻሸት ልምዱ አልነበር? "እጣንህን ቡናህንና ስንደልህን አግብቻለሁ። ጃንጥላህን ደሞ አገባለሁ።" የእናቴ ልጅ ነኝ ገባኝ። ዝም አልኩ።

@OLDBOOKSPDF

የተጠቀለለ ብር አውጥቶ ሊሰጠኝ ሲል አሁንም አፈትጉሃን ተቀብሎ ወደ ናትራ አሸጋገረ::

"አባቴ አትቆጣ፣ አባቴ አትቆጣ" እያለ ወጥቶ ከመኪና ውስጥ መሆን አሰበት:: ቀንበጡ የሚያምር እትፍ ጫት ይዞ መጣ::

"መርቀኝ አባቴ"

ባልዞርሽ ፊት ለፊቴ ተቀምጣ ጥርሷን ገሽልጣለች፤ መሳቅ ሳይሆን መደንገጥ:: የምለው ሲጠፋኝ::

"ፈረሱ ይስገር እንጂ፣ ያለሰዓት ነው የመጣነው" አለ አፈትጉሃን ዮናኤል:: የመገፋፋት ያህል እያቻኮለ ይሂቸው ባይወጣ ኖሮ ያስመለሰኝ የያኔው ስሜት መጥቶብኝ ነበር:: "የሊሎቹንም ደሞዝ ሥጥ" ሳልለው መሄዱ ቆይቶ ቆጨኝ:: ባልዞርሽን ከበስተጓላዋ መመልከት ልብን ደስ ያሰኛል:: እሷን ትተኃት ሄድ ባልኩትኖር፤ እንደአህያ አዚያ ጥግ አስሬ አሳድራት ነበር:: ልስቅ?

"ሺጋ አላደረኩም"?" አለ ዮናኤል ሲመለስ:: "እንግዲህ ካለልን ወፍጮ ቤቱ ገብያው ይደራና እኛም የዘላለም ተጠዋሪው እንሆናለን፤ የታባቱ!"

"ጫማ ሳታወልቅ?" አልኩ ክንድ ተኩል የእግሩን መዳፍ እያስታወስኩ::

"አይዞህ አምልኮ የሚጀመረው እንዲህ ነው:: ቀስ በቀስ እየበዛን፣ እየተባዘን እንሄድልሃለን::"

ምንጩ ያልገባኝ ፍርሃት ነካኝ::

"የዛች ልዥ አምላክ ነው"

"የቷ?" በሚል አየሁት

"ንግድ የምትዠምረው"

ሲሊን ነው::
"በእጣኑ፣ በቡናውና በሰንደሉ ንግዷን ገድ ትላለች:: ወፍጮ ቤቱ ገበያው ደርቶ ያለላት እንደሆን ሐሙስ፣ ሐሙስ እየመጣች ድርጎውን መውሰድ ነው::"

@OLDBOOKSPDF

ፈገግ አልኩ፡፡ የተንኮል እንደሆነ ገብቶታል፡፡

"ምነ?" አንዳንዴ ሆነ ብሎ የሚያመጣው የገጠር የአነጋገር ዘዬ አለው፡፡

"ላንተ ደሞ የያዘልህ እንደሆን ባልዞርሽን.."

"አንተ እውነተኛው ባለአውሊያ ነህና!"

ተሳሳቅን፡፡ ናትራ ምሳ ለማዘጋጀት ተፍተፍ ማለት ጀመረች፡፡ ሹቲዋን ለውስጥ ሱሪዋ አጉርሳ የሴትነት ቅርጿን አጋኖታል፡፡ ቀኝ እግሯ ብቻ ባጠረው ሹቲ ተጋልጦ ያለ ተቀናቃኝ ውበቱን ይምነሽነሽበታል፡፡ ከቤት ወጣ ስትል ልብ ዋልሎ መምጫያ ጊዜዋን ይዋጃል... ስትመጣ...

"ሰው ይፈልግሃል" አለችኝ ናትራ ሰገግ ብላ፡፡

"ማነው?"

"ኧረ ጉድ ነው፣ አሁን ምን የሚያስኩራ ነገር አለው?"

"ማንን ነው የምትይው?" አፈትጉሃን ቀና ብሎ አያት፡፡

"ያኛው የቆሎ መምህሩ፣ ግባ ብለው እሳቸውን ጥሪያቸው አልገባም አለ"

ረድ ሠርዌ... ረድ ሠርዌ... እሱም ተቀይሟል? በምን? ግን እኮ መቀየም የሚገባው እሱ ነበር፡፡ እንደ ዮሴፍ ለባርነት ተላልፎ ሲሰጥ ዝም ብዬ ወደቤቴ ገባሁ...

...ስወጣ ደነገጥኩ፡፡ የረድ ሠርዌን አምሳል፣ በአለባበስ ዘምና ማደ የግቢው ጉብታ ላይ ቆሟል፡፡ ከበስተጓላው ቁመተ መሳላው፣ ጭንቅላተ ሞላላው፣ አንገተ ሰላላው አንድ አይኑ የተከላሸው፣ ሌላኛው የተቅላላው ደጀን መስሎ ተገትሯል፡፡

"እንደምን አሉ መምህር" አለኝ የረድ ሠርዌ አምሳያ፡፡ መንፈሳዊ ቅኝ ሊገዛን ለመጣ የዉኤሰማ ኮሎኒ በባንዳነት የሚያገለግል መስሎ ታየኝ፡፡

@OLDBOOKSPDF

"ሠላም" ለእርስም ይሁን" ትንቢት የተነገረለት፣ የስንትና ስንት ዘመን ጥበቃ ወደ ዕድሜ ድካምነት ያለወጠው ሰይጣን "እንቱ" ሊለኝ?

ላለፈውም፣ ላለውም፣ ለመጪውም ትውልድ በምስክርነት ታጨሁ። ከዚህ ማፈግፈግ የታሪክ ተወቃሽነት አያስከትል ይሆን?

"ምን ነበር?" አልኩ እንዳላወቀ።

"እንደው መምጣታችንን እንዲያውቁት ነው። ተገናኝተናል።" አለ በአንድ አይኑ እያየኝ። በቀይ ዓይን ስታይ የከሰል ፍም እመስል ይሆን?

"አልገባኝም"

"እዚያ ወዲያ፣ ከመንገዱ ባሻገር አምሳያ ወንድምዎ ቆሟል። ይዩት፣ ውኃ ሰማያዊ ሸሚዝ ለብሷል። ፎቶው እንደደረስዎ ሰምተናል" በእርግጥ እንዳለው ሰው ቆሞ ይታየኛል። መልኩን አልለየሁትም እንደረድ ሠርዌ ተመሳስሎው የሚያደናግር...

"ታዲያ?..."

"ከፈቀዱልን ሌላ ጊዜ ብንጫወት፤ ሰው ሁሉ ዕጣ-ፈንታውን ነው መኖር ያለበት።" ቀድሞ ሞላላ እራሱን ታቦት እንደተሸከመ ሁሉ ቀስ ብሎ ወደኋላ አዞረው፣ የረድ ሠርዌ አምሳል ተከተለው፤ የእኔ አምሳል መንቀሳቀሳቸውን ሲመለከት የጀርመን፣ ሲጋሲዮንን አቅጣጫ ይዞ መጓዝ ጀመረ።

ምንድነው? ቢያወሩት "እብድ" የሚያሰኝ እንግዳ ህይወት እየኖርኩ እንደሆነ ተሰማኝ። ሐሰተኛው መሲህ ድንገት ጎንበስ ሲል አየሁት። እግሬን አንጠራርቼ ስመለከት የጃኬን ሽብሽብ፣ ማጅራት በእጫጭር ጣቶቹ እያሻሸ እንደሆነ አየሁ። የተገፉ፣ የተጣሉ፣ ዘመን የከዳቸውን ማስታወስ የቅዱስ እንጂ የእርኩስ ተግባር አይመስለኝም ነበር። እንደሸመል ቀጥ ብሎ የቀጠነ ገላውን ዘረጋግቶ ሽቅብ ሲሄድ ሞላላ እራሱ ብቻ ገዝፎ ዓይን ይጠልፋል።

አርስቶትል እንደሚለው በሰው ልጅ ልምድ ላይ ያልተመረኮዘ እራሱን በራሱ መንገድ የሚገልፅ "እውነት" ተፈጥሮ ውስጥ ተሸሽጎ አለ፤ ያንን እውነት ከተፈጥሮው የምንረዳው ከተፈጥሮው ውጭ በእኛ ልምድ ላይ የተመረኮዘ ባህርይ ውስጥ መገኘት ሲችል ነው። እና

@OLDBOOKSPDF

ሞላላው ተሟሎ አዚች ምድር ላይ የሚንከላወሰው በእኛ ልምድ ላይ የተመረኮዘ ግንዛቤ ሊፈጥርልን ስለሚሻ ይሆን?

"ታሰ ምነው?" ናትራ፣ ይሄንን ስም የት አገኘችው?

"ምንም" በእግሬ ቆንጥጬ የያዝኩትን ምድር አላልቼ ወደ ውስጥ ዘለቅሁ:: ቤቱ ሴት የተንጎዳጎደበት ጠረን ይዟል "ምነው?" አፈትጉሃን መጽሐፍ መደርደሪያው ሥር ተከማትሮ ተቀምጧል:: በተረከዙ የቆመው መጫሚያው ሳይበልጠውም አልቀረ:: እሱ ላይ ለመፈተሽ ፈለግሁ::

"አሁን ያስጠራኝ ማን እንደሆን አውቀሃል?" ስል ጠየኩት ጉዝጓዜ ላይ እየተቀመጥኩ:: የምላ ሽታ! ከቡና መንተክተክ ጋር! አባወራ ብቻ የሚያውቀው ጠረን::

"ሠርዌ አይደለም እንዴ?"

"አይደለም"

"ታዲያ"

"መንትያ ወንድሙ"

ግራ በመጋባት አየኝ

"አብሮት ማን እንዳለ ታውቃለህ?"

"ማን?" ናትራ እስክትወጣ ጠብቁ

"የእኔ መንትያ"

"ምንድነው የምትለው?"

"እ፣ የሚገርመው ደግሞ ከእነሱ ጋር ሐሰተኛው መሲህ አብሯቸው ነበር::"

"በአቡነዘርአብሩክ!" ፊቱ ላይ ሣቅ እንደጭልፈት እያንገበበ "እንዴት ያለ ነው? ለምን እኔን አላገናኘኸኝም?" ወደመጽሐፍ ማገላበጡ ተመለሰ::

@OLDBOOKSPDF

"ቁመቱ መላላ፣ እንገቱ ሰላላ..."

ቀና አለ...

"ጭንቅላቱ ሞላላ፣ አንድ አይኑ የተከላሸች፣ ሌላይቱ የተቅላላች"

ፊቱ ላይ የሚያንገዋብበውን የሣቅ ጭልፊት፣ ከጥልቅ ነፍሱ የወጣ የድንጋይ ዓሣ አየር ላይ ሲውጠው አየሁ።

"እውነትህን ነው?"

"እዎ፣ ምነው?"

"ስለዚህ ሰው አባቴ ዘወትር ይነግሩኝ ነበር። ቁመናው አሁን እንደገለፅከው ነው። ካደኩ በኋላ ስጠይቃቸው መጽሐፍ ገልጠው አስነበቡኝ። አሁን እዚህ ነበር እያልከኝ ነው?" ከቅምጡ ቀልጠፍ ብሎ ተነሳ፤

"እዎ" ፍርሃቱ እኔም ጋ ተጋባ።

"እዚህ ምን ፍለጋ መጣ?..." ወደ አልጋው አምርቶ ተቀመጠ። "በእርግጥም የዓለም ፍፃሜ፣ የፍርድ ቀን ደርሷል ማለት ነው? ግን እውነትህን ነው አልአዛር? ወይ ጉድ! ለምን የእኛን አካባቢ መረጠ? እኛም እግዚአብሔር የለም በሚል ማጣቀሻ መስጠት አብዝተን ነበር። ወዳጅ አገኘሁ መስሎት ይሆን?"

ዝም!

"ወይ ጉድ..."

ዝም!

"ወይ ጉድ... ለመሆኑ አንተ ወንድም ነበረህ እንዴ?"

"እኔ አላውቅም" ከአፈትጉሣን በላይ ሆዴ እየነዘነዘኝ ነው። "ግን..."

"ግን ምን?"

"አንዲት ሴት እናትህ እኔ ነኝ ማለት ጀምራ..."

@OLDBOOKSPDF

"ካደከ?"

"ካደኩ"

"እሺ"

"አንድ ሰሞን ትረብሸኝ ነበር:: በኋላ በአደጋ ሞታ ቤቷ ሲፈተሽ ከእሷ ጋር የተነሳሁት ፎቶ ተገኘ::"

"ምን እያልክ ነው?"

"እውነቱን ነው:: አብሬአት ፎቶ አልተነሳሁም:: ግን ቁርጥ እኔን ከመሰለ ወጣት ጋር ፎቶ አላት:: በኋላ መንትያዬ መሆኑን ለመቀበል አዳግቶኝ የእሷም እናትነት ልቤ ላይ እንደተንገዋለለ አለ:: ዛሬ አሳዌ መሲሁ ይዞት መጣ:: ለምን? የእኔም ሆነ የረድ ሠርዌ መንትያ ምን ይሰራለታል?"

ናትራ "ጉድ ጉዷን" አጠናቃ ለሁለታችንም ዝርግ ሰሃን አቀበለችን::

አፈትጉሃን ሳህኑ ላይ እንዳተከረ:-

"ለምን ፈልጎን ይሆን?" ሲል ቅዝዝ ባለ መንገድ እራሱን ጠየቀ፣ ክርር ያለ ነገር ውስጥ መግባቱ ትክክል ቢሆንም ማለዘብ ፈለኩ::

"የአንተ ታውቋል፣ የእኛ ነው ግራ የሚያጋባው"

"እኔን ለምን?"

"ለዘኪምስነት መሆኑ ግልጽ ነው::" ስል ሳቅሁ:: እርሱ ግን አልሳቀም::

"አፈትጉሃን ዘኪምስ" ጨመርኩለት:: "የእርሶ ዕዳው ገብስ ነው:: ዛፍ ላይ ወጥቶ ሐሰተኛው መሲህ ሲያልፍ ወደቤትዎ እንደሚጋበዝ ሆኖ መዘጋጀት::"

ዝም! ፀጥ! ጭር! ጭውውው....

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፲፫

የቁጣ ልጆች ነንና ሐሰተኛው መሲህ ወደኛ ቢመጣ አያስገርምም። በእኛ ላይ ማድረግ የሚገባውን ሁሉ በራሳችን ላይ አድርገን ጠብቀነዋል፤ እምነተ-ቢሶች፣ እምላክ-ቢሶች፣ ምግባረ-ቢሶች፣ ወዳጅ-ቢሶች... የካድኳቸው ሁሉ ፊቴ ላይ ተደቀኑ። ልቤ ሳይራራላቸው የሸሸኋቸው። ምናምኒት እንዳላደረጉልኝ ሁሉ ለአፍታ እንኳ ትውስታዬን የማያደናቅፉት...

...ሲፈን፣ እህቶቼ፣ አባቴ፣ እናቴ፣ ለገነት፣ ጡረታ ድልድይ፣ ሰባራ ባቡር፣ ቹቹ እና የቹቹ እናት፣ ጠናጋሻው... ህይወቴ ቁጠ ቀዳዳ ታኒካ ነው፤ የከተቱበትን ሁሉ የሚያፈስ፣ ውለታ እና አደራ የማያውቅ ለእኔ የሴጣን መልእክተኛ ሲያንሰኝ ነው። ቀድሜ ሰይጥኛለሁ። የሚሆነው ሁሉ ለመሆኑ ተመቻችቼ ጠብቄዋለሁ። ድኝ ከሚዘንብበት፣ የእሳት ማዕበል ከሚያጥለቀልቅበት የመናፍስት ፀብ ውስጥ ተሳፍሬ ነፍሴ መቅኖ ብታጣ፣ ለዚህ ሁሉ እኔ ተመቻችቻለሁ። ሥጋዬ የሐንስ ራዕይ ላይ ተጠቅሷል። እፈልገዋለሁ፣ ባይጠቀስ እንኳን ከጠቃሹ ችግር የተዘለሰ ነው።

ኡ! ኡ! ኡ! ኡኡኡ....

የማንነቴ አዘቅት ውጦኝ ሳይጠረቃ እያወቀ አፉን በሰፊው ከፈተ። ሰው የራሱ ማንነት ጭራቅ ይሆንበታል?

ደጃፌ መሰስ ብሎ ተከፈተ፤ እንደእኔ ግራ ተጋብቷል። አንዳንዴ ስቅቅ እያለ ይጮኻል። ጻክ ገብቶ አታሞ ጀርባውን ለእኔ ሰጠ። ከነጋ በኋላም፣ ዝናብ ሳይዘንብም፣ ምናልባትም ድሎት በመፈለግ እየገባ መጋደም ጀምሯል። ያ-ሐሰተኛ ነብይ በአጫጭር ጣቶቹ ጀሮዎቹን ሲዳስስለት ምን ተሰምቶት ይሆን? ከአለም ጅማሬ አንስቶ የኖረ፣ እስከ ፍፃሜዋ ሲያደባ የጠበቀ አጫጭር ጣት ሲዳሰስ ምን ምን ይል ይሆን?

@OLDBOOKSPDF

ጃክ በእኔ ዝም ማለት አልተማመነም መሰል መለስ እያለ በሽብሸቦ ፊቱ ይመለከተኛል። ወይስ የሚነግረኝና ከሐሰተኛው የሰማው ይኖረው ይሆን? …ቤቱን ሮጌ፤ ቀለም ሞላው።

"ጃክ? አላበዛኸውም አንተ ሶላቶ! ጭራሽ?"

ነፀብራቅ ከመጣች በኋላ ብቻዬን ሆኜ ቤት ስትገባ የመጀመሪያ ቀኗ ነው።

"በል፣ እንደ ዘመዶችህ በጦርና በጋሻ ሳናስወጣህ አውቀህ

ው-ል-ቅ!"

ከመናር ብዛት ጣሊያንኛው ጠፍቶት አማርኛ ለምዷል መሰል መሰስ ብሎ ወጣ።

"ቤቱ እኮ ውሻ፣ ውሻ ይሸታል፤ ፀጉሩም ይበናል። ለምን ዝም ትለዋለህ?"

ዝም

"ምን ልጠይቅህ ነበር የመጣሁት? እ-አዎ እ… ቴፕ አለህ?" ከአጭር የሌሊት ልብሷ ውስጥ አንድ ካሴት ክር መዘዘች።

"የለኝም ብዬሽ ነበር" ትዝ ሲለኝ "ደሞዙስ?"

"እኔ'ኮ ደሞዝ የለኝም" የታችኛው ከንፈሯን ጣል አደረገችው የበለጠ ልጅ መሰለች።

"ማለቴ የኔ? ስውየው የሰጠሽ?"

"እ-እዛ ሼልፉ ላይ፣ መጽሐፍ ውስጥ…"

"እስኪ አውጪው… ሄደሽ ቴፕ ግዢ"

"እ" የተወጋች መሰለች። የምክንያቷን ጎን የወጋሁት መሰለኝ። ቴፑን እዚህ ቤት ለመምጣት ሰበብ አድርጋው ይሆን?

"ልትገዛ? ቴፕ? እስማበታለሁ?"

"ላንቺ ነው" @OLDBOOKSPDF

"እ" ሌላ የጎን ውጋት፣ እንደ ንፅህናዋ ቢሆን ከጎኗ ደምና ውኃ ተቀላቅሎ መፍሰስ ነበረበት::

"በስንት? ማለቴ? ልሳምህ?..." ወደእኔና ወደብሩ ተመለከተች:: አንድ ሦስቴ ወደዛ ወደዚህ ስትል የማር ወለላ የመሰለ ጭኗ ውንውን ከሚለው የሌሊት ልብሷ...

...እኔን መርጣ ሳመችኝ:: ጉንጬ ላይ፤ በቀዝቃዛ ከንፈር:: ቀፈፈኝ ከስሜት የተፋታ ከንፈር፣ ለድርጎ፤ ለሸንገላ እንደሆን አውቃለሁ:: ሴተኛ አዳሪ ሞክሬ የማላውቀው ለዚያ ነበር...

ብሩን አውጥታ ሳትቆጥር ግማሹን በእጇ ሠፍራ "ይሄ ይበቃል" አለች::

"ከገዛሽ በኋላ የተረፈውን ትመልሻለሽ" አልኳት::

እንደ ቴፕ የተወታተበ ኬብል ያላት ነፀብራቅ...

ናትራ ብር ብላ ሄደች:: ተመልሳ መጣች ጭንቅላቷን ብቻ ወደ ቤት ከትታ "እዚች ሾላ ገበያ ነው የምገዛው፣ ስመጣ ደሞ እስምሃለሁ!" አለችና ሄደች:: በሌሊት ልብስ ልትሄድ? እሷ ምንም አይመስላትም:: ፈገግ አልኩ::

ወደ እሪያዎቹ እንዲገቡ የተፈቀደላቸው እነዚያ ሁሉ አጋንንቶች እኔ ጭንቅላት ውስጥ ነበሩ:: ናትራ ለጊዜውም ቢሆን የገላገለችኝ ስንት ያውጣ?

እኔ ግን ከናትራ የምፈልገው ምንድነው? እሷ እንደመሰላት በእሷ መሳም? አይደለም ናትራ በቴፕ ፍላጎት በኩል ውስጥ የከተተችው የሰው ልጅ ሁሉ ምኞት ናሙና ነው:: ለእኔ ናትራ የቃበዘችበት የአንድ ሰውን አለመቻል የሚያመላክት አይደለም:: በናሙናነት መቃበዟ ናሙና መቻል መኖሩን ማረጋገጥ ነው የእኔ ግብ::

ሰው በዳቦ ብቻ የማይኖር እንግዳ ፍጡር ነው:: የጥበብ፣ የመመራመርና የእምነት ፍላጎቶቹ በህይወት ለመቆየት የሚያስፈልጉ መሠረታዊ እስከመሆን ደርሰዋል:: ሩሲያዊው ደራሲ ፊዮዶር ዶስተየቭስኪ "...The secret of man's being is not only to live" ያለው ለዚህ ነው:: "but to have something to live for" የሰው ልጅ መኖርን ብቻ በሌጣው አይሻም:: የሚኖርለት የህይወት ፍቺ

@OLDBOOKSPDF

ይፈልጋል፤ እንዲያ ካልሆነ በምድር ላይ ከመቆየት ይልቅ እራሱን በራሱ ቢያጠፋ ይመርጣል ይላል ዶስተየቭስኪ። እውነታን ብቻ አይደለም የምናብ ቅንብርንም እንሻለን። ከልበ ሰፊዎች የተገኘ ምናብ መሠረታዊ ፍላጎታችን እስከመሆን ደርሷል። ሙዚቃ… ድርሰት… ቲአትር… ዳንኪራ… ስብከት… ስዕል… የጥበብ ፍቅር ከራሱ ከሰው ልጅ ክብር እየላቀ የመጣበት ጊዜ ነው።

ፈላስፋው Nietzsche ቁጭ ብሎ ሲያሰቅስ እህቱ ኤልሳቤት ትደርሳለች።

"ምን ሆንክ?"

"ፈረንሳይ ውስጥ የጎዳና ላይ አመፅ ተነስቷል"

"እና?"

"እሳት እየተቀጣጠለ ነው እሱ"

"እና? የምታውቀው ሰው አዚያ አለ? እርግጥ የሰው ልጅ ላይ የሞት አደጋ ሲያጋጥም ባያውቁትም ሀዘን መሰማቱ አይቀርም፤ ግን…"

"መች ለሰው ሆነና፣ ሉቭሩ ውስጥ እሳቱ ከተዳረሰ እነዛ እኔ የምወዳቸው ልዩ ስዕሎች ሁሉ መውደማቸው አይደል?" ሲል ለቅሶውን ቀጠለ። እንዲህ ሲሆን ቆይቷል፤ ወደፊትም እንዲሁ ይሆናል። የሰው ልጅ በገዛ እጁ ሥራ ዋጋው እያነሰ መሄዱ ዘልአለማዊ እውነት ነው።

ምን ያህል እያሰብኩ እንደቆየሁ እንጃ! ናትራ በሮዝ ብርሃን ቤቱን ስትሞላው ተሻምቼ ፊቷ ላይ ሰፈርኩ። የገዛችው ብርማ ቴፐሪከርደር ደረቷ ላይ ተለጥፎ ፊቷ ላይ እብረቅራቂ ብርሃን ሲረጭ አዲስ የተከላች የብር ጣዖት መሰለች። ሠላም ስኪ ማለት አሰኘኝ። ከአጥንት ብል ለሚፈውሰው ሮዝ ብርሃንሽ እሰግዳለሁ፣ ልብ ለሚያራውጠው አፍላነትሽ እንበረከካለሁ… ከምን ለመሸሽ እየሞከርኩ ነው? እራሴን ለመቆጣት ሞከርኩ።

"በሌሊት ልብስ ገበያ ሄድሽ?"

"ምናለበት?"

ዕውነት ምን ችግር ያለበት? ዝም፤

@OLDBOOKSPDF

"ታድዬ፣ አላስችል ብሎኝ መንገድ ላይ የቴፑን ማሸጊያ ገነጣጥዬ እየሁት። ሳምኩት፣ ና ደሞ እንተንም ልሳምህ"

እምቢ ማለት አልቻልኩም። በፀሐይ የተከነበበ ቀዝቃዛ ከንፈሯ ጉንጬ ላይ አፈን ተጠግቶ አረፈብኝ። ቀድሞ የነበረውን የህይወት ትኩስ ደም ሁሉ ከውስጤ የሚመጥ የሞት ቅዝቃዜ።

"የታለ ሶኬቱ?... ይኸው! የታለ ካሴቱ?... ይኸው! የታለ የካሴት መጉረሻ? ...ይኸው! የታለ ድምፅ መጨመሪያው? ...ይኸው!...ታድዬ"

እንደ ኒች ከሰው ሞት በላይ የምታስብለት ሙዚቃ ዓለምን ለመናኘት ተፍጨረጨረ። ቴፑ አንድ አይና ይመስላል። አንድ ትልቅ ድምፅ ማጉያ በስፊው ተበልጥጦ እኔ ላይ አፍጥጧል... ሐሰተኛውን ነብይ አስታወሰኝ...

...መቼም በሐሰተኛው ነብይ ላይ ትንቢት ጠቀስ ፕሮጀክት ሲነደፍ ዝርዝር ጥናቱ ላይ እኔ እና ረድ ሠርዌ ሳንጠቀስ አንቀርም። የት ቦታ እና መቼ ጊዜ ሐሰተኛው እኔ ደጅ ቆሞ እንደሚያስጠራኝ ሁሉ የዘልአለም መዝገቡ ላይ ቀድሞ ሠፍሯል... የሀሳቤን መዘወሪያ አሽከርካሬ ፊቴን ወደአሁን ስመመለስ ታገልኩ።

ናትራ ዘፈኑን በዘፈቀደ ዳንኪራ አጅባለች። ስትሽከረከር የሌሊት ልብሷ ከብብቷ ጀምሮ ይነፋፋና ሮዝ ጃንጥላ ትመስላለች። አይኗን ጨፍና ትሾራለች። ናትራ ሳትሆን ተፈጥሮ ናት የምትፈነጥዘው አልኩ።

ምንም አዲስ ነገር የለም

ከቶ አልከፋም ግዴለም

ጤና ሰጥቶኝ በህይወቴ

መኖርን ብቻ ነው ፍላጎቴ

ከቴፑ ጋር አካሏ በገመድ የተያያዘ ይመስል ዘፈኑ ሲያበቃ ዳንኪራ መሰል መሽከርከሯ ተገታ። የደስታ የመሰለኝ የናትራ መሽከርከር ለካ በለቅሶ የታጀበ ኖሯል። የአይኗ ሽፋሽፍት በእንባ ተጠባብቆ መጥታ እኔ ጉዝጓዝ ላይ ቁጭ አለች።

"የማነው ዘፈኑ?" አልኳት

@OLDBOOKSPDF

"የብዙዬ" እንባዋ እንዳይታይ መሰሰኝ ጭኔ ላይ ፊቷን ደፋች:: ከዘፈኑ እኩል እየዘፈነች እንደሆነ ጭኔ ላይ በሚንቀሳቀስ ከንፈሯ አወኩ::

"በነፍስ በስጋዬ እያለሁ ባለም ላይ

ፈጣሪ አደራውን ሞተህ ባይኔ እንዳላይ"

ዝም! ሀዘን በብር የገዛሁ መሰለኝ:: እንዲህ ስትሆን አይቼ አላውቅማ:: እውነትም ደግሞ የብዙዬ ዘፈኖች ሆድ የሚያባቡ ሆነው አገኘኋቸው:: ግጥሞቹን ሆን ብዬ ተከታተልኳቸው

"አልመለከትም ደስታና ጉዳቴን

እሰውጠዋለሁ ስላንተ ህይወቴን

ፍቅር ስለሆነ የቃኘው መንፈሴን

ካንተ የበለጠ አልወድም እራሴን!"

ናትሪ ድንገት ከጭኔ ላይ ተነስታ በወፍራም እንባ የተጠባበቀ አይኗን ደቀነችብኝ:: አምበሬ ጭቃ ይሆን የምታነባው?

"ተበድያለሁ አይደል?"

"እ" አልኩ:: ይሄ ፊደል ፍቺው ምን ይሆን? አዎ ተበድለሻል? ወይስ...

"ተበድያለሁ፤ ካልፈለገኝ ለምን ደስ የሚል ጊዜ አብሮኝ አሳለፈ:: ዝም ብሎ ህመሜን መፈወስ ይችል አልነበር? አሁንስ ከዚህኛው ህይወት፣ ተሸማቅቄ እቤት የምደበቀው ይሻለኝ ነበር::"

"እ" አልኩ፤ ይሄ ፊደል...

"ብዙዬ መቼም ሴት ናት፤ በፍቅር መበደሏ አይቀርም:: የበደላት ወንድ ከሌላ ሴት ጋር ሆኖ ዘፈኗን ሲሰማ እንዴት ያደርገው ይሆን?"

"እ"

@OLDBOOKSPDF

"መቼም ሁሳም ካገኘ ይገርመኛል፤ እንደዚህ እየወቀሰችው? እንደዚህ እንደምትወደው እየነገረው? እንደዚህ ሞትህን እያሰማኘ እያለችው?..."

"እ" ሌላ ለዳንኪራ የሚመች ዘፈን ጀመረ ናትራ ከጉዝጓዙ ላይ ተመንጭቃ ተነስታ መወዝወዝ ያዘች። ዳንሱ ዳንስ አይደለም። ዝም ብሉ መፈንጠዝ። መስከ ላይ የተለቀቀች ሮዝ ጠቦት መስላ ታየችኝ።

የትኛዋ የተውኳት ሴት በእኔ እንዲህ ሆና ይሆን? ሌላ የወቀሳ ጎረምሳ የልቤን ደጃፍ ቆረቆረ። ሲፈን... ለገነት... ወደፊትስ? ነፁበራት... ናትራ...

...ናትራ፤ ውበቷ ጊዜ የሰጠው አፍላነቷ ነው። ፈጣሪዋ ብዙውን መጠበብ ያሳረፈው እግሯ ላይ ነው። እግር እንዲህ ያምራል? አበባዋን ንቆ ግንዷን ማሳመር በውበት የተገላቢጦሽ አፍቃሪ ላይ መዘባበት አይሆንም?

ሙዚቃው መፈንጠዙን አቁሞ በሌላ ደርባባ ዘፈን ሲተካ ናትራም የተረበሸ መንፈሷን አባብላ እያስተኛች አጠገቤ ተቀመጠች። ዓይኖቿ አብረቅርቀው ሲታዩ ከማሳዘን ይልቅ ደስ ያሰኛሉ። 'እግር ያስተፈስህ ልቡ-ሰብ፣ ዐይን ያስተፈስህ ልበ ሰብ' ለምን አልተባለም? ድሃ ድህነቱን ይረሳ ዘንድ እግር እና ዓይን አቅርቡለት ቢባልስ?

ጭኔ ላይ በግራ ጆሮዋ ጋደም አለች። እኔና ናትራ ወዴት የምንሄድበትን ምን መሣፈሪያ እየጠበቅን ይሆን?

"ዝፋኝ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው?" አለች፤ የድምጿ እርግብግቢት ጭኔ ላይ ይሰማኛል።

"ለምንሽ?"

"እንደብዙዬ ያንን የእኔን ጉድ መግቢያ መውጪያ ማሳጣት ለማረኝ። እጮኛው ፊት፣ ሚስቱ ፊት፣ ልጆቹ ፊት፣ የልጅ ልጆቹ ፊት... እስከ ዕድሜ ፍፃሜው እያሳደድኩ መውቀስ። ለሌሎች የማይነግረውን ቁስል ልቦናው ላይ መትከል።"

እንደ እግዚአብሔር እርግማን ከዘር ወደ ዘር የሚተላለፍ ቁስል መትከል አትፈልግ ይሆን? ፍቅር ግን እንደሚባለው ንፁህ ነው? ተፈቃሪን ይሄን ያህል የጥላቻና የፍቅር ጉራማይሌ ላይ ከጣለ በእርግጥ

@OLDBOOKSPDF

ፍቅር ቅዱስ ነው? ጎልዳፋዋን አስልቶ፣ ሲጋዋን አግርሮ ለጦር ስልፍ ካወጣ በእርግጥ ፍቅር እርኩሰት አይደለም?...

"እ?" አለችኝ

"እ" አልኳት ድዝዝዝ የሚል ነገር ጭኔን እየተሰማኝ

"ተበድያለሁ እኮ፣ አልተበደልኩም?"

"አይመስለኝም"

"እንዴት?"

"ማፍቀር እራሱ ጥቅም ነው። በማፍቀር መናወዝ መቼም የትም ከማይገኝ ስሜት ጋር ያስተዋውቃል። በአንፃሩ ደግሞ ማፍቀር አለመቻል ፀፀት ነው። በሰው ህይወት ውስጥ ጣልቃ ያስገባል። እንዳልሽው ዘፈን ኖረ አልኖረ የዘልአለም ወቀሳ ልቡ ላይ ተተክሏል።"

"አንተ እንደዚህ ነው የምታስበው?"

"አዎ"

"መቼም ወንድነህ፣ በፍቅር ሴት መበደልህ አይቀርም። የበደልካት ሴት ሳትዘፍን እስከ ህይወትህ ፍፃሜ እየተሳደድክ፣ ለሌሎች የማትነግረው ቁስል በልቦናህ ላይ ተተክሎብሃል?"

"አዎ"

"እ?"

"አዎ!"

"እውነትህን ነው?" ተነሳች። የሚያብረቀርቁ አይኖቿ ልቤን ደስ አሰኙት።

"አዎ..."

"ስሟ ማነው?"

"ሲፈን"

@OLDBOOKSPDF

"እና? በደልካት? በፍቅር?"

"እም! ማርገሏን ስትነግረኝ አባረርኳት"

"እ?" አሁን ደሞ ይሄ ፊደል ውጋት ሆነ...

"እም! ዘልአለም እየተፀፀትኩ እኖራለሁ። ደጃፌን ሁልጊዜው የማልዘጋው ለምን ይመስልሃል?"

"እኔጃ!"

"ደጃፍ ከፍቶ መጠበቅ የእሷ ፍቅር ጅማሬ ስለነበር ነው! እጠብቃት ነበር፣ በእኩለ ሌሊት ትመጣና የቀዘቀዘ ልብሷን እስከነቷኝ 'እየሁ ለፍቅር የሆንኩትን' ትለኝ ነበር። ልብሷን አውልቃ በቀዝቃዛ ገላዋ ደርባዬን ትታቀፈኝና 'አንተ ደሞ ይቺን ለፍቅር ትከፍላለህ አሙቀኝ!' ትለኝ ነበር። አሁንም ከስንት ስንት ዓመታት በኋላ የምትመጣ ይመስለኛል። ከስንት-ስንት፣ ስንት-ስንት ዓመታት በኋላም ደጃፌን ከፍቼ እጠብቃታለሁ።"

አንገቱ ላይ ተጠምጥማ ፊቱን አንገቷ ውስጥ ከተተችው። አለቀስኩ እንዴ? የእሷ ብቻ የሚመስላትን በወንዶች መካድ ለሲፈን አጋራሁባት። ከእንግዲህ ናትራና ሲፈን ደባላሞች ናቸው። አንዷ ሌላኛዋ ላይ የመፅናናት ፅጣ ይጣጣላሉ።

ቴፐሪከርደሩ እንደ ሐሰተኛው ነብይ በአንድ ዐይኑ ይመለከተናል። የዓድቃንን ትንቢት መሙላት ለሐሰተኛው ነብይ ሐሰተኝነት ማጠናከሪያ አይሆንም? ታዲያ ለምን ሆን ብሎ ከትንቢቱ በተቃራኒ አይጓዝም? ጅል ነው? ለከሳሾቹ ክስ ስኬት ታጥቆ ያገለግላል?...

ከነዝናባ ሀሳብ ሸሽት ናትራን ሙጥኝ አልኩኝ። እስተቃቀፌ ሲጠብቅባት በግድ አላቅቃኝ እየችኝ። ግንባሬን ሳመችው። በፍም የተከበበ ቀዝቃዛ ከንፈር። በመሳሟ እንድትቀጥል አልፈለኩም ነበር። ጉንጭና ጉንጩን፣ አፍንጫዬን፣ ከንፈሬን፣ አገጩን፣ አንገቴን... እያገላበጠች ሳመች። የምሸሸው ሐሰተኛ መሲህ በቴፐሪከርደሩ በኩል አስታኮ በአንድ አይኑ ይመለከተኛል።

"ለምን እንደሳምኩህ ታውቃለህ?" ዐይኖቿ መደራረት ጀምረዋል።

@OLDBOOKSPDF

"አላወኩም"

"ባለፈው እንኳን ነይ ስትለኝ እምቢ አላልኩም? ለዚያ ነው"

ዝም! መላ አካላቷ ግሎ ስለምን ከንፈሮቿ ይቀዘቅዛሉ? ጉንጯ እንኳን ፍም እስኪመስል የጋለ ነው ታዲያ…

"ስሚ ደስ ይላል፤ ግን አይያዝም"

ዝም፣ ደግማ ልትጠይቀኝ ስትል አፏን ያዝኩት። ቴፕሪከርደሩን ማፈር ቃጣኝ። የፊቱን አቅጣጫ ስቀይር፣ የረድ ሠርዌ ባይጥ አድፍጣ ታየችኝ። ስለበላሁ ሳይሆን የሚበላ ነገር መግዛት እንደምችል ስላረጋገጥኩ ረሃቤ ያን ያህል አልጨከነብኝም። መራቤ እንዳለነው።

"እስኪ ምላ ሥሪ"

"ምን ልስራ"

"ምንም ስሪ፣ ግን እዚሁ ቤት!" ናትራ ስትወጣ ሀሰተኛው ነብይ በቴፑ በኩል ጭንቅላቴ ላይ ጉብ ብሎ ያታክተኛል።

ሳእል ከለመዱትና ከተቆራኙት አጋንንት በዳዊት መዝሙር ዕረፍት እንዲያገኝ እንዲሁ እኔና ቤቴ በናትራ መፈንጨት ከሀሰተኛው ነብይ ንዝንዝ ፋታን እናገኛለን።

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፲

"ቤት ለእንቦሳ"

ያሚረተብኝ መሰለኝ:: ናትራ ከቀደም ፍቅረኛዋ መካድ የተነሳ ውስጧ የሰረገ ጅምሯን በእኔ ብቅ ማለት አነቃቅታ...

"እንቦሳ አትፈልጉም? ቤቱ ላይ እንዲፈነጭ" ገባ፣ ፊቱ በፀሐይ ተጠብሷል:: ፀጉሩን በግራ እጁ መልሶ እናቱን አሰበሰ:: ሁኔታዬን ሲያይ ቆጠብ ብሎ ወደ መጽሐፍ መደርደሪያ ሄደ::

"ዛሬ ወደ ወፍጮ ቤቱ ሄጄ ነበር" ብሎ የሚያስገርም ነገር እንደገጠመው እንዳውቅ የተነፈሰ ሳቅ አሰማኝ

"አለቃችሁ እንዳገኘኝ 'እንደአህያ ፃድቅ የለም' አለኝ 'እንዴት?' አልኩት::

"ጭንቅላቷን ወደ መሬት አቀርቅራ፣ ጆሮዋን ለእግዚአብሔር ቀስራ፣ ሳትታበይ፣ በፈጣሪዋ ፊት ተናንሳ...

"እቋርጬ 'ጥንቸልስ?' ስል ጠየኩት:: በጆሮ ከሆነ ሁለቱም አይተናነሱም በሚል::

"ጥንቸል እንደአህያ ፃድቅ አይደለችም:: ጆሮዋ ወደኋላ ነው:: ከጀርባዋ እንዳትታማ ትሰጋለች::"

"ይሄ ሰውዬ ዋዛ አይደለም በሚል 'ሰውስ?" ስል ጠየኩት::

" 'የሰው ጆሮ ካየኸው ጥያቄ ምልክት ነው:: ለዚህ'ኮ ነው ሲጠይቅ ኖሮ ሲጠይቅ ሞቶ እንደገና ገነትን ከህይወት በኋላ የሚጠይቀው...' ግዴለህም ይሄንን ሰው ማዳመጥ ያስፈልጋል:: ቢያንስ የሚኖረውን ህይወት Justify ለማድረግ ይሞክራል:: ጥሩ ገፀባህሪ

@OLDBOOKSPDF

ይወጣዋል::" ጨዋታው ያሳደረብኝን ስሜት ለመረዳት ዘወር ብሎ ገረመመኝ::

ዝም፤ ዝም ውስጥ ስንት ጉድ አለ ግን? ዶ/ር አሮን አንዳንዴ የሚያወራው የተነገረውን ሳይሆን እንዲህ ቢሆን ያምራል ያለውን ነው:: የወፍጮ ቤቱ ባለቤት በዚህ መልክ ነገሮችን ከተገነዘበ...

"ታለስ ምን ሆነሃል?"

"ደህና ነኝ" ጉዝጓዙ ላይ ተቁነጠነጥኩ::

"ደህናማ አይደለህም"

"ከራሴ ጋር እየተወቃቀስኩ"

"እሺ?" የመረጠውን አንድ መጽሐፍ ይዞ ወደ አልጋው አመራ:: "በምን?" ተቀመጠ

"ሰውን እንደምሽግ መጠቀሜ ተገቢ አልነበረም:: ግን አደረኩት ከፍርሃቴ የተነሳ::"

"ሰብአዊ ፍጡርን እንደምሽግ የሚጠቀሙ ፀፀት የሚሰማው ሰውነት የላቸውም:: ለማንኛውም ንገረኝ የምን ፍርሃት ነው?"

"ሐሰተኛው ነብይ ደጃፌ ድረስ መጥቶ አስጠራኝ::" ቀና ብዬ አየሁት፤ ሊያምነኝ አይገባም::

"ለአንድ ደራሲ ከራሱ ከዋናው ሰይጣን ጋር መገናኘት ይጠቅመዋል:: ብዙ ሊጠይቀው ይችላል:: በማይረባ ምክንያት በፈጣሪው ላይ ማመፁ በራሱ ታላቅነቱን ይፃረራል:: እኛ ብንክድ እኛን ለመፍጠሩ ምንም ተጨባጭ ማስረጃ ባለመኖሩ ነው:: እሱ ግን ሲፈጠር ጀምሮ ህልው ሆኖ ከፈጣሪው ጋር ነበር..."

ንግግሩን ከመልኩ ጋር መደባለቅ ተስኖኝ ዝም ብዬ አየዋለሁ::

"ሐሰተኛው ነብይስ? ሐሰተኛነቱ ቀድሞ ከታወቀ፣ ድል እንደሚሆን በትንቢት ከተነገረው ለምንድነው ይሄን ሁሉ ዘመን በተስፋ የሚቆየው?"

ዝም፤ ዝም ውስጥ ብዙ አለ

@OLDBOOKSPDF

"ምን አልከው? ምን መሰሰልህ? ሐሰተኛ ነብይ መሆኑን እሱ ነገረህ ወይስ አንተ አወክው? እንዴት?" የያዛትን መጽሐፍ ባይጧ ላይ አስቀመጠ::

"መጀመሪያ ስለሐሰተኛው ነብይ የሰማሁት ከረድ ሠርዌ ነው:: መልኩን ልቅም አድርጎ ነግሮኝ ስለነበር ገና ሳየው አወኩት::"

"ሠርዌ ለአንድ ትልቅ መንፈሳዊ ምስጢር እየተዘጋጀ ይመስለኛል:: በራሱ መንገድ ትክክል ሊሆን ይችላል! ግን እውነቱን ወዳንተ ሲያጋባ መጠየቅ ያለባቸው ብዙ መፋለሶች ሳይኖሩ አይቀሩም:: ዮናኤልም ተረብሾ አግኝቼዋለሁ:: እሱ እንደሚለው የጥንት መጽሐፍት ላይ ስለሀሰተኛው ነብይ ትንቢት ተነግሮ ሰፍሯል:: የትንቢት ነገር በቀጣይ ዘመን ከመፈፀሙ በፊት ብዙ መንፈሳዊ ሰዎች በራሳቸው፣ መመሪያውን ተከትለው ሊፈፅሙት ይነሳሳሉ:: ምናልባት በዚህም ዘመን..."

ያስቀመጣትን መጽሐፍ አነሳ

"ምናልባትም በዚህ ዘመን ትንቢቱን ለመፈፀም የተነሳሱ ልበሙሉዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: በተለይ ወጣቱ የለውጥ እንቅስቃሴ አስነስቶ ሲከሽፍበትና ተስፋ መቁረጥ በነካካው ማግስት እንዲህ ወዳሉ መንፈሳዊ ጀብዱዎች ይሳባል::"

ባዕድ ፀጉሩን ወደ እናቱ አስተኝቶ የያዛትን መጽሐፍ በዝምታ ያገላብጥ ጀመር::

"ምንም አይነት ትንቢት ጀብደኞችን ከማነሳሳት ውጭ በራሱ ተፈፃሚነት የለውም እያልክ ነው? በዚህ ዘመን ተአምር መጠበቅስ አይቻልም?"

"የእኔን አስተያየት ነው የጠየከኝ?" ፀጉሩን ማስተኛቱን ረስቶ ዳግም ከግራ ወደቀኝ በእጁ ሞገቀ::

"አዎ"

"ትንቢት፣ ተአምር በሳይንስ በኩል ካልሆነ በእምነት በኩል ብዙ ጠብቀን አጥተናል:: የእማልክቱ መኖሪያ ተብሎ የተሰየመው ሰማይ በሳይንስ ታሰሶ እስካሁን የህይወት ፍንጭ አልተገኘበትም:: በብዙ ዓመት ብርሃን መጓዝ ስንችል የተቀረውን የጠፈር ክፍል እናስሳለን::

@OLDBOOKSPDF

እስከዚያ ግን የትንቢት፣ የዳግም ምፅአት፣ የዓለም ፍፃሜ፣ የሙታን መነሳት... ተአምር መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት በላኪ ይሻለዋል።"

"የልዕለ ተፈጥሮን መኖር በአካል አለሳ ጠፈር ስጠፈር በመንከራተት ነው ምላሹ የሚገኘው?"

"ታዲያ?"

"የተፈጥሮ ህብር በራሱ የልዕለ ተፈጥሮን መኖር አያረጋግጥም፤ ዓለም ላይ የተሰራ ነገር አለ፤ ያ የተሰራ ነገር ስለ ሰሪው የሚጠቁመው እንዳች ዕውነት አይኖርም? የሞክሼህን የቱርካዊውን የሃሩን ያህያ መጽሐፎች ያመጣህልኝኮ አንተ ነህ። የዓለምን የህይወት ቅንብር እያዩ ፈጣሪ የላቸውም ከማለት በላይ ፍጥጥ ያለ ክህደት የለም ይላል። ለምሳሌ ግዙፎቹን ፍጡሮች ተውና ኢምንቶቹን ነፍሳት አጥና። ለምሳሌ ምስጥ፣ አንድ የምስጥ ሥርዎ መንግሥት የራሱ መተዳደሪያ ደንብና የጉሮ ምድብ ተዋረድ አለው። ሠራተኛ መደብ ሲያንስ ሌላ ሥርዎ መንግሥት አጥቅቶ የምስጥ ባሮችን በመፈንገል ለልጆች ምግቢት፣ ለፅዳት፣ ለሥራየቤት... እየደለደለ ያስራል። ለንግሥቷም ብዙ ባሮች ይመደቡላታል። ክፍሏን የሚያፀዱ ጭምር። እና? ...ይሄ በአጋጣሚዎች ስከትክት ማለት የተገኘ ውጤት ነው? ሠሪማ አላቸው።"

"እሺ ልዕለተፈጥሮ በመኖሩ እንስማማ፤ ግን እንዴት? የት? ይገኛል? ለዚህ ዓለም ለውና ለተቀረ ሥራው ግድ አለው? ወይስ ታላቁ ሰዓት ሰሪ እንደሚያደርገው ሰዓቱ እራሱን በራሱ እንዲሰራ ከማድረግ ውጭ የት እንደደረሰ የማረጋገጥ ግድ የለበትም?"

"አለ፤ ግን በዓለምና በፍጡራኖቿ መካከል ምንም ጣልቃ ገብነት የለውም ማለት ያው 'የለም' ከማለት እኩል ነው።"

"ስለዚህ አለ፣ ዓለምንና እኛን ለዕጣ ፈንታችን አልተወንም ማለት ነው?"

"'Man is a helpless toy in the hand of nature forces' እንደተባለው ነው። ዝናቡም፣ ፀሐዩም፣ አቧራውም፣ ጎርፉም፣ ረሃቡም፣ ጥጋቡም፣ ብርዱም... ሲፈራረቅበት የኖረ፣ ግን እንደሰራው የማይታወቅ ምስኪን አሻንጉሊት።" አልኩ የማልጎምጎም ያህል።

@OLDBOOKSPDF

"So, የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት በቅጡ ሳይስተዋል ተቃዋሚው ሐሰተኛ መሲህ ከየት ይመጣል? መጀመሪያ ወደፊት የሚያሽከረክር መኖር አለበት የጎታችን ህልውና ለማረጋገጥ" የዶክተር አሮን ጥሩ ባህርይ ሰው ከውስጡ ያለውን እቋምና ዕውቀት እንዲያወጣ ለማገዝ እንጂ በክርክር ለማሸነፍ ወደመነጋገር አይገባም።

"እውነት ለመናገር፣ ለሌላው ለማስረዳት በሚከብድ አኳኋን የሆነ ነገር ተሰምቶኛል፤ ገብቶኛል ማለት ይቀላል ከፍልስፍና በላይ፣ ከዕውቀት በላይ፣ ከመረዳት በላይ፣ ከማውጠንጠንም በላይ..."

"እና ሐሰተኛው መሲህ ለመምጣቱ እርግጠኛ ነኝ እያልከኝ ነው?"

"አግኝተኸው ብትፈርድ ይሻላል"

"ጥሩ" ፀጉሩን ያስተኛ ሳይሆን ቁመቱን ከአናቱ በሰያፍ የከረከመ መስሎ "ታዲያ ሐሰተኛው መሲህን ማወቅ የሚያስጨንቅ ወይም የሚያስፈራ ነገር አለው?"

"ይረብሻል"

"ምን የሚረብሽ ነገር ተናገረህ?"

"ምንም፣ ግን ወደራስህ መጥፎ ድርጊቶች ተመልሰህ ማንነትህን እንድትከልስ ያስገድድሃል። ምክንያቱም የጨለማውን መንግሥት ሊያሰፍን የመጣ ሰው አንተን ሲመርጥህ ምን ያህል በኃጢያት የተጨማለቁ ነኝ የሚል ውርክብ ውስጥ ከራስህ ጋር ትገባለህ።"

"ስለዚህ ምን አደረክ? ማለቴ Human Shelter ስላልከው እንድታስረዳኝ ነው።"

"ናትራ..." ንስሃ መግባት ኃጢያት ከመስራት በላይ ለምን ይከብዳል? በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥነ ልቡናም ቢሆን

"እሺ?" የንስሃ አባቴ

"ቢቃ፣ መሸሸጊያ አደረኳት፣ ከፍርሃቴ ተደበቅሁባት፤ የራስን መዳን ብቻ በማሰብ ሌላውን መሸሸጊያ ማድረግ ያው Human shelter አይደለም?"

@OLDBOOKSPDF

"እንደገባኝ እሷም ሰው የሚያስፈልጋት ሰዓት ላይ ናት። የሆነ ግንኙነት መፍጠሩ ለእሷም ከሆነ ከባድ ስሜት እንደሚገላግላት አስባለሁ። ግንኙነታችሁን ወደላቀ ደረጃ ማሳደግ። አሁን ባለው መጣጣም ላይ የሚመሰረት ነው። "ለእንቦሳ" አለመብቃት የአንድ ወገን ስህተት አይሆንም። እስከ. ዝም ብለህ ያለህበትን ሁኔታ አጣጥመው፣ ምናልባት ወደሌላ የህይወት ዘዬ ይመራህ ይሆናል።"

ዝም፤ የናትራ ሮዝ ብርሃን የደጃፌን ተፈጥሯዊ ቀለም ቀይሮታል። ሮዝ ደመና በደጃፌ ላይ ይሄዳል፤ ይመጣል። ምናልባትም ሥሟ ሲጠራ ስምታ ወሬ ለመቃረም እያንገርበበች ይሆናል።

"ወደ ለንደን መመለስ ነው። ብዙ የትብብር ፕሮጀክቶች ውድቅ ሆኑ። ያሳዝናል፤ በተረጂ ሥም የድሎት ህይወት የሚቋምጥ ተራድኦ ድርጅት በዛ። ይቅርታ አድርግልኝና ሰብአዊነት ጠፋ። በዚህ ላይ በቅርቡ የወጣው የተራድኦ ድርጅት መተዳደሪያ ደንብ ትልቅ ማነቆ ሆኗል። እግዚአብሔር የሰውን ዕጣ-ፈንታ ለሰው ለራሱ ትቶታል። ማዕበል ቢመታን፤ እሳት ቢነሳብን፤ ተስቦ መግቢያ ቢያሳጣን፤ ቸነፈር ቢንሰራፋብን... ለሰው ደራሹ ሰው ብቻ ነው። ግን ሰውን ለሰው የመተውን ያህል አሰቃቂ የተፈጥሮ አደጋ በጭራሽ የለም።"

ተስፋ የቆረጠ ይመስላል። በግራ እጁ የደረሰበትን ቁመት በሰያፍ ለኩቶ...

"አንተጋ የማስቀምጠው ዕቃ አለኝ። ባህሪህ ለዚህ አደራ ያበቃሃል። ብዙ ጊዜ እንዳየሁት ገንዘብ አንተ እጅ ላይ ኖሮ በአካባቢህ ያሉ ሰዎች ደግነትህን አትነፍጋቸውም። ከፋ ቢሆንም ያንተን ልግሥና አያጡም። እንዲሞት የምትፈልገው ሰው ቢኖር እንኳን የሚቀምሰው ከሰጠኸውና ካዳንከው በኋላ እራስህ ትገድለው እንደሆን እንጂ ከደግነትህ ሳይቋደስ አይቀርም። ይቅርታ ይሄን የምለው አደራ ያኖርኩት ትክክለኛ ሰውጋ እንደሆነ እንድትረዳው ነው።"

ዶክተር አሮን እየነገረኝ ያለው ከዚህ በፊት ያደረኩትን ሳይሆን ወደፊት ማድረግ የሚገባኝን እንደሆነ አድርጌ ወሰድኩት። ከአደራው ጠላትህም ቢሆን አቋድሰው ማለቱ ሳይሆን አይቀርም። እንዲህ አይነት ሙገሳ ይከነክናል፤ ስሜቱ አመፀብኝ...

"አንተ ባልነበርክበት ጊዜ የሆነውን ልንገርህ። ምናልባት ከትክክለኛው ማንነቱ ጋር ያስተዋውቅህ ይሆናል"

@OLDBOOKSPDF

ፀጉሩን ላገ፣ የጣለውን መጽሐፍ አነሳ፣

"እኔና ሬድ ሠርዊ ቸገረን። ለነገሩ ጋዜጠኛ ሁሉ ነው የተቸገረው። የባሰባቸው ጋዜጠኞች 'እርዱን ቸገረን' እያሉ በየኤንባሲው ደጅ ጠኑ። ጋዜጠኛ ለመርዳት የያዝነው በጀት የለም ተባሉ አሉ።

"...እና እኔና ሬድ ሠርዊ ችግር ለመቀነስ እዚች ቤት ውስጥ በደባልነት መኖር ጀመርን። ሁለት ችግረኛ ሲተባበር ችግር ይበዛል እንጂ አይቀንስም። ችግር በዝቶ ችጋር እስኪሆን ድረስ፤ ረሃብ እራሱ እኛን መጎትጎት እስኪቸከው ድረስ...

"...ሰው የመሆን መጥፎ ኃይል፤ በሰው ተፈጥሮ ላይ ያለው ስልጣን የሚረጋገጠው የመሠረታዊ ፍላጎት እጥረት በተፈጠረበት ሥፍራ ነው። ከተፈጥሮዬ ጋር ተዋወቅሁ። እፍኝ ቆሎ አገኘሁ። ከየት እንደሆነ እንጃ፤ የቡና ቁርስ ሲያሲዙኝ ያስይሉኝታ አፍሼ ይሆናል። ከመሬት ፈስሶ ለቅሜም ሊሆን ይችላል፤... እና...ሬድ ሠርዊ ቤት ውስጥ አሉ። በረሃብ ሰመመን ውስጥ የተኛ መስሏል፤ ማካፈል የሚሉት ጣጣ አለ፣ ሰው ማለት ይሄ ነው። ስቆረጥም ሬድ ሠርዊ እንዳይሰማ በውኃ እያለዘብኩ ብቻዬን በልቼ ጨረስኩ።"

አለቀስኩ? እንጃ! አይኔን የሆነ ነገር ጋረደኝ።

"ከእስቀያሚው እውነት ጋር የተፋጠጥኩት የመጨረሻዋ ጥሬ አፌ ውስጥ ከጠፋች በኋላ ነው። ስብከንከን አደርኩ። ሬድ ሠርዊ በማለዳ ታጣፊ አልጋውን ማጣጠፍ ጀመረ። ቆዳ-ቆዳ የሚሸቱ ብራናዎቹን መሸከፍ ያዘ። እኔ ከንብንቤን ሙጥኝ አልኩ። ስለፈጣሪዬ ጥፋት እኔ አፈርኩለት። የት? እንዴት? ለምን?... ተፈጥሬ ጥሬ ብርቅ ሆነብኝ? ከሰማይ ወፎች፣ ከአውር አሞሮች አንሳለሁ?"

ዝም! ፀጥታ እንደመርግ ተጫነን...

"ሬድ ሠርዊ እንደተከናነበኩ እንዲህ አለኝ። 'ይቅርታ አብረን መኖራችን ለፈጣሪም አልበጀው። ማታ ከደጀሰላም ያመጣሁትን ቅምቃሚ እንዳትሰማ አድርጌ በውኃ እያማገሁ በላሁት። ለእንደኔ ያለሰው የሞት፣ ሞት ሞት ነው። ግና የሰይጣንን ፈተና ማለፍ ተሳነኝ' አለኝ።"

ዶክተር አሮን ካልጋው ተነሣ፣ ወደመጻሕፍቱ መደርደሪያ አመራ፣ መነፅሩን አውልቆ በእጁ ያዘ። አንድ ዱካ ስቦ ጀርባውን ለእኔ

@OLDBOOKSPDF

ሰጥቶ ተቀመጠ። ለማንበብ ከሆነ መነዕሩ አስፈላጊው አልነበረም ለማልቀስ ነው።

"ዛሬ አንድ የአማርኛ ሥነ ፅሁፍ ተስፋ የሆነ ትልቅ ሰው አጣን"

"ማንን?" እኔን ይሆን? በእርግጥም ይሄንን ልቡና ይዤ እንደቤተመቅደስ የነፃችውን ኪነት ልቀላቀል አልችልም።

"ዓለማየሁን!"

"ምን? ዓለማየሁ?"

"አዎ! ገላጋይ

"ምን ሆነ አልከኝ?" ከጉዝጓዜ ላይ ተነሳሁ።

"እራሱን አጠፋ! የአንተና የሥርዌን አይነት ብዙ ታሪክ ሳያሳልፍ አልቀረም። መቀጠል አልቻለም..."

ዝም! ሐዘን እንደ ተናደ ምርጊት ወደቀብን።

"ታዲያ ለፈጣሪያችንስ ቢሆን ከመኖሩ አለመኖሩ አይበጀውም? ከእንዲህ ያለ የበከተ ታሪክ ጋር ከሚነካካ አለመኖሩ አይታደገውም?"

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፲፭

"እሰግድ ለኪ፣ እሰግድ ለኪ ቅንብቢት፣ እሰግድ ለኪ ቅንብቢት ቤተ መምኅፃን"

ሰምንን የተቀየምኩት ጠፍቶ ሐዘን ተተካ:: አልፈርስ ያለ የደቂት ጎጆላ ይመስላል::

"እመፀኛ፣ ወንጀለኛ፣ ነፍሰ ገዳይ፣ ቀማኛ... ነኝና ሰላም ለኪ ቅንብቢት ቤተ መምኅፃን" ጓንጥ የጭኝቅላት መሸፈኛ ኮፍያውን አወለቀ:: በብብቱ የያዘውን የተጣጠፈ ማዳበሪያ በር ስር አስቀምጦ ወጣ:: ወዲያው መቡነን ጀመረ:: የፀሐይ ጨረር በደቂት መራወጥ ሲረበሽ አየሁት::

"የግራዝማች ዋለሉ ያለህ፣ ምነው? ምነው? ቡናኝ ይወድልናል?" ወፍራም ፊት፣ ወፍራም ሆድ፣ ወፍራም ደረት ያላቸው የአከራዩ እህት እንደሆኑ በአፍንጫቸው መከናከን አወቅሁ::

ረድ ሠርዌ ማራገፊያ ኮፍያውን በእጁ እንደያዘ ገባ:: ግማሽ የደቂት ጭንቱን አራግፏል:: ፊቱንም በኮፍያው ጠብጥቧል?...

"...ማየ ቀበና እንደጭፍራ ታዞ ከሰውም ከከብቱም ሲሶ ሲሶውን በተሰቦ ያጠፋል:: ቅንብቢትም ቀድሞ በአዳም ዘመን እንደተረገመች ሁና የዘሩባትን ዘር ቆርጥማ ያልዘሩባትን ሦከና እሜኬላ ታበቅላለች:: ወዮለት ለዚያ ዘመን የቅንብቢት ሰው"

ደቂቱን ይዞ የት እንደሚቀመጥ ግራ ገባው:: ቆይቶ ባለሦስት እግሯ ዱካ ላይ ተሰይሞ ወጉን ቀጠለ::

"እንግዲህ በቃኝ፣ የወፍጮ ቤቱ ሀማም በቂ እንደሆነ በህልሜ ተገለጠልኝ:: ከመጡ ያንን ማዳበሪያ ስጥልኝ፣ አደራ በምድር አደራ በሰማይ"

@OLDBOOKSPDF

ፊፅም ያላየሁት ፍርሃት የልቤ ላይ ስራይ እየሆነ ይመስለኛል። የማያስፈራ ንግግር ሁሉ አስበርግጎኝ ያልፋል። ልክ ካፍካ የተሰኘው ደራሲ እንደሚያስበው ያለ መጨበጫ የሌለው ቅዠት አከል እውነት ከፊቴ የተጋረጠ ይመስለኛል። ካፍካ በእንዲህ ያለ ህይወት ውስጥ እልፎ ሳይሆን ይቀራል? ቅዠቱ የሱ ብቻ ይመስል ያሽሞነሙነዋል። ቅዠቱ የሰው ልጅ ሁሉ የወረደ ዕውነት እንደሆነ አያስብም። እያሽሞነሞነ በፍርሃት ጨሌ ተፈላጊ ጥበብ ያስመስለዋል።

"ዶክተር አሮን ብር አስቀምጦልሃል" አልኩት።

"ኧረ ድንቅ፣ እንዲያማ ከሆነ ጠንቋይ ማረፊያ ላይ ቤት እከራያለሁ። እዚያ ላይ ሠፍሮ ቁልቁል የሚማትር አሳጋጭ መንፈስ አለ። ከሆነ ተስማምጬ ካልሆነ ሰምጥጬ አደብ አሲዘዋለሁ። ሰነገሩማ የሐሰተኛ መሲሑ መንገድ ጠራጊ ነው አሉ። በስመ ክርስትናው ዮሐንስ ማሸፉ ነው፣ በምቱረክሳድ መሸፉ ነው። የሚያስቀድስ፣ ጋኔን ኧረ ሰአታትም ይቆማል አሉ። ሰልሉ ነው፣ ዘማዊ ቄስ ሲያጥነው የሚያክላላ..."

"ምሳ ተሰርቷል ይቅረብልህ?" ከዚህ በፊት እንዲያፍታታ፣ እንዲያብራራ እለምነው እንዳልነበር? አሁን ግን ሁሉን ትቶ ዝም" ቢለኝ መረጥኩ።

"የላመ፣ የጣመ ነው?"

"ፓስታ ነው"

"ፓስታ ሹታ? ይቅርብኝ! ባይጧ ችምቻሚ አላተረፈችም? እሱ ይሻለኛል።"

ከራስጌ እንደነበር አድርጌ ካስቀመጥኩበት፣ አንስቼ ሰጠሁት። እጁን ሰድዶ ችምቻሚ ዘግኖ፣ ከጉልበቱ ብዙም ሳይርቅ አንዳንድ ጥሬ እያስፈነጠረ አፉ ውስጥ መክተት ጀመረ። ቸንቹ ገጥጦ ታየኝ።

"አባ ጊዮርጊስ ዘ ጋስጫ በተጋድሎው ወራት የላመ፣ የጣመ ምግብ አቀረቡለት አሉ። ከምግቡ ጋር የመጣለትን ወይን ጠጅ እያየ መንፈሱን ከፉኛ ተፈታተነው። እናም ነፍሱን ሲገሥጻት...

"አንፍስየ ከመ [illegible] ወበክሐሰ ትርጎቢ."

@OLDBOOKSPDF

ተርጉምልኝ እስከለው ጠብቆ ሲያጣ ተረጎመው።

"'ነፍሴ ሆይ በዚህ ልትጠግቢ በወዲያኛው ልትራቢ ትወዳለሽን' አላት።"

ብሩን ከጥራዙ ላይ በግምት መጥኜ ሰጠሁት። 'ውጣልኝ' ማለቴ ነው? ግን ምን እየሆንኩ ነው?

ዝቅ ባለድምፅ እንዲህ ብሎኝ ወጥቶ ሄደ:-

"ሲሆን ከመንደርና ከሀገር ወጥቼ፣ ጎራ ዞሬ፣ በረሃ አቋርጬ፣ ዋዕይ መአልቱን፣ ቁር ሌሊቱን፣ ድምፀ አራዊቱን፣ ፀብዐ አጋንንቱን ታግሼ መንፈሳዊ ተጋድሎዬን ማካሄድ ነበረብኝ። ግና..."ወጣ።

እንደጎዳሁት ገባኝ፤ እሱም ከጎዳኋቸው፣ ውለታቸውን ከዘነጋሁት ከማላስታውሳቸው ወገን ይሁን! ምን ማድረግ እችላለሁ?

ኡ! ኡ! ኡ! ኡ! ኡ!...

"ናትራ! ናትራ! ናትራ!... የትነሽ?" ከቤት ተፈንቅዬ ወጣሁ። ረድ ሠርዊ ዳገቱን በተጠራሞተ አኳኋን ተያይዞት አየሁ። ጃክ ጥግ ይዞ፣ ከእግሩ ላይቀና ብሎ እኔና ረድ ሠርዊን እያፈራረቀ ያየናል። ዘባዘበ ፊቱ ከእግሩ ተርፎ መሬት ይልሳል-ቱሊያም!!

"ናትራ! ናትራ!..."

የሚገርመው ቤቷ የቱ እንደሆነ አላውቅም። ከማን ጋር እንደምትኖር፣ ከእናቷ? ከአባቷ?... ተመልሼ ወደ ውስጥ ስዘልቅ ከበስተኋላየ...

"ያለ ተመልካች አገኘኋት፣ በፊት ቢሆን እንዲህ ያለ ድርጊት የግራዝማች ዋሰሉ ያሰህ! አድባሯ ደም ጠምቷታል ማለት ነበር።"

...ገባሁ! የማደርገው ነገር አጣሁ። እውነት ናትራን የምፈልጋት ከሲጣናዊ ሀሳብ ስመገላገል ብቻ ነው? ወይስ... ወደ መጽሐፍ መደርደሪያው ሄድኩ። ርዕሳቸውን እንኳ አንብቤ መምረጥ አልቻልኩም። እንዳመጣልኝ እጄን ሰድጄ ከበድ ያለ መጽሐፍ አነሳሁ። ስገላልጥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ደመነፍሴ ነገረኝ። እኩሌታው ላይ ገምሼ የመጣልኝን ማንበብ ጀመርኩ።

@OLDBOOKSPDF

"ምድርን በኃይሉ የፈጠረ፣ ዓለሙን በጥበቡ የመሰረተ፣ ስማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው። ድምፁን ባሰማ ጊዜ ውሆች በሰማይ ይታወካሉ፣... ነፋስንም ከቤተመዛግብቱ ያወጣል።"

እግዚአ፣ ከሐሰተኛው መሲህ ጋር ሆነን እርሱን ነው የምንዋጋው? ለመሆኑ ከነፋስ በተጨማሪ በቤተመዛግብቱ ምን ምን ይኖሩት ይሆን? ኃይሉስ ምድርን ከመፍጠር ባሻገር ለምን ያገለግለው ይሆን?...

...እንቀፁን ለመድገም ሳስብ መጽሐፉን ገጥሜው ኖሮ የትኛው ገጽ ላይ እንዳነበብኩ ጠፋኝ። ስፈልግ ብዙ ቆየሁ። እንዴት አይነት ገለፃ ነው? እውነትም መለኮታዊ ተሳትፎ ይኖረው ይሆን እንዴ? ጥፍጥናው ከአእምሮዬ ሳይጠፋ ቃላቶቹ ብን ብለው ጠፉ።

የተለየ ብርሃን ቤቴን ሲሞላው ቀና አልኩ። ነፀብራቅ መስላኝ ነበር። ናትራ ባልተለመደ አለባበስ ብቅ አለች። ገፅታዋ ተለየብኝ፣ ተኳኩላለች ልበል?

"ታለዬ" አለችኝ

"ወዬ፣ ፈተናዬ" አልኳት መጽሐፍ ቅዱሱን እያስቀመጥኩ።

"እንደዚህ እያልክ መጥራት ትተህ አልነበር?"

"ዛሬ ቆንጆ ሆንሽብኝ" አንገት ላይ ሽብ የሚደረግ ሪቫን ያለው፣ አበባ የተፈነጣጠቀበት ስስ አላባሽ ከጉርድ ቀሚስ ጋር ከአፈረው እግሯ በታች ሁለት ድንቢጥ የመሰሉ የእግር አውራ ጣቶች ከሽፍን ጫማ የአፍንጫ ቀዳዳ ብቅ ብለዋል።

"አምረሻል ፈተናዬ፣ የትሄደሽ ነው?"

"ልንገርህ አትቆጣም?"

"ለምን እቆጣለሁ?"

"ትምህርት ቤት"

"ልትመዘገቢ?"

@OLDBOOKSPDF

"አዎ" ብላ በሹፈት ሳቀች። አይኖቿ በጥቁር ክፈፍ ተከብበው ጎልተዋል። ተኩላለች?

"ታዲያ?"

"እኮ ልመዘገብ፣ ከሁለት ዓመት በኋላ ፊት ለፊት ስንገናኝ። ደነገጠ፣ እንዳልከውም ሳይፀፀት አልቀረም። እኔ ለማግኘትም፣ ለማናገርም እንደድሮው አልተርበተበትኩም። እሱ ግን..."

ትክ ብዬ አየኋት ከአለባበሷ ጋር ትልቅ ሆናለች።

"የታባቱ!"

ዝም፣ ከመጽሐፍ መደርደሪያው አጠገብ ሸሸሁ። ቁመትም ጨምራለች። ከፍ ያለ ጫማ አድርጋለች ወይስ ምንድነው?

"ቤት ገብቼ ልብስ ቀይሬ መጣሁ"

"አይቻልም፣ እንደዚሁ፣..." የምትመለስ አልመሰለኝም።

"አንተ ነበርክ የናፈከኝ፣ እሱን ትቼ ወዳንተ ብርርር"

"ታድዬ" አልኩ በሆዴ።

"አሁንምን ላድርግልሽ?"

"እ-የሚፈነዳ ነገር እንግዛ..."

"ምን?"

"አዎ" ከንፈሯም በመጠኑ ቀላልቷል።

"ለምናችን?" እያልኩ ጉዝጓዜ ላይ ተቀመጥኩ። ናትራም የተፈጥሮ አንዱ አካል ትሆን። የሚበጠብጠውን ማቅጠኛ። አጠገቤ መጥታ ተቀመጠች። ንጥር ሽቶ ሸተተኝ።

"ለማፈንዳት፣ እያፈነዳን ቀልባችንን እንግፈፍ"

በዕርግጥ ናትራ ሳትሆን የሚፈነዳ ነገር ነበር ያስፈልገኝ የነበረው። እንዴት አላሰብኩትም?

@OLDBOOKSPDF

"ምን እንግዛ?"

"የመኪና ጎማ፣ ዷ! ሲል... ግን በምን እናፈነዳዋለን?" ጆሮዬን፣ አይኔን፣ አፍንጫዬን... በአዳዲስ ነገር ከበበችው::

"እ-ሺ ሽጉጥ የት ነው የሚሸጠው?"

"ሽጉጥ አይሸጥም"

"እ-ሺ ለፖሊስ ጉቦ ሰጥተን ጆሮአችን ላይ ይተኩሰው::"

ዝም ብዬ አየኋት::

"ጋግርቴን ስጠላው፣ አንተ ጋግርቴን ትወደዋለህ? መኪና ገዝተን ጭሱን እያፈነን እናፈንዳው? ደሞ ገንዘባችን አይበቃም::

እጀን ለድጀ ጉንጫን መዳፌ ላይ ሞላሁት:: ወደትከሻዋ ጭንቅላቷን ዘንበል አድርጋ እጀን ጠበቅ አደረገችው::ጨፍና ስትገልፃቸው አይኖቿ አብረቀረቁ...

"ቆይ፣ ቆይ... መጣልኝ፣ ጠብቀኝ" ብላ ከንፈሬ ላይ ሳም አድርጋኝ ሄደች:: ቅዝቃዜው እንዳለነው:: ሩጫዋ የአለባበሷን ደርባባነት ገፈፈው:: ስትመለስ በቀለም ተከባ ነበር:: ፊኛዎች፣ እየነፋች ቤቱ ውስጥ ትለቃቸው ነበር:: ግማሽ ያህሉቹ እንደተንሳፈፉ አንዱን አንስታ ሰጠችኝ::

"ከጆርባዬ አፈንዳብኝ"

"እ?"

"እዎ፣ ቀልቤ ግፍፍ ሲል አዲስ ልጅ እሆንልሃለሁ:: ስደነግጥ ልቤ ሲመታ፣ ሰውነቴ ሲሞቅ፣ የምሞት ይመስለኛል:: ከዛ መኖር እፈልግና... ሁለመናዬ ቅዝቅዝ ሲል ሞቼ የምኖር ይመስለኛል:: ብዙ ጊዜ ሞቼ ሲጋራ አጭሻለሁ:: አላሳዝንም?"

ፊቷን መልሳ ከፊት ለፊቴ ተቀመጠች:: ፀጉሯ ተተኩሷል:: ይሄ ሁሉ ዝግጅት ፍቅሯን ለመሸኘት ይሆን? ወይስ ያፈቀረችው ያመሰጠውን ልታሳየው?

"በላ" @OLDBOOKSPDF

"አፈንዳ ካልሸኘ ቀስ ብዬ ቆይቼ..." ዷ! ጥበቃዋን አጥፍቼ ገና ነው ስትል አፈነዳሁባት:: ህይወት ድንገት ያላትን እንቅስቃሴ ሁሉ የገታች መሰለች:: ቆይታ ካሰቻት መሰል ስትዞር ፊቷ ቀልቷል:: በሙቀ ከንፈር ሳመችኝ::

ናትራ? ናትራ? ናትራ?... የሚያሰኝ መሳም::

ተመንጭቃ ሄዳ የሚንሳፈፉትን ፊኛዎች እያወረደች ትረግጣቸው ጀመር:: ቀኑ የደረሰ ፊኛ ዷ! ይላል::ጊዜው ያልደረሰው ግን ከመሬት ጋር በጫማዋ ስትለትመው ተፈናጥሮ ብድግ ይላል:: እንደልጅ ቦረቀች:: ሲፈነዳ ጆሮዋን ይዛ ጥቂት ከድንጋጤ ጋር ትቆያለች::

"ያቺ ናትራ ናት? ፊኛ ገዝታ ስትገባ አይቻለሁ፣ የግራዝማች ወለሉ ያለህ፣ ምን ጠላት ገባ? ፈረንካ ረከሶባችሁ እንደው ወዲህ በሉት"

"ኡፍፍፍ... ጠንቋይ ማረፊያ ቤት በሰራን:: የጠንቋዩን ቀልብ እየገፈፍን... ይረግሙን ይሆን?..."

ሳልወድ በግድ ሳቅሁ።

"የጠንቋይ እርግማን ምን ያደርገን ይሆን?" ቀልባችሁ ይገፈፍ! ስላሉን ቀልባችን ተገፍፎ... ቀልብ መገፈፍ ግን ምን ያደርጋል?"

ናትራን የምፈልጋት ለዚህ ነው:: በአየር ላይ ስክንፍ ጠልፋ ታወርደኛለች:: የጠፈርን ጉዳይ ወደ ሁለት ሰዎች ግንኙነት ዝቅ ታደርገዋለች:: ትናንሽ ነገሮች ላይ መጣድ ልብን ደስ ያሰኛል::

እቅፌ ውስጥ ገብታ መፍለክለክ ጀመረች:: የእኔ ማቀፍ ተመችቷት የሚያውቅ አይመስለኝም:: እጆን ካቀፍኩበት አውርጀ ደግሞ እሞክራታለሁ:: እንደተጠመደች የጫካ እርግብ በሰው ሥር መሆኗ የሚስማማት አይመስልም::

ከሞት የተረፉት ፊኛዎች በቀለማቸው ፉክክር ይዘዋል:: ቀለም ከናትራ መአት ያድን ይመስል ከመቼው ከሞት ፍርሃት ወደ ህይወት ፍካት ተሸጋገሩ? ፈገግ ሥል:-

"ታለዪ"

"ወይዬ ፈተናዬ"

@OLDBOOKSPDF

"ፈተናዬ አትበለኝ"

"እሺ ፈተናዬ" በዚች ፋታ የምትፈጠርን የሴት ጥያቄ ስሸሸ ኖሬአለሁ:: ምናልባትም የናትራ...

"ትወደኛለህ እንዴ?"

ይሄ የሴቶች ጥያቄ በአንድ መልስ የሚያበቃ አይደለም:: ይበልጡኑ ለሌላ ጥያቄ ማመቻቻያና ለቀጣዩ ምላሽ መፈናፈኛ ማሳጪያ እንጂ::

ዝም

"አትወደኝም?" ካልወደድከኝ ለምን አቀፍከኝ? ለምን ሽቶዬን ማግህ? ለምን ዓይኖቼን በዓይኖችህ አባበልክ? ለምን ፊኛ እናፈንዳ ስልህ እሺ አልክ?..."

...እነዚህን ሁሉ ምክንያቶች የመውደድ መግለጪያ አድርጋ ዝም ማለት ትችል አልነበር?

...ግን... አልወዳትም? እወዳታለሁ? ከእሷ ጋር ስሆን መደሰቴ ወደየት ያደላል? ጀርባዋን በመዳፌ ማሻሸት ጀመርኩ:: የአላባሿ ልስላሴ እጄን ተሰማኝ:: ጨርቁ እየተንሸራተተ እጄ ከጀርባዋ ጋር መፍጠር የፈለገውን ህብር ያከሽፈዋል:: እሷም የጨርቁ ልስላሴ ብቻ ሳይሰማት አይቀርም::

"ከበደህ አይደል? እወድሻለሁ! እጠላሻለሁ ማለት ከበደህ? አስጨነኩህ? ተወው እያወቅሁ ነው የጠየኩህ! እኔን የሚወደኝ የለም"!"

"የምሆንልሽንና የማደርግልሽን ማየቱ አይበቃም? በፊት እንደዚህ ነበርኩ?" ይሄ ሁሉ ዋጋ እንደሌለው አውቃለሁ:: እነሱ ቃል መቀበል አይሰለቻቸው! እኛ መካድ አይታክተን:: እግዚአብሔር ወንድ መሆኑን ዘንግተው እንዴ በጨረቃው ሌላ ጊዜ በጨፈቃው ሲያምሉን ይኖራሉ::

"ልሂድ"

ቅጣት አንድ! ቅጣቱ ከጎዳኝ ቋሚ መቅጫ ይሆናል::

"ትሄጂ?" እቅ[illegible]:: "ሂጂ"

@OLDBOOKSPDF

"አልሄድም!" ሴላ መቅጫ ፍሊጋ፡፡

"ኡ-ሺ! ቴፑን አምጨፈና..."

"አልፈልግም! እንደውም እሰብረዋለሁ..."

"ጥሩ" ጠናጋሻው እንዲህ እያለ ይሆን እህቱን ያደብናት የነበረው? እቅፌ ውስጥ ተፍተለተለች፡፡ ድሮም እቅፋቴ አይመቻትም፡፡

"እንዲህ የምትሆነው ትምህርት ቤት ስለሄድኩ ነው?"

"አዎ" ለመገላገል፡፡ የፍቅር ግንኙነት ከስሜት መለዋወጥ አልፎ በቃል-ምልልስ ሲተካ ይታክተኛል፡፡

እቅፍ አድርጋ አንገቴ ላይ ሳመችኝ፡፡ ከንፈሯ ከመቼው ግሎ ከመቼው እንደሚቀዘቅዝ፣ የአንገትጌዋ መቋጠሪያ መቀነት ደረቴ ላይ አርፎ ቆረቆረኝ፡፡ ስፈታው እጄን ያዘችኝ፡፡

"ቆይ! በሩን ልዘጋው"

ይሄንን ከእውኑም ከህልሜም አላሰብኩትም ነበር፡፡ ጭንቅላቷን እስግጋ ውጭውን ከማተረች በኋላ ደጃፉን ሸጉራው መጣች፡፡ ጫማዋን መቼ አውልቃው አጥራ አገኘኋት? ቁልቁል እያየችኝ ዝም ብላ ቆመች፡፡

መቸኮሌን ልትሰልል ይሆን? ዝም!

ተንበርክካ የአንገትጌዋን ሪቫን እንድፈታ ጠጋ አለችልኝ፡፡ ምን የሚያስቸኩለኝ ነገር መጣ፡፡ አንዳች ነገር ይጉተጉተኝ ጀመር፡፡ ተፈጥሮ ተርቦ መብላት እና መሻት ኖሮ ማግኘት ላይ ነው የሰውን ልጅ ከነድክመቱ የምታገኘው፡፡ ጉርዷን ወደታች ስጎትት

"ትወደኛለህ?" አለችኝ

"በጣም"

"እንዴት?"

"እንደዚህ! አሁን እንደምሆነው?"

@OLDBOOKSPDF

ትንፋሽ የፀነሰ ሳቅ። "ቆይ፣ ይሄን እንኳን አታውቅም?" የጉርዷ ጎን ላይ፣ ሽንጧን ተንተርሶ ቁልቁል የወረደ ዚፕ ተረተረች።

እኔ የማውቀው የራሴ ዚፕ ያለበትን። ስከፍት እየተርበተበተች፣ የምትሆነው እያጣች…

"ወይኔ፣ ወይኔ ጉዴ፣ ወይኔ" አለች።

"ምነው?"

"ምንም"

"ይቅር?"

"አ-ይ፣ አይቅር"

አቅፌ እስሬ ከተትኳት። የውስጥ ሱሪዋን ዝቅ ሳደርግ…

"ወይኔ፣ ወይኔ ጉዴ፣ ጉዴ…"

"ይቅር?"

"አ-ይ"

እየሳምኩ አለዘብኳት። ቆይቼ ሰውነቷ ሲላላ ወደጭኗ ስጠጋ…

"ወይኔ፣ ወይኔ… ጉዴ…ጉዴ…"

"ጨቤ፣ አሮንጋ፣ ሾተል፣ ጦር፣ ለበቅ… ያወጣሁ እስኪመስለኝ ድረስ። ግን ደስ ይላል። እስሬ እየተቁነጠነጠች፦

"ወይኔ፣ ወይኔ ጉዴ፣ ጉዴ፣ ጉዴ…"

"ይቅር?"

"አይቅር"

"ወይኔ!"

ጨበ.

@OLDBOOKSPDF

"ወይኔ"

አሮንጋ

"ጉዴ"

ጦር

"ጉዴ"

ለበቅ... ጥብቅ!... ስንጥቅ!... ጥንቅቅ።

"ጉ--ዴ!" ፊቷን ወደግድግዳው መልሳ ተኛች። ወይም የተኛች መሰለች። በመሆኛው ሰዓት የምንሆነው የማን ሀፍረት ነው? የጥድፊያችን ባለቤት እርሱ ማነው? ከዚህስ አትራፊው ክፍል የቱ ነው?

ትከሻዋን ስቤ ወደእኔ ላዞራት ሞከርኩ። ከወገቧ በላይ ጥንክርክር አለችብኝ። የራሷን ክንድ ላይ ተደፍታ ዝም። ጥያቄዎቼስ?

"ታሰዩ"

"ወዩ ፈተናዩ"

ተቃውሞዋን በረጅም ትንፋሽ ገልፃ

"ዓይንህን ጨፍንልኝ በእናትህ"

"ለምን? ሰርፕራይዝ ልታደርጊኝ?"

"ኡፍ! ቀልድ አይደለም!"

"እ-ሺ፣ እሺ..."

"ጨፈንክ?"

"እም"

"ፕሮሚስ?"

"ፕሮሚስ"

@OLDBOOKSPDF

ስትንቀሳቀስ ተሰማኝ። ከአጠገቤ ተነሳች። ደጃፉ ተከፈተ፣ ወጣች፣ ሄደች።

ያስጨፈነችኝን ዓይኔን እንድገልፅ ሳትፈቅድልኝ ሄደች። የውስጥ ሱሪዬ ጠፋኝ። በተስፋ መቁረጥ ሱሪዬን በሴጣው ላደርግ ስል ሱሪዬ ውስጥ የውስጥ ሱሪዬን አገኘሁት።

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፲፯

የሰው ልጅ እንደሌሎቹ እንስሳት ሁሉ ለተፈጥሮ የሚያስገባው እሰራት ወሲብ እና ምግብ ነው። ስንጠግብና ስንረካ ተፈጥሮ ባለእዳነታችንን ከሥጋችን ላይ ታነሣለች። የሰውን ልጅ ሥርዓት መሠረት ያደረገው እምነት ደግሞ በልቶ መጥገብና ፍትወት ፈፅሞ መርገብ ነፍስን እንደማያሳርፍ ይለፍፋል። የነፍሴን ማገረፍና አለማረፍ ከእኔ በላይ ማን ያውቃል? ምክንያቱም ንጉሥ ዳዊት እንዳለው ህግህ በልቤ ውስጥ ነው።

ናትራ ሊሊት እጇን ብቻ ወደ ቤት ውስጥ አስገብታ የረድ ሠርዌ ጆንያ አጠገብ ቴፕሪከርዱን አስቀምጣ ሄደች። ቴፕሪከርደሩ በአንድ አይት እያፈጠጠ ሲያስደነግጠኝ ተነስቼ ፊቱን ወደግድግዳ መልሼው ተቀመጥኩ። ለምን ቴፕሪከርደሩ አንድ ዓይን ብቻ ኖረው? ሐሰተኛ መሲሁስ? ሁለት ዓይና ቢሆን እዝማናት ያጣቀሰ የዓይን ጨረሩን መቋቋም ስለማንችል ይሆን? የአንገቱ መሰለል? የጭንቅላቱ መሟለል፣ የቁመቱ መንቀዋለል... ምልክትነቱ ምንድነው?

ትናንት የሐሰተኛው መሲህ ድንኳን ከምን እንደደረሰ ለማረጋገጥ ወደ ጠንቋይ ማረፊያ ሄጄ ነበር። የሚያብረቀርቅ ነገር ባየሁ ቁጥር የድንኳኑ የወርቅ ጉልላት እየመሰለኝ ቆም እያልኩ ሳረጋግጥ ልደታን አልፌ ዙሪያ መንገዱን ቃኘሁ። ምንም የለም! ግን አንዳንድ ሴቶች "እረ ጉድ ነው?" እያሉ ወደ ጠንቋይ ማረፊያ ሲጓዙ ስላየሁ ተከተልኩ። መብረቅ ካሳረረው ዛፍ ጥቂት ፈቀቅ ብሎ እንዲት ግድግዳ ያልተማገረላት ሰቀላ አየሁ። አንዳንድ ሰዎች ሰቀላውን ሳይጠጉ ሁለትም ሦስትም ሆነው ቆመዋል።

"እረ ጉድ ነው" ለጊዜው ያገኘሁት መረጃ ነው። ከእኔ ፈቀቅ ብለው የቅስና ገዋና በረጅሙ የለቀቁ ሰው አየሁ። የምንኩስና ቆብ ሆነ ጥምጥም ጭንቅላታቸው ላይ ስላልደፉ ሉጫ ፀጉራቸው ያብረቀርቃል። ጠጋ ብዬ ጠየኳቸው።

"አባ፣ ምንድነው?"

@OLDBOOKSPDF

"ምን?" በሞጭሟጫ አይናቸው መልከት አደረጉኝ::

"ሰው፣ ሰቀላው፣ ማለቴ ከተማው ላይ..."

"እስዎ ምንድነዎት?"

ለእንዲህ ያለ ድንገተኛ ጥያቄ አልደናገጥም:: የዘወትር መልስ አለኝ::

"ጋዜጠኛ ነኝ"

"ጋዜጠኛ ከሆኑ ይኸውልዎ ምእመኑ ደጀ ሠላሙን ትቶ እዚህ ማንገርበብ ከጀመረ ቀናት ተቆጠሩ?"

"ለምን?"

ሞጭሟጫ አይናቸውን በሰፊው እጆታቸው ደባብሰው

"እዚህ አንድ አባት፣ ምን እንደታያቸው አይታወቅም የኮሸሽላ ጎጆ ቀልሰው ዘግተው ተቀምጠዋል:: እኔ እንደልደታ ገበዝነቴ ሄጄ ጠየኳቸው:: ዝም ብሉ እንባቸው ይፈሳል፣ ምን እናድርግልዎ? ብላቸው 'ለወገቤ መታጠቂያ ሰንሰለት፣ ለጀርባዬ ካገኛችሁ አለብላቢት ፈልጉ' አሉን:: እሱን ሰጥተን እያየናቸው ነው::"

"ከየት መጣሁ አሉ?"

"አዬ እሱን ማን ጠይቆ? እሳቸውስ መች መልሰው? በእት ለመዝጋት ከፈለጉ ብዙ መቃብር ቤት እኛ ዘንድ አለ፣ ብቻ እምቢ አሉ:: ያመጣንላቸውን ምግብም አይነኩም:: አንዳንዴ ትምቻማ ወዳፋቸው ይላሉ አሉ፣ ይሄንንም ሌላ ሰው ነው ያየው::"

"ጠንቋይ ማረፊያን ምን አስመረጣቸው?"

"እያወቅነው ይሄን እንጠይቃለን? ስሙን እራሱ ልብ ማለት ነው:: እስኪይተው:: ለእኛ ወደ ደጀ ሠላሙ ቢቀርቡልን ደግ ነበር:: እምቢኝ አሉ፣ ቢቸግረኝ እሳቸው በሰሩት የኮሸሽላ ጎጆ ላይ፣ በእናቴ ይሄንን የቆርቆሮ ሠቀላ አስበጀሁላቸው::"

"እንደው ምን አይነት ቁመና አላቸው?"

@OLDBOOKSPDF

"ድቅቅ ያሉ ባህታዊ ናቸው:: አዲስ የመነኩሉ ይመስሉኛል:: ለጀርባቸው መግረፊያ ለበቅ እንኳ አልያዙም፣ መሃርም የላቸው፣ መታጠቂያ ለንሰለትም እኛ ነን የሰጠናቸው:: ብቻ የታያቸውን ከመጠርጠር በላይ እርግጠኑን አልደረስንበትም::" የጨቀየ አይናቸውን ወደሆቀላው ጣል አድርገው አጨነቆሩ::

ይሄ ሁሉ የትንቢቱ አካል ነው? ከቤቱ መጥቼ ይሄን እንድሰማና እንዳይ ከላይ ተፅፏል? ወደ ጠንቋይ ማረፊያ የመጣሁበት ምክንያት የእኔ አልነበረም? ትንቢት ይፈፀም ዘንድ የተከናወነ የልዕለ ተፈጥሮ ሴራ ነበር? ከዚህ በኋላ ወደምን እንድነዳ ይፈለግ ይሆን? መጽሐፍ አጣቅሼ እንዲህ ነው የማልልበት ውጥንቅጥ ውስጥ ምን ከተተኝ?...

...ለመሰናጃ ጥቂት ጊዜ ብቻ ያለኝ ሆኖ ተሰማኝ::

"...የማይገለጥ የተከደነ፣ የማይታወቅም፣ የተሰወረ ምንም የለም:: ስለዚህ በጨለማ የምትናገሩት ሁሉ በብርሃን ይሰማል፣ በእልፍኝም ውስጥ በጆሮ የምትናገሩት በሰገነት ላይ ይሰበካል::" እንዳለ መሲሁ የልዕለ ኃይል ረቂቅነት በጭንቅላታችን ላይ ታንገርብባለች:: ሌት ቀን አትልም፤ ሁሌም ንቁ ናት:: እንግዲህ ከዚህ መሸሸጊያችን የት ናት? ወደኋላየ አየሁ፣ ምንም የለም:: ወደጎን እና ጎን ተመለከትኩ ከየካ ጫካ በስተቀር የሚታይ ነገር አጣሁ:: እዚህ ማጣቱ ውስጥ ግን እርሱ ተሸሽጎ አለ:: ለምናልባቱ ወደሰማይ አየሁ:: ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቁጣ ወደ እኛ ሲወርድ 'ሰማይና በውስጡ የምታድሩ ሆይ ደስ ይበላችሁ' መባሉ ተፅፏል:: ግን ሰማይም ደስ ያለው አይመስልም:: በውስጡ ያሉትም ቢያንስ በሰው ልጅ የማየት ችሎታ ውስጥ አልተከሰቱም:: 'ለምድርና ለባህር ወዮላችሁ' ስለተባለ ሰማይና በውስጡ የሚያድሩ ስለምን ደስ ይላቸዋል? በሰው ላይ መአት ሲዘንብ ደስ መሰኘት የጻድቅ ልብን ያመለክታል?

ሠፈሬ ስደርስ ልቤ ናትራ... ናትራ... ናትራ... አለች:: ናትራ አካባቢው ላይ የለችም:: ጃክ የናትራ የሆነውን ሁሉ ለመውረስ እንደፈለገ አይነት የሌሊት ሲጃራ ማጨሻ ግንዷ ሥር ተኝቷል:: እርግጠኛ እየሆንኩ የመጣሁት ነገር አንድ ቀን ጃክ አፍ ፈትቶ በብሉዝ መዝፈኛ ድምፅ አብሮት ያረጀ ታሪክ እንደሚነግረኝ ነው::

"ይኸውልህ እንዲህ ሆነ..." ቢለኝ እደነግጣለሁ? ጃክን አይናገር አይጋገር ብሎ ስንቱ ፀያፍ ታሪኩን እፊቱ እየጣለ አለፈ? ምናልባትም የማይፈታ ማኅተም ያለው የመልእክ መጽሐፍ የሚተዳው እንደ ጃክ በየመንደሩ ልብ ከማይባሉ ቃዘቢዎች ይሆን ይሆናል::

@OLDBOOKSPDF

ወደ ቤቴ ልገባ ስል።

"ተው አንተ ልጅ ተው! ገንዘብም ጡር አለው፣ በወር አራት ጊዜ ቤት ኪራይ ይከፈላል?" አሉኝ። ዘወር ብዬ አየኋቸው።

"እስኪ ደሞ ለፊትህም አዘንለት..."

ትቻቸው ወደውስጥ ዘለቅሁ። አንድ ቀንም የቤቴን ደፍ አልፈው አያውቁም። እንደገባሁ ፊቴን የምመለከትበት ነገር መፈለግ ጀመርኩ። የፊቴ አንድ ወገን ድልድል ብሎ ያበጠ መሰለኝ። ምንም የሚያንፀባርቅ ዕቃ የለኝም። ቴፑ ብቻ ፊቱን ወደግድግዳ እንደመለሰ እያብረቀረቀ ተቀምጧል። አንስቼ በመስተዋቱ በኩል ፊቴን ለመመልከት ስሞክር እውስጡ ካሴቱ እንዳለ አየሁ። ወደ ሶኬቱ ወስጄ ከፈትኩት። የናትሪ ብዙዬ በሚያስፈነጥዝ ዘፈኗ ተቀበለችኝ። እንደናትሪ እያነባሁ መሽከርከር አማረኝ። ናትራ ጡሿን ለእኔ ትታ ሄዳለች። ናፍቆት አፍተለተለኝ...

...እንግዲህ እንደናትራ የሊሊት ሲጃራ አጫሽ መሆኔ ነው። ጃከን ከግንዱ አካባቢ አባርሬ፣ ውርሴ የሆነውን ግንድ ተፈናጥጬ፣ ሲጃራዬን ለምጥጬ፣ ጋግርቷን ተጭኜ...

"ወይኔ፣ ወይኔ ጉዴ፣ ጉዶ..." ድግምት መደጋገም አይደለም? እኔም በሚደጋገሙ ሁለት ቃላት ተደገመብኝ መሰለኝ።

"ወይኔ" እና "ጉዴ"

"መቼም ወንድነትና ሳልካድ አልቀርም" እላለሁ። የተካጂዎችን ጦስ ከሔዋን ዘር ወደ አዳም ዘር አዞራለሁ።

ማጫወቻው እንዱን ዘፈን ሲጨርስ መለስ ብዬ ተመለከትኩት። ዘመኑ የአንድ ዐይናዎች መሆን አሰበት። በሥጋ ቴፕ ሪከርደሩ፣ በነፍስ ሐሰተኛው መሲህ። ኃይላቸው ተመጣጣኝ ሆኖብኛል። ናትራን ለመሸሽ ዘፈኑን አስቁሜ ወደ መጻሕፍት መደርደሪያዬ ኮተት ስል ሄድኩ። ሪድ ሠርዌ ስለቀድሞው ሐሰተኛ መሲህ የተዛፈ መኖሩን እንደነገረኝ ትዝ አለኝ። የአለቃ ተክለኢየሱስ ዋቅጅራ "የጎጃም ታሪክ" መጽሐፍ ቀድሞ ያነበብኩት ቢሆንም ሪድ ሠርዌ የነገረኝን ልብአላልኩም ነበርና ማፈላለግ ጀመርኩ። አንዳንዴ ፍለጋዬን የሚያደናቅፍ ውብት ያለው ትረካ ሳገኝ ሁለት ሦስት ገፅ አነባለሁ። በመጨረሻ በጥቂቱ የተዛፈውን የሐሳዊ መሲህ ታ[illegible]ሁት። እንዲህ ይላል፦

@OLDBOOKSPDF

"ደግሞ በአፄ ዘድንግል መንግሥት በአማራ በኩል ሐሳዊ መሲህ ተነሳ። እኔ ክርስቶስ ነኝ ብሎ እናቱም መርዓተ ወንጌል ትባላለች። ብዙ ሰው ይከተለው ነበር። 12 ሐዋርያት 72 አርድእት (ደቀመዛሙርት) 36 እንስት መረጠ።

«ንጉስ አፄ ዘድንግል በሰማ ጊዜ ጭፍራ ሰደደበት። አብረው የተሰበሰቡት ደቀ መዛሙርቱ ጭፍራውን ባዩ ጊዜ ተበተኑ። ብቻ እርሱ ተያዘ። አስረውም ለንጉሱ አመጡለት። ንጉሱ አፄ ዘድንግልም መረመረው። በምን ምክንያት ነው ክርስቶስ እኔ ነኝ ያልህ አለው። ሐሳዊ መሲህም "አዎን ክርስቶስ እኔ ነኝ። ከድንግል ማርያም የተወለድሁ፣ የሞትኩ፣ የተነሳሁ፣ ወደሠማይ ያረግሁ። አሁንም ደግሞ ከቤተ እስሓዛብ ከመርዓተ ወንጌል ተወለድሁ። ከቤተ እስራኤል ተወልዶ እኛን ባዕድ አደረገን አይበሉኝ ብዬ" አለው። ንጉሡም አፄ ዘድንግል ይህንን በሰማ ጊዜ ተደነቀ። እንዲዚህም አለ። 'ሰይጣን በሰው እያደረ ይጫወትብናል' ብሎ አንገቱን በሰይፍ ከለለው። ራሣውን አምራና ጅብ በላው። ደቀ መዛሙርቱ ግን ሞቱን በሰሙ ጊዜ ከየሸሹበት ተሰብስበው ይሰብኩና ያስተምሩ ጀመሩ። ከሙታን ተነሣ፣ አረገ አያሉ። ከዚህ በኋላ መሰዊያ ሠሩ፣ ቁርባንም አሳረጉ። ሥጋሁ ለክርስቶስ አምላክነ ዘነሥአ እመርዓተ ወንጌል እግዝእትነ ብለው አቀረቡ።»

እዚህ ትርክት ውስጥ የእኔን ሥፍራ ፈለኩ። አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ውስጥ? ሰባሁለቱ አርድእት ውስጥ?... ከዚያስ የሐሳዊ መሲሁ አመፅ በምድር፣ በአንድ ንጉስ ፊት የሚጠናቀቅ ነው? ወይስ እኔ እሱብ እንደነበረው ሰማይ እንደመጽሐፍ ተጠቅሎ እስኪያልፍ፣ ተራሮችና ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው እስኪወሰዱ ድረስ ባለ የመጨረሻ ሠልፍ የሚለይለት ነው? ከአፉቸው እሳት፣ ዲን እና ጢስ ከሚያወጡ የሰማይ ሰራዊቶች ጋር ነው? ወይስ በሩብ ገፅ በሚጠናቀቀው የምድር አሉሼ አሉሽ?...

እ! እ! እ!....

...ናትራ! ናትራ! ናትራ። ነፍሴን አስጨነኳት። አንገቱን በንጉሥ የተከለለው ሐሰተኛ መሲህ ትንቢቱ ያጣቅሰው ነበር? ይሄም

@OLDBOOKSPDF

የተነገረለት ሐሰተኛ ባይሆንስ? የእኔ አስተዋፅኦ እስኪያዝ መከተል፣ ሲያዝ መሸሽና፣ እንገቱን ሲቆረጥ መሠዊያ አዘጋጅቶ አረገ እያሉ ስጋወደሙ ማቅመስ ነው?... ዕጣ ፈንታዬ ያጨኝ ለዚህ ነው? ከሰው ልጅ ታሪክ ሁሉ በአስፀያፊነቱ የሚመዘገብ ሁነት ውስጥ ተሳታፊ ሆኜ መብነን? እንደትፋት፣ እንደሽንት የወደኩበትን ሥፍራ የማረክስና የማስፀየፍ ሆኜ መቅረት፣ ከማደጌ በፊት፣ ከመወለዴ በፊት፣ ከመፀነሴ በፊት የተደለደልኩበት የህይወት ትወና ይሄ ነው?

ኡ! ኡ! ኡ!...

...አእምሮዬን የሚያደነዝዝ ነገር ፈለኩ:: ጫት፣ ጭስ፣ መጠጥ.. ሌላም:: እንዳበደ ከቤት ወጣሁ:: ብር እንዳልያዝኩ ሳስታውስ ተመልሼ ዶክተር አሮን ካስቀመጠው ካርቱን ውስጥ ጥቂት ብሮች መዘዝኩ:: ካርቶኑ መጽሐፍም የተከተተበት ነው:: መጻሕፍቶቹን ርዕሳቸውን እንኳን ማየት አልፈለኩም:: ዶክተር ካነበበ በኋላ ስለሚያመጣልኝ በምርጫው ባልስማማ እንኳ በመጽሐፍቱ ጥሩነት አንድ ቀን ንባቤ ተደናቅፎ አያውቅም::

የቀበናን ጫት ተራ ለማሰስ እንደወጣሁ ናትራን ከወደ ጀርመን ድልድይ አቅጣጫ፣ በአሳቻ መንገድ ስትሄድ አየኋት:: እየሸሸችኝ እንደሆነ ቢገባኝም ተጣራሁ...

"ናትራ! ናትራ! ናትራ!..."

እግሯ ልቧን ተሸክሞ ሸመጠጠ - ለምን? ለምን? ለምን?...

...የልቤ ጥያቄ እግሬን ከሞት የምሸሽ ያህል አፈጠነው....

...ለምን? ለምን?... ለምን... ቀረብኳት... ደረስኩባት፤

ናትራ? ናትራ?...

"...ትልቅ ነህ፣ እንዳታየኝ ብዬህ ነበር:: አሁንም አትየኝ::" አለችኝ መንገድ መንገዷን እየተመለከተች::

እግሬ የልቤን ያልተሟላ መልስ ይዞ ወደኋላው አቀና:: ምን ማለት ነው? ምን ማለት ነው? ምን ማለት ነው?

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፲፯

እኩለ ሌሊት የናትራ ሲጃራ የሸተተኝ መስሎኝ ወጣሁ:: ግንዱ ላይ አልነበረችም:: ለምርቃናው ሙቀት ነፋሻው አየር መድህን ሆኖ አገኘሁት:: አክራዬ ሞተሩ እንደደከመ መኪና አስር ጊዜ እራሳቸውን እየቆሰቆሱ የተቆራረጠ ማንኮራፋት ያሰማሉ::

የግቢው ድንበር ላይ እንደቆምኩ አቀበቱን ማተርኩ:: ባለራዕዩ እንዳለው የሆነ መሰለኝ:: "በለስም በብርቱ ነፋስ ተናውጣ የቃሪያዋን ፍሬ እንደምትጥል የሰማይ ከዋክብትም ወደቁ::" እንዳው በትንብቢት አቀበት በወዳደቁ ከዋክብት ተኩሎ ተመለከትኩ:: ትዝ ሲለኝ ነገ ተክልዬ ስለሆነ ጧፍ ነጋዴዎች ሌሊቱን ቦታ ቦታ ይዘው ያድራሉ:: የጧፋን ሽታ ተንቀዋላዩ ነፍስ እያዘለ ለአፍንጫ ያደርሳል:: ከብቅ እንቅ በላይ እልፎ እልፎ ጫካው ውስጥ የወዳደቁ ኮከቦች ያበራሉ::

"ታለ! ታለ?..."

የሊሊ ድምፅ እንደሆነ ወዲያው ለየሁት:: ብስጭት ተሰማኝ:: በህይወት መንገዴ ላይ ነጦዬን ለማስፀየፍ ሆን ብላ የወደቀች ወቀሳ መስላ ታየችኝ:: ቀድመው ቦታ ቦታ ወደያዙት የኔብጤዎች ሄጄ መዝገፍ አወጣኋት:: በጧፍ ብርሃን እየታገዝኩ ስገመግማት ልጅ ከማዘሏ በስተቀር እንዳለፈው ጊዜ በድሪቶ አልተድበለበለችም?

"አይ! ለእናቴ ንግድ እንደምጀምር ስላልነገርኳት! ገንዘብ ከየት አመጣሁ ማለቱ ስለጨነቀኝ! ባለግሽ እንዳትለኝ ስለፈራሁ ወንድሜን አዝዬ ስልመና ወጣሁ! እዚህ አድርና ነገ ሳልለምን ወደ ቤቴ እሄዳለሁ..."

ዝም! ምን ይባላል? ምርቃናዬን እያቀጣጠለ ሙቀቴን ካባባሰው ንዴት ወጥቼ እጇን ይዤ ወደቤቴ ወሰድኳት::

"እዚህ አደሪና ነገ ትሄጃለሽ"

@OLDBOOKSPDF

መንታ ጭንቅላት እንደመሰለች ፀአዳ ጋቢ ያከናነበችው ወንድሟ...

...እናቷ የራሳቸውን ብልግና ትተው ይቺን ልጅ ከእጻ በገላገሏት፤ ጭራሽ የራሳቸውን ትተው እሷን እንዳትባልግ ብለው ይቆጣጠራሉ? ጉዝጓዙ ላይ ገረባ መካከል እንደተቀመጠች ትቻት ወጣሁ።

በሊሊ ፊንታ፣ እሷ ያየችውን ለማየት እዚህ መንገድ ዳር ማደር አስፕኝ። ጃክን በአይኔ ማተርኩት፣ ነፀብራቅ ካባረረችው በኋላ በኩርፊያ ቤቱን ዘወር ብሎ አላየም፤ ይሄ ሶልዳቶ...

...አቀበቱን ተያያዝኩት። የወደቀት ከዋክብት መንገዱ ላይ የከሰመች ብርሃን አንጥፈዋል። በየዛፎቹ መካከል፣ በቅጠሎች ሽውሽውታ የወደቀት ከዋክብት በእንቅልፍ ሰመመን ውስጥ ያሉ አስመስሏቸዋል። ብርሃናቸው ይስለመለማል። አንዳች ተፈጥሯዊ ትዕይንት ውስጥ እየተጓዝኩ ልደታ ግርጌ ድሬ ሠፈር ደረስኩ። ረድ ሠርዌ ትዝ ስላለኝ ወደ ሠቀላው የሚወስደውን አቋራጭ አቀበት ተያያዝኩት።

የወደቀት ከዋክብት የረድ ሠርዌን ሠቀላ በጥቂቱ ከበዋል። የቆመ ሰው አይታይም። ሁሉም ነጭ የተመለሰ አፈር መስለው ተኝተዋል። ወደ ሠቀላዋ ስቀርብ ከአፈር ክምሮቹ አንዱ

"ወዴት ነው?" አለኝ

"እዚህ"

"እዚህ የት?" ወደ ግራዬ ዞሬ ሳወራ ከበስተቀኜ መጣ። መንዳት ቢፈልግ ሳላየው ይጠቀልለኝ ነበር።

"እዚህ አባታችን..." ተንተባተብኩ።

"በዚህ ሰዓት?" እህል ውኃ የማያሰኝ ቆመጥ ይዟል።

"እንተዋወቃለን..."

"አትመስልም፣ ነጠላ እንኳ ትከሻህ ላይ ጣል ሳታደርግ..." ሌላኛው ከወደ ግራዬ ሌሊ ወረኛ።

@GEDBOOKSPDF

"ዘመድ ነን"

እልኩ አደጋ ላይ እንደወደቁ ተሰምቶኛል።

"የመነኩሰ ምን ዘመድ አለው?

የቆም ተስካር ያበላ ቀን መሞቱን ገንዘን እርማችንን እናወጣ የለም?" ሌላም ተጨመረ። ሽባ አድርገው ደብድበው ለእስጠባቂያቸው ሙያ መስራታቸውን ለማስመስከር የቸኮሉ ይመስላል።

"ተዉት" ከወደ ሰቀላው አንዳች ድምፅ መጣ።

"አባታችን?"

"ተዋቸው፣ ይግቡ"

"ከምን እንደገቡ፣ ምን እንደረገጡ ይታወቅና ፀሎት ቤት..."

"ይተዉዋቸው"

ቅር እየተሰኙ ለቀቁኝ። ሰቀላው ከቋሚ ውጭ ሳጋ አልተበጀለትም። መካከል ላይ ከጋን ትንሽ ከፍ የምትል ጎተራ መሰል ጎጆ አለች። ውስጧ በምንጣፍ ተንቆጥቁጧል። ጫማዬን ሳላወልቅ መግባቴ ስህተት ሆኖ ተናነቀኝ። ረድ ሠርዌ ወይባ ለብሶ የሰንሰለት መታጠቂያ ታጥቋል። ጀምብ ለበቅ አንድ ጥግ፣ በሌላው በኩል ማሪያም ልጇን ታቅፋ የሚያሳይ ምስል በብዙ የክብር ጨርቅ ተከቦ ተሰቅሏል። መግቢያው ገደማ የብረት ዘንግ ግድግዳ ተደግፏል። ግድግዳው ዙሪያውን የጥዋ ልብስ በመሰለ ጨርቅ ተሸፍኖ ጎጆዋ ከውጭና ከውስጥ ፍፁም የማትገናኝ ሆና ተሸከፋለች።

"ድሃው አልአዛር"

እጠራሩ ውጥረቱን ቀነሰልኝ።

"እነሆኝ ረድ ሠርዌ"

ፈገግ ሲል ቸንቹ ተሸኮርምማ ብቅ አለች።

"ከስንት ያምና ፀሎት በኋላ ትናንት ማታ እራሱን ገለጠ"

@OLDBOOKSPDF

"ማን?

"ፒንሙ"

"እርሱ ማነው?" መቀመጫ በአይኔ ማተርከ የለም:: ዛሬ ቆመን ማደራችን ነው::

"ፒንሙ አራተኛው የአጋንንት አለቃ ነው:: እንደዚያ በያምና በፀሎት እየተገላበጠ ሲቃጠል ያለእሱ ይሄን ያህል ቀን የሚችል ሌላ አጋንንት የለም:: ትናንት ማታ ግን 'ተቃጠልኩ' እያለ መጣ::

"'ለምን መጣህ?' አልኩ::

"'ለምን የምመጣ ይመስልሃል?' አለኝ::

"እኩል ማውራቱን ተውና የተጠየከውን መልስ' አልኩት::

"'ገርሞኝ እኮ ነው' አለ:: በወዳጅነት ልብ የሚያነሆልለው እንዲያ ጨዋታ በማለዘብ ነው::

"'ካልሆነ ከፀሎት ቤቱ ውጣ፤ አንተም በሚቻልህ እኔም በጀመርኩት' ስለው ተርበተበተ::

"'በእነ ሔኖስና በነቃይናን ዘመን እንዳደረኩት፣ አመጣጤ በጠላትነት ጌታዬ አስነስቶኝ ነው::

"'እኮ ተልዕኮህ ምንድነው?' ስለው

"እርኩስ ትምህርትን ማስፋፋት ነው፣ ጥንቆላ፣ ሟርት፣ ስመ አጋንንት እንዲጥፉ ማበረታታት ነው:: አንዳንዴ ጮኼ አስተምራለሁ:: ሳልጮህም ቀርቤ እንደባለቅኔ እያንሾካሾኩ ምስጢሩን ሁሉ በጆሮአቸውና በአይናቸው አጠግባቸዋለሁ:: ይሄንንም ብዙ ሊቆች ገልጠው ፅፈውብኛል:: ይሁንና ሰው ዝንጉ ነው:: በመጣሁ ቁጥር እንደ አዲስ ይቀበለኛል:: ታዲያ፣ ጠምና ጠሎቱን ይቀንሱልኛል?"

"'እሱማ እንዴት ይቀነሳል? ባይሆን ይጨመራል እንጂ' አልኩት:: 'የሚማልዱኝ አልካለሁ፣ እኔም ፍጡር ነኝ፣ ተቃጥለህ ኑር የሚለኝ የለም' እያለ እየወደቀ እየተነሳ ሄደ::"

ዝም፣ የፀጥታ @OLDBOOKSPDF አዘቅት ውስጥ ወደቅን::

ፔንመ ቁልቁል ከተንከባለለ ማረፊያው የእኔ ቤት መሆኗ ነው።

"ፔንመ የሐሰተኛው መሲህም መንገድ ጠራጊ ሆኖ ወደምድር እንደተላከ ገብቶኛል። እውነተኛዋን ትምህርት በሐሰተኛዋ መቀየጥ የእሱ ተልዕኮ ነው። እንክርዳድ ይዞ ይዞራል። ጥሩ ስንዴ ሲያገኝ ይበርዛል።"

በዚህ መካከል ከወደ ውጭ ድምፅ ተሰማ

"አባታችን ሌላ እንግዳ መጥቶ ካልገባሁ ይላል"

"መልሳት፣ መች አጣኂት?"

"ሦስተኛ ሌሊታቸው ነው። እንዴ ቢያናግሩኝ እያሉ ነው።"

"ፔንመ የከተማዋን ቆንጆ ለማስናከያ ልኳት ነው። መች አጣኂት?" አለኝ ወደእኔ ዞሮ።

"አልችልም"

"ደግ፣ ነገ ልሞክር እያሉ ነው"

"እንጃ፣ ከሆነልኝ" ብሎ ጆሮውን ወደውጭ እንደጣለ "እንበለ መከራ አይትረከብ ጸጋ" አለና "እርግጥ ነው፣ ያለመከራ ጸጋ፣ ያለድካም ዋጋ አይገኝም።"

"ባለፈው ቀን ሀሰተኛው መሲህ እኔጋ መጥቶ ነበር" አልኩ ድንገት

"ኖላዊ?"

"አዎ"

"ምን ፈለኩ አለ?"

"ምንም አላለም፣ መምጣቱን እወቁት ብሎኝ ሄደ።"

"ውሻ አጥንት እንዲማትር እሱም ነፍስ ወዳለው ሁሉ መቋመጡ ተፈጥሮው ነው። ጭፍራ፣ ጅሪ፣ ጀሌ፣ ጋሻጃግሬ፣ ደቀመዝሙር፣ አርድእት... ይፈልጋል። ጊዜው ስለደረሰ ጌትነቱ አጭር መሆኑን

@OLDBOOKSPDF

አውቋል። እኔንም እንነጋገር እያለ ይወተውታል። ይሄንን ፆም ፀሎት እንዳገባደድኩ አንድ ሌት መጥቼ ቤቱን አደግምበታለሁ። ግዴ አዘጋጅተህ ጠብቀኝ የተፀለየበትን እንረጫለን። አይዞህ፣ የመጨረሻው መፍጨርጨር ነው።"

በጠፈር ውስጥ በወደቁ ከዋክብት መካከል ግብኔን እያወዛወዝኩ ወደቤት መመለሴን ቀጠልኩ።

"ሁሉን በሚያውቁ፣ የፊቱን መጪውን በጎበኙ ትንቢት ተናጋሪዎች ይህቺ ቀን አልተፃፈች ይሆን? የትኛው ትልምና ግብ የእኛ ይሆን?"

ብቅ እንቅ ስደርስ ከበስተጓላዬ የሴት ድምፅ ሰማሁ። እንዲት የተከናነበች ሴት በወዳደቁ ከዋክብት መካከል ወደ እኔ ስትመጣ አየሁ። አጠገቤ ስትደርስ በሎልጯላው የጣፍ ብርሃን መልኳን አየሁት፣ አላውቃትም። ነጭ ቀለም የተቀቡ ጉቶዎች መስለው የተቀመጡት እጣን ሻጮች ተረጋግተው የተኙበት ቦታ እኔን ምን አስፈራኝ?

"ምን ነበር?"

ሐምራዊ ክንብንቧን ከላይዋ ላይ ገፍፋ በአንገቷ ሰላምታ ሰጠችኝ። አንገቷ በታላቅ ወርቅ ተንቆጥቁጧል። ንጥር ሽቱዋ ለመላው ቅንብቢት ሳይዳረስ አልቀረም።

"አባታችንጋ ጉዳይ ኖሮኝ ብመጣ ይኸው ሶስተኛ ቀኔ ስመላለስ። ከሩቅ ነው የምመጣው።"

"ምን ነበር ጉዳይሽ?" በተጨናበሰው ብርሃን ውስጥ እንካ. ፊቷ ኃይል አውጥቶ ሊረታ ይጣጣራል። ብስል ቀይ ናት። አንገቷና ሽንጧ የተመዘዘ ነው።

"እሱስ የምነግራቸው ለራሳቸው ነበር። ግንባር ለግንባር የሚያገናኘን በኖረና..." አይኖቿን አንከባለለችብኝ። ጋኔን ከአገር በመልክ መርጦ ለአሰናካይነት ያቀረባት እርሷ ናትና ማን ወንድ ይቋቋማታል?

"ጥብቅ ምስጢር ነው"

@OLDBOOKSPDF

ከጋኔን አለቃ ፔንሙ ጋር በምን ተዋውላ ይሆን? የሥምሪት ሪፖርት ታቀርብለት ይሆን? 'ዛሬ ሁነኛ ዘመዳቸውን አግኝቼ ግንባር ለግንባር ሊያገናኘኝ ቃሉን ሰጥቶኛል' ትለው ይሆን?

ፔንሙስ? ቀልደኛ ይሆን? 'አንቺስ ምን አደረግሽለት?'

እየተሽከረመመች "ገና ነው"

መንታ ጦር ይመስል በሁለት አቅጣጫ ገጥማ እየተቀበቀበች በምን ትቻል?

"ነገ ሌሊት ልሞክርልሽ፤ መቼም ዛሬ ተመልሼ አልሄድም"

"ኧረ ነገ ሌሊቱን ይደርሳል፤ ታዲያ እርስዎ ለለፉበት..."

ዝም! ሊሊ እቤት ባትኖር ይገርት ልሄድ ኖሯል? የታላቂቱን ጋለሞታ ከዝሙቷ ወይንጠጅ ከስከሩ ልቆጠር?

"ግዴለም፤ ከሆን በኋላ ይደርሳል?"

"አድባር ትስጥልኝ..."

"ለመሆኑ ስምሽ ማነው?" ስል ጠየኳት:: በዝሙት ወይን ጠጅ ሰዎችን ስካር ላይ የጣሉ የብሉይ ዘመን ሴቶች ስም አእምሮዬ ላይ አልደረደርልህ አሉኝ::

"ኤ-ል-ሳ-ቤ-ት" ቀስስ እያለ ስሟ ጆሮዬ ላይ ሲለፋደድ መደንገጥ መታኝ::

ኤልሳቤት

ኤልሳቤት

ኤልዛቤት

ቀድሜ ፊቱን ወደታች መለስኩ:: ከምድር መፈጠር በፊት የነበረ፣ ስም ይሄ ነው?

ቤት ስገባ ሊሊ ወንድሟን አዝላ ጉዝጓዜ ላይ ተኝታለች:: ከማዘል ትካት የምትገላገለው መቼ ነው?

@OLDBOOKSPDF

ልቡናዩ ወደፔንሙ ተወካይ ሸሸ።

ኢልሳቤጥ

ኢልሳቤጥ

ኢልሳቤል

ኢልሳቤል

ኢልዛቤል. . . . . . . . . .

ኢልዛቤል!!

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፲፰

አመንዝራዎች በታጠቡበት በሰማርያ ኩሬ ከኤልዛቤል ጋር ስንቦጫረቅ ብንን አልኩ:: ደስታዬ ስኃጢያት ምትክ እንደተሰጠ የበኸር ልጅ ጨከነብኝ:: ጉሮሮዬን ፈጥርቆ ከመግደሉ በፊት ተመንጭቂ ነቃሁ:: ይሄ ምልክትነቱ ምንድርነው? ለወትሮው ህይወት መሰከንተሪያዋ ወደፊት አልነበረምን? ስለምን የእኔ ህይወት ካለፈ ዘመንና ታሪካቸው ከተጠናቀቀ ሰዎች ጋር ተቆራኘ? ስለምንስ ህይወቴ ልመልሰው በማልችለው ጥያቄ ተሞላ?

Life is not a problem to be solved ያለው ማን ነበር? ህይወት ከመከፈቻዋ ጋር የተጣጣች ክርችም ጓጉንቸር አይደለችምን? ስለምን ፈላስፋው ህይወት ምላሽ የሚያስፈልጋት ጥያቄ አለመሆኗን ማወጅ ላይ አተኮረ?

"Life is not a problem...?"

አዎ... አስታወስኩ Soren Kierkegaard ነው:: ጠይቆ፣ ጠይቆ... ልቡ ላይ ምላሽ ሲያጣ Life is a reality to be experienced አለ:: ህይወት ልምድ የሚቀሰምባት ተጨባጭ ዕውነት ብቻ ብትሆን የእኔ ነገር ከተፈፀመ ዘመንና፣ ጊዜአቸውን ከጨረሱ ሰዎች ጋር ምን ያደርጋል? ሐሰተኛው መሲህ ከእኔና ከደጃፌ ጋር ምን አለው? ኤልዛቤል ስለምን እውነቴንና ህልሜን ኀበኘች?...

...ከዚህ በኋላ መምህርነቱ ቢቀጥል ነፍሴ ከስንት ፈላስፋ ጋር ተላትማ ትዘልቀው ነበር? አርስጣጣሊስ የተፈጥሮ ህግ መዛነፍና መቃረን ሳይኖርበት የሚካሄድ ሥርዓት እንደሆነ አላስተማረምን? የእኔን ህይወት ምን ከተፈጥሮ ህግ ውጭ አደረገው? ፈላስፋዎች ሁሉ ነገር የላቱ ናቸው:: ህይወት ከህግ ውጭ በከንቱ ውልደት ጀምራ በከንቱ ሞት የምትጠናቀቅ ከንቱ መናወዝ ብቻ ናት!

@OLDBOOKSPDF

...ካንት አመክንዮ (Reason) እና ተሞክሮ (Experience) ቀንደኛ ግብአቶች እንደሆኑ አልመሰከረም? እኔ ስለውቀትና እውነት ለየትኛው ዕውቀቴ እና ዕውነቴ ህይወት ውስጥ አመክንዮና ተሞክሮ ቅዱሳን መዘባበድ ከተጨባጭነት አገለገለኝ? ኑሮዬ በእርኩሳንና አልወጣም?

ወደ መጻሕፍቶቼ ማተርኩ። መጽሐፍቶቼ ያለሁበትን ሁኔታ ለመሸሽ የሚጠቅሙ አዙሪቶቼ ናቸው። ፍሮይድ መጻሕፍት ዕውነታን መሸሺያ መሣሪያዎች ናቸው ብሎ ያስባል፤ እውነትነት ሳይኖረው አይቀርም። ደራሲነት ደግሞ ከአፍ የወጣ አፋፍ አይነት፣ ሳንፈልግ የልቡናችንን የምንሰፈልፍበት ሙያ ነው። ተነስቼ መጻሕፍት መደርደሪያው ላይ አፈጠጥኩ። ወዲያው አንድ ነገር ተከሰተልኝ። አፈትጉሃን የናኤል "በኢየሱስ ላይ የሆነ ነገር ለመፃፍ ያሰብክ ትመስላለህ" ያለኝ እውነት ነው። እምነት እና የእምነት መሪዎች ላይ የተፃፉ መጽሐፍት ሳይበዙ አይቀርም። እስኪ... እስኪ...

"The Case for Christ" ጥሩ መጽሐፍ ነው። ኢየሱስን በተመለከተ የሚነሱ ጥያቄዎች ሁሉ ለመመለስ የተፃፈ ነው። በእርግጥ ኢየሱስ መስቀል ላይ ሞቷል? ለምን የመስቀል ላይ ቆይታዩ በሦስት ሰዓት ብቻ አበቃ? መስቀል ላይ ሆኖ "ተፈጸመ" ካለ በኋላ ጎኑን ሲወጉት ደምና ውኃ ለምን ወጣ? የልቡ ምት አልቆመም ነበር ማለት ነው? የኢየሱስ ህይወትና የአሕዛብ አማልክቶች ሁኔታ መገጣጠም እንዴት ይታያል?... ለሚሉ አጥጋቢ ምላሽ ይሰጣል። ደራሲው Lee Strobel ሌሎችም መጻሕፍት አሉት። እኔ ግን ይሄ በቅቶኛል።

ተቁነጠነጥኩ

"Jesus papers" የStrobel መጽሐፍ ሳይደርሰው በመቅረቱ መልስ የተሰጠባቸውን ጉዳዮች መልሶ እንዳዲስ የሚያነሳ ደራሲ የፃፈው ነው።

"The murder of christ" አነሳሁት። አጠገቡ "The life of Christ" አለ። እውነትም ኢየሱስን ለመታደግ ወይንም ለማጥቃት ሳላውቀው እየተዘጋጀሁ ነበር። "Jesus A new Vision" እና "Jesus in contemporary schoolarship" የተሰኙ ሁለት መጻሕፍት የፃፈው አንድ ደራሲ ነው። Marcus.J.Borg.

ይሄን ከመጽሐፍት ጋር መዘባበዴን የተድሞው አርታኢ ቢኖር ቆርጦ ይጥለው እን@OLDBOOKSPDF ነኝ። ሁኔታዬ ለእሱ መታበይ

ይመስላል:: ብልዝ ጥርሱን እያሳየ "አውጥቼዋለሁ" ይለኝ ነበር፣ ነፍሱን ይማረውና::

"God is not Great (How Religion poisons everything)" ይሄንን ያ የጋኤን አለቃ ፔንሙ እራሱ የጻፈው ሳይሆን አይቀርም:: ፔንሙ ቀለምና ክርታስ በእጁ ይዞ ርኩስ ትምህርቱን እየጻፈ መጽሐፍ አድርጎ ያሳየ አራተኛው የአጋንንት አለቃ ነው አሉ::

"Some mistekes of moses" የራሴን የመጽሐፍት ስብስብ እራሴ ፈራኋቸው:: የሆነ ቀን እነዚህን ስብስቦች የገመገመ ረድ ሠርዊ የስላቅ ሳቅ ሲያመልጠው አይቼ ነበር::

"ምነው?" ስል ጠየኩት::

"እንደውነው፣ ግና ልቡናን ማንቃት ይበልጣል"

"ከምንድነው ልቡናን ማንቃት የሚበልጠው?"

"ብዙ መጽሐፍት ከማንበብ::"

ሳልናደድ አልቀረሁም:: ቆይቶ

"እብዝና መጻሕፍት ያዘነግእ ልበ ይልብሃል" ጥቂት ቆይቶ ተረጎመው:: "መፃሕፍትን አብዝቶ ማንበብ ዝንጉነትን ያመጣል ሲል ነው:: በፆሙና ያገኘኸው ሐሳብ ነው ሀብት የሚሆን::"

የመደርደሪያው ታችኛው አግዳሚ ላይ አንድ የተጣጠፈ ወረቀት ተቀምጦ አገኘሁ:: አነሳሁት:: ስገልጠው የነፀብራቅ እጅ ፅሁፍ ተጋፈጠኝ:: መቼ መጥታ ነው? አነበብኩት::

"ታለስ፦

*ቤትህን ለውሻ፣ ለመሸባቸው እናትና ልጅ ትተህ የለህም:: Really its Awesome, anyways ለአስቸኳይ ጉዳይ ፈልጌህ ነበር:: ከቻልክ ነገ አምስት ሰዓት ላይ ግቢ እንገናኝ:: ድባብ እጠብቅሃለሁ::*

(ነፀብራቅ)

@OLDBOOKSPDF

የትኛውም ወንድ የየራሱን ኤልዛቤል በስቃይ ከግራ ጎኑ ይሻላል። ህይወቱ የኤልዛቤሉና የአማካሪዋ የአባቡ ነው፤ ኤልዛቤሉ ከአባቡ ጋር ከምታደርገው ምክክር ምን መደናቀፊያ እንደሚፈጠር የሚያውቅ ወንድ የለም። ስለምን የነቢዩ ኤልያስን መደናቀፊያ ሴት ለረድ ሠርዊ እና ለእኔ ማዳረስ አስፈለገ?...

ሔሮዲያዳ ለዮሐንስ መጥምቁ፣ ደሊላ ለሦምሦም፣ የጲጥፋራ ሚስት ለዮሴፍ መጥፊያ እንደሆኑ ሁሉ...

...ደጃፌን የሚያግደረድር እጅ በራፌ ላይ እንዳለ ሰማሁ። ጃኬ ኩርፊያው አልቀበት በሶልዳቶ ተንኮል ድንበር ሲገፋ መሰሉኝ ነበር።

ናትራ ናት፤

ቷ! ድንጋጤ

ናትራ! ናትራ! ናትራ!...

ዷ! ንዴት።

"ምን ፈልገሽ መጣሽ?" ለመጻሕፍት መደርደሪያው ትኩረቱን ሰጠሁ። እጄ ላይ የነፀብራቅ ደብዳቤ አለ፤ አጣጥፌ ያገኘሁበት ቦታ መለስኩት። ከበስተጀርባዬ እንቅስቃሴ አለ። ናትራ በሁኔታዬ ደንግጣ አልሄደችም ማለት ነው። ወዲያው መብራቱ ጠፋ። ከበስተጀርባዬ እቅፏቷ ተሰማኝ።

ጓ! የሆነ ነገሬ...

ጉንጧ ማጅር ግንዴ ላይ ተለጥፏል። በሽቶ ተጥለቅልቃለች። ነፀብራቅና ናትራ ተደበላለቁብኝ። ነፀብራቅን በሽቱ፣ ናትራን በተፈጥሮ ሽታ ነበር የምለያቸው። ጥላቻ በሚመስል ስሜት ሰውነቴ ሲሽማቀቅ ሰማሁ።

"ታለ? ታለ? ትናንት የሁለታችንም እዚህ ድረስ መጡ።"

"እነማን ናቸው የሁለታችንን?" ንግግሯ ሳንባዬን ድዝዝዝዝ... አደረገው።

"የእኔ መምህሬ! ... ጀዋ ያቺ፣ ፈልጋህ የመጣች የማትመስለው..."

@OLDBOOKSPDF

"እና?"

"እና የእኔ አግቢኝ አለኝ... እድሜ ላንተ አልኩ..."

"ጥሩ"

የድል ቀኔን እናክብር ልትለኝ ነው የመጣችው? ወይንስ ድኋን ለእኔም ልታካፍል?...

"እና..."

"ቆይ... እምቢ እንዳትለኝ፣ እሺ በለኝ መብራቱ እንደጠፋ አቀፈኝና ትንሽ አረፍ ብዬ እነግርሃለሁ::"

ዝም አልኳት::

ከጆርባዬ ዞራ መሬት እንደተዘረፈጥኩ ጭኔ ላይ ተቀመጠች::

"ታለ? ታለ? ታለ?... እሺ በለኝ፣ እሺ በለኝ..." አቀማመጧን ከጎን ወደፊት ለፊት አድርጋ ወገቤን በጭኖቿ ዋጠቻቸው::

ምን እያደረገችኝ ነው? ወዴት እየመራችኝ ነው? እንዴት እንድንዘልቅ ልታደርግ ነው?...

...አ! አንቺ የኔይቱ ኤልዛቤል ከጎኔ አጥንቴ አጥንት ነስተሽ... ሳቂ መጣ:: በቅጡ የተፀነሰ ስሜት...

...ወገቤ ላይ እንደተጠመጠመች ወደጉዝጓዜ ይዛት፣ በጨለማ ግርዶሽ፣ እውነትና ሀፍረትን ብርሃን ነስተን- በድክመታቸው ተጠቅመን...

"ወይኔ! ወይኔ! ጉዶ! ጉዶ..."

"ይቅር?"

"አይ-አይቅር!..."

ልቤ ዝቅ ካለችበት አንሰራርታ አቀበቱን ትያይዘዋለች::

"ቆይ! ወይኔ! ቆይ ጉዶ!"

@OLDBOOKSPDF

ደስ የሚል ነገር አለበት? ዝም ብዬ ማድመጥ ዝም!...

"እሺ ቆይ፣ ወይኔ ጉዴ፣ ቆይ... እሺ፣ እሺ አየር አጠረኝ..."

"ይቅር"

"አይቅር፣ ጉዴ! ጉዴ! ጉዴ!...ጉ..ዴ!... ጉ.. ዴ... ጉ... ዴ... ጉ..."

ፀጥ! ፀጥታ ውስጥ ስንት ያልተመዘገቡ ጥያቄዎች መልስ ያገኛሉ? ይሄንን ፀጥታ ለዘልአለም ማግኘት ይሆን ዕድቅ? እረፍት ያለበት ፀጥታ! እረፍት እና ፀጥታ እንደባልና ሚስት ቁልፍ ተቆላልፈው ማገናዘብ ለሌለበት ለተፈጥሮ ሕግ አሳልፈው ሰጥተውናል። እረፍትና ፀጥታን ለማግኘት ስንት ሌሊት ናትራን ቃበዝኩ?

ናትራ፣ ንጥር ሽቶዋን የተፈጥሮ ጠረኗ አሸንፎት ናኙ። ፊቷን ወደ ግድግዳው መልሳ ፀጥ ብላለች። እንደእኔ እረፍትና ፀጥታን እያጣጣመች ይሆን? ወይስ እንዳለፈው ሌሊት አይኔን አስጨፍናኝ ልትጠፋ? ዘልአለማዊ አዙሪት ውስጥ ገብቼ ይሆን? ናትራን ማግኘት... ናትራን ማጣት... ደግሞ ናትራን ማጣት... ደግሞ ናትራን ማግኘት...

"ታለ?"

"እ?" ዓይንህን ጨፍንና ልሂድ ልትል?...

"ወሬውን ልጨርስልህ?"

"ኡ-ሺ" ሸገገኝ? ከሴት ጋር በኩስታራ ወሬ መግባባት የሚከብደኝ ይመስለኛል። ከስሜት ቅብብል ያለፈ ትልም ያካተተ የሴት ልጅ ጨዋታ...

"መጣች"

"እሺ"

"ከታለ ጋር ልንጋባ ነው አለችኝ።"

"እ?"

"እሱም ቀድሞ መጥቶ እንጋባ አለኝ።"

@OLDBOOKSPDF

ዝም፣ የድል በዓል የሽንፈት በዓልም ውስጡ አለ ያለኝ ማን ነበር? ናትራ በህይወት አንድ እንዳሸነፈች ቆጥራ በሌላ መሸነፍ አፈ-ቷ ቆሟል።

"አንተም እኔም በፍቅር የተበደልን ጎረቤታም ወፎች ነን። እሱ የሚያገባኝ ሊጎዳኝ ነው። እሷም አንተን የምታገባህ ልትጎዳህ ነው።"

ወዴት፣ እንዴት እየወሰደችኝ ነው?

"ሁለቱንም እናግባቸው"

ዝም

"ታለዬ"

"ወዬ፣ ፈተናዬ?"

ዝም አለች፣ የሆነ ነገር ሳይገባት አልቀረም።

ዝም አልኩ፣ የሆነ ነገር ገባኝ...

ወጥታ ስትሄድ የበሩ ወጋገን የፈጠረው የቤቱ ደብዛዛ ብርሃን ሲጋረድ ታወቀኝ።

ቀላል ፈተና...

...ከአፍ ባልወጣ የሆድ ምላሽ ሁሌም እንዲህ መግባባት ቢኖር...

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፲፬

ከሼልፉ ሥር ካሉ መንትያ ባለመዝጊያ ሳጥኖች ውስጥ ከአንደኛው የተጣጠፉ ልብሶቼን አወጣሁ:: እምክ፣ እምክ ይሸታሉ:: የመጽሐፍት ሰው አይቶ እንዳይንቃኝና ልውሰድ እንዳይል የተዘጋጀ መደበቂያ ሳጥን ነበር:: ልብሶቼን እያራገፍኩ አልጋው ላይ አሰጣኋቸው:: ዲዛይን ያለው ሹራብ፣ ሰማያዊ ጨርቅ ሱሪ፣ ከውስጥ የሚለበስ ሸሚዝ...

ሌላኛውን ሳጥን ከፍቼ ካሉት ሦስት ጫማዎች ከሱሪዬ ጋር የሚመሳሰለውን ስኒ ጫማ መረጥኩ:: እንዲህ ያለ አለባበስ ግቢ ስሄድ የማዘወትረው ነበር:: መምህርነት በሁሉም ጠንቃቃ ያደርጋል:: ተማሪዎች ፊት ተዝረክርኮ መቆም የመማር ማስተማር ሂደቱን እንደሚጎዳ እሙን ነው::

ነፀብራቅ ለትላንት ወይም ለትላንት ወዲያ ከእኔ ጋር ቀጠሮ ይዛ ነበር:: መልክቱ በደረሰኝ ማግሥት የተቀጠርኩበት ሥፍራ መገኘት ለእኔ ኃላፊነቱን እንደመወጣት ነው:: በግዴለሽነት የሚያስተቸኝም እንዳልሆነ እምናለሁ::

ልብሶቼን በየተራ እያነሳሁ ወደአፍንጫዬ አስጠጋሁ:: እምክነቱ ልብሶቼን እንደጃክ ተጠግቶ ወደ ደባልነት ሳይሸጋገር አልቀረም:: እራግፌ መለባበስ ጀመርኩ:: ታክሲ ሳልይዝ በእግሬ እየተናፈስኩ ልብሶቼንም ማናፈስ ሳይኖርብኝ አይቀርም::

ከቤት ስወጣ አይኖቼ ጃክን ቃበዙ፣ የናትራ ግንድ እንደተሸናፈ በከለኛ ተንጋሎ ቀርቷል:: ወደመንገዱ ስገባ ድንገት ፊት ለፊቴ ሐምራዊ መጎናፀፊያ ጣል ያረገች ሴት ተጋፈጠችኝ:: ሽቶዋ የእጣን ጢስ ተደባልቆበት አካባቢውን ናኝቶታል:: ክንብንቧን ከላይዋ ላይ ገፍፋ በአንገቷ ሰላምታ ሰጠችኝ:: አንገቷና ጆሮዋ በወርቅ ተንቆጥቁጧል:: ጣትዋ ቀለበት፣ የእጅ አንጓ [illegible] ተገጥግጦበታል::

@OLDBOOKSPDF

"አስታወስከኝ?"

"ይመስለኛል" በወንድ ድክመት ላይ የተመሰረተ ውበት ተሰጥቷት እንደምን ትዘነጋለች?"

"የአባታችንን ነገር እንዴት አደረክልኝ? ሁለት ቀን አለፈው"

"ተመልሼ አልሄድኩም" አለቃዋ ፔንሙ በረድ ሠርዋ ፃም ፀሎት እንደጠንቋይ ማረፊያ ግንድ በቁሙ እየተቃጠለ ሁለት ቀን መጠበቁ በንዴት እንበልብሎት ኤልዛቤል ላይ ሳይጮህባት አልቀረም።

"ቃልህን'ኮ ሰጥተኸኝ ነበር" አይኖቿ ከቀን ብርሃን ጋር እየተፎካከሩ ያበራሉ። ክብ ፊቷ ላይ እንደ አልማዝ ፈርጥ ለውበት ሁነኛ ቦታ ላይ የተሰካ ዓይን...

"እንደምታውቂው ቦታው... ሰዎቹ..."

"አንተ ቤት ገብተን እናውራ?"

"ቀጠሮ..." ለከሸፈ ቀጠሮ ያነሳሳኝ ሆን ብሎ ፔንሙ ይሆን እንዴ?

"አልቆይም..."

የአይኖቿ ልመና ፈጥርቆ ያዘኝ። "እሺ" ብዬ ፊቴን መለስኩ። ከበስተኋላዬ መሆኗን ሳስብ...

...ቤት ገብቼ እራሴ የምቀመጥበት ነገር አጣሁ። ለካ ቤቴ ለጥሩ አሰባበስ አይሆንም? ወደ አልጋው ጠቆምኳት። ስትቀመጥ ፀሐይ አግኝቷቸው የማያውቁ ባቶቿ ተጋልጠው አንፀባረቁ። ጉዝጓዜ ላይ...

"ሠርዌን-ማለቴ አባታችንን ለምን ነበር የፈለግሽው? ማለቴ የፈለግሻቸው?..."

ሳቅ ስትል ሌላ ፈተና ከከንፈሮቿ ጀርባ አሸመቀ። የጥርሷ ግጥግጥ...

"አንተም አባታችን ትለዋለህ?"

"እንዴት? ማለቴ..."

@OLDBOOKSPDF

"ረድ ሠርዌ የሚለውን የሽሙጥ ቅጥያ አልረሳልኝ ያለው እሱ ብቻ ነው ብሎኝ ነበር"

"ተገናኝታችሁ ነበር እንዴ?"

"መመረቂያ ፅሁፌን ስሰራ እንገናኝ ነበር።"

ምንድነው? ግራ አጋባኝ፤ ቆንጆ ሴት ከመልኳ መመኪያነት ውጭ ብዙም በትምህርትና በንባብ የምትተጋ አይመስለኝም ነበር። ፔንሙ ከከተማው ሀሰሳ በኋላ እንደ አለላ የመዘዛት..."

"የምን መመረቂያ? ማለቴ..."

"የብሉይ ኪዳን ተዛራሪ ሴቶችን ከFeminist Theory አንፃር የተቸሁበት ወረቀት ነበር። ሠርዌ በጣም አግዞኛል"

"የትኛዎቹ ሴቶች!"

"አስቴር፣ ሩት፣ ደሊላ፣ ኤልዛቤል... ዲቦራ...እ..." ወደላይ ስታንጋጥጥ የአንገቷ ጌጦች ፊቴ ላይ ፈለቁ፣ የትኛውን ብርሃን አጥምደው ለቀቁብኝ? ነው ብርሃን ይታሰባሉ?

"እ... ኢያዔል..."

"ማናት እሷ?"

"የሔቤር ሚስት፣ መጽሐፈ መሳፍንት ታሪኳን የሚያወሳው በጥሩ ሥራ ነው። እኔ ግን ጭካኔዋ ነው የታየኝ"

"እንዴት?" ከሴቶች ጋር በዕውቀት ላይ ማውራት ከወንዶች ይለያል። ስሜት የተሞላ አይነት ይሆንና ግን ኮስታራ..."

"እንዴት? እኔ አላውቃትም"

"በእስራኤላውያንና በአሶር መካከል ጦርነት ተካሂዶ ነው። የእስራኤላውያኑ ኃይል እያየለ ስለመጣ የአሶር ወገን የሆነ ጦር መሪ... ስሙ ማን ነበር?... እ?..."

@OLDBOOKSPDF

ሥም ስትፈልግ እንጋጣ ለዚየስ የምትፀልይ የሴት አምላክ ውበት ይነበብባታል። ባላገኘችውና ለዘልአለም እንዲሁ በቀረች ስል አሰብኩ።

"እ-ዎ፣ ሲሳራ ይባላል። እና ሽሽቶ ኢያዔል ድንኳን ይደርሳል። አስገቢኝ፣ ሽሽጊኝ ሰውም ቢፈልገኝ በዚህ የለም በይ ብሎ ይለምናታል። እሺ ብላ ካስገባችው በኋላ የድንኳን ካስማ ነቅላ..."

ሲዘገንናት ሴላ ውበት፣ እንደዘገነናት በቀረና ዘልአለም ደስ ባለኝ...

"መዶሻ ይዛ በሲሳራ ጆሮ ውስጥ ካስማውን ትመታዋለች። ሲሣራ ከመሬት ጋር ይጣበቃል። ክፉ አይደለች? ጨካኝ! በዚህ ሥራዋ ግን ትፀድቃለች?...."

"በጥናት ነው ኤልዛቤል የሆነችው?" ስል አሰብኩ።

"የት ነው የምትሰሪው?" አሁን ይሄ ጥያቄ ለምን አስፈለገ?

"ትምህርት ቢሮ"

"ከትምህርት ቢሮ ነው ፔንሙ ይዞሽ የመጣው? የመንግሥት መዋቅርን ተቆጣጥሮታል በይኛ"

"እ?"

ያሰብኩ መስሎኝ ነበር።

"ማነው ይዞኝ የመጣው?"

ሚስጢሯ ተገለጠ ይሆን? በፔንሙ ተራዳኢነት ምን ታደርገኝ ይሆን? ይሄ ሁሉ ውበቷ ወደመጨረሻው አስቀያሚነት ይለወጥ ይሆን? ዘመኗን ሁሉ በውስጠ ታዋቂነት ያጠራቀመችው ዕድሜ እንዴ ይከመርባት ይሆን?"ተይው"

"አልተወውም" የሀሳብ ትንቅንቅ ያሰኛት ትመስላለች። የእጇ ሸዋሊያ ተቅጨለጨለ።

"እርሺው"

@OLDBOOKSPDF

"አልረሳውም"

ሳቅሁ

"ምን ያስቃል?"

"በራሴ ነው"

"እንዴት?"

"ይኸውልሽ፤ የመጀመሪያ ቀን ሳገኝሽ ማንን መስለሽኝ ነበር መሰለሽ?"

"ማንን?"

"መሳቅ የለም" ከእራሷ ጋር ከሴሰኑና ከዝሙቷ ወይን ጠጅ ከሰከሩ ወገን እንዴ ተፅፌአለሁና ነገሮች ከፍጥነታቸው በላይ እየፈጠኑ ሳይሆን አይቀርም።

"አልስቅም፣ ሙ...ት!" እጇን በአየር ላይ ለመሃላ አወናጨፈች።

"ኤልሳቤት ስትይኝ ኤልዛቤል ያልሽ ነበር የመሰለኝ። ከረድ ሠርዌ ጋር ስናወራ ፔንሙ የሚባል የአጋንንቶች አለቃ መሰናከል እየፈጠረ ነው ስላለ..." ምን አዘላበደኝ።

እንዳሰብኩት አልሳቀችም። አይኗን ጨፍና ጭንቅላቷን ወደኋላ ጋለል አደረገችና ቆየች።

ንግግሬ እንደቀልድ ካልታየላት አንዳች የተደበቀ ዕውነቷን ነክቼዋለሁ ማለት ነው።

"ዋናው አጋንንት ጓደኛህ ነው።"

"እ?"

"አ-ዎ፣ እሱ ነው አጋንንት። ይሄን ሁሉ የሚያደርገው ለምን እንደሆነ አውቀሃል? የሚከተሉት ሰዎች የፈጠረው? ብቻውም በፆም ፀሎት ሰበብ ዘግቶ የተቀመጠው? እ?"

"አላውቅም"

@OLDBOOKSPDF

"እኔን ሸሽት ነው:: ያደረገውን ሁሉ ብናገር የትኛው የሱ ተከታይ ያምናል? እ? እኔን ቀጥቅጠው አይገድሉኝም? ይገድሉኛል?"

ግንፍልፍል ያለ ንዴት ውስጥ ገባች:: ብዙ ምዕተ አመታት ተከድኖ የበሰለ ንዴት...

"ምንድነው? ማለቴ?..."

"ጓደኛህ ከእኔ ልጅ አለው፤ የሚሸሸው ይሄንን ነው:: ትምህርቱን የጨረስኩት አንድ ዓመት ዘግይቼ ነበር:: ጥናት እሰራለሁ ብዬ ሰራልኝ... አረገዝኩ:: ከእሱ ምንም አልፈልግም፤ ግን"

ይሄ የእሷ እውነት ነው? ወይስ የፔንሙ ከፆም ፀሎት ፍላት የማምለጪያ ደባ... በዚች ህይወት የትኛው ላይ እርግጠኛ መሆን ይቻላል? የትኛውን ተቀብሎ የትኛውን ገሸሽ ማድረግ ይቻላል?

"ሊክድ አይችልም፤ ቁርጥ እርሱን ነው... ግን እንደነገርኩህ እንዳትነግረው:: ከቻልክ አገናኘኝ፤ ካልቻልክ አንድ ቀን እንደበረርኩ እገባለታለሁ::"

የምለው ጠፋኝ...

"እንዳልከው 'ኤልዛቤል' እያለ የሚያስተዋውቀኝ በተከታዮቹ አስቀጥቅጦ ለማስገደል ነው:: ደሞ ያደርገዋል፤ ያደርገዋል..."

ሌላ ረድ ሠርዌ እያስተዋወቀችኝ ነው? ወይስ ምንድነው? በህይወት ሥም ቅዠት ነው የተሰጠን:: ቅዠት! መዳከር... የሚያባርረንን በቅጡ ሳናውቅ በሽምድምድ ሸሽት ልብ ማውለቅ...

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፯

ከዚህ አለም ደባ እና ትንግርት ጋር የሚያስተናንቀኝ ምንድነው? እዚህ ሠፈር፣ እዚህ ከተማ፣ እዚህ ሀገር የቀረኝ አለ? እሥሮ የያዘኝ ዝምድና ሆነ ሀብት አለኝ? ሌጣዬን እንደተወለድኩ አይደለሁምን? በጥቂት ጊዜ ልመና ከሚገኝ ነገር በላይ እዚህ ክፍል ውስጥ የተከማቸ ምን አለ? ...ከቻልኩ ሀገሩን፣ ካልቻልኩ ከተማውን፣ ካልሆነልኝ ደግሞ ሠፈሩን ጥዬ ለመኮብለል የሚከለክለኝ ምንድርነው? እንግዲህ ሐሰተኛውም፣ እውነተኛ ሐሰተኛ መሲህ ከሆነ እንደውሻ አነፍንፎ ይድረስብኝ:: ኤልዛቤልም በማያንቀላፋው ተንቀዥቃዥ ጌታዋ እየተጠቆመች ትምጣ:: ረድ ሠርዌም የእግዚአብሔር ሰው ከሆነ ሥራው በፈጣሪው የተከናወነለት ሰው ሆኖ ሳይለፋ በኮከቡ እየተመራ ያግኘኝ...

...ጥቂት መጻሕፍትና ዶክተር አሮን የተወልኝን ካርቱን ብቻ ይዤ ወጣሁ:: የጣሊያኑን የጃከን ትዝታ ሳላደምጥ፣ የብሉዝ መጫወቻ ድምፁን ሳያፍታታ ቅንብቢትን መልቀቂ ቅር አለኝ:: ጃክ ፓስታ ከበላ በኋላ በስተርጅና ወብርቶ ጥላ ፈልጎ መጋደሙን ትቶታል:: እንደጉብዝና ወራቱ በሴት ወደሚነሳ የከላባት ጦርነት ዘምቷል:: ናትራን የተሰናበትኳት ጉዝጓዜን ወደኋላ ትታ ከእኔ በራቀች ሴሊት ነበር::

"ሰላም ለኪ. ቅንብቢት፣ ቅንብቢት የየካ ተራራ ቤተ-መምኅፃን ሆይ! ሰላም ለኪ."

ረድ ሠርዌ እውስጤ ለሁለት ተሰንጥቋል:: የሚናፍቀውና የሚያስፈራው:: የሚያስፈራውን እርቆ የሚናፈቀውን ማግኘት ቢቻል...

"ሰላም ለኪ. መምኅፃን ቅንብቢት!!"

ወደኋላ ላለማየት እየተጠነቀቅሁ ቅንብቢትን ለቀቅሁ:: የቃበናን ሙት ወንዝ ስሻገር ልቤ ቅጥ ባጣ ሁኔታ ከፋኛ ይረግጥ ጀመር::

@OLDBOOKSPDF

ንጉሥ ሰሎሞን ሳሚ የቂድሮንን ፊፋ እንዳይሻገር ባስማለበት መንገድ ቃንቢትን ሳለመልቀቅ ቃሌን የሰጠሁት መንፈስ ይኖር ይሆን?

"ሰላም ለኪ ቀበና!"

በሳሚ ላይ ዳዊትና ልጁ ጠቢቡ ሰሎሞን እንደዶለቱት ያለ ቃል ጆሮዬ ላይ ቃጨለ።

"ያማልክቱን ንቆ የቀበናን ደፍ ተሻግሯልና ሽበቱንም ከደም ጋር ወደመቃብር አውርድ"

ሽበት አውጥቻለሁ ይሆን? ፊቱን በመስታወት ካየሁ እንደቆየሁ አስታወስሁ። ምን መስዬ ይሆን? በፀጉሮቼ መካከል የተንጨፈረሩ አንዳንድ ሽበቶች ብቅ፣ ብቅ ብለው ይሆን? እራሴን ከዘመናት በኋላ እንደ አዲስ ስተዋወቅ ምን ይሰማኝ ይሆን?...

...የመኪና ጡሩንባ ተደጋግሞ ሲያናፋ ከሀሳቤ ባነንኩ። ነፀብራቅ መኪና ውስጥ ሆና እጇን ነቅነቀችልኝ። ቆሚ ስመለከታት የተቃራኒ አቅጣጫዋን ቀይራ የኔን አንዓር ያዘች።

"ግባ"

ገባሁ ሽቶዋ...

"ወዴት ነው?"

"ወደየትም" አፍንጫዬን ኮልኩሎ መንፈሴን አነቃው-ሽቶዋ...

"ዝም ብለህ ነው ዕቃህን ቀርቅበህ ከቤት የወጣኸው?"

ዘወር ብዬ አየኋት፣ ፀጉሯን በአጭሩ ተቆርጣ ቀይ ቀለም ተቀብታዋለች። ፊቷ ላይ ደርበብ ያለ ደም መሳይ መንፈስ እንደ አይነርግብ ተጋርዷል። ዲያብሎስ በስምያን ልጅ በአስቆሮቱ ይሁዳ ልብ እድሮ አሳልፎ እንዲሰጥ አሳብ እንደገባበት ሁሉ በነፀብራቅም እንዲሁ ለማድረግ ምን...? ካልሆነ፣ የመንፈስ ምሪት ከሌለ፣ በዚህ ሰዓት እዚህ እንድትጠብቀኝ እንዴት ሆነ?

"ክላስ የለሽም?"

@OLDBOOKSPDF

"ዝም ብዬ፣ አሳይመንት ሰጥቼ ተማሪዎቼን ሳይብሪሪ ላኳቸውና መጣሁ..."

ጥርጣሬ፣ እንዴት...

"ወዴት እንደምትሄድ አልነገርከኝም?"

ዝም፣ የምሸሸው ከእሷም ጭምር አልነበረም?

"ምንድነው በካርቱን የቀረቀብከው?"

"መጽሐፍ"

"ቤት እየቀየርክ? አይደል? እኔን እየሸሽህ?.. አይደል? Really its Awesome!"

ዝም! የወንድና የሴት ግንኙነት ወደ ጭቅጭቅ የሚያመራበት ቦታ፣ ጊዜ፣ የሙቀት መጠን... መጠናት አልነበረበትም?

"እሺ ወደየት መሸሽ ነው የፈለከው? ሳድርስህ..."

ዝም

"ለካ እየሸሸኸኝ ነው? አይደል እንዴ? መሸሻህን ካወኩብህ ምን ሸሸኸኝ? ግን ምን እየሆንክ ነው? ምን እየሆንኩ ነው ልበል እንጃ..."

ዝም፣

መኪናዋን የንዴቷ ተካፋይ አደረገች። እግሯን በተራ በተራ እየረጋገጠችበት አስፈነጠረች። ሠፈር፣ ከተማ፣ አገር... ሳይሆን ዓለምን ለመልቀቅ ነበር ከቤቴ የወጣሁት፣ የቅንብቢት ኑሮ ሳይሆን ህይወት እራሷ ኖራለች የቸከችኝ።

"እግርሽ እንዲህ ያምር ነበር ግን?" ስል ጠየኳት።

"Really? በዚህ ሰዓት የታየህ የእግሬ ውበት ነው? እየሞትን እንደሆን አልታየህም? አብረን እየሞትን ነው።"

ከመፍራት ይልቅ አልሀ መጣብኝ፤

"እብሮ ከመኖር ይሻላል"

@OLDBOOKSPDF

"እ?"

"አዎ፣ አብረን ከምንኖር አብረን መሞታችን ስቃይ ይቀንሳል"

መኪናዋን አበረደችና ጥግ ይዛ አቆመች:: የጃንሜዳ ሽንጣም ጎዳና ላይ እንዳለን ገባኝ:: ጥቂት በእነዳዷ ብትቀጥል ኖሮ አንበሳ ግቢን ጥሰን፣ የአንበሳውን ፍርግርግ ገልብጠን የአንበሳ ጥሩ ምሳ እንሆን ነበር:: ጥሩ! አንድ ሀንዳዊ የሃይማኖት አባት ያለው ትክክል ሆኖ ተሰምቶኛል:: የሰው ልጅ ብቻ ነው ከተፈጥሮ የመብላት መበላት ህግ ውጭ ሲሞት ሥጋውን የሚቀብረው:: ማሀቪራ ይባላል:: እሱ በመሰረተው በጃይኒዝም እምነት ሰው ሲሞት አይቀበርም፣ አይቃጠልም:: ምኑንም፣ ምኑንም በልቶ እንደኖረ የተፈጥሮ ዕዋውን ያወጣል:: አስከሬኑ እየተመተረ ለጥንብ አንሳ ይሰጣል:: ከጥንብ አንሳ ጋር ተዋሀዶ ይቆይና ወደሌላ ሥጋ በል ይተላለፋል እንዲህ... እንዲህ የመብላት ዕዳውን በመክፈል ዘልአለም ሲሰለቅ ይኖራል::

ነፀብራቅ መሪውን ለቃ ፊቷን ሙሉ በሙሉ ወደ እኔ አዙራለች:: ይሄ ሁሉ ቁጣ የት ነበር?

"ጥቂት በመንዳትሽ ብትቀጥዪ ኖሮ ዛሬ አዳራችን አንበሳ ሆድ ውስጥ ነበር:: ተቃቅፈን፣ አየሽው አንበሳ ግቢን?" ማስዘብ ፈለኩ::

"እሆሆሆሆይ! ምን ጉድ ነህ ግን? Really its Aweful!" አለች::

"እኔ ግን ከንስር ይልቅ ፈጣን፣ ከአንበሳም ይልቅ ብርቱ ነኝና እንደ ሶምሶም አንበሳውን እሰብራለሁ::"

"እሆሆሆሆይ!"

ይቺ እሆሆሆይ የመሀይማኑ እህቶቼም ነበረች:: እሆሆይ ምሁርና ጨዋ በአንድ ላይ የሚኖሩበት የጋራ አጋኖ ሥፍራ ናት::

"እ? ምን አልሽ?"

"ስለምኑ?"

"ስለንስርነቴ፣ ከአንበሳ ስለመላቁ" ደረቴን ነፋሁ::

"ፅኑዕ ልቡም እንደ አንበሳ ልብ የሆነው ፈዕሞ ይቀልጣል::" አለችና የመኪናውን ሞተር ቀሰቀሰች::

@OLDBOOKSPDF

ማለዘቢያዬን ለመምቻነት ተጠቀመችበት:: ልቤ ፈፅሞ እስኪቀልጥ እንደምትጠብቅ አውቃለሁ:: ነፀብራቅ የግቢው ዓይን ነች:: መምህር ከነተማሪው የሚቃብዝላት:: ወደ ሥነ ልቦና አማካሪዎች ከሚሄዱ ወንድ ተማሪዎች ግማሹ ነፀብራቅን አፈቀርን የሚሉ እንደሆኑም አውቃለሁ:: ግን ይሄ ለእኔ ምኔ ነው? አንድ ሰሞን መግቢያና መውጫያዋ ላይ በስልክ እንጨት ስልት ተተክልኩ:: በቃ! እሷም ለሰውነቴ ሳይሆን ለቅምጥነቴ ነበር ልዩ ትኩረት የምትሰጠው:: ሌሎች ላይ ፈፅማ ለመኩራቷ የእኔም አስተዋፅኦ አለበት::

"ምሳ እንብላ?"

"ከዛስ?"

"ከዛ የት?"

"እውቶቡስ ተራ ትወስጂኛለሽ"

"ለምን?"

"አንድ ጓደኛ አለኝ! ቤቱ እዛ ነው..."

"እና? እዚያ አሳድረኝ ለማለት ነው ቤትህን የለቀከው? ሰውኮ አንድ ቀን ቢያሳድርህ ሁለተኛ አይደግምም"

አዘንኩ! አዘንኩ እየተጫወተች ነው:: እንደ ፀጉሯ የተቅላላ ንዴት ውስጥ እንደሆነች ያስታውቃል::

"የምሄደው ብር ልሰጠው ነው::"

"የምን ብር?"

"ዶክተር አሮን እኔጋ አስቀምጧል! ለተቸገሩ ጋዜጠኞች..."

"አንተ ብቻ ነህ የተቸገርከው:: ብዙዎቹ ወይ እስር ቤት ናቸው! የቀሩትም የፈረንጅ እግር ሥር ተነጥፈው..."

"ቢሆንም! አልቸገረኝም አልፈልግም ማለት ያለበት እሱ ነው::"

"እስኪ ጅል አትሁን! ገንዘብ እንክርፍፈህ ስትሄድለት አልፈልግም የሚል አለ? Really?"

@OLDBOOKSPDF

ዝም

"ማነው ስመሆኑ?"

"ሙሴ ፀሊም ይባላል" ለሙሴ ፀሊም በጥላቻ ሳልሰጠው ቀርቼ መንፈሴን ከማጉደፍ እራሴን መከላከል እፈልጋለሁ:: በዚህ ላይ ከቻልኩ ከተማዋን ስለቅ ሳልከውን የቀረሁት አደራ እንዲኖር አልሻም::"

"አውቀዋለሁ፣ እሱ ተርፎት ለሴቶች አንዳንድ ነገር ሲገዛ የሚውል አይደለም እንዴ?"

"አውቃለሁ "ላዳ" ታክሲ አለኝ ብሏል ግን..."

"እኔን "ላዳ" ያድርገኝ 'እንትን፣ ምንድነው እሱ'ቴ...አይደለም እንዴ..."

"ስለማንም ምንም ነገር ካንቺ መስማት አልፈልግም:: ደግሞ'ኮ ተራ ነገር ላይ ማተኮር የምሁር ዘርፍ አይመስለኝም::"

"Really its Awesome!"

ለኩርፊያ አንድ ጋት የቀረው ኩም ያለ ዝምታ ውስጥ ገባን:: ይሻላል::

* * *

ትዳር የገደለው ፍቅር አጋድመን የእንባ ማድረቂያ ምላ በላን:: ሳንጋባ መጋባት በየትኛው ቀዳዳ ሰርጎ ገባ? የቡራኬ ቁራሽ አልሰጠኂትም እንጂ ቁርጥ ትዳር፣ ያውም ወልዶ፣ ወልዶ የደከመው ትዳር... በእንዲህ አይነት ትዳር ሳለመድከም አባቴን ሆኖ መፈጠር ይገባል:: እሱም ቢሆን በአገር ፀብ እየገባ ስልቹነት ውስጥ የሚከተውን ትዳር ነክ ድግግሞሽ ሲያናጥብ ስለኖረ ይሆናል...

"የት አልከኝ?" ጠፍቷት ሳይሆን ሐሳቤን ቀይሬ እንደሆን ለማረጋገጥ ይመስላል::

"አውቶቡስ ተራ"

@OLDBOOKSPDF

ወሬ የሚሸመውት እፏ እና አይኖቿ ፈንግል እንደገባባቸው ጫጩቶች ፀጥ ብለዋል፡፡ ፀጥ ያሉት እግሮቿና እጆቿም ጭምር ናቸው፡፡

"ታለ?"

"እ?" ደሞ ፍቅር ለምተብት ትዳር ወይዬ ልበል?

"ካንተ ጋር አግኝተነው አብረን እንመለስ?"

ዘወር ብዬ አየኋት ከንፈሯና አይኖቿ ለወሬ ሽሚያ ተነቃቅተዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከእሷ ባህርይ ጋር የማይሄዱ ጥያቄና ምላሾች አሏት፡፡ የሚርበደበዱላት የግቢው ልዑካን ተሰባስበው ይሄን ጥያቄዋን ቢሰሙ ተፈጥሮ ውሏን የሳተች ባይመስላቸው አይቀርም፡፡

"እሺ አልክ?"

"እድርሰሽኝ ትመለሻለሽ እኔ እመጣለሁ"

"እ-ሺ፣ እዛው አካባቢ ልጠብቅህና ስትጨርስ አብረን እንመለሳለን፡፡"

"ይጨንቀኛል፣ ተረጋግቼ መቀመጥ አልችልም፡፡"

"ላንተ'ኮ ስል ነው ተማሪዎቼን..."

"እንደ ትልቅ ውለታ አትደጋግሚው" ቀስ በቀስ መብቶቿና የበላይነቷ እየተኮረኮመ፣ በመጠን እየተሸማቀቀ ሲሄድ ይታወቀኛል፡፡ ዛሬ ይፈራል መስሏት የመጨረሻ አማራጯን በአብሮ መሞት...

"እሺ በለኝና ለእኔ ውለታ ዋልልኝ"

በእኔ ጥንካሬ ነው ከተለማማጮቿ ጋር ያልተሰለፍኩት? አይደለም! በድክመቴ ነው፡፡ ለምንም ነገር የምሰጠው ትኩረት ዕድሜው የአጭር አጭር፣ አጭር ነው፡፡ ይሄ ደሞ እሷን እልህ አጋብቷታል፡፡ መውደዷን ማሳየቷ ለእኔ እንደ ድል እያከበርኩ የማጣጥመው ሳይሆን ህይወቴን በመከራ የሚሞላ ድግግሞሽ የሚሆንብኝ ነው፡፡ አሰቃይቶ መሰቃየት ይሆንብኛል፡፡

@OLDBOOKSPDF

"ሰቃዮቼን ይዘሽ ተመለሽ፤ እኔ ጉዳዩን እንደጨረስኩ ተሳፍሬ እመጣለሁ::" ወፍራም ፈሳሽ በሚመስል መሰልቸት ውስጥ ሰጥሜ ዋኘቼ ለመውጣት እቸገራለሁ:: ወይ መተንፈስ አለመቻሌ አይገድለኝ ነገር...

"ምንም አይነት ሰቃ ያንተ መያዣ እንደማይሆን አውቃለሁ፤ ተደብቀኸኝ ስትጠፋ'ኮ ነው የደረስኩብህ? ዛሬ ከተለያየን መቼም ቢሆን እንደማላገኝህ መንፈሴ ነግሮኛል፤ መቼም!"

ስለነፀብራቅ የሚፅፍ ሰው ካለ እርሱ ሁልጊዜም ተወቃሽ ይሆናል:: የእሷ የሆኑና የእሷ ያልሆኑ ባህርያት ተደልድለው በኑሮዋ ውስጥ አይከሰቱም:: ልታደርጋቸውና ልትናገራቸው የሚገቡ ነገሮች ጉራማይሌነት ይበዛቸዋል:: በዚች ሰዓት ቁጣም ሆነ ልምምጥ ሁለቱም በነፀብራቅ ዘንድ ውጤት እንደማያመጡ ይሰማኛል::

"እሺ፤ እንደራደር"

"ምን? በምን እንደራደር"

"እንቺ ጋ እመጣለሁ፤ የተወሰነ ጊዜ ብቻዬን መሆን እፈልጋለሁ:: እንኳን ሰው እግዚአብሔር ቢፈልገኝ እንኳን አታገናኚኝም፤ እንደውም አንቺ ጋ መኖሬ በፍፁም መታወቅ የለበትም::"

በፍተሻ አየችኝ

"እ? እንስማማለን?"

"ታሰዬ"

"ወዬ፤ ፈተናዬ" አመለጠኝ::

"የምን ፈተና አመጣህ? ፈተንኩህ? Really? So shameful, Any ways ምን የሚበላ ነገር ሰርቼ ልጠብቅህ? አብረን እራት... ካልፈለክም ክፍልህን አዘጋጅቼልህ... ካልፈለክም ቁልፉን... ካልፈለክም..."

ጥርሷ እስከገባ እንደምግቧ በማንኪያዋ እየኮረኮረች የምታስቀኝ፤ ከእሷ ፈፅሞ የማይገኘውን ነፃነት እያሳየች...." የበቂዋን ያህል ነፍሴን

@OLDBOOKSPDF

ኮድኩዳ፣ እንዳልገባችኝ፣ ካልጨለመ የማልታቀፍ ዕዩፍ እንዳላደረገች አሁን ምን ይሁን ትላለች?

"ታለ? ሳስብ ነው ያደርኩት፣ የሆነ መጥፎ ነገር feel አድርጌአለሁ። ለዚህ ነው ሁሉንም ጥዬ ወዳንተ የመጣሁት። ባልወድህ እንደዛ ይሆናል? እ? ይሆናል? እ?..."

ከንፈሯና አይኖቿ በነገር ሲተባበሯት አፈራችዋለሁ።

"እሺ?"

"እዎ"

"Really?"

"definitely!"

የቀን አሳሳሟን አልተወችም። አቅፋ ጀርባዬን እያሻሸች ጆሮዬ ውስጥ የመሳም ድምፅ ከተተች። ሊፒስቲኳ እንዳይበላሽ ነው እንዳልል ምሳ ስንበላ በሶፍት ጠርጋ ጥላዋለች... በሶፍት የተጠረገ ሊፒስቲክ ወደተጣለበት ተዙሮ ይፈለጋል? እንዲያ እየሆነ ነው አሁን...

...እዚህ ዓለም ላይ አይሆንም ተብሎ በእርግጠኝነት የሚደመደመው ነገር የቱ ነው? ነፍሴ አፈከፈከች። በጥፍር ተሮቶ በማረሻ ቢታረስ የማይዘለቅ ጭንጫ ደረመን ነፍሴ ላይ ፈሰሷል።

@OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ፳፩

አውቶቡስ ተራ አንድ ድንቅ ነገር ሆነ፤ የከተማ አውቶቡስ ሊወጣብኝ ለጥቂት ሳተኝ:: መጀመሪያ ደነገጥኩ፣ ቀጥሎ ከመጻሐፉ ጋር አጣቀስኩ:: ነብዩ ዮናስ ከዕጣፈንታው ሲሸሽ አይደል ዓሣ ነባሪ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀን እንዲቆይ የተደረገው? እኔም ምናልባትም ከተልዕኮዬ ስላፈገፈኩ ይሆናል የከተማ ዓሣ ነባሪ ሊውጠኝ የነበረው::

የከተማው ዓሣ ነባሪ የብዙ ሰዎችን ትኩረት ወደእኔ ስቦ ሄደ::

"ወንድሜ አይተህ ሂድ እንጂ"

"ፍሬንድ፣ እየተጠነቀቅክ"

"ልጁ ሀሳብ ጎዳና ላይ፣ ሀሳብ እንደሁ አያልቅ..."

"ፍሬንድ" ያለኝን ጥቁር ልጅ ጠርቼ ጠየኩት::

"ሙሴ የሚባል ጋዜጠኛ? እዚህ አውቶቡስ ተራ? ላዳ ታክሲ ያለው? ቆይ እስቲ?..." አጠገባችን ወዳለ ሙዚቃ ቤት ሄዶ ጠይቆ መጣ:: ፊቱ ላይ የሽሙጥ ሳቅ ያነበብኩ መሰለኝ::

"ሙሴ የሚባል ጋዜጠኛ እዛ፣ ከአውቶቡስ መናኸሪያው ጀርባ አለ! ና ላሳይህ"

"ከዓሣ ነባሪው መናኸሪያ ጀርባ" አልኩ በሆዴ! ቀደመ ተከተልኩ... ፊት ፊቴ እያለ ያወራ ጀመር::

"ሙሴ ዘመድህ ነው?"

"አይደለም፣ አብረን እንሰራ ነበር?"

"እሱጋ ልትኖርነው የመጣኸው?"

"አይደለም" ህይወት እውስጡ አርራለች

"ከሆነ አንድ ምስጢር ልነግርህ ነው"

@OLDBOOKSPDF

ይሄ አራራ ምን ያስቀባጥረዋል? አልኩ በሆዴ። "የምን ምስጢር?"

"እዚህ አውቶብስ ተራ "ላዳ" ማለት ታክሲ ሳይሆን..." ዓይኖቹ እንደ ሐሰተኛው መሲህ የተቅላሉ ናቸው

"እ?"

"ትናንሽ የሽሌ ቤቶች አሉ፣ የሚከራዩ..."

"እና?" ጠባብ አፉ ምን መጥፎ ነገር ሊተፋ ይሆን?

"እነሱን ነው "ላዳ" የሚሏቸው። ጓደኛህ አልጋውን ለሴተኛ አዳሪ ለቆ ቆጥ ላይ እያደረ..."

ቆምኩ። ጅማት የሚሸመቅቅ ምስጢር ሰምቼ... "እርግጠኛ ነህ?"

"አዎ"

እንደቆምኩ ቀረሁ...

"ጓደኛህ እንደውም በቀን አይደለም የሚያከራየው፣ በተደፋ ነው የሚቆጥረው..."

"በተደፋ ምንድነው?" የሆነ ነገር ቅልብሽ ሊለኝ ደረቴ ላይ መሯሯጥ ጀመረ።

"ፍሬንድ ይቅርታ ግን ብታውቀው ጥሩ ነው ብዬ..."

"ገባኝ" እንዴት ላይገባኝ ይችላል?

"'በተደፋ' ማለት ሴቷጋ ወንድ ገብቶ ሲወጣ የምትደፋውን ውኃ መቁጠር ነው። በተደፋ አስር ብር ይቀበላል።"

ማነን? የት ውስጥ ነው የተወሸቅነው?...

"በፊት አልፈልግም ብሎ ለሌላ ሰው ሰጥቶት ነበር፣ አሁን ሥራ ሲያጣ ነው መልሱልኝ ያለው። እና ባለ "ላዳ" ከሆነ..."

የት ጠብቂ የሙሴ ፀሊምን "መስቀል" ላግዘው? መስቀል ከተዋረደ ህይወት በላይ ይከብዳል? ሚስጥሩን እንደሥጋው ይሙ

@OLDBOOKSPDF

አልቆረብኩበት ይሆን? ከዚህ የትሌት አዘቅት ውስጥ ተመዝዘህ ወጥተህ እንደምን ሌሎችን አክብረህ ልትይዝ ትችላለህ?

"ፍሬንድ?"

"እ?"

"ቤቱን ከሩቅ አሳይቹህ ልመለስ--አረንጓዴ ቱታ የተሰጣበት፤ ቀይ ላስቲክ የተጋረደው ...እ..."

"ተወው፤ አልገባም:: አንተ ለለፋህበት ትንሽ ብር ልሰጥህ..." ኪሴ ገብቼ ነጥዬ ጥቂት ኖቶች መዘዝኩ:: ሰጠሁት:: በዝቶበት እንደቆመ ቀርቷል:: እኔ መንገዴን ቀጠልኩ:: ብዙ የሬሳ ሳጥን የመሰሉ ቤቶች ደጃፍ ላይ ሴቶች ተኳኩለው ቆመዋል:: በቀን?...

...ሙሴ ፀሊም ቤት ጋ ከመድረሴ በፊት ባለቅያሽ ታጥፌ ወደዋናው መንገድ ተቀላቀልኩ:: ፈጣሪና ፍጡሩ ለሙሴ ፀሊም አጣብቂኝ ህይወት ግድ የሰጣቸው አይመስሉም:: ይተረማመሳሉ:: ፈጣሪ የእያንዳንዱን ፍጡር ህይወት ከምን ጋር እያነካካ ፄፈው ይሆን? "ለፍተህ፣ ጥረህ፣ ግረህ፣ በግንባርህ ወዝ ብላ" ማለት ውስጥ ስንት የፈጣሪ ነውር ተሸፋፍኖ ኖሯል?

ወደ አማኑኤል የሚወስደውን ጎዳና እንደ አፈትጉሃን፣ አንድ በሁለት ጫማ ጥፍጠፋ እየተራመድኩ ቀጠልኩበት:: ፍሬደሪክ ኒቼ ይሄን እውነታ ይሆን እፈራዋለሁ ያለው:: (I'm afread of the real world.)

የተቀጠበልን ህይወት ነውር ከሆነ ነውርነቱ የቀጣቢው አይደለምን? እውነት ያስጠላል፤ ምድር የልጆቿን በዚህ መልክ መዋረድ እያየች ምን አስቻላት? በፍካሬ ኢየሱስ ዘመን አፍ አውጥታ ፈጣሪዋን አልጠየቀችምን?

"ምን አደረግሁ ጌታዬ"

"ባንቺ ያለው ሰው ሁሉ እኔን አላወቀምና ይህን ምልክት ማድረጌን እንዲያውቁት ነበር" ሲል የምድር ፈጣሪ አልመለሰላትም? ዛሬስ? የሰው ልጅ የያኔዋን ምድር ያህል በውርደት መቅሰፍት ሲመታ እያየች ስለምን ዝም አለች?

"ምን አደረገ? ልጁ ምን አጠፋ? የውርደት ደረመን ነፍሱን ወርሶት፣ ቆሳስሎ፣ መግሎና ተልቶ በጎዳና መውደቅ ምን ይሉት ፍርድ ነው?..." አትልም? 

@OLDBOOKSPDF

ከበስተጊዳዬ ሥሜ ዘሎ ጆሮዬ ገብቶ ከውስጠኛው አለም መንጭቶ ውጭኛው ዓለም ላይ ጣለኝ፤ ዞርኩ። ደነገጥኩ። ሙሴ ፀሊም ቱታ ለብሶ በተዝረከረከ አራሯጥ ወደእኔ ሲመጣ አየሁት። ወፍሯል፣ የእግዚአብሔርን የሰባ ውርደት እርሱ ተሸክሞታል። አጠገቤ ሲደርስ "መምህር ሆይ" ብዬ እግሩን በእንባዬ ማጠብ አሰኘኝ።

"ታስ? እ-ል-እ-ዛር..." ትንፋሽ ለመዋጥ ጉልበቱን ይዞ ቆየ።

በፊት 'ታስ' ብሎ ነበር የሚጠራኝ? 'ላጽቂት' አልነበር ያወጣልኝ ስም? ስለምን ዛሬ? ውርደቱ ላይ አነፍንፌ የደረስኩ ስለመሰለው መለማመጡ ይሆን?

"ታስ? የት መጥተህ ነው? ሰው ይፈልግሃል ብለውኝ ስወጣ፣ ያ-መፃጒት መስሎኝ፣ አንዳንዴ ሲቸግረው እኔጋ ስለሚመጣ..."

ነውር ላይ ተዛዝለን፣ እስከ አንገታችን

"...አንተን አየሁህ፤ አንተነህ የፈለከኝ? ልጆች ቤቱን አሳዩህ?..."

ነገሩን የከፋ የሚያደርገው በነውሩ ሀፍረት የሚሰማው ከሆነ ነው።

"እዚህ ሠፈር ነህ እንዴ? እኔ ወደ አማኑኤል ሰው ለመጠየቅ..." ይበቃል። እጄን ኪሴ ከትቼ የያዝኩትን ሁሉ ብር ስጠሁት። "ግማሹ ያንተ ነው። የቀረውን ለዮሐንስ እና ለስምዖን ዘአምድ ስጣቸው። አሁን እቸኩላለሁ"

"ግን ለምን ሰጠኸኝ?" ማነሴን አወቅህ? ማለቱ እንደሆነ የገባኝ ከራቅሁ በኋላ ነበር።

ኡፍፍፍፍ...

...አይጥ፣ ጉርጥ፣ ምስጥ፣ ጊንጥ፣ መፃጒት፣ ላጽቂት፣ እንቁራሪት፣ እንሽላሊት፣ አንበጣ፣ ፌንጣ፣ ዝንብ፣ ተርብ እባብ... የምታፈላ መካነ ነፍሳት ናት ይቺ ህይወት!!

"Man is a helpless toy in the hand of nature force" ያለው ማን ነበር?


@OLDBOOKSPDF


@OLDBOOKSPDF

# ክፍል ሁለት


## ወደ ዓይነምሣ ሰዎች

@OLDBOOKSPDF







@OLDBOOKSPDF



@OLDBOOKSPDF



ዓለማየሁ ገላጋይ

# የዓይነምሣ ሥር ስሥር

የዓይነምሣ ሠርመዴ ላይ ስፈናጠጥ ወደፈለኩት አቅጣጫ መብረር የምችል ሆኖ ይሰማኛል:: ሽቅርቅር ምድር ላይ ሆኖ ሰማይን መቃበዝ ምን አመጣው? ስለዚህ መብረር ብችልም ሳያስፈልገኝ ቀርቶ እተወዋለሁ:: የዓይነምሣን ሠርመዴ ከሩቅ ሳያት ወገቧ ላይ የደመና ድግ ታጥቃ እናቷ ላይ የበረዶ አክሊል የደፋች ይመስለኝ ነበር:: ግን ጉልበቱን በርታ-በርታ እያልኩ ወደ እናቷ ስቃረብ በውርጭ የገረጣ የደጋ ሣር ሆኖ አገኘዋለሁ:: ጠጅ ሳር መስሎኝ ከመሬት ነጥቄ አፍንጫዬ ሥር ሳስጠጋው ቀድሞ ቅዝቃዜው ለሰርኔ ይደርሳል:: ነጭ ችፍርግ... ነጭ ቅጠል... ነጭ ግንድ... ነጭ ፍሬ... ያላቸው ብዙ ተክሎች ሠርመዴን ያፈረሰ ቄስ አስመስለዋታል::

የዓይነምሣ ሠርመዴ አዲስ አበባን ቁልቁል ለማየት የሚያስችል ሁነኛ ቦታ ብትይዝም የጉም አይነርግቧ ግርዶሽ ሆኖ ዓይንን እያሳውሰም:: በከንቱ ማዶ ከማማተር እግሬ ስር ወደሚካሄደው ተፈጥሯዊ ውብ ትዕይንት አተኩራለሁ:: በእቅፍ የሚያዙ ድንክ ቀበሮዎች የደጋ አይጥ ለማጥመድ የጉድጓድ አፍ ላይ ዓይናቸውን ሰክተው ያለእንቅስቃሴ በንቃት ይጠባበቃሉ:: ጥበቃቸው የአንድ አንጓር አይደለም:: መንታ ነው:: ስታደባ የሚያደባባት ሌላ በላተኛ ይከሰት ይሆናል:: ይሄ መቼም የማይበጠስ ተፈጥሯዊ ማተብ ሳልቶ የሚታየው የሰው ልጅ ዘንድ ብቻ ነው:: ሰው ስለበለጠው ብቻ በአንበሳ መታደኑ ቢቀርለትም! በራሱ ሰው ከመበላት የማይተናነስ ዕጣ-ፈንታ ተጥሎበት የከፋት ወጥመድ ተዘጋጅቶለታል::

ከድንኩቹ ቀበሮዎች ከፍ የሚሉ ሌሎች የአይጥ ዝርያዎችም አይቻለሁ:: መፃጊት እሱ ይሆን? የነጣቂ ንቃት ያለው፣ ፀጉሩ የሚያብረቀርቅ ልም ነው:: ድንኳ ቀበሮ ገባ ጠረኑ ሲደርሳት ትፈተለካለች:: ይሄኔ መፃጊት እንደመጣ እረዳና ሳልንቀሳቀስ እጠብቀዋለሁ:: ሲያየኝ ተጠንቅቆ ይመለሳል:: የሰው ልጅ በሁለት እግሩ

@OLDBOOKSPDF

ሒያጅ እንግዳ እንስሳ መሆኑ ግራ ያጋባ እንደሆን እንጂ በቅልጣፌ ከአይጥ መብለጡን ያልተረዱ ይሸሹታል ስል አሰባለሁ::

ዕጣ ከፍሏ ከሰው ልጅ ጋር የሚመሳሰለው ጥንቸል መሬት ለመፎገር ጡብ ጡብ እያለች ቁጥቋጦ ተገን ይዛ ትቀመጣለች:: እንዲሁ ምድር ጫሪ፣ ሌላውን የሰማይ አጣሪ አድርጋ የደለደለችው ተፈጥሮ ብቻ ናት? ወይስ ፈጣሪ በነገረ ሰሪነት ተሰቶባታል?

የዓይነምሣ ሡርመዴ በጉም ጢሳጢስ ታፍኖ ተከሉቿ በረጋ ሁኔታ ሲያረግዱ ስመለከት የእግዚአብሔር መንፈስ በዚህ ያረፈ ይመስለኛል:: ለተፈጥሯዊው ሽቅርቅር ትዕይንት በዳኝነት ሳይሆን በጎብኚነት መንፈስ፣ የዕድሜ ቁጢት ሳይቋጭ፣ በተበይ ክፉ ዕጣ ሳይቆጭ... መደመም ብቻ::

ከዓይነምሣ ሡርመዴ ላይ ትንሽ ዝቅ ሲሉ ስገነት ያላት ደርባባ የአምልክ ዛፍ ከጉም ግርጌ ተንሰራፍታ ትታያለች:: እንደጠንቋይ ማረፊያው ዛፍ አላረረችም:: ቀሚሷን እንዘርፍፋ የልጅ በረከቷን በአርምሞ የምትቃኝ የተረት ውስጥ እናት ትመስላለች:: እዚህ እየኖሩ እንዴት እንደ እስራኤላውያን ከአንድ ሰው በላይ የማያናግረውን ድብቅ አምላክ መቀበል ይቻላል? ምድር አለመፎከቷ በራሱ ከሚታዩ አማልክት አንዷ እያደርጋትም? ጥንጁት የመሰሉት የሡርመዴው ላይ ባሮች፣ ችምችም ችፍርጎች፣ የዱር ሐረጎች፣ አውጦች፣ አጋምና ቀጋዎች፣ የዋንዛ ፍሬዎች፣ ያጋቱ ላሞች፣ ቁራ፣ ጨሌዎች፣ የበሬ ጨዎች፣ ምንጮች... እያንዳንዳቸው ለአንዳንድ አምላክነት ያንሳሉ?

የሡርመዴ ሥር ምንጮች አንዳንዶቹ ፍልቅ ፍልቅ ሲሉ ቁጡ ጣእትነት ይታይባቸዋል:: አንዳንዶቹ ምንጮች በፀጥታ፣ አልፎ፣ አልፎ ድንብል የመሰለ የአየር ቋጠሮ ይለቃሉ:: ለውበት የሚጨነቁ ጣዖቶች መሆናቸው ነው:: ምንጮቹን ቀረብ ብዬ የመፍለቂያ ስርጉዳቸውን በዓይኔ ሰርስሬ ለመመልከት እሞክራለሁ:: የዓይነምሣ ባላባቶች እንደሚሉት ሡርመዴው መሬት ያልረገጠ ባህር ላይ የሚንሳፈፍ የድንጋይ መርከብ የመሰለ ነው:: እስሩ ብዙ አይነት የውኃ ውስጥ አውሬዎች አሉ:: ድንብል መሰሉ የዓየር ቋጠሮ እነሱ የሚተነፍሱት ይሆን? አንዳንዴ መኖሪያ ጎጆዬን የሚያርገፈግፍ ነገር ሲገጥመኝ ከሡርመዴ ባህር የነበለለ ጉርምጥ፣ ሽርጠን፣ ሰደፍ... ወይም ኤሊ መሰል አላ... ምስስ የረገጠው መሠረት ውስጥ ተቀርቅሮ እየመሰለኝ ይጨንቀኛል:: አንድ ውኃ ጠጥተን ለጭንቁ ሳልደርስ ልቅር? መተዛዘንና መፋቀር [illegible] ምድር ልጆች ወግ ነው::

@OLDBOOKSPDF

በመንገድ ሳልፍ ወይም ደጃፌን ለመክፈት ስሰንፍ

"ኬሰማ" (እንግዳ)

"በርሲሳ" (መምህር)

"በርሲስ አዲስ አበባ" (የአዲስ አበባው መምህር) እያሉ እየጠሩ ጠላ ወይም በርበሬ በተን ያለበት ልድልድ እርጎ የሚያጠጡኝ ስለየትኛው ዋጋየ ነው? ኋላ ላይ ብቸኝነቴ ቢጨንቃቸው የትምህርት ቤቱን አትክልተኛ በባልንጀራነት ሳይመድቡልኝ አልቀረም። ጋሽ ቢራራ በጠዋት ይመጡና ደጃፌ ላይ ቆመው ይጣራሉ።

"ኬሱማ?"

ዝም እላለሁ።

"ደርገጌሳ" (ጎረምሳው) ዕድሜዬን ለማስላት እሞክራለሁ።

"ኢልማ ወለጋ" (የወለጋ ልጅ)

"እኔ'ኮ የወለጋ ልጅ አይደለሁም" ያልኳቸው ቀን አልቀበል ብለው።

"ቁርጥ የወለጋ ልጅ፣ እንዳንተ መልከመልካሞች ናቸው ወለጎች፣ ቁመታቸው ይምጣብኝ" አሉ። ቁመቴን ከራሳቸው ቁመት አንፃር እያዩ መሆን አለበት።

"አቦ ቢራራ" እላለሁ፣ ድምፃቸው በርበሬ በተን እንዳለበት ልድልድ እርጎ ወፍራም ነው። "አቶ ቢራራ" ቢኳቸው እንደማይወዱ አውቃለሁ። "በርሲሳ" ሲባሉ ነው ደስ የሚላቸው። አትክልተኛ ቢሆኑም አንዳንዴ ተማሪዎችን የአትክልት መደብ ደልድለው ስለሚያስቆፍሩ እራሳቸውን እንደ መምህር ይቆጥሩታል። በሩን ከፍቼላቸው ወደ ጠፍር አልጋዬ ተመለስኩ።

"አደኬ ታቴ" አሉኝ። አንዳንዴ ቋንቋ አለመቻሌን ይዘነጉታል።

"ማል ና ጀዳን?" (ምን አሉኝ) እርምኛ አለመቻሌን ማንቂያ ጥያቄዬ ናት።

"ያልኩማ ብቸኛ ሆንክ ነው።"

@OLDBOOKSPDF

በዓይነምግዎች ብቸኛ መሆን አድባሯን የሚያስወቅስ የማኅበረሰቡ ድክመት ነው።

"መኒ ኬ ቀበናዬ" (ቤትህ ቀዘቀዘ) ፊቴን በማየት የትዳር ነገር መነሳቱን እንዳልወደድኩ ያውቃሉ። አይናቸው ሥር በትላ የሞቶች ትልቅ ኪንታሮት አለች፣ በጣታቸው ያሻሿታል።

"ሂን ቆሩ አረቂ ዱጋ ጂሬ"

"ማልና ጀዳን?"

"ያልኩማ ብርድ ነው አረቂ እንጠጣ ነው"

ያሳዝኑኛል። እኔ ብቸኛ ሆንኩ አልሆንኩ ምን አስጨነቃቸው? በፍጥነት ለባብሼ የወታደር ጫማዬን አድርጌ እንወጣለን። የሞቶች ኪንታሮታቸው እንዳገኘችው የብርሃን መጠን መልኳን ትቀያይራለች። ኪንታሮቷ ያጮለቀች ፀሐይ በጨረር ዘንግ ስትጠቁማት ሐምራዊ ቀለም ይረብባታል።

ውኃ ጠጥቶ መትፋት የጀመረው መሬት መንገዳችንን በእርጥብ ድምፅ አጅቦታል።

"ጨፍ፣ ጨፍ፣ ጨፍ...."

"እንግዲህ ዓይነምግ የተባለበትን ጠየክ አይደል?"

እንዴ ጠይቄ ስንቴ እንደመለሱልኝ ዘንግተውት ይደጋግሙልኛል። ከቸከኝ ሌላ ጥያቄ አቀርብላቸዋለሁ። ካልሆነ ዝም እላቸዋለሁ።

"የዓይነምግና የአካባቢዋ ባላባት፣ የእኔ አያት ማለት ነው፤ አዛዥ አባ ተምግሥ ምኒልክን ጋብዘው "ግዛቱን እዩልኝ፣ ህዝቤን መርቁልኝ አሉ። አቤት የተጣለ ሠንጋ፣ አቤት የተወራረደ ብርንዶ በኋላ

"ተምሴ" አሏቸው ቁልቁል አዲስ አበባን እያዩ

"ጃንሆይ፣ የእኔ ሥም'ኮ ለቁልምጫ አይመችም" አሉ አዛዥ

ተማግቁ

@OLDBOOKSPDF

"ይቺን ቦታ ምን አልካት?"

"ምንም አላልኳት፣ ዝም ብዬ ገዛኋት" አሉ።

"ብል ይቺማ የዓይን ቁርስ ምሳ እራት ናት። በዚሁ ጥራት"

"አይ ጃንሆይ ይሁን ካሉ ይሁን እንጂ..."

"ምነው?"

"ሰው የዓይን ቁርስ፣ ምሳ፣ እራት ሲል ይውላል? ባልፈቀድነው ጠርቶ ያስከፋናል።"

"እንግዲያው የዓይኔ ቁርስ ምሣ" በላት።

"ጃንሆይ ከእርሶ አላውቅም"

"ምን አሰብክ?

"ምሣ ቁርስንም እራትንም ያማክላል። ዓይነምሣ ትባል"

"ደግ፣ ይሁን አሉ። ይቺን አውቃለሁ።"

"ጨፍ፣ ጨፍ፣ ጨፍ..." የእግራቸው ዳና በውኃ ላይ ታትሞ ለአፍታ ይቆይና ይጠፋል። ምናልባትም ዘልአለም እንዳለ የሚያቆያቸው የአይናቸው ሥር ሐምራዊ ኪንታሮት ብቻ ነው።

ኬላ ወርደን አረቂ እንጠጣለን። ኬላ ከተማ ለመምሰል በረጅም ዘመን ጣዕር የምትሰቃይ መንደር ናት።

ጋሽ ቢራራ አረቂ ሲጠግቡ ልብሳቸው ያበጀውን ጤዛ በመቀታቸው ማትነን ይጀምራል። እንደ ዓይነምሣ ሠርመዴ በሚንሳፈፍ ጉም ይሸፈናሉ።

"እኔ ቢራራ ብዙ አውቃለሁ" ማለት ይጀምራሉ። ያኔ ተደጋግፈን ወደየቤታችን።

ይሄ የሚሆነው ትምህርት የሌለ ዕለት ነው።

ትምህርት ካለ፣ ከተማሪዎች ጋር ያለኝን ክፍለጊዜ ጨርሼ ወደቤቴ ሳቀና ሆን ብዬ ጋሽ ቢራራ የሚገኙበትን የጓሮ በር

@OLDBOOKSPDF

እመርጣለሁ:: ጋሽ ቢራራ በራሳቸው ጉም ተከበው እንደሠርመዱ የደመና ድግ ታጥቀው አገኛቸዋለሁ::

"በርሲሳ" እላቸዋለሁ ያሉበትን ስሜት ለማወቅ::

በመጠኑ ፈገግ ይሉና አይናቸው ሥር ያለችውን ሀምራዊ ብጉ ይነካካሉ::

"ማልታቴ?" (ምነው?)

"እስካሁን የግል ማህደሬ 'አትክልተኛ' ይላሉ እሉ:: መለስም ብዬ አላየሁትም እንጂ::"

ገንዘብ ከሌለኝ አስተዛዝኜ እለያቸዋለሁ:: አያስችላቸውም:: መንገድ አጋማሽ ይደርሱብኛል::

"ፈርሶ አሳዱግኑ በርሲሳ በርሲሳ ወል ሀጆኑ" ይሉኛል:: በወፍራም ድምፅ ብሉዝ የምሰማ መሰለኝ::

"ምን አሉኝ?" እላቸዋለሁ::

"ያልኩማ ጠላ እየጠጣን 'መምህር፣ መምህር' እንባባል ነው::"

ዓይነምሣ ላይ እየኖሩ መጥፎ ነገር የሚታሰበው መቼ ነው? እኔ ክፉው፣ ከከተማ ሲሚንቶ ጋር ነፍሴ ተቀላቅላ የቀዘቀዘች ክፉ ማሰብ የምችልበት ጊዜ ካጣሁ፣ ማን? ሌላ ማን? መሬቷን፣ አየሯን፣ ጋሽ ቢራራ የትምህርት ቤቱን አጥር፣ የጠላ ቤቱን ጉብን... ሁሉንም መሣም ያምረኛል::

ጠላ የምጠጣው ጋሽ ቢራራ ቤት ከሆነ ወደጓሮ ዞረን ዳገው ሥር እንቀመጣለን:: ጭጋግ እስኪጋርደን ድረስ የምናየው ውበት ልቤን ይነሳኛል::

"ያ" እያሉ የሚጥመለመለውን ጭጋግ ይጠቁማሉ::

"ያ፣ አዲሳባ ስድስኪሎ ነው:: ባቡር መንገዱ አይታይህም፣ ያ ተበታቹ የምኒልክ ቤተመንግሥት ነው:: አፈር ይብላኝ እምዬ እሳቸው እውነትም በሳቸው ቤት ያ-ክፉ ገባበት"

"መንግሥቱ"

@OLDBOOKSPDF

"ከሱ በፊት"

"ጉንጼ እሳቸው ምን አደረጉ ደሞ::"

"ያረገ ነገርማ እንዲህ ነው:: በጠፍ መንግሥት ዘመን ደጃዝማች እያለ ልጅ ኢያሱ ደጅ አስጠንተውት፣ ቀን-ቀን ቤተመንግሥት እየዋለ ማታ ማታ በበቅሎ ዓይነምሣ እየመጣ ያድር ነበር:: እዚች ቤት ከአባቴ ጋር አንዳንዴ እዚች ታዛ ሥር ሲያወጉ ያድሩ ነበር:: "አባይነሽ! ፋርሳስ ኑፌዲ አካይ ወጂን" (አባይነሽ ጠላውን አምጪ፤ ቆሎ ጨምሪና፣)"

ከዓይነምሣ ሳይወጡ አባይ በምን አባብሏቸው የመጀመሪያ ልጃቸውን አባይነሽ አሏት? አባይነሽ ጠላውን በገንቦ አስቀምጣ ትሄዳለች:: ተመልሣ የምኒልክ ዋንጫ ታመጣና ትቀዳለች::

"ለእኔ በብርሌ አድርጊልኝ" ይላሉ ጋሽ ቢራራ "ቦጭ ሲል ፊቴ ጠላ ብቻ ይሆናል::"

ፊት ልጃቸው እኔን እያየች "ኢሲኒፋ ማሊን ኢሳኒ ሁቶኡ?"

"ምን አልሽኝ?" በአማርኛ እንድታደርግልኝ

"ለርሶሳ በምን ልስጦት አልኩ"

"ለእኔ ዋንጫው ይሻለኛል::

"ከዛ በኋላ ሲነግስ አባቴን ዞር ብሎ ሲያይ ነው? እዚህ ራስ ካሣ ግቢ፣ በፊት አጥር ጥጋቸው ያሳስደረሱትን ሲነግስ ይጋብዙታል:: ካባውን መሬት ለመሬት እየጎተተ መጥቶ እዚህ ሳይደርስ ይመለሳል:: በኋላ ካረጀ፣ አባቴም ከሞቱ በኋላ ድንገት እዚህ መጣ:: እምይዝ የምጨብጠውን አጣሁ:: ቤቱን መለስ ቀለስ አድርጎ አይቶ፣ አጀቡ መቼም እንዲህ ከእንዲህ አይባልም፣ በስርቆሽ በር ሲወጣ ሲል ባርኔጣውን የአፈጠጠ የአጥር እንጨት ላፍ እያደርግበትም:: ደነገጥን፣ ደነገጥን..." ቆሎ አፈሱ፣ ቃሙ::

...በኋላ "እኔ ቢራራ" ብዬ እንጨቱ ላይ ፎክሬ መጥረቢያ ላመጣ ስል በተንኮል እያየኝ

"ቀድሞ ነበር እንጂ፣ አይኔን እንዳወጣኸው አቆጥረዋለሁ" አይልም::

@OLDBOOKSPDF

"ጉድ ፈላ አልኩት። እንጨቱ ያለው አጥሩ ወገብ ላይ ተናገር። የነገር ሆኖ እንጂ ሲሆን፣ ሲሆን ቀብቶ ያወልቃል እንጂ ቆብ ይገባል? ለወትሮም የእሱ ቁመት!" ጠላ ተጎነጨ።

"አብዮቱ ቢቀድማቸው ነው እንጂ ዓይን ለዓይን ብለው በባርኔጣው ፈንታ ዓይኔን ያስወልቁኝ ነበር። በዚህ ቂም ይዤ ሲወርዱ ከተማሪዎች ጋር ሌባ፣ ሌባ ብያለሁ። ይቺን አውቃለሁ።"


የሚታየው ገር፣ የሚጠጣው ገር፣ የሚበላው ገር፣ የሚደመጠው ሀሰተኛው ማነህ ገር... እዚህ መሀል ሰይጣን ቢኖር ሥራ አይፈታም? እንዴት ሆኖ ትዝ አለኝ? እኔጋ ከመጣ አመት ሊሞላው ነው፣ ይሆን?...

"እሃ፣ እሃ፣ እሃ... ንጉሥ መጥቶ እኔ ቤት ካረፈ በኋላ ቤቱ 'መነቆዳላ' ተባለ።"

"ምን ማለት ነው?" ረድ ሠርዌ ከስንት ጊዜ በኋላ ታወሰኝ? ትርጉም በእርግጥም ለተርጓሚው ዕዳ ነው።

"መነቆዳላ አይደለ? እንግዲህ ምን ማለት ነው? 'ንጉሥ መቀበሪያ ነው።" ትምህርት ቤት ሆነው አረቄ ያስነሳው ጭጋግ ከጓቸው እንዳልነበር ጠላ በላዩ ሲደፉበት እረግቦ ቁልጭ ብለው ይታዩ ጀመር። ሀምራዊ ኪንታሮታቸው ካረቁውም፣ ከጠላውም ደርሷት የተነቃቃች ትመስላለች።

@OLDBOOKSPDF



# ከዓይነምሣ ባሻገር

እንዳንዴ በምሽት፣ አዲስ አበባ መሬት ላይ የተነጠፈች ሰማይ ትመስላለች። እንደ ኮከብ ጭልጭል የሚሉ የብርሃን ጢዛዎች ይታያሉ። አንዳንድ ቦታዎ የብርሃን እባብ ይዝለገለግባታል።

"ደርገጌሣ" ይሉኛል ድምፃቸው ካፋቸው በወፍራሙ ሲመጣ ደርበብ ብሎ ነው።

"እ?"

"ይኸውልህ የዓይነምሣ ነገር እንዲህ ሆነልህ" ጠላቸውን በብርሌ ሲያንቆረቁሩ ገፈቱ ቀጥታ ወደጉሮሮዋቸው እንደሚወርድ ይታወቀኝና የእኔን ትናጋ ይበላኛል።

"እንዴት?" በምኒልክ ዋንጫ ጠላዬን እያንቦጫቦጭኩ

"ከሩቅ የስድስት ኪሎን ጎዳና እናያለን፣ መንገድ የለንም... ከሩቅ የምኒልክን ሆስፒታል እና ያለን መታከሚያ የለንም፣ ከላይ የአዲስ አበባን የውኃ ጋን እያየን ቧንቧ የለንም።"

በዓይነምሣ ላይ የከተሜነትን መአት እየጠሩ ይመስለኛል። ቶሎ የነገር መምሪያውን ወደሌላ አቅጣጫ እጠመዝዛለሁ።

"እውነት ግን ዓይነምሣ ሥር ሥሯን ባህር አለ?"

"እንዴ? ምንትላለህ? ዓይነምሣ ማጠንፈፊያ አላት። ውኃው ወደውስጥ ይሰርጋል፣ አፈርና ድንጋዩ ከላይ ይቀራል። እስር ያልከ እንደሆን ዓሣ ነባሪ ሁሉ አለ ይባላል። በክረምት ከትል ከፍ ከፍ የሚሉት ዓሣዎች ወደ ላይ ስለሚገነፍሉ ዓይነምሣ በዓሣ በል ወፎች ትወረራለች፣ ይሄንን አውቃለሁ።" ሀምራዊዋ ኪንታሮት ከፀሐይ መግባት ጋር ከሰማለች።

@OLDBOOKSPDF

የእኔ ችግር የያዝኩትን ዝቅ፣ ዝቅ ማድረጌ እንደሆን የገባኝ ጋሽ ቢራራን ስግባባ ነው:: እሳቸው ሲያወሷት ዓይነምሣ ባላት ላይ ትጨምራለች እንጂ አትቀንስም:: ጥሩ፣ ጥሩው እየተመረጠ ለዓይነምሣ ይሰጣል::

"ታዲያ ዓይነምሣ ሰው አላጣችም:: ከዘፋኝ ጥላሁን ገሠሠ የዚች የዓይነምሣ ልጅ ነው:: ያው ትንሽ ዝቅ ካልክ ፈረንሳይ ለጋሲዮን ነው:: በፊትማ እዚች ቤት ሲሰራ ነበር አሉ፣ ዓሣ ነባሪውን ፈራ:: ብዙነሽ በቀለም እዚሁ ነበረች..."

ናትራ በስንት ጊዜ ትገዝ አለችኝ? እኔ ግን ምንድነኝ? 'ወይኔ ጉዴ! ወይኔ! ጉዴ!' ጆሮዬ ላይ ተላከከ::

"ከስፖርተኛ ያልክ እንደሆን አበበ ቢቂላ፣ ዋሚ ቢራቱ ሆነ ማሞ ወልዴ የዓይነምሣን ውኃ ጠጥተው የኖሩ ናቸው..."

በወፍራሙ የተገመደ ድምፃቸው፣ ምናልባት እንደማግ ፈትል የቀለጠ ሰም ላይ ቢልኮሰኮስ ትልቅ የአሳሽ ጧፍ ሳይወጣው አይቀርም:: ፈገግ አልኩ

"አንድ ጊዜ፣ ያኔ ገና አትክልተኛ ነኝ፣ እንዳሁኑ መምህር አልሆንኩም..." ብርሌ አንስተው ለራሳቸው ያልተዋጠላቸውን ንግግር በጠላ ለማወራረድ ሞከሩ...

"ኢትዮጵያ አሸንፋለች አሉ፣ እንዴት ዝም እንላለን አረንቻታ እንጠጣ ፈረንሳይ ወርደን፣ አልኳት የልጆቼን እናት ነፍሷን ይማርና:: ያኔ አባይነሽ ተወልዳለች? እንጃ ብቻ

"እሺ ጥሩ ነዋ፣ እንጠጣ አረንቻታ" አለችኝ:: ተያይዘን ፈረንሳይ:: ስንደርስ አረንቻታ አዘዝን፣ ሆ! ሆ! ሆ! ይባላል:: እንዳላወቀ ጠየቅን::

"ምን መጣ?"

" 'ኢትዮጵያ አሸነፈች'

"'ማንን አሸነፈች?'

" 'ጣሊያንን'

" 'ደገመችት?'

@OLDBOOKSPDF

" 'ይላሉ'

" 'ስንት ማረከች ኢትዮጵያ?'

" 'ምንም!'

" 'ስንት ገደለች?'

" 'ምንም!'

" 'ታዲያ እንዴት ድል አደረገች?'

" 'በሩጫ!'

" 'ሸሽታ?'

" 'አይ ተወዳድራ'

" 'ምን ታሾፋለች፣ እንደው ዝም ብሎ ሥራ ማስፈታት አለ? አረንቻታችን ታከስራለች?'"

"አረንቻታችንን በመወዘቻ ገልብጠን ይዘን መጣን፣ ሳምንት ጠጣነው፣ የድሮ አረንቻታ"

አንዳንድ ጊዜ የሥነ ፅሁፍ መፈተኛ ጥያቄዎች እነሳባቸዋለሁ::

"መወዘቻውን ከየት አመጣችሁ? ነው ወይስ መወዘቻ ይዛችሁ ትዞራላችሁ?"

ትንሽ ደንቀፍ ያደርጋቸውና "የባለቤቱ እህት ልጅ ኬላ ትኖራለች፣ የሷ ነው መወዘቻው"

ፈትሬ ስይዛቸው አሳዘኑኝ:: እንደወትሯቸው ይሄን አውቃለሁ ሳይሉ ጨዋታ መደምደማቸውን ከእኔ ማደናገሪያ ጥያቄ ጋር አያይዤ በመጠኑ ተፀፀትኩ::

ጨለማው ልጥልጥ እያለ ሄደ:: አዲስ አበባ በየደመናው መካከል እንደ ጅብ የሚያበሩ አይኖቿን ታጮልቃለች:: የምለው ጠፍቶኝ ዝም ብዬ ጠላዬን በምኒልክ ዋንጫ እንበጫቡጫለሁ:: ዕቃዎች በሙሉ በፋሽን መተካካት ከከተማ ሲገፉ እንደ ዓይነምዣ ያሉ መኖሪያዎች

@OLDBOOKSPDF

መሰደጃቸው ይሆናሉ። በምኒልክ ዋንጫ ጠጥተን፣ በምኒልክ ትሪ በልተን፣ በካሲም ተከናንበን የጠፍር አልጋችንን እናሞቃለን። ጋሽ ቢራራን ወደ ጎን ማተርኳቸው። ከኪንታሮታቸው ጋር ይጨዋወታሉ።

"ብርሲሳ አዲስ አበባ" ሲሉኝ

"ብርሲሳ ዓይነምሣ" ተሽቀዳድሜ

ጨለማው ላይ ዓይናቸውን እንደተከሉ ፈገግ ሲሉ አየኋቸው። ካስኳቸው ይሆን? 'የዓይነምሣው መምህር' ማለት እንደጦርሜዳ ኒሻን የሚኩሩበት የህይወት ጀብዷቸው የሆነው ለምንድነው? መምህርነትን ስለማይመጥኑ?

"ኦሮሞ ሲመርቅ 'ኡልፊና ዱክና አሲኒ ሀኬኑ' ይላል።"

"ማል ና ጀዳን" አልኳቸው

" 'የጨለማን ግርማ ሞገስ ይስጥህ' ማለቱ ነው። አየህልኝ የዚህን ጨለማ ግርማሞስ? በምን ይገሠሣል? አማራ ጨለማን ይፈራል፣ ኦሮሞ ጨለማን ያከብራል። ይሄንን አውቃለሁ።"

ከግርማሞገሣሙ ጨለማ ጋር ፊት ለፊት ተፋጠን ዝም አልን።

* * *

ልጆቹ ያልተሳገ ውልግድግድ የባህር ዛፍ ግንድ ላይ ተቀምጠው ሲማሩ አንጀቴን ይበሉታል። አዲስ አበባ የምኒልክ ዋንጫዋንና የምኒልክ ትሪዋን እንጂ የመማሪያ ቁሳቁሶቿን ወደዓይነምሣ አትልክም። ትምህርት መምሪያውም በትምህርት ቤቱ ሁኔታ ይኩራራብታል እንጂ አያፍርበትም።

"አንተ ዛሬ መጥተህ ነው፣ የዛሬ ዓመት እዛ ጥላ ስር ነበር የምናስተምረው" ይላል ዳሬክተሩ ከአዲሱ ግድግዳ ላይ ጥርስ መጎርጎሪያ ጭድ እየመዘዘ።

በትምህርት ቤቱ ላይ ያስመዘገቡት ድል እስኪያረጅ መሟላቱ እንጂ መጉደሉ ላይታያቸው ነው በቃ? ይሄ ፊት ለፊቴ ጥርሱን በጭድ የሚጎረጉር ጎረምሳ ለኔ የነገረኝን ድሉን ስንት ሪፖርት ላይ ጠቅሶት ይሆን? OK ክፍሎቹ እንዲያውም በነካ እጃቸው ለምን የተማሪዎቹን

@OLDBOOKSPDF

መቀመጫ አልሰሩም? ለሌላ ድል ወደጊላ ብለውት ይሆን? ወይስ ለእኔ ትተውልኝ?

"ትናንት ከትምህርት መምሪያ ሰው ፈልጎህ ነበር። እዚህ ድረስ መጥተው."

የምንጭሩን ግራ ጎን ከፍ አድርጎ በጭድ እየነካካ ሽሙጥ እንዳለበት ገባኝ።

"ትናንሾቹ ነገሥታት የሚፈልጉትን ይምጣ ይላሉ እንጂ እዚህ ድረስ መጥተውም አያውቁ"

የፈለገኝ ማን እንደሆነ እምብዛም ሳልጨነቅ ደርሼበታለሁ። አንድ የእኔ ተማሪ የነበረ ወጣት ነው። እኔ ባላስታውሰውም ጠርቶ ሠላም ሲለኝ ማነጋገር ሳልፈልግ ቆምኩ። የትምህርት መምሪያ ኃላፊ እንደሆነ ሲነግረኝ ሥራ እንዲፈልግልኝ ጠየኩት። ግር እንዳለው በሚያሳብቅ መንገድ ሲያፈጥብኝ...

"ለልምድ ፈልጌው ነው" አልኩት።

"እንግዲያው አንድ የከተማ ገጠር ትምህርት ቤት አለ" ብሎ እዚህ መደበኝ። እሱ ምን ያህል ከፍ ገቶ እንዳለ አላውቅም። ለእኔ ግን የመኖሪያ ቤት ስቀይር እንኳን ያንን ያህል አልተቸገርኩም። እሱ ነው እዚህ ድረስ መጥቶ ሲፈልገኝ የሚችለው።

"ጥሩ" (እንደጠና ጋሼው)

"ይቺም ቦታ ሆና ጠላት ላፍራ?"

ከመረዘ የማይለቅ ሽማግሌ መስሎ ታየኝ።

"ወጣት አይደለህ? እንዴት እንደዚህ ታስባለህ?"

"ምን ላድርግ? እኔ አላመንኩም እንጂ ከትምህርት መምሪያ ሳይሆን ከትምህርት ቢሮ ነው ይባላል እዚህ ድረስ መጥተው የፈለጉህ ምን ላድርግ?"

ጭዱን በምላሱና በከንፈሩ አጣብቆ አፈናጠረው።

@OLDBOOKSPDF

ጉዳዬ ምንድነው? በእግረመንገድ መውደዴ ከሰው ወደ ቦታ ተሸጋገረ? የእኔ ጭማሪ መውደድ ለዓይነምሣ ምኗ ነው? ቀስቄሺ መውደዴን ካጋባሁ በኋላ በግዴለሽነት መስያየት የውርደት ስራ አይደለምን? በእንዲህ አይነት ሁኔታ እዚህ ምን ያህል ጊዜ እቆያለሁ? እንደሴቶቹ የዓይነምሣም ወረት ማብቃቱ ይቀራል? ያኔስ?

የትምህርት ቤቱን የስርቆሽ በር ትቼ ወደዋናው መውጫ አመራሁ:: ዳይሬክተሩ ከኋላዬ እየተከተለ ማልጎምጎሙን ቀጥሏል::

"ሰው ትልቅ ነገር ትቶ ከትንንሾች ጋር ትንንሽ ነገር ላይ ይሻማል? ዩኒቨርሲቲ ሌክቸረር የነበረ... የምን ሥጋ፣ አልጋ ሲሉት... ምንድነው?..."

በፊትም ከከተማ ለፈለሱ ሰዎች የንቀት አመለካከት ማሳደሬ ትክክል ነበር:: ተማሪዎች ከመለቀቃቸው በፊት ፈጥኜ ግቢውን ለቀቅሁ::

"በርሲሳ፣ አከም ጅርታ"

የማላውቃቸው፣ ወተት አይብ እና ቅቤ ተሸክመው ወደ ከላ የሚወርዱ ባተሌዎች

"አካም" ሠላምታ የነፍስ ምሣ እና እራት ነው፤ በፊት ሰላምታ ሲያቀርቡልኝ አላሳልፍ ያሉኝ ይመስለኝ የነበረው እንዴት ነበር?

"ኬሰማ፣ አካም ጅርቱ?"

ሥጋችንን አሸር ባሸር ምግብ ቶሎ እንደምትለየው ሁሉ ነፍሳችንም የለበጣ ሠላምታ በፍጥነት ይጎሰብጣታል:: በአፍ አመል ተነካክቶ እጅ እጅ ያለ ሠላምታ ከማቅረብ፣ የቀረ በስንት ጣዕሙ::

ዋናውን ጥርጊያ ተነጥላ አቀበቱን የምትሳብ የእግር መንገድ ወደቤቴ ታደርሰኛለች:: አጫጭሮቹ ሳሮች ባቴን ሲኮረኩሩኝ፣ ከሱሪዬ ዘልቆ እየተሰማኝ፣ ቀልዳቸውን ባለመሻት ረግጬ መንገዴን ተያያዝኩት:: በዚህ ቅፅበት ሩሲያዊው ባለቅኔ ሌርሞርንቶቭ ምድርና ሠማይን አነፃፅሮ የተናገራት ተጓድላ ታወሰችኝ:: ምን ነበር ያለው?... አዎ!

@OLDBOOKSPDF

ጓገደምን ከሰማይ አስበልጠን ከምድር ጋር ፍቅር ባለመውደቅ እንችላለን? የገነት ደስታ'ኮ የማይጨበጥ ህልም ነው። እጎንብሶ የምድርን ላቦት በአፍንጫ መማግ የሚሰጠንን ፍሰሃ ከእኛ በላይ ማን ሊገነዘበው ይችላል?"

ማንም!!

ምድር እርጣ ቁሬማ ስትሆን ተሰፋ እንደጨረቃ ሰማይ ላይ ተንጠልጥላ በገነትነት ለመፃተኞች ታበራለች። ወደ ሰማይ የሚያንጋጥጥ አማኝ ጨካኝ ምድር ወልዳ የከዳችው ብቻ ነው። ዓይነምሣ በማህፀኗ የሚንቧቹ ሸርጣን፣ ጉርምጥ፣ ሰደፍ፣ ዓሣነባሪ፣ የውኃ ውስጥ ተሳቢ...እላት። መፃዒት፣ እንዝዝ፣ ገበሎ፣ ሐንጻን፣ ላጽቂት፣ ቱልት፣ ፍጁል፣ እንፍርት፣ ጥርኝ፣ ፋደት፣... ገፅታዋን ሸፍነዋታል። ሰማይዋን ጨሰቁ፣ ጭላት፣ ላሮስ፣ ዋኖስ፣ ቡሊት፣ ሰሬኔ፣ ሾለቅ... ብርሃን ክልክለዋታል... እዚህ ሥር ያሉ ወደ ሰማይ ያንጋጥጣሉ? ሰማያትን እየከፋፈሉ ይመራመራሉ?...

...ጠፈር፣ ምጽነበት፣ ሰማይውዱድ፣ ሔኖስ፣ ኢዮር፣ እርያም፣ መገበረ ፀባዖት.... እያሉ ሰማይን መበለት በምድር ተስፋ ማጣት አይደለምን? የሄራን መላእክት ለሰው ልጆች ምህረትና ይቅርታን መለመን ለምን?

የቀጭኗን መንገድ ትልም ተከትዬ ስጓዝ እከራዬን ከሩቅ አየኋት። ደማቅ ብርቱካናማ ቀሚሷን በፈትል መቀነት ሸብ አድርጋ ትማስናለች። ብዙ ጊዜ ከእኔ ጋር አንገጣጠምም። ጠዋት ሥራ ስሄድ ሌሊት ያለበችውን ወተት፣ ያጠራቀመችውን ቅቤ የቀቀለችውን እይብ ይዛ ወደ ኬላ ወርዳለች። ስትመለስ የከብቶች በረት ታፀዳለች፣ ምናምን ትቀቅላለች፣ ጎንበስ ቀና ብላ ከብቶችን ከእረኞች ተረክባ በጊዜ ትተኛለች። ዛሬ ያገኘኋት ያለሰዓት ስለመጣሁ ነው። እየቀረብኩ ስመጣ ጋሽ ቢራራ የሚጠሩበት የሽሙጥ ስሟ አፌ ላይ ደርሶ መለስኩት።

"ቃሊቴ" ይሏታል ጋሽ ቢራራ።

በእሮምኛ ብዙ የንዴት ቃላት ትወረውርና ወደ እኔ እያየች

"በቋንቋው ልንገረው?" ትላቸዋለች።

"ምናለ? ንገሪያ" ይላሉ ከነገር እያፈገፈጉ። ጥቂት አሮምኛ ያክላሉ።

@OLDBOOKSPDF

"መካከለኛው ልጅ ይመስክር፣ በዳበሳ ይታወቃል" ትላለች።

"ማሎ፣ ማሎ፣ ማሎ..."

የተባለውን ልጅ በአይኔ ፈልጌ አጤነዋለሁ። ሐምራዊ ኪንታሮት የለውም እንጂ...

ጋሽ ቢራራ፣ በቦረንትቻ እና በደንቃራ የሚያስፈራሩኝ ማታ ኮተት ብለው ሲመጡ እንዳላያቸው ይሆን?

"መምሩ እንደምን ዋልክ?" አለችኝ። መድረሴን ልብ አላልኩም ነበር።

"እንደምን ዋልሽ?" እንዲህ እየታተረ የሚማስን የአምልኮ ቃልኪዳን ያሻዋል? ስል አሰብኩ።

"ቤቱ ተሰቅልቋል፣ ታዛው ስር ለጊዜው አረፍ በል፣ አሁን ከው ብሎ ይደርቃል።"

ቤቱ እበት ከተለቀለቀ ለሶስት ቀን ከከብቶች ሽታ ጋር ልሰነብት እንደሆን ገባኝ፤ ታዛው ስር ተቀመጥኩ።

አከራዬ በፊያሽኮ ጠላ ይዛ መጣች። ታቀርባለች እንጂ ትጠጣለህ ብላ አትጠይቅም። ትንሽ ቆይታ የቅጠል ጭስ ሽታ የሚያንገፈገብበት በበርበሬ የታሸ ትኩስ አይብ ከጥቢኛ ጋር አቀረበችልኝ። ፊያሽኮውን በእጄ ስዳስሰው ደስታ ይሰማኛል።

"በሞትኩት መጠጫ ሳላመጣ ብላ ተመለሰች። ከትንሽ ቆይታ በኋላ ከጠላው ጋር ተሳምዶ የጠላውን መልክ የያዘ ክቡር ዘበኛ ብርጭቆ አመጣች

"መምሩ?"

"እሜት?" የመምህርና የመምሬን ልዩነት አላወቀችም? ወይስ...

"ሽማግሌ አላየህም?" ከፊያሽኮው ወደ ክቡር ዘበኛ ብርጭቆ ጠላ እየቀዳችልኝ።

"የቱ ሽማግሌ?"

@OLDBOOKSPDF

በሽኩርምሚት ዓይን ገሬመመችኝ

"አላየሁም፣ ዝም ብዬ፣ ወዲህ ወዲያ ሳልል ነው የመጣሁት" መውደድ ያለባት ይመስላል። በቁር ተነስታ ስለምትንጎዳጎድ ጉንጯ ላይ ቀጭ መሳይ ጥቁረት ያንግዋብባበታል እንጂ ቆንጆ ነች። አንዳንድ ሴቶች በጣም ካልቀረቡ የመልካቸው ሁኔታ በግልፅ አይታይም።

ትንሺ ልጇ መጥታ ቀሚሷን ያዘች። ከሽንሽን ቀሚሷ ጋር ስትታይ የትልቅ ሴት ቁመና ይታይባታል።

"ፈርሶ ፈዲ" አለች የእኔ ፊያሽኮ እያለች።

አከራዩ ሆዷን በመዳፏ ደግፋ "እዚ ብዙ ነገር አለ፣ ያንተ ሽማግሌ..." ብላኝ ሄደች።

የቀትር ፀሐይ በጉም ተጋርዷል። በጉሙ ሽንቁር አውታረ ፀሐይ ሾልኮ መሬትን በስምንት እግር ለመርገጥ የሚጣጣር ትልቅ ሸረሪት መስሏል። ከስር የመጣሁባት የእግር መንገድ ጉብዝና ከተሰማው የመስክ ሳር ጋር ትንቅንቅ ገጥማለች። ብቅ፣ ጥልቅ... እያለች፣ እየተደፈቀች መጥታ ከግቢው ካብ ጋር ተሳስማ ትቆማለች። እንዲህ ያሉ የእግር መንገዶች እንዴት ይፈጠራሉ? ስለምን ሰው ሁሉ በአንዲት መስመር ላይ እግሩን ይተመትማል? አዲስ መንገድ መተለም የሰው ልጅ ሁሉ ፍርሃት ነው? ለምን?... እንዲት የጎርኪ ግጥም ትዝ አለችኝ።

"እረጅም ጎዳና ጠመዝማዛ መንገድ

መንደር መስክ አቋርጦ ተሻግሮ የሚሄድ

አካፋ ወይ ዶማ አልነካውም ከቶ

ኮቴ ነው የሠራው መንገዱን አስፋፍቶ።"

ሲራራ ነጋዴ ሸቀጥ በማቀባበል ብቻ ሳይሆን ሐገር ከሀገር የሚያገናኝ የእግር መንገድ በመፈለምም አስተዋፅኦ አለው ማለት ነው?

ጠላዬን ተጎነጨሁ፣ እርጥብ ቅጠል ተማግዶ የተሞቀው አይብ ጣዕሙም ጭስ-ጭስ ይላል። ትክክለኛው የተፈጥሮ ጣዕም ሆኖ ተሰማኝ።

@OLDBOOKSPDF

"መምሩ?"

"እመት?"

"ነምቢ ሰበር ባዴ ቱሬ"

"እ?"

"ሰው ፈልጎህ ነው ማለቴ ነው"

"መቼ?"


"ትናንት አይደለም፣ ከዛ በፊት"

"ምን አይነት ሰው?" ዴያሬክተሩ ትዝ አለኝ።

"ፀሐይ የመሰለች ሴት፣ ሚስት ጥለህ ነው እንዴ ካገርህ የመጣህ?"

ግራ ተጋባሁ፣ ናትራ መምህሩን እንደታየችው ተሽቀርቅራ መጥታ ይሆን? እሷን በመተዌ ልታስቆጨኝ? ላግባሽ ብዬ ደጃፏ ላይ እንድቆም?... ፈገግ አልኩ። ለመሆኑ እዚህ መሆኔን እንዴት አወቀች? ታላሳቅ የሒሳብ ሊቆች ሊሳተፉበት የሚገባ ቀመር።

@OLDBOOKSPDF





# ከዓይነምሣ ወዲህ

ምስሶዬ ሲነቃነቅ ነቃሁ:: የዓይነምሣ የውስጥ ለውስጥ ጉርምጥ የምሰሶው መሰረት ውስጥ ተቀርቅሯል ማለት ነው:: ጭስ የጠጣው የሣርክዳን እርጋፊ ተበተነ:: በደብረብርሃን ብርድ ልብስ ላይ ካሊም ደርቤ ስለምተኛ ለቅዝት የሚዳርግ ሙቀት ውስጥ እዋኛለሁ::

ዓይነምሣ ባህር ላይ የተንሳፈፈች የማጥለያ ታንኳ ሆና ትታሰበኛለች:: ከሁሉም ዓይነት ዘር ሳትሰስት በገፍ የጫነች የኖህ መርከብ:: የካሊም መቃብሬን እንደ አልአዛር ፈንቅዬ ወደህይወት እመሰሳለሁ ስል የከብት እዳሪ የተለቀለቀው ወለል እግሬን አስፈራራው:: ነጠላ ጫማውን በአይኔ ፈለኩ:: አከራዬ መደቡ ላይ ሰቅላዋለች:: በጣቴ ጡብ፣ ጡብ እያልኩ ከእነ እርጥበቱ ጫማዬን ሰካሁ::

ለካ ህልሜን የለወጠው የከብት ሽታ ውስጥ ስዋኝ ስላደርኩ ነው:: ቀንዱን ተከርክሞ በሽኮናው እንደፀጉር እየደመደመ ሊያናግረኝ ያደረው ዜንጠ በሬ ትዝ ብሎኝ ፈገግ አልኩ::

መስኮቴን ከፍቼ አፍንጫዬን ነፃ አወጣሁ::

"ሠላም ለኪ ዓይነምሣ"

ጓሮዬ ቁልቁለት ላይ የተለቀቀ አዛባ ለንበሌጦቹን እየረፈረፈ እላያቸው ላይ ተኝቷል:: ፀሐይ ስለማያገኘው አልተጋነነም እንጂ ሽታው አገር ያዳርስ ነበር:: ከአዛባ መፋሰሻ ግራ ጎን የእታቅማ ጥላ ሥር ትኩስ ፈርስ በጥንቃቄ ተደፍቶ ይታያል:: ተደፋ ከማለት ተቀመጠ ሳይቀል አይቀርም:: ለአንድ ሰው እንዲበቃ ሆኖ ተቀምጧል:: እንዲሁ የቡና አተላም አለ::

መጀመሪያ ልቤ መታ፣ ቀጥሎ እራሴን የሚያረጋጋ ሀሳብ ማፈላለግ ጀመርኩ::

@OLDBOOKSPDF

ፍጡር ሁሉ ከሰው ልጅ ግብር ያስፈልገዋል። ሁሉንም ጠቅልሎ የያዘው የሰው ልጅ ሌሎቹን ፍጡራን ሁሉ የሚያስብበት መተዳደሪያ ሊኖረው ይገባል።

"መምሩ?"

እባብ፣ ነብር፣ ዘንዶ... ብቻ ሳይሆን ሌሎቹንም እንስሳት ማምለኪያና መገበሪያ ሥርዓት...

"ያ በርሲሳኮ"

"አ!" ልማድ ግድ ብሎኝ የጎጆዬን በር ሳልሸጉረው ቀርቼ ኖሮ አከራዬ፣ ፊቷን ብቻ አሾልካ ትመለከተኛለች።

"መስኮት ለምን ከፈትክ? አትክፈት!"

"ለምን?"

"ለምንማ የእነ ጌቶቹ ሁሉ መዋያ ማደሪያ መጥፎ ቦታ ነዋ"

"እነጌቶቹ?" በትንሹ የተቀረፀች ትልቅ ሴት የምትመስለው ልጅ ፈልፍላ ገብታ የእናቷን ቀሚስ ያዘች። ሳያት "ፈርሶ ፈዲ" ያለች መሰለኝ።

"አዎ፣ እናንተ መጥፎ መንፈስ ትላላችሁ እኛ ጌቶች እንላለን።"

"ታዲያ እነ ጌቶች ሌላ ቦታ አጥተው ነው እኔ ጓሮ፣ ራስጌዬ ላይ ውለው የሚያድሩት?"

"መምሩ?"

"ወይ"

"መስኮቱን እስኪ ዝጋው፣ ትንሽ አትፈራም?"

ዘጋሁት፣ ተዘውትሮ የማይታየው ጥርሷ ጉራማይሌ የተነቀሰ ኖሯል። "ለምን አንቺ እዚህ አተላ ምናምን ትደፊያለሽ?"

"ስላልተደፋለት ይቀራል? ሰው ይደፋል እንጂ"

"ፈርስ ካልተደፋልኝ ብሎ?"

@OLDBOOKSPDF

"እዎ፣ ለሰውም ለከብቱም ጤና አይሰጥም:: አባትና ልጅ እንዲህ ሆነው ተፈጠሩ፣ ምን ያደርጉ?"

"እነማን ናቸው አባትና ልጅ?" ወደ አልጋዪ አመራሁ::

"ብረን እና ትቻ፣ አባትና ልጅ ከብት የሚተናከሉ እንደሆኑ አታውቅም? እስኪ ሥም አታስጠራኝ!"

"አንድ ቀን በረንትቻ ስታከብሪ እስኪ ጥሪኝ"

"ምንቸገረኝ፣ የተማረ ሰው አስቸጋሪ ብዬ እንጂ አሁን ግንቦት ስለሆነ በዚህ ሰሞን አከብራለሁ"

"የት ነው የሚከበረው?"

"ብረት ውስጥ"

"ምን ምን ይደረጋል?"

"ታየው የለ?"

"ባታከብሪስ?"

"ከብቶች ጤና ያጣሉ ዳፋው ለልጆችም ተራፊ ነው:: አንድ ታማሚ ልጅኮ አለኝ::"

"እዚህ?"

"እዎ! አላየኸውም? ድንገት ነው፣ ወዲህ ወዲያ ማለት ከጀመረ አልጋ ያዘ:: ጭንቅላቱ እየተሰቀ፣ አንገቱ እየሰለለ፣ አንድ አይኑ እየሟሸሸ..."

ድንጋጤ ነው የተሰማኝ? እንጃ! መስማቴን ትቼ የህመምተኛውን ተክለ ቁመና ከማውቀው ሐሰተኛ መሲህ ጋር አነፃፀርኩ:: ስንት ሐሰተኛ መሲህ ነው ያለው? ስንት የአርማጌዶን ጦርነት?... ስንት ጊዜ ሞተን ልንነሳ ነው?

"ይሄ ሁሉ የጌቶቹ ሥራ ነው" ብላ አስሯ የቆመችውን ልጅ ራስ ታሻሽ ጀመር::

@OLDBOOKSPDF

"እራሰ ሞላላ፣ አንገተ ሰላላ፣ ቁመተ መሳሳ፣ አንድ አይኑ የተኮላሸች፣ ሌላይቱ ዓይኑ የተቅላላች፣ ክናዱ ረጅም፣ ጣቶቹ አሜጭር... እስከ ጊዜው ሀመምተኛ፣ ጊዜው ሲደርስ ጦረኛ..."

አንዳንድ ነገር እንደ ጭንቅላት ውስጥ ባይገባ ይሻላል።

"ሥራ አትሄድም እንዴ?" አለችኝ

"ስንት ሰዓት ሆነ?"

"እኔ እንኳን ኬላ ደርሼ ከመጣሁ የትና የት?"

የሰው ፊት ማየት ሊከተል ነው፣ ርዕሰ መምህሩ ለምን እንደቀረሁ ሲጠይቀኝ ኃላፊነቱን በአግባቡ በተወጣሁበት ወቅት እንደማናግረው ላልሆን ነው። ይቅርታ መጠየቅ፣ መለማመጥ፣ ምናልባትም መዋሸት ሊያስፈልግ ነው። እሱን ለመምሰል ከግድግዳ ላይ ጭድ መምዘዝ ሊያስፈልግ ይችል ይሆናል።

"ይቅር! ሥራው ይቅር!"

"እኔ ተኝተህ ማርፈድህን አላወኩም። ትምህርት ቤቱ ደጃፍ ላይ ስደርስ 'ያቻት፣ ያቻት' ይሉኛል። ምንድነው? ስል አንቺ ቤት የተከራየ ልጅ ተፈልጎ ይሉኛል። እሱማ እኔ ከመውጣቴ ቀድሞ ነው ከቤት የሚወጣ፣ የለም! እላለሁ። እዚህ ስመጣ አለህ"

"ማነው የፈለገኝ?"

"ያቺ ፀሐይ የመሰለች ልጅ ቆማ ነበረ"

ለባብሼ ወደ የዓይነምሣ ሠርመዴ ለመሄድ ቆረጥኩ። ከሦንጤ አጎንብሼ እጠጣለሁ። አንዳንዴ በውስጥ ግፊት ምንጩ ሲፍለቀለቅ ጉንጭ ላይ የሚድፎነፎን ጨቅላ የሚሰጠውን ደስታ ይችራል። ይሄ ነፃ የተፈጥሮ መደሰቻ የማን ዕቅድና ፈጠራ ነው? ነገሮች ያለ ፈጣሪ ተፈጣሪ ሊሆኑ አይችሉም መቼም። እናስ? ተፈጣሪውን ብቻ ማየት የፈጣሪን መኖር ማረጋገጫ ይሆናል? ዛፉ፣ ሳሩ፣ ኩይሳው፣ ምንጩ፣ ትላትሉ፣ ጉንዳኑ፣ ቁሜጩ፣ እራሱ ማየት መቻላችን፣ መስማት ማሽተታችን፣ ስንዳብስ የምናገኘው ደስታ ሁሉ ባለቤት አይኖረውም ማለት ውስታቢስ መሆን አይደለም? እና? ማየታችን ፈጣሪን ካላየው ማሽተታችን ላይ ካልደረሰ፣ ስመዳሰሳችን ከራቀ... የእግዚአብሔርን

@OLDBOOKSPDF

መኖር በምን ልናረጋግጥ እንችላለን? ዲቪድ ሒዩም እንዳለው የፈጣሪን መኖር የምናረጋግጠው በእምነት ብቻ ሊሆን ነው? እንኳን ባላየሁት ባየሁትም ማመን ካቆምኩ ለዘገየሁት ለእኔ እንዴት ያለ እምነት ይታዘዝልኛል?

ከቤት ወጣሁ፤ ተፈጥሮን በቁሜ ጠጣኋት!

...እዚህ መሬት አታርጥም፣ የዓይነምኳ መሬት አልተረገመችም። እሾህ አሜኬላ አታበቅልም፣ ሽኮና የሚነክስ እባብ የለም። የእባብ ጭንቅላት የሚረግጥ አዳም እዚህ አልተፈጠረም፣ እግዚአብሔር የዓይነ ምሣን ሰው በመፍጠሩ አልተፀፀተም...

የራስ ካሳን የጌሾ ጫካ ከሩቅ እያየሁ አቀበቱን ተያያዝኩት።

...መራራ ክፉ ቅጠል እዚህ የለም፣ ሥሩ መቅመቆ የሚመስል፣ መራራ፣ የፍሬው ገለባ ጉሮሮ ለመውጋት የተዘጋጀ ቀንድ ያለው ተክል ተፈልጎ አይገኝም። የሚነድፍ፣ የሚቀስፍ ለክፉ መሬት የተዘጋጀ ተሳቢ አላየሁም...

"አቶ አላአዛር" የሆስፒታል ወይም የደሞዝ ክፋይ የሚመስል ጥሪ፤ ቶሎ አልዞርኩም

"አቶ አልአዛር ቢዘን"

ይኸዋ፣ የሰማይ ቤት መዝገብ በክርስትና ስም በመሆኑ ክላይ የተላከ እንዲህ ሊጠራኝ አይችልም፤ ተፅናናሁና ዞርኩ። መነፅር ያደረገች የቀይ ዳማ ሴት። ፊቷን በሂጃብ ጠቅልላለች።

"እኔን ነው?"

"አዎ" ከእርሷ ራቅ ብሎ፣ የዳገቱ መጀመሪያ ላይ የመስከ መኪና ቆሟል። መነፅሯን አወለቀች ከፊቷ ቀድሞ የአንገቷ ጌጣጌጥ ተዋወቀኝ አንድ ነገር ታወሰኝ።

"ኤልሳ ነኝ፣ አረሳኸኝ?"

አስታወስኩ። "ኤልዛ" ብትለኝ የበለጠ ትውስታዬ ውስጥ በገባች ነበር። ኤልዛቤል፤

"ሃይ!" የምልሽ ልክና።

@OLDBOOKSPDF

"ወዴት ነው?"

"ወደዚህ፣ ወደመንገላወድ"

"ሥራ ትተህ? እንደሌላ ሥራ እንኳን አይደለም፣ በልጆች ህይወት ላይ ይፈረዳል?"

መዋሸት፣ መሸኮርመም፣ ማስመሰል… የሚጠይቀው የአሰቃ ፍጥጫ መጣ…

ኤልዛቤል ዞራ መኪናው ትምህርት ቤቱጋ እንዲጠብቃት ለሾፌሩ ተናግራ ተመለሰች። እኔን ታፋጥጠኛለች? ምን ብዬ ላባራት?

"ወደቤትህ እንመለስ፣ እኔ ይሄን ዳገት መውጣት አልችልም።"

"መጀመሪያ እዚህ መሆኔን በምን አወቅሽ?"

"ትምህርት ቢሮ እኮ ነው የምሰራው።" መነፅሯን መልሳ ደነቀረች።

ሁልጊዜ መሽሞንሞን አይሰለችም? ከሰው እይታ መደናገር ምን አላት? በዚህ ልልከፋት?

"ቤቴ ሰልችቶኝ መስሎኝ የወጣሁት" የቀረችንን እርቀት ለማጥበብ አንድ ሁለቴ ተራምዳ ድምጿን ዝቅ አድርጋ

"ብዙ ነገር ተነጋግረን ነበር፣ በምስጢሬ ላይ ያወያየሁህ አንተ ብቻ ነህ…"

"እኔ ምን ላድርግ? ከምትይው ሰው ጋር ከተያየን ቆየንኮ" የረድ ሠርዌን ሥም መጥራት ከበደኝ? ወይስ…?

"ይቅርታ አድርግልኝና እሱንም በአይኔ ማረጋገጥ እፈልጋለሁ። ሠርዌ ምዕመኖቹን በትኖ ከጠፋ ሦስት ወር ሆኖታል"

"እና?" አስመደንገጤ

"ይቅርታ ግን፣ አንተ ቤት አለመኖሩን በዓይኔ ማረጋገጥ አለብኝ።"

@OLDBOOKSPDF

የቀደመ ይቅርታ የሚከተለውን ጥርጣሬ ከስድብ ማስቆጠሩን ይከላከላል። ይቅርታና ሌባ ነህ ቢባል አንድ ሰው... ትክ ብዬ አየኋት።

"አይቼ ብቻ! የማደርገው ስለጨነቀኝ ነው።"

ምንም ሳልናገር እንገቴን እንደደፋሁ አልፌአት የቤቱን አቅጣጫ ያዝኩ።

ማሳደድ፣ ጥርጣሬ፣ አለማመን... ከጠደ ከተማ የሚመጡ ወረርሽኖች ናቸው። እንዲህ ያለ ስምለም ምድር ላይ አይበቅሉም። የሚሸመጥጡ፣ የሚለበልቡ ባህሪያት የቁሬማ መሬት ብቃዮች ናቸው።

ቤቴ ደረስን፣ ፀሐይ የመሰለች ሴት አስከትዬ ስመጣ አከራዬ ተሽከረመመች። ጎሽ! ቤቱን ወግ አሳየኸልኝ የምትል ትመስላለች። ያልተሸጎረ ደጃፌን ከፍቼ ኤልሣቤልን አስቀደምኩ።

"እሺ፣ አሁን አመንሽ?"

"እውነት፣ ይሄ ቤት አንተ የተከራየኸው ነው?" ሲላ ጥርጣሬ፣ በትንሽ ካርቱን ታጭቀው ከተቀመጡ መጻሕፍት ውጭ ምንም ማረጋገጫ የለም።

"ያንን ካርቱን ከፍተሽ እይ" አልኳት። ይሄን ያህል እንድታምነኝ መጣር አስፈላጊዬ ነው? ኤልሣቤል አልፋ ስትሄድ የቤቱ መደብዘዝና መጨለም ከእሷ መንቆጥቆጥ ጋር ተነፃፅሮ መቃብር መሰለኝ። ቁጢጥ ብላ መጻሕፍቶቹን ማገላበጥ ጀመረች። በሩ ብርሃን እንዲያስገባ በእጄ ደገፌ ቆየኋት።

«Womens evolution»? ስለምንድነው? ማለቴ እንግዳ ርዕስ ነው። የሴቶች ብቻ ዝግመተ ለውጥ አለ እንዴ?"

"Feminist የማይሉት አላቸው? እግዚአብሔርም ሴት ነው እያሉ ነው?" መውጋት ፈልጌ። ቀና ብላ አይታኝ እንዴ ራቷን አበራችብኝና አቀረቀረች።

"ስለምንድነው?"

"ሴቶች በዝግመተ ለውጥ ያካበቱት ነገር እና ከወንዶች የሚበልጡበትን ክህሎት የሚያትት ነው። በአስተዳደርም ከወንዶች ይልቅ የሴቶቹ ሠላማዊ እንደሆነ ለማሳመን ይጥራል። እንደውም

@OLDBOOKSPDF

ወንዶች ከዘራቸው ውጪ ምንም የማያስፈልጉ እንደሆኑ ነው የሚያስረዳው::"

ትስቃለች

"ምነው?"

"እኔም ረድ ሠርዌን መፈለጌ ትክክል አይደለም፣ ዘሩን ሰጥቶኝ ሄዷል ማለት ነው::"

ማለት የፈለኩት ይሄንን ነበር? ጠማማ ጭንቅላት ትርጉም ላይ መንጋደዱን ይገልፃል::

"መንታ ወንድም እንዳለው ታውቂያለሽ?" ሆን ብዬ ፍለጋዋን ላደናግርባት መነሳቴ ነበር::

ቁጢጥ ካለችበት ተነስታ አየችኝ::

በሩን ለቅቄ መስኮቱን ከፈትኩ::

"ታውቂያለሽ?"

"አውቃለሁ"

ያልጠበኩት ምላሽ ነበር:: እንዴት ወደ አሰብኩት ማደናገሪያ መሄድ እንደምትችል ግራ ተጋባሁ::

"አንተም መንታ ወንድም እንዳለህ አውቃለሁ::"

"እ?"

"አዎ"

"ስለዚህ ተልዕኮሽ ሌላ ነበር ማለት ነው::"

"አዎ"

"ኤልዛቤል?"

"አዎ!"

@OLDBOOKSPDF

እዚህ ላይ ምን ማለት፣ ምን ማድረግ ይቻላል? እራሴ ደርቄ ቀረሁ። ከጥንት ትንቢት ጋር ፊት ለፊት መገፋፊያ ሰዓቴ ደረሰ።

"ሐሰተኛውን መሲህ ታውቂዋለሽ?"

"አዎ"

"ስለዚህ ረድ ሠርዌ ጋ የሳከሽ እሱ ነው?"

"አዎ" ቁጢጥ ያለችበትን ቦታ ትታ ጠፍር አልጋዬ ላይ ተቀመጠች።

"ረድ ሠርዌም አንተም ምሁር አይደላችሁም እንዴ? ማለቴ እንዲህ ያለ ተአምር እናንተ ባላችሁበት ዘመን ሲፈጠር ትንሽ አያጓጓችሁም? ለመመርመር አትነሳሱም? ምሁርነት እኮ የብዙሃኑን የዕውቀት ጥያቄ የመወከል ኃላፊነት አለበት። ለየትኛው ህይወታችሁ ፈርታችሁ ትፈረጥጣላችሁ? አንተ እዚህ ጨለማ ጉረኖ ውስጥ መደበቂያ የዕውቀት ደረጃ ላይ ነው ያለኸው? ለምንህ? ስለምንህ ትፈራለህ?"

ፊት ለፊቷ የተለቀለቀው መደብ ላይ ተቀመጥኩ።

"ስለዚህ ከረድ ሠርዌ አልወለድሽም"

"አዎ"

"የፈለግሽው ለማሳሳት ነበር?"

"ለማሳሳት? መጀመሪያ ከአፈ-ታሪኮቹ ውጣ፣ እሱ የእኛ ታሪክ አይደለም። ማሳሳት ሳይሆን ማሳወቅ ነበር የፈለኩት።"

"ምን ልታሳውቂው?"

"እኔ ያየሁትን፣ እኔ የተረዳሁትን።"

"ምን አየሽ? ምን ተረዳሽ?"

"እኔ ካየሁትና፣ እኔ ከተረዳሁት የሆነ ነገር ለመገንዘብ መሞከር ጠመዝማዛና ያልተረጋገጠ ወሬ አይሆንብህም? ምሁር ቅድሚያ የሚሰጠው ለFirst hand Information ይመስለኛል"

@OLDBOOKSPDF

አከራዬ በሩን እያሽከረመመች ከፍታ ጠላ በፊያሽኮ አስቀመጠች። ሁለት ቅጠልያ መልክ መያዝ የጀመሩ ክቡር ዘበኛ ብርጭቆ አኖረች። ሁልጊዜም" ይሄን ላምጣ? ብላ ጠይቃ አታውቅም። አፍንጫዬን ስለድ ከላይዋ ላይ የእርጥብ ቅጠል ጭስ እየተነነ ደረሰኝ።

ኢልዛቤል አውስጧ ያለው ወቀሳ እያቁነጠነጣት አከራዬ እስክትወጣ ጠበቀች። ሆን ብዬ ተነስቼ ጠላውን በመቅዳት ሥራ አስፈርቶኛል። በአለፈ ጊዜ ተጠምደ ተጠመድኩ። የምትናገረው መብከንከን እንዳለችው የምሁር ጠባይ መሆን ባልተጨበጠ ነገር አልነበረበትም፣ ያሳፍራል። ሰይጣን ከነቀንዱ ቢመጣ የሰሙትን በማየት... ያዩትን በመዳሰስ... የዳሰሱትን በመቅመስና በማሽተት ጉዳዩን ከአፈታሪክ ነጥቆ ለሳይንስ ማቅረብ እኔ የደረስኩበት ደረጃዬ ነበር። እኔ ግን አገሬን ጥዬ፣ አጎዛዬን ጠቅልዬ በፍርሃት ፈረስ...

"እንድትገናኙ እፈልጋለሁ"

"ከማን ጋር?" ጠላውን እያቀበልኳት። አልፈልግም ትላለች ብዬ ሳስብ ቀምሳ ማስቀመጫ ትፈልግ ጀመር። ከአልጋው ወርዳ የካርቶኑን አንድ ክዳን ገንጥላ ጠላዋን እሱ ላይ አስቀመጠች።

"ከማን ጋር አልኩሽ?"

"ከፈራኸው ጋር!"

መጀመሪያ መፍራቴን መቀበል ይኖርብኝ ይሆን? ፈርቻለሁ? በእንደዚያ ያለ ሁኔታ ውስጥ እንዴት መፍራት ሳልችል ልቀር እችላለሁ?

"አንቺ አልፈራሽም?"

"እስካገናዝብ መፍራት ተፈጥሮአዊ ነው። ግን ጭንቅላቴ ውስጥ ያለው መረጃ እንደብዙዎቹ ምዕመናን ከእምነት አፈታሪክ ጋር የተያያዘ ብቻ አልነበረም፣ ስለዚህ ብዙ rational ጥያቄዎች መጡብኝ፣ እነዚያን አመክንያዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ህይወቴንም መስጠት ካለብኝ ማፈግፈግ ውርደቴ እንደሆነ አመንኩ።"

እንዲህ የሚያስብ፣ እንዲህ ይንቆጠቆጣል?

ሳቀች

@OLDBOOKSPDF

"ምነው?"

"ምንም!"

"ገገሬኛ" ፈሪነቴን ከመቀበል በላይ መሳቂያነት አለ?

"ቤትህን ስመለከተው የፍርሃትህ መጠን ምን ጉድጓድ ውስጥ እንደከተተህ ገባኝ። ቤትህን አይደለም ነፍስህን ነው ያጨለምካት። ብርሃን የሌላት ጉሮኖ ውስጥ የገባችው መንፈስህ ናት"

"ተይኝ!" ማለት አሰኘኝ። ጠላውን ተጎነጨሁ። እሷም አንስታ ፉት አለች። ፍርሃትን እንደጠላው ገፈት የምላስ ጫፍ ላይ አስቀምጦ ማፈናጠር ቢቻል? ኤልዛቤል የአፏን ውስጥ ገፈት ባንቀጠቀጡ ጣቶቿ ተቀብላ፣ ካርቶኑ ጫፍ ላይ አኖረች። እኔ በዘፈቀደ ያፈናጠርኳት ቅንጣት ገፈት የት ተሰጥፋ ይሆን?

"ጴጴብኤ ኢሲን ተበችሱ ዲሴ" አለች አከራዩ። ያንን የእርጥብ ቅጠል ጭስ የታጠነ አይቤ አምጥታ ምሰሶው ሥር አስቀመጠች። ልትወጣ ካለች በኋላ ተመልሳ ከጢብኛው ቀርሳ ከአይቡ አጥቅሳ ቀምሳ፡
.

"ጋሪዳ አከዱቢታናን ጻዶሜ" ብላ ወጣች።

እኔና ኤልዛቤል ተያየን። በሁኔታው የተደሰተች ትመስላለች።

"ኦሮምኛ ቻልክ? ምንድነው ያለችው?"

በአንዳንድ ቃላት ምሪት ምን ለማለት እንደተፈለገ መገመት ችያለሁ።

"መጀመሪያ 'እየተመላለስኩ አላጫውታችሁ አልኩ' ነው ያለችው። ቀጥላ 'ጥሩ ነው እንደነገሩ ቢሆንም ብሉ' አለች።"

እርምጃ ውስጥ ሆና ሳያት የጠፋብኝ ውበቷ እየጎላ መጣ።

"ፍርሃትህን አንድ ቀን እካፈልሃለሁ። እዚያ ፍርሃት ውስጥ እኔ የማልሞክረው ጀግንነት እንዳለ ገብቶኛል። ጅብ እየጮኸ፣ ያለ ኤሌክትሪክ ብርሃን፣ ያለ ማንበብ.. ማደር? እሞክረዋለሁ! ይቅርታ ግን፤ ፈሪነትህን ስነግርህ አለመቃወምህ በራሱ ሌላ ጀግንነት ነው።"

@OLDBOOKSPDF

አይቤውን አቅርቤላት ጎን ለጎን ሆነን በፀጥታ በላን።

"ብይ እንጂ?"

"በቃኝ፣ ጣፍጦኝ ብዙ በላሁ፣ ይልቅ ይሄን መጽሐፍ ልዋስህ። የእኛን ዝግመተ ለውጥ ማወቅ ግዴታ አለብኝ አይደል?"

"ጥሩ" እንደጠናጋሻው።

"ሾፌሩን ባላስቆየው አድር ነበር፣ የእውነት! የማያውቁትን ኑሮ ከመድፈር በላይ ጀግንነት የለም! አንድ ቀን እኔ፣ አንተ፣ ኖላዊ፣ የሠርዌ እና የአንተ ወንድሞች ሆነን እንወያያለን። ከዚህ በኋላ እንደማትጠፋ እምነቴ ነው።"

ልቤ ነው ቃል የገባላት።

"ልሂድ" ለሰለሰች ልበል?

"ልሸኝሽ?"

"አትሸኘኝ ብልህ ዝም ብለህ ልትለቀኝ ነበር?"

ተሳሳቅን!!

@OLDBOOKSPDF



# የዓይነምሣ አድማስ

ጋሽ ቢራራ ያለማቋረጥ ያወራሉ፤ እሳቸውም እኔም የጋራ ወቀሳ አለብን። የእኔን አከራይ ጨለማ እየለበሱ የሚያደርጉት ከፍርሃት አይቆጠርም?

"አፍላ ሳለን ኬላም፣ ፈረንሳይ ሌጋሲዮን ጨለማ ነበር። ቤላ ብትሄድ ጭር ማለቱ፤ መዝናናት ሲያምረን ጠላና ጠጅ ቤት ያለው ሰድስት ኪሎ ነው። ሴቶቹ ብርጭቆ ይመስላሉ።

የአከራዬ ከቡር ዘበኛ ብርጭቆ ትዝ አለኝ። 'ከጠላ የዋለ ከቡር ዘበኛ ብርጭቆ ቅጠልያ ለብሶ ጦር ሠራዊት ይመስላል።' ብዬ ሳቅ እንደ ትንታ ተናነቀኝ።

"እሺ" አልኩ ሳልወድ በግድ።

ሆድዬ፣ የጠጁ ቤት ባለቤት ትንሽ አረጀች እንጂ አሷም ብርጭቆ ናት። የጣሊያን ቅምጥ ስለነበረች ጣሊያንኛ ይቀናታል። "ባፋንኩሎ" ትልና ቂጣችንን ትረግጠን ነበር። ለኛ ታዲያ ጨዋታ ነው። እንዘፍንላታለን።

ቤቷ ሰድስት ኪሎ

እነሽምሽም ደጅ፣

ያለእግር ያስኬዳል

የሆድዬ ጠጅ" እንላለን።

አቤት ሳቅ፣ አቤት ጨዋታ፤ ሁሉም ቀረ፤ ይሄንን አውቃለሁ።

"የአከራዬ ሥም ማነው?" ነገር ነገር አለኝ እንዴ? ምናልባት ሀምራዊ ኪንታሮታቸው ኤልዛቤልን ስላስታወሰኝ ይሆናል።

@OLDBOOKSPDF

"ማን? ቃሲቱ?"

"አዎ"

"ቡልቡላ ትባላለች" ከመሬት ምናምን ፈለጉ።

"ለምን ቃሲቱ ይሏታል?" ለምን ኤልዛቤልን ዝም አልኳት?

"እንደው፣ የጨዋታ..." አቀርቅረው የጫማቸውን ጭቃ በሰንጥር መሳይ መነካካት ጀመሩ።

"ልክ ነዎት?" ልክ አለመሆንን ከመቀበል በላይ ጀግንነት የለም።

"አማላጅ ሁነኝ አለች እንዴ?" ድምፅ የሚወፍረው ምን ሲበዛበት ነው?"

"ባትልስ?"

"ሌላው ውስጥ ለውስጥ ያማታል። አቤቷ የሚሄድ የለም። አየህ? እሷ የምትሰራው ጥሩ አይደለም።"

"ቦረንትቻ..."

"አይደለም። ቦረንትቻ ማንን ይጎዳል? እኛም እናደርጋለን፤ ጤና መጠየቂያ ነው፣ የከብቶችና የልጆች።"

"ታዲያ?"

"መጥፎው ደንቃራው ነው። የልጇን ህመም ወደሌላ ሰው ለማስተላለፍ ደንቃራ ትሰራለች። ሰው ፈራ፣ የልጇ በሽታ ሀይለኛ ነው። እና ብትተውና ከሰው ብትቀላቀል አይሻላትም? የልጇን ህመም ወዳንተ ብታስተላልፍ እንደማለት ነው?"

በስንት ጊዜ እናቴ ትዝ አለችኝ? የጉልት ውሎዋ፣ የጠንቋይ ቤት አምልኮዋ... እናቴ አባቴን፣ አባቴ እህቶቼን... እየጠሩ በአይነህሊናዬ ላይ ተሰልፈው አለፉ። ቡልቡላ ቤት ያደረሰኝ ምናልባትም የቹቹን ዕዳ መክፈያ ጊዜዬ ደርሶ ይሆናል፤ አልፈራሁም።

አረቄ ጠግቤ በሚያስካካ የጅብ ሠርገኛ ታጅቤ ወደቤቴ አቀናሁ።

@OLDBOOKSPDF

"ቡልቡላ!"

"ው–ይ!" ሳትተኛ አትቀርም።

"ጠጥቼ መጣሁ!"

"እ–ሹ" እያለች ቡሉኮ አገልድማ ከቤቷ ወጣች። እጇ ላይ ኩራዝ አለ። ያልተሸጎረ ቤቱን ከፍታ አስገባችኝ። የእጇ ጥንካሬ፣ በአንድ እጇ ፋና ወጊ ሆና በአንድ እጇ የማንጠልጠል ያህል ደግፋኝ አልጋዬ ላይ ዘረገፈችኝ። ኩራዙን መስኮት ደፍ ላይ አስቀምጣ፣

"ቡልቡላ?"

"ው---ይ"

"ጠጣሁ"

"እ---ሹ! እንኳን ጠጣህ፣ እዚህ ቤት ተኮራምተህ ሳይህ ይቆጨኝ ነበር።"

"ልጆችሽን ትወጃለሽ?"

"እንዴ? ይጠየቃል? የቀይ ጥቁር የሆንኩት ለእነሱ መስሎኝ?"

"የሚያመውን?"

"አዎ፣ የበለጠ"

"ጥሩ፣ እኔ ላይ የእሱን ህመም አዙሪ፣ እኔ አልረባም! እናቱ..."

"ማሊ! ማሊ! ማሊ!..." እያለች ሙሻ አስቀሰች።

"ስወለድ ጤነኛ አልነበርኩም። እናቱ የእኔን ህመም ወደሌላ ልጅ አዙራ ነው ጤነኛ የሆንኩት"

"ማሊ! ማሊ! ማሊ!... ይሄ የእናቶች ሁሉ ጣጣ ነው። ወልደናል መቼም... ማሊ ማሊ! ኩኒ በላ አበለያን ኬናቲ"

"ስለሰከርኩ አይደለም"

@OLDBOOKSPDF

"እኔ መች ሰክረህ ነው አልኩ?" ባሽረጠችው ቡሉኮ አጎንብሳ ተናፈጠች::

"ሲሄር ሞሲሱ?"

"እ?"

"ልዳርህ? እንደእናት ደግሼ ልዳርህ?"

"ዳሪኝ ማለት በኦሮምኛ እንዴት ነው?"

"ኔሄርሞሲሳ ኢንሳ"

"እንደሱ" አልኳት ሲያቅተኝ:: ግንባሬን ሳመችኝ:: ከንፈሯ እንደናትራ ይቀዘቅዛል:: በስንት ጊዜ ናትራን አስታወስኩ?

ያኔ ሳይሆን አይቀርም እንቅልፍ የወሰደኝ:: ስነቃ ነግቷል:: ወደትምህርት ቤት ልሂድ ልቅር? የሚል ሀሳብ በራስ ምታት ጋር ተባብሮ ጭንቅላቴን ወቀረኝ:: ወደምንጭ ወርጄ በምንጩ ፍልቅልቆሽ ጉንጬን እየተሳምኩ፣ አጎንብሼ መጠጣት አማረኝ:: የሰው ጣልቃ ገብነት የሌለው ቀዝቃዛ ውኃ::

"አቶ አልአዛር"

እድር፣ ዕቁብ፣ ደሞዝ፣ ህክምና... ላይ እንደምጠራ ሆኖ ተሰማኝ::

በሩ በሽኩርምሚት ተከፍቶ ያልጠበኩት ፊት ታየኝ:: የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር::

"እንዳትሰፋ ልነግርህ ነው የመጣሁት?"

ተባረሃል ሊለኝ? ተባረሃል ማለት የሚሰጠው ደስታ አላደርስ ብሎት እዚህ ድረስ መጥቶ ሊነግረኝ?

"እንዴት?"

"ለካ ትልቅ ቦታ ያለህ ሰው ኖረሃል::

"ምንድነው የምትለው?"

@OLDBOOKSPDF

"ከትምህርት ቢሮ ትልቅ ሰው መጥቶ ተለዋጭ ደብዳቤ እስክናስገባ አቶ አልአዛርን ከሥራ ዕረፍት ስጠው:: የመንግሥት ሥራ አሰባት አሉ::" ብሎ ከግድግዳ ላይ መዘ የሚያወጣው ጭድ መፈለግ ጀመረ::

"እና?"

"ተለዋጭ ደብዳቤ እስኪደርሰኝ በቦታህ ተተኪ መምህር መድቤአለሁ::"

ግራ ተጋባሁ

"እንደዚህ ያለ ትልቅ ሰው እኛ ትምህርት ቤት ይመጣል ብዬ እንዴት ልገምት? ትምህርት ቢሮ የሚሽቆጠቆጥለት? ያጠፋሁት ካለ ይቅርታ"

"ጥሩ" መገላገል ፈለኩ

"የማደርገው ነገር አለ?"

"አለ" አበሸቀኝ

"ምን?" ተሽቆጠቆጠ

"በህብረተሰቡ ትብብር ከተገደገደ የትምህርት ቤት ግድግዳ ላይ ጭድ መምዘዝህን ተው!"

"እሺ፣ ግን ማን ነገረብኝ?"

"ሐሰት ነው?"

"እረ በፍፁም" ብሎ ከእኔ ግድግዳ ላይ የተማገረ ፍልጥ ፈልጎ ስነጠረ::

"በል አሁን ሂድ"

"እሺ" ዞሮ ሲሄድ ከኋላው አየሁት:: ጠርቼ በሩን ማዘጋት አማረኝ:: እንዲህ ከመሆን፣ ሥልጣን፣ ሥራ፣ መብላት፣ ህይወት... ለምን አይቀርም? የሰው ልጅ የትነው ያለው?... ኤልዛቤል ትዝ አለችኝ፣

@OLDBOOKSPDF

...እንግዲህ የሐሰተኛው መሲህ መዋቅር ዛሬ ለእኔ አረፍት ከነደሞዙ በመስጠት ሥልጣኑን ማሳየት ጀመረ ማለት ነው:: ከዛስ? የት ድረስ? እምን ድረስ ድብቅ ስልጣኑ የተዘረጋ ይሆን?...

...ምንጭ ሄጄ መንበጫረቅ ቢያምረኝም ሳልችል ቀርቼ እንቅልፍ ጥርግ አድርጎ ወሰደኝ::

"መምሩ?"

ባነንኩ፣ ለማረጋገጥ ዝም አልኩ:: በህልሜ ይሆን?

"መምሩ?"

"ወይ"

ድምፅ ስትሰማ በሩን ከፈት አድርጋ ጭንቅላቷን አሰገገች::

"ዛሬም ትምህርቱ ጋ አልሄድክም?"

"አዎ"

"ለምን? ረፈደ?"

"አይ"

"እህስ?" ገባች::

"የአመት ፈቃድ ወሰድኩ" የወተትና የአይብ ዕቃ በነጠላዋ እንዳዘለች ነው::

"ለምን?"

"ልትድሪኝ አይደለም እንዴ? ሠርጌ እኮ ነው::" ቀልድ እያማረኝ::

"ታዲያ አሁን ነው እንዴ? ስንት ጣጣ አለው?"

"ምን ጣጣ አለው?"

"መጀመሪያ ልጃገረድ ትመርጣለህ::" ቆም ብላ ነገር አበሳሽሁ አይነት እያየችኝ "ያቺ ፀሐይ የመሰለችውን ነው የምታገባ?"

@OLDBOOKSPDF

"እይ፣ አንቺ ታስመርጪኛለሽ"

"እንደሱ ከሆነ እንግዲ፣ ለጃገረድ አይደለም የምታገባ?"

"አዎ"

"ጥሩ የጋሽ በዳዳ ልጅ ጨዋ ለሰች። እዚህ እንደምትመጣ ፀሐይ የመሰለች በረሃብ አትገድልም። ሥራ ትወዳለች"

"መልኳስ?"

"መልክ ምን ያደርጋል? መሃን አትሁን፣ ገልቱ አትሁን እንጂ።"

"እይ መልክም ያስፈልጋል።"

"እንደሱም ከሆነ የጋሽ ቀልቤሳ ልጅ አለች። ሔለን ናት"

"ሔለን የምትባል?"

"አዎ"

"አልፈልግም"

"ተምራለች፣ ሙያ ታውቃለች፣ መልክም ብትል እንደፀሐይ ባታበራም..."

"ትቅር፣ ይሄኔ ስሟን የቀየረችው እራሷ ናት"

"በምን አወክ?" የቅቤ እቃዋን እንዳዘለች መደቡ ላይ ተቀመጠች።

"እ-ሺ፣ የጋሽ ደበሌ ልጅስ?

"የቱ ደበሌ?"

"ባለፈው ጊዜ የሞቱት? እዚህ ላይ ጫካው ውስጥ፣ እሷ ሀዘን ላይ ስለሆነች ታቆየናለች። ሌላ ይሻላል"

"ጥሩ"

"እ..." እያለች በአይነህሊናዋ የዓይነምሣን ልጃገረዶች ስታስስ አቋረጥኳት።

@OLDBOOKSPDF

"ቆይ መጀመሪያ ወጪያችንን እናስላው እስቲ..."

"ምን ወጪ አለ? ወልተኢ ወስደን..."

"የት ነው ወልተኢ?"

"የሙሽራ ልብስ የሚሰፋ:: ያበሸ ቀሚስ ከፈለግን፣ ካልሆነ የፈረንጅ አበባ ያለው፣ የሙሽራ ነጭ ሹራብ፣ ነጭ ካልሲ፣ነጭ ቆዳ ጫማ እናደርግና መሸፋፈኛዋን ነጭ ሻሽ..."

"እኔስ ምንድነው የምለብሰው?"

"እዛው ወልተኢ አለ፤ ነጭ ሱሪና ኮት፣ ነጭ ሹራብ፣ ነጭ ሸሚዝ፣ ነጭ ቆዳ ጫማ፣ ቆብ ታደርጋለህ፣ ፈረስ እንፈልጋለን::"

ያ-የአርማጌዶን ጦርነት ባይኖርብኝ እንደዚህ አድርጌ እዳር ነበር:: ሐሰተኛው መሲህ እንደማያሸንፍ እያወቀ ከሚረግፉ ኮከቦች ጋር አብሮ መቀመቅ ለመውረድ ምናለ በሰላም እንድንኖር ቢተወን? የማሸነፍ እድል ይኖረው ይሆን? ቡልቡላ ዝም ብላ ትመለከተኛለች::

"ድግሱስ?"

"ድግስ ውስጥ አንተ ምን አስገባህ? እኔ ጋ አንድ ወይፈን አለ እሱ ይበቃል"

ተነስቼ ባቅፋት? ብስማት... ገና አውቃ ሳትጨርሰኝ፣ እኔ ማነኝ? ይሄንን የዋህነት ማጣት በቁም እሳት ከመለብለብ ያንሳል?

"ልታለቅስ ነው እንዴ? በልተወው፣ የጋሽ አገኘ ልጅ አለች መልክ ካልክ እሷ ደስ ትላለች:: ማታ እንጨት ወደ ኬላ ይዛ ስትሄድ እንደዘበት አድርገን እኔ አቁሜ አናግራታለሁ:: ትንሽ ሙያ ላይ..."

"ሙያውን አንቺ አታስተምሪያትም?"

"አስተምራለሁ እንጂ፣ ወተት ማለቡን፣ አጓት እና አሬራ ማውጣቱን፣ እይብ ደሞ፣ ቅቤ..."

"ከብት የታለንና ማለብ የምታስተምሪያት?"

@OLDBOOKSPDF

"ሁሉም በአንድ ነው የሚጀምረው፣ እኔ አንዷን ጥገት እሰጣለሁ።"

ስቃይ ያለበት መውደድ ተሰማኝ።

"ስሟ የከተማ ነው? እራሷ የቀየረችው?"

"ዋጋሽ አገኞ ልጅ?"

"እ"

"እሷ እቴ፣ እናት አባት ባወጡላት ስሟ ናት። ሲፈን ትባላለች።"

ሰውነቱን ምን ተረተረው? ደረቱን ምን ደቃው? ሲፈንጋ ምን ተጎርዶ የቀረኝ ነገር አለ? ከሥሟ ጋር ምን አለካከፈኝ? ከእሷ በፊትም፣ ከእሷ በኋላም 'ሲፈን' የሚለውን ስም አለመስማቴ ለልክፍቴ መነሻ ይሆን? ሲፈን፣ ሲፈን፣ ሲፈን...

"እዎ፣ ሲፈን" አለችኝ። ጨዋታዋ ሸምጥጦብኝ ነፍሴን መተረው። በጉዳዩ ላይ መቀጠል ተሳነኝ።

@OLDBOOKSPDF



# የዓይነምሣ ደጆች

እግብቼ ይመስለኛል። ፈረስ ላይ እንደተቀመጥኩ በጎረምሳ ታጅቤ "ሆ!" ይባላል። "ሆ!" ፈረሱ በርግጎ ለልጓም እስኪያስቸግር ድረስ፤ ኮርቻው ፈረስ ላይ ሳይሆን የዓይነምሣ ሠርመዴ ላይ የተቀመጠ ይመስለኛል። ለልጓም ያስቸገረው ሠርመዴ ሲርገፈገፍ እላዩ ላይ ያሉት ጥንቾሎች፣ ሽክክዎች፣ ፍልፈሎች፣ መጻጺቶች... ይንጠባጠባሉ። እኔም ሠርመዴውን መቆጣጠር ተስኖኝ ቁልቁል መውደቅ ስጀምር እንደምንም ተመንጭቄ ነቃሁ።

ሆሆታው እንደቀጠለ ነው፤ እንዴት? ድጋሚ መንቃት ያስፈልገኝ ይሆን?

"ቡልቡላ? ቡልቡላ?" ወዲያውም ሰዓቱን ለመገመት ነበር። ቆይታ እጇን በቀሚሷ እያደራረቀች መጣች።

"ይሄ ካሊም ሙቀት እየለቀቀብኝ በቀን እቃዥ ጀመር"

"ምን ቃዠህ?"

"ሲጨፈር"

"እፏን ከልላ ሳቀች። የጥርሷ ጉራማይሌ ያምራል እንጂ አያስጠላ፣ ለምን ትሸፍነዋለች?

"ቅዠት አይደለም፣ እውነት ነው"

"እ?"

"እም፣ የጠገቡ ጎረምሶች ቅዳሜ፣ ቅዳሜ እንዲሁ ናቸው። ሌሊት በጠላ ይጀምሩና ረፋድ ላይ በጭፈራ ያውካሉ"

"ጭፈራ ምን ያውቃሉ?"

@OLDBOOKSPDF

"ያውካል እንጂ ያለወቅቱ ሲሆን!"

"ምን እያሉ ነው የሚጨፍሩት?"

"ልታስጨፍረኝ አማረህ? ማሊ? ማሊ ማል ሲጀዴ?"

"ምናለበት ቡልቡላ? እኔና አንቺ ነን ያለነው::" ወዲያው ነፍስ ባለማወቅ ሁሌም ቤቱን የምትደፍረው የመጨረሻ ልጇ መጣች:: እሷን ላይ 'ፈርሰ ፊዲ' የምትለው ይመጣብኛል:: ቦርጫ ሽንሽን ቀሚሷን ስትሉት...

"እረ ምን አልኩህ?"

"እሺ ግጥሙን ከነዜማው ንገሪኝ"

ትንሽ ተሽኮርምማ ልጇንም እኔንም ማትራ "ምንድነው የሚሉት እቴ?" እያለች ቀየችና ከእነዜማው አለችልኝ::

"ሺታዬ ኪያኮ ያሺታዬ ኪያ፣

ማልቱ ሲባሌ ቢያ፣"

"ድምፅሽ ያምራል"

"እንግዲህ ፉተታህን ተው"

"ሙች!"

"አ! አ! ሰውዬ ምን ነካ?" ልትወጣ ስትል?

"ቡልቡላ?"

"ወይ"

"ማታ ትንሽ ረበሽኩሽ እንዴ?"

"በፍፁም! አንተ ሞቅ ሲልህ ጨዋታ ብቻ ነው እንጂ..."

መደብ ላይ የተቀመጠውን ሱሪዬን ለማንሳት በውስጥ ሱሪ ስካሳ ወደበሩ ዞረችልኝ:: ልጇ አፈጠጠች ተመልሼ ከኪሴ ውስጥ ብሮች አውጥቼ እጇን ዘረጋሁላት::

@OLDBOOKSPDF

"ምንድነው?"

"የቤት ኪራዩ እና ጥቂት ደሞ..."

"አንተ ደሞ ዘመድ ሲሉህ ባዳ ትሆናለህ? ይሄ ጥሩ ነገር ነው?"

"ለራሴ ብዬ ነው። ሲያስፈልገኝ ካንቺ እወስዳለሁ። ደሞ ሥራ ስላቆምኩ..."

"ምንም ይሁን? ይሄ ቤትኮ ከተከራየ ሁለት አመቱ ነው። አንተ ባትመጣም አይከራይም። ለዚህ ብር መቀበል ግፍ አይሆንም? ጭቦ ሊታሰራኝ ነው የምትፈልገው?"

"አልገባሽም። ሥራ አቁሜያለሁ። እስካለሁ በብላሽ መኖሬ አይቀርም። ስለዚህ ዛሬ ብሩን ብትቀበይኝ የሌለኝ ጊዜ አይከብደኝም። እባክሽ ለእኔ ስትይ ተቀበይኝ"

"አይ ያንተ ነገር፣ ብቻ ይሁን፣ ታዲያ ይሄ ሁሉ ብር ነው?"

"እንደተቀማጭ ቁጠሪው"

"እየተነጋገድን ምኑን ተዛመድን? እኔ ሁነኛ ዘመድ አገኘሁ ስል እንዲህ ታደርገኝ? ማሲ? ማሲ? ማል ሲጀዱ?" እያለች ወጣች። እንዲህ ታደርገኝ? ማሲ? ማሲ? ማል ሲጀዱ?" እያለች ወጣች። ወዲያው እርጥብ ቅጠል ሲጨስ ይሸተኝ ጀመር። ጭስ ጭስ የሚል ጥቢኛ ከእርጎ ጋር፣ ወይም...

...ቡልቡላ ሌማቷን ሳይሆን ልቧን ነው የምትከፍተው፣ ወጪቷን ሳይሆን ፍቅሯን ነው ጥዳ የምታበስለው፣ ማዕዷን ሳይሆን መውደዷን ነው ሰው ፊት የምታቀርበው። ጠላ ይዛ መጣች

"የወጣቶቹን ዘፈንክ አልተረጎምሽልኝም"

"መላም የለው?" ፊቷ ላይ የሚንቀባበው ጥቁር ነገር ከፀሐይ ስትመጣ ይገንናል።

"እንዴት? እስኪ ይተርጎምና ልስማው"

"ምንድነው የሚሉት እቴ? እዎ!

ሺታዬ የኔ፣ @OLDBOOKSPDF

ማነው ካገር ያስወጣሽ ደመኛዬ1' ነው የሚሉት::"

"ታሪክ አለው?"

"ብሴት ሲጣሉ ሲፈልጉ እንደፈሊጥ የያዙት ነው:: በሬት ሺታዬ የምትባል ሴት የተቀማ ሰው የዘፈነው ነው ሲሉ ሰምቻለሁ" ብላ ወጣች::

እኔስ ሲፈንን ለሚቀማኝ የማወጣው ዘፈን ይኖረኛል? በፍቅር መትከንከን የራሱ ጥቅም ሳይኖረው ይቀራል? በፍቅር አለመነካት በደል አይሆንም? ቡልቡላ እንኳን ከዚህ ሁሉ የሥራ ናዳ በኋላ ጋሽ ቢራራን ታስታውስ የለም?

"ሸማግሌ አይተሃል?" ትለኛለች በጨዋታ መሃል::

"ሸማግሌ አይተሃል? ትናንት?" እያሰብኩ ስትጠይቀኝ ደነገጥኩ::

"አላየሁም፣ ለምኑን"

"ጃርሳ አዱ ጀለቱ" አልጎመጎመች::

"እ?" የሚበላ እንደተከደነ አቀረበች::

"ኃመ ሁጃ ሁቀብኒ ኢሲገዲ ካቴ" እየተትከነከነች መሰለኝ:: እኔ አሆን ስሜቱን የጠራሁባት?

"ማልና ጀዳን?"

"አንተ? ኦሮምኛ ለመድክ እንዴ? ጉዴ? አሁን ምን አልክ?"

"ሽማግሌው ናፍቆኛል አልሽ"

"እንደሱ አይደለም"

"እንዴት ነው?"

"አንተ አወቀው እንጂ"

"ነገ አውቀዋለሁ"

"እንዴት?"

@OLDBOOKSPDF

"ሰው አጠይቃለኝ፣ ቃላቶቹን ይገፍለሁ::"

"ማሊ? ማሊ? ማል ሲጀዬ? ማሊፊ፤ ማን እስ ቢሉህስ?"

"እንግራለኝ"

"ኡ! ኡ! ተዋረድኩ፣ እራሴ ያልኩትን ልንገር"

"እሺ"

"ይሄ ወረኛ ሽማግሌ ወሸከቶ ወሸከቶ... ይበቃል? አይበቃም?" ልቧ የተሰበረ መሰለኝ::

"ይበቃል"

"አውደልዳይ ሽማግሌ እንዱጋ... ነው ያልኩ"

ስሜቷ እንዳይነበብ ቶሎ ወጥታ ሄደች:: የእኔም ልብ ለፀብ እንደተዘጋጀ ፈረስ ደረቱን ፎገረ:: እኔም በሴቶች ላይ እንደጋሽ ቢራራ ያመፅኩ ሰሞን የስንት አወያይ ልብ ደረት ደረቱን ደልቆ ይሆን?

ተመልሳ ስትመጣ ፊቷን እንደታጠበች ገባኝ::

"አትበላም እንዴ? ነገርና ገበታ አንድ ላይ አቀረብኩልህ? የእኔ ነገር"

"አብረን ጠላውን እንጠጣ፣ የሚበላውንም፤ ካልሆነ አልነካውም::"

"እኔ በዚህ ሰዓት ስንት ሥራ አለብኝ መሰለህ::"

በገዛ ገበታዋ አግደርድሬ አብራኝ የሚበላውን ቀማመሰች:: ጠላውንም እንደ ከተሜዎቹ ቡላ ክብርዘበኛ ብርጭቋችንን እያጋጨን ጠጣን::

"አ! አባኩን በዴ" አለች የገዛ ጠላዋ ገፍትሮ ሲጥላት ሲሞክር "ወዮ፣ ወዮ... አንተ? ተዋረድኩ!"

"ትተኚያለሻ! ምናለ"

@OLDBOOKSPDF

"ልጆቹስ? ሥራውስ?" እጇን አፏ ላይ ሳትጥል ስለሳቀች ተራማይሲዋ።

"ለዛሬ ይቅሩዋ!"

"መች እነሱ ይቅር ይላሉ?" ስለወበቃት የደራረበችውን ገላልጣ ደረቷን አራገበች። በዚህ መካከል የከሰመ ንቅሳት ከአገጭዋ ጀምሮ ቁልቁል ሲወርድ በሰመመን ታየኝ።

"እንዴ? ንቅሳት አለሽ እንዴ ለካ?"

"የዛሬውን ተዉና ዘናጭ ነበርን" ብላ ስታየኝ ለማሳፈር የጨረፍታ ዓይን ጣልኩባት። "ሙት የዛሬን አትይ፣ ፎቶ ምስክር አለ። ዛሬ፣ ዛሬ የሽማግሌ መጫወቻ መሆኔን አትየው"

በመትከንከን ሀፍረቷን የጋረደች ሆኖ ተሰማኝ።

"ዛሬ ምጣድ ላይ ሳልወድቅ አልቀርም፤ ኡ! ኡ! ማሊ? ማሊ? ማል ሲጀዴ?..." ወጥታ ሄደች። የሆነ ነገሯ ቤት ውስጥ የቀረ ሆኖ ተሰማኝ።

"ማሊ? ማሊ?..." አልኩ።

ድንገት በሩን በርግዳ

"እንዲህ ሲሆን፣ ሽማግሌን ሄደሽ እነቂ እነቂ ይለኛል። አዋርጂ፣ አዋርጂ ይለኛል። ያለበት ቦታ ላይ ሄደሽ ጉብ በይበት ይለኛል"

* * *

"በርሲሳ ዓይነምሣ" አልኳቸው፣ የተቋጠረ ፊታቸው አሁን ነፍስ እንደዘራ ሁሉ ለመፍታታት ሲንቀሳቀስ ታየኝ። ኪንታሮታቸው እንደዓይነምሣ ሠርመዴ ከስሯ ባህር ያለ ይመስል ዋለለች።

"ፊርሶ አሰዱግኑ በርሲሳ በርሲሳ ወልሆጀኑ" አልኳቸው ደግሜ የቤታቸውን ታዛ ለቅቀው ወደ እኔ ሲመጡ።

"አካምጅርታ ደርገጌሳ" ስላቸው አባይነሽ ወጥታ በእጇ አፏን ሸፍና ሳቀች።

@OLDBOOKSPDF

"ጠላ ከሆነ እዚሁ አንጠጣም?" አሉ ውጭውን እንደፈሩት ሁሉ እጀን ያዝ እያደረጉ።

"አይ፣ ያቺም ታስፈልጋለች፣ እንደውም ጠጅ ብጤ ቢገኝ፣ ኮስተር ያለ። ትናንት ደግሞ ተቀብለን አይደለም እንዴ?"

"ጠጅ ከሆነ ቤላ ነው ጥሩ፣ ቤላ ሽምቡሩ የምትጥለው ጠጅ! ብቻ ዋጋው አይቻልም።"

"ይሁን፣ ታዲያ መንገዱ አይርቅብንም?"

"በዚህ በጉራራ ወንዝ፣ በራስ ካሳ ጫካ አድርገን እናቋርጣለን። ቅርብ ነው።"

መንገድ ገባን።

"ጫካው እንዴት ያምራል?" ሳንባዬን ከፍቼ ብዙ አየር ለመሳብ ሞከርኩ።

"እንደውም አሁን መንምኖ ነው። ራስ ካሣ እያሉ የረገፈ ቅጠል እያስለቅሙም ነበር። እዚህ ገብቶ የተገኘ ፍዳውን ያያል። የእኔ አክስት የራስ ካሣ አሽከሮች እዚህ አግኝተው፣ ደበደቡዋት። ያም ሳያንስ ሦስት ቀን ሙሉ ጌሾ ሲያስወቅጧት አቆይተው ለቀቁዋት። ከዛ ጊዜ እንስቶ መቅኖ ራቃት። በዚያ ሳቢያ በወሩ ይሁን በሁለት ወሩ ሞተች።"

"አባቶት ባላባት አይደሉም እንዴ?"

"ነው እንጂ፣ አባ ኬዶ ባላባት ነበሩ። ጃንሆይ ውለታ ረስተው ጆርባ መስጠታቸውን የሰሙ አሽከሮች አባቴን ለማዋረድ ያሉት ነበር እንጂ።"

"ይገርማል" መሬቱ የረገፈ ቅጠል በስብሶበት ሲረግጡት ይመቻል።

"ለነገሩ የሥጋ ዘመዴ ራስ ካሣ ናቸው።"

"እንዴት?"

"እናቴ የራስ ካሣ የሩቅ ዘመድ ሆና እቤታቸው ስትኖር ነኝን አረገዘች። ተጨነቀች፣ ተጨነቀች ራስ ካሳ ቤት እንዲህ ያለ ስህተት

@OLDBOOKSPDF

በፍፁም ተቀባይነት የለው ኖሮ በኋላ በአማካሪ ለአካባቢው ባላባት ሰጠችኝ። ራስ ካሳ ይሄንን ሲሰሙ የእኔን ቤት የልጅ መፈልፈያ ማድረግ ነው እንዴ? ብለው ተቆጡ።

"አባ ኪያ፣ አንተ ልጅ አትወድም፣ እኛ ልጅ እንወዳለን ምን ይሁንን?" አሏቸው። እኔን የአባኪያ ሚስት እናቴ ሆነው ተቀበሉ። በኦሮሞ ባህልም ተጋርደላቸው፣ ቅቤ ተቀብተው፣ በአዲስ አራስ ደንብ እየተጠየቁ ሰባት ቀን ቆዩ። አባኪያ እና እናቴ ምለዋል ይባላል።"

"ምንድነው የሚምሉት?"

"ደንብ ነው"

"የመማል?"

"እዎ፣ 'ከልጁ ብለየው ይለየኝ፣ ከልጁ ባሳንሰው ያሳንሰኝ፣ ከልጁ ብቆርጠው ይቁረጠኝ...' ብለው ይምላሉ። አባኪያ ሲሞቱ ከልጅ ሁሉ ጋር ሀብቱን እኩል ተካፈልኩ። ከተጣልኩበት አንስተው ይሄን ማዕረግ ያሳዩኝ ኦሮሞዎች ናቸው። ስጣላ እንኳን "አንተ ውዳቂ" ብሎ የሚሰድበኝ የለም። ተፈንካክቼ "ሁዱ አባ ኬቲ" ተባብለን መለያየት ብቻ።

ሀዘን ልባቸውን እንደወረረው ያስታውቃል፣ ገና ጠጁን ሳንቀምስ ጠጅ የተትረፈረፈበት ወሬ የጀመርን መሰለኝ።

"አሁን ግን ነገር እየተለወጠ ይመስላል። የኦሮሞን ደም እናጠራለን የሚሉ ወጣቶች ነውር መስራት ጀምረዋል። እኔ ከኦሮሞ በላይ ለኦሮሞ አልሞትም? እስ ተወለደ እንጂ ምን አገኘ? እኔ ግን ሰው መሆኔን ያገኘሁት፣ ብዙ ውለታ የተዋለልኝ በኦሮሞ ባህል ነው። የተወለደ የሥጋ ጉዳይ አለበት፣ እንደኔ ከወደቁበት የተነሳ ግን የማተብ ጉዳይ አለበት? የቱ ይበልጣል? ወልዶ መታረስ የአባት ነው፣ ሳይወልዱ አራስ ቤት ሰለባዕድ ልጅ መታረስና የጎረቤት የአራስ ጥሪ ማምጣት እንዴት ያለ ባህልና ማንነት ነው? የወረስኩት እኮ አባኪያ የኖረበትን፣ ወዙ ያረፈበትን ትልቁን ቤት ነው።"

ፀጥ! ብዙ ነገር ያረገዘ ፀጥታ! ይሄ ለጋስ ባህል የተገኘው ከዚህ ለጋስ ምድር ነው። እጥረት የሌለበት ተፈጥሮ፣ የቸር ማንነት ምንጭ ነው ስል አሰብኩ። የጫካውን ድባባማ ብርሃን ወጥተን ቤላን ከሩቅ የምናይበት ገላጣ ቦታ ስንደርስ ጋሽ ቢራራ አይናቸውን ደባበሱ።

@OLDBOOKSPDF

"ያው የሽምቡራ ቤት፣ የው ገና ከዚህ ጠጁ ሲሸት" ሰውነታቸው ሲነቃቃ የጨመተችው ኪንታሮት ልትፈካ ያሰበች መስላ ታየችኝ፡፡

"ጠጁ አልሸተተህም?"

"እ" አልኩ ግን አልሸተተኝም ምናልባት ኪንታሮታቸው የአፍንጫቸው አንቴና ሆና ታገለግል ይሆናል ስል አስቤ ፈገግ አልኩ፡፡

በኢየሱስ ቤተክርስቲያን አፀድ ስር ስናልፍ ጋሽ ቢራራ ግንቡን እየዳሰሱ ፊታቸውን ደባበሱ፡፡ አቆልቁለን ጥቂት እንደተጓዝን ብዙ የተሽሰሙ ፈረሶች የታሰሩበት ባለበረንዳ ቤት አገኘን፡፡ የሽምቡራ ቤት መሆኑ ነው፡፡ ትልቅ የጫጫታ እና የደማቅ ቀለም ኩሬ ውስጥ ተዘፈቅን፡፡ ያንን ኩሬ እንደሙሴ ለሁለት ገምሰን ስንሸጋገር አንዳንድ ድምፆች ተነጥለው ይፈናጠቁ ጀመር፡፡

"ሰኚ ቆንዳላ" (የባላባት ዘር!)

"ጎሚቻ ገዳ"(ትልቁ ሰውዬ!)

"ኮቱ ገረና አስ ታኢ" (ና ወዲህ፣ እዚህ ቁጭ በል፣ የጥንት ወዳጄ!)

"ኬሱማ ቀብዴ ዱፍቴ" (እንግዳ ይዘህ መጣህ?)

"አባቢያ ዓይነምሣ!" (የዓይነምሣ ባላባት!)

ጋሽ ቢራራ ለሁሉም ምላሽ እየሰጡ እኩያቸው ወደሆነ ሰው ዘንድ ሄደው ተቀመጡ፣ አጠገባቸው ያለከፍት ቦታ በመዳፋቸው እየጠፈጠፉ እንድቀመጥ ጋበዙኝ፡፡ የሽንቡራ ጠጅ በጥንቱ የጠሐያን ሊትሮ ጠርሙስ መጥቶ ተገሸረ፡፡ ጠርሙሱ ከጠጅ የዋለ ሆኖ የቢጫነትን ጠባይ አምጥቷል፡፡

ጨዋታው ሁሉ በኦሮምኛ ሆነ፡፡ አልፎ አልፎ ለእኔ የሚደርሰኝ ቃል፡-

"ሂተበቱ?" (አትጫወትም?)

"ተበዱ" (ተጫወት) ብቻ ሆነ፡፡

@OLDBOOKSPDF

ሽምቡራ ከወደ ኋዳ ብቅ ስትል ያ ሁሉ የጉብ ሠራዊት ለእፍታ ፀጥታ ይመታውና መልሶ ወደ 'እምምም--ታው' ይገባል:: ሽምቡራ ከወገብ በላይ እና በታች የአንድ ሰው ውህድ የማይታይበት ቁመና አላት:: ከወገብ በላይ ኮስማና ሆና ዝቅ ሲሉ የዳሌ ክምር! ጠጁን የሚያግዝ የአምሮት ስካር ጭንቅላትን ይመታል:: ደግሞ ለማማለል እርፋ አትቀመጥም፣ ብድግ ስትል የአዳም ዘር ፀጥታ ይመታዋል፣ ልትቀመጥ ስትመጣ እንዲሁ ለመተንፈስ ተቸግረን፣ በግዕረሞት የተማረከን መስለን ፀጥ! ነፍሳችን መለስ ስተል::

"አንድ ጠርሙስ ለሽምቡራ" የሚል ድምፅ እንደሞት ህትታ ይሰማል:: ሽምቡራ በጭንቅላቷ ብቻ ታመሰግናለች::

እኔም ከጠጁ ጥቂት ከወሳሰድኩ በኋላ ሽምቡራ መጥታ ቁጭ ስትል እንደቢንጎ ጨዋታ ተሽቀዳድሜ

"አንድ ጠርሙስ ጠጅ ለሽምቡራ!" አልኩ:: ጭንቅላቷን በምስጋና ንቅንቅ ስታደርግልኝ እኔን ማየቷ እራሱ አንድ ጠርሙስ ጠጅ እንደሚያንሰው ተሰማኝ::

"አንድ ጠርሙስ ጠጅ ድገም ለሽምቡራ" ሽምቡራ ወደእኔ መማተሯ እስካልተቋረጠ ድረስ ጠርሙስ ጠጅ ግብዣ መደርደሩን ሊቀጥል ሲሆን ጋሽ ቢራራ ጎሸም አድርገው አነቁኝ::

"አባቢያ! ኬሉማ ማልፈካቱ ዱፈ?"

(አባቢያ፣ ዛሬ ደሞ ምን አይነት እንግዳ ነው ያመጣኸው?)

"ዋን አትበርቴ ሂቤኩ ዲፈማ ጎዲፋ"

(የእናንተን ልማድ አያውቅም፣ ይቅርታ አድርጉለት)

"ደርገጌሳ፣ የእነሱ ልማድ ሌላ ነው:: በሽምቡራ ይፎካከራሉ:: ሽምቡራን የጋበዘ በልበ ድፍንነት ማንንም አልፈራም ያለወንድ ነው:: ከዚህ ሲወጡ በዱላ ይፈላለጣሉ" አሉኝ::

ጠጅ በደፈነው ልቡና "ቢሆንስ?" የሚል ሀሳብ መጣብኝ:: ለሽምቡራ የማልችለውን ምክቶሽ ጎጥሜ እያገላበጡ ቢነርቱኝ ያንስባታል? ሽምቡራዬ! ሽምቡራ ኪያ!...

@OLDBOOKSPDF

ጋሽ ቢራራ እንደሰከርኩ ገብቷቸው ሂሳብ ከፍለው ለመሄድ ተዘጋጀን። ካልከፈልኩ ብዬ ሳስቸግር "ከከፈልክ የእኔ እንግዳ መሆንህን አይቀበሉም። እንድትጋብዘኝ ብቻ ይገባህ የመጣሁ መስሏቸው ይተናኮሉሃል።" አሉኝ።

ስንወጣ የእመሻሽ ፀሐይ በዕድሜ ማለቅ ትካዜ ተጠልላ ጠበቀችን። ብርሃኗ ወደ ብጫ ወስዷት የጠጁንና የጣሊያኑን ጠርሙስ ዘዬ የተከተለች አስመስሏታል።

"ጥሩ ቀን ዋለ" አልኩ።

"ሀዴምኑ" (እንሂድ!)

ሄድን። በጠጅ ፈረስ ጫካውን ፉት ብለን ሲመሻሽ ዓይነምሣችን። ጋሽ ቢራራ ሰብቻዬ ወደ ቤቴ እንድሄድ ሲገፋፉኝ "አልችልም" አልኩ። "አድርሱኝ"

"ቀረብ አድርጌ ልልቀቅህ?"

"ጥሩ!"

ካቀረቡኝ በኋላ

"ሳታደርሱኝ አይሆንም"

በትንኮለኛ ዓይን ገረመሙኝና እንደማልለቃቸው ስለገባቸው ቀደም፣ ቀደም አሉ።

"ቡልቡላዬ ኪያ ኮ ያ ቡልቡላዬ ኪያ፣
ማልቱ ሲባሴ ቢያ፤" ልቤ በተደራረበ
ድምፅ ዘፈነላት።

@OLDBOOKSPDF



# የዓይነምሣ ጀምበር

የሸምቡራ ጠጅ እንደንዳድ የሚያቃኘር ትኩሳት ይለቃል። ከሊሙን ገፍፌ ጣልኩ፣ ምንም! ትኩሳቴ ዝም ብሎ ከእያንዳንዱ የሰውነት ክፍሌ ይፈልቃል። ከቤት ወጥቼ ታዛው ሥር ቁጭ አልኩ። መነጋጋት ጀምሯል። ዓይነምሣ እንደእኔ ትኩሳት ጭለማዋ ከሆዷ ይፈልቃል። አንድ ቀን፣ ዓይነምሣን ብቻ የሚገልፅ ዳሳሽ ልቦለድ መፃፍ አሰብኩ። ምንም ታሪክ የሌለው፣ ዝም ብሎ ያለ ገፀባህሪ መሬቷን፣ እንስሳቷን፣ ተክሏን፣ የሆዷን ውስጥ ባህሯን፣ ባህሏን... የሚዳስስ።

ሩሲያዊው ባለቅኔ ሚካኢል ሌርሞንቶብ ከመቶ ሃምሳ ዓመት በፊት የነበረችውን ሞስኮ በተመሳሳይ መንገድ ፅፏታል። "Panorama of Moscow" በሚል ርዕስ። ያንን መነሻ አድርጌ "Panorama of Ayenemessa"ን መፃፍ። ህይወትን ከከተማ ጋር አነካክሰው ለቀሩ ሰዎች ምላሽ የሚሆን ሥራ ይወጣዋል። የሰው ልጅ አካባቢውን ከተፈጥሮ ነጥሎ በሲሚንቶ ሲተካ እራሱም እንግዳ ጠባይ ወርሶ ከሰውነት ተራ እንደሚወጣ የሚያሳይ ሥራ ይሆናል።

የሌርሞንቶብ አገር ልጅ ማክሲም ጎርኪ በአንድ ግጥሙ የመጀመሪያዋን ድንግል መሬት ምንም ጥቅም እንደማትሰጥ ድንጋይ ቆጥሮ እግዚአብሔርን 'በዘበትነት ወረወርካት' ብሎ ይወቅሳል። እንደጎርኪ እምነት ምድር ከድንጋይነት የወጣችውና ወደ ዕንቁዳዚዮንነት የተሸጋገረችው በሰው ልጆች ተከታታይ ሥራ ነው። እንደማስታውሰው እንዲህ የምትል ናት።

"You? Heck-you

Just threw her like a stone in the sky

But me, I made her in to a dear emerald.

...."

@OLDBOOKSPDF

የእኔዋ ዓይነምሣ ይሄንን የጎርኪ አቋም ትነታረካለች። ፊንግ አልኩ፣ 'ሳይወጠወጥ ወስከንቢያው ቂጥጥ' ማለት ይሄ ነው። ገና ሳይፃፍ ለፍልሚያ...

ወገግ ማለት በጀመረው የዓይነምሣ ሰማይ ሥር ቡልቡላ 'ጉድጉድ' ማለት ጀምራለች። ጭሱ የሚትጎለጎል ውኃ በቶፋ ይዛ ወደ ከብቶቹ ቤት ሄደች። ሰዓቱ ብዙ የዓይነምሣ እናቶች በተመሳሳይ ትርኢት የሚያሳልፉበት ነው። ጥቂት ቆይታ ጭሱ የሚትጎለጎል ትኩስ የታለበ ወተት ይዛ ትመለሳለች።

ይኸው! ቀጥላ ያጠራቀመችውን እርጎ ለመናጥ ወደማዕድ ቤት ትገባለች። ከዚያስ? ከዚያማ እሳት አንድዳ አይብ ለማውጣት እንስራውን ትጥድ ይሆናል።

ቡልቡላ ድንገት መጥታ ወደእኔ ቤት አሰገገች። በሰላም ማደሬን ለማረጋገጥ ሳይሆን አይቀርም። ጉሮሮዬን ጠራረኩ፤ እንዲህ ትደነግጣለች ብዬ አላሰብኩም ነበር። አደነጋገጧ አስደነገጠኝ።

"ማሊ? ማሊ? ማል ሲጀዬ" ጭንቅላቷን ደግፋ ቁጭ አለች። ድንጋጤው ሲያልፍላት "በዚህ ሰዓት ለምን ወጣህ? እኔማ ካሊሙ መሬት ተጥሎ ሳይ ደነገጥኩ፣ እንደገና ድምፅ ስታሰማ ደነገጥኩ።"

"ማታ እኔን ትተሽ ሳታስገቢኝ ቀረሽ፤ ለዚህ ነው ብድርሽ"

"ሽማግሌው ካንተ በልጠ?" እሽኩርምሚታም ሳቅ እየሳቀች ተነሳች።

"መብሰጣቸውንማ ትናንት አየሁ"

"አንተም እንደሽማግሌ ነገረኛ ነህ? አሆሆሆይ" ወደ ጓሮ ሄረች። ከአፍታ ቆይታ በኋላ ትኩስ ወተት አምጥታ ቀምሳ ሰጠችኝ።

"ቁርስ እስኪደርስ ሆድ ይደግፋል"

"ወገብ የሚደግፍማ ምን ያደርግልኛል?" ዛሬ ምን ነካኝ?

"ኡ! ኡ! ኡ! አንተ? ምን ጉድ ነው የምታወራ? ሽማግሌ ሲጨቃጨቁ እዛ ምን አድርሱን?"

@OLDBOOKSPDF

የዓይኖም‌ማ ቀዝቃዛ ነፋስ ሙቀቴ ገና ብቅ ሲል እየጦለበ መድህን ሆነኝ። ለሆድ ውስጥ ቃጠሎ ወተቱን እየረጨሁ ማበራረድ ጀመርኩ። ወገግ ሲል ቡልቡላ የወተት ዕቃዋን ሸክፋ ቁልቁል ወረደች። እኔም በሙቀት የተጓደለ እንቅልፌን ላሟላ ገባሁ።

* * *

ከህልም ወደ ህልም የተሸጋገርኩ እንጂ የነቃሁ አልመሰለኝም። ታዲያ የማየው እውነት ከሆነ እንዴት ጥሩ የለበሰች ሴት እኔ ቤት ምን ታደርጋለች? ከኋላዋ ቡልቡላ መዝጊያውን ደግፋ ቆማለች። እውነትና ብርሃን አጥበረበሩኝ።

እራሴን አረጋግቼ ስመለከት ነፀብራቅ መሆኗን ተረዳሁ። የሚንቀለቀሉ ከንፈሯና ዓይኖቿ ጨርሰው ሞተዋል። ፊቷ ላይ ከፍተኛ ሀዘን ወድቋል። አይኔን ጨፈንኩ። የከሰል ጭስ እንደጠጣ ሰው አሽልቤ እስከወዲያኛው ባልነቃ መረጥኩ። እኔ ብሎ ለቡልቡላ ተቆርቋሪ።

"ስንት ቦታ ተንከራተትኩ? ስንት ሰዎች ጠየኩ?"

አየኋት፣ የያዘችውን የላስቲክ ዘንቢል የቆመችበት ለቃ ወለሉ ላይ አስቀመጠችው። መጥታ አልጋ ላይ ስትቀመጥ የቤቱ ብርሃን ቀነሰ። ቡልቡላ መዝጊያውን ለቅቃ ሄደች ማለት ነው። ነፀብራቅ እግሯን እንስታ አልጋው ላይ አውጥታ ጀርባዋን ስጥታኝ ጋደም አለች። ሰውነቷ ያተኩሳል፣ በዓይኖም‌ማ ብርድ ሰውነት የሚግለው የሽንቡራን ጠጅ በጠጡ ማግሥት ብቻ ነው። እንዳልነካት ተጠንቅቄ ትንፋሼን ዋጥኩ።

"ለምን? ይሄ ሁሉ ለምን?"

ሽቶዋን ምን አበነነው? የሚያውቃት አፍንጫዬ አጣት።

"እራስህን ትጠላለህ?"

"እንዴት?"

"ቢሆን ነው እንጂ፣ ሰው እንዴት ይሄንን ያሽቆለቆለ ኑሮ ፈልጎ እዚህ ድረስ ይመጣል? ኩበት፣ ኩበት ትሸታለህ እኮ፣ የወለልህን ሽታ ሆነሃል።"

@OLDBOOKSPDF

እኔ አልታወቀኝም:: እውነት ኩበት፣ ኩበት እየሸተትኩ ነው ሽምቡራን የተመኘሁት? ሳቅሁ

"ትስቃለህ?"

"እዚህ መሆኔን እንዴት አወቅሽ?"

"ተንከራትቼ፣ ተንከራትቼ እዚህ ደረስኩ:: ደስ አለህ?"

ዝም!

"አንተ ምንም አያስደስትህም" ጫንጫን እየተነፈሰች ቆይታ...

"አንድ የፖስታ ግራጁዌት ተማሪ ስለአሳይመንት ሲያናግረኝ ቢሮ መጥቶ 'ጓደኛሽ እኛ ጋ ሥራ ጀምሯል' ብሎ ነገረኝ:: የአንተን ክፋት፣ የእኔን ጉዳት የተመለከተው አምላክ ቢሮዬ ድረስ..."

ጠጅ ቢሸታት ሌላ የወቀሳ አጀንዳ ታገኛለች በሚል ዝም አልኩ::

"ቆይ ይሄንን ቤት ተከራይተኸው ነው? ወይስ አያትህ በግድ እንድትኖርበት በግዛት አውርሰውህ?" ከንፈሯና አይኗ እንደአልለእዞር ከሙታን መንደር ተጠርተው መንቀሳቀስ ጀምረው ይሆን?

"ንገረኝ እንጂ..."

ነገር ማቅለያ ስፈልግ ሩሲያዊው ባለቅኔ ሌርሞንቶቭ የገጠማት ትዝ አለችኝ::

"My house is every where

It's roof reaches to the very stars

From one wall to the other runs a road that can be measured by the soul.

But not by the eye"

"የከንቱዎች፣ የተሸናፊዎች ግጥም ነው:: ቤትህ የትም የሚሆነው መፈጠርህ ላይ ምንም ሳትጨምር ስትቀር ነው:: እንደተፈጠሩ ኖሮ @OLDBOOKSPDF መሞት የሰው ልጅ ሳይሆን የእንስሳት

ሶባ ፈንታ ነው። የቤትህ ከዳን ኮከቦችን የሚዋሰነው መኖሪያህ የትም የሚሆነው እንስሳ ስትሆን ነው።"

"እሪፍ ጭንቅላት አለሽ፣ እስኪ ድገመው ሳትይ በአንድ ጊዜ ቀርፀሽ..." አበዛሁት፣ ጠጄ። ከማውራት ከተቻለ ማቀፍ...

"እረፍ፣ እጅህን..."

ሽምቅቅን ቀመስኳት። ተነስታ እግሯን አወረደች። መልሳ ሰቀለች። ትራሱን ስባ ግድግዳውን ተደግፋ ቁጭ አለች።

"እየተያየን እንድናወራ እፈልጋለሁ"

ዝም

"ተነስና ፊት ለፊቴ ቁጭ በል"

ዝም። እራሷ ወደግርጌ ወርዳ ፊቷን ወደ እኔ አዞረች። በአይኖቿ ልትግጠኝ ተዘጋጀች።

"መብራት የለም?"

"የለም"

"ጠፍቷል? እስኪ ሞክረው"

"መብራት የለም፣ ኩራዝ ነው"

"Really? So shameful, any ways አንተን ፍለጋ የተንከራተትኩት ትክክል ነበር። አንተን የሚያውቁ ሰዎች አንድም አልቀሩኝም።" የተሰማኝን ለማረጋገጥ ፋታ ወስዳ አየችኝ። ቀልማማ ከንፈሯና አይኖቿ መንቀልቀል ጀምረዋል።

"በአካል ያሉትን፣ የሌሉትን ሰዎች ሁሉ ታሪክ አዳምጫለሁ። የሁላችንም ቁስል ተመሳሳይ ነው። እንባችን ቢሰፈር እኩል ነው። ሲፈን... ለገነት... ሲሲ... ናትራ... እኔ... እናትህ... አባትህ... እህቶችህ... ጠናጋሻው... ቿቿ... የቿቿ እናት... ብዙ የፈሰሱ እንባዎችን እንደመንደር ውኃ መውረጃ ያለምንም ሀፀት ተሻግረሀቸው አልፈሃል።"

@OLDBOOKSPDF

ምንድነው? የነፍስ ደረመኔ ማሳከክ ጀመረኝ:: ነፀብራቅ ይሄው ናት:: ለበቀል የተሳለች ሰይፍ ናት:: በቀል ነው ግን?...

"ብዙ ያልቋጨኸው ህይወት ውስጥህ አለ:: ደፋር አይደለህም:: ጀግንነት ይጎድልሃል:: መቋጨት ድፍረት ይጠይቃል:: በሴት ህይወት ውስጥ ጥያቄ እንደሆንክ ማለፍን ደጋግመሃል:: መቋጨት ማግባት አይደለም:: የምትሸሸው ትዳርን አይደለም:: ህይወትህ እንደ ጆሮ ጌጥ ተንጠልጥሎ ትወዛወዛለህ:: ለማረፍ አልታደልክም:: ይሄ ደሞ ከሌላው ይልቅ በራስህ ላይ ጨካኝ መሆንህን ይናገራል:: ከእኛ ጋር ሳይሆን መጀመሪያ ከራስህ ጋር ታረቅ:: ሌላውን ሳይሆን መጀመሪያ እራስህን መጉዳት አቁም..."

የነፀብራቅ ንግግር "ጭ---ው" በሚል ድምፅ እየተደረበ-እየተደረበ መጥቶ ጨርሶ ተዋጠ:: ከንፈሮቿ ሲቆለማመጡ ይታየኛል:: ከድክመቴ ጋር ፊት ለፊት የሚጋፈጥ ማነው? ነፀብራቅ እንድታጠቃኝ ተመቻችቼ ጠብቄአታለሁ:: የምትናገረው እውነት ነው፤ የጠራቻቸው ሰዎች በሙሉ በእኔ የተጎዱ እንደሆኑ ግን አስቤው አላውቅም:: ልበድፍን ያስመሰለኝ ይሄ ነው:: ሰው ለሆነ ሰው ለራስ ይቅርታ ከማድረግ የከበደ ነገር የለም:: ነፀብራቅ ያሰለችውን ቦታ ሁሉ ላስስ? ያገኘቻቸውን ሁሉ ላግኝ? እንዴት በደፈናው ለራሴ ይቅርታ አደርጋለሁ? ከእንግዲህ አይነምሣ የወቀሳ ሥፍራዬ መሆኗ ነው:: ነፀብራቅ ላገኘቻቸው ወቃሾች በሙሉ የት እንዳለሁ ትነግራለች:: አበቃ!

@OLDBOOKSPDF



# ከዓይነምሣ

አገርን እንዴት ይሰናበቷል? ከዛፉ ጋር ተቃቅፎ ይላቀሷል? ወይስ ከምንጩ ጋር ይጨማጨሚል? በደመናው ይሸኟል? ወይስ ሽታውን ማስታወሻ አድርጎ በጉዲፈቻ ያሳድጓል? ህመሙን ለመዋረስ ይጋጩዋል? ከመንፈሱ ይዋረሱዋል?... ወይስ?...

ነፀብራቅ ነፍስና ሥጋዬን ገድላ፣ ለጭዳ እንደታረደ ከብት የተጋደምኩበት ተራምዳኝ ሄደች። እውነቷን ነው፣ እንደ አዬ በካፋ ሙከት የገዛ መታረጃዬን ካራና የገዛ ማርመጃ አዋዜዬን አንገቴ ላይ አንጠልጥዬ የምዞር ከንቱ ነበርኩ። ያለአንዳች ውሸት መቀላቀል በገዛ እውነቴ የገዛ አንገቴን ሰጥቼ ታረድኩ። ያለበዳይ ተበደልኩ፣ ያለአጥቂ ተጠቃሁ፣ ያለገፊ ተገፋሁ... ማን ላይ አለቅሳለሁ?

"ሰው በድዬ ነበር እኔም እንደዋዛ፣

ቁናው ቁናዬ ነው ትንሽ ዙሩበዛ፤

ያሉት መኪንንት ማን ነበሩ?

ሰውኃ ሙላት እንደዘፈነው አዝማሪ የሰው ዘር ተደበላልቆ ሲጎርፍ እያየሁ ዳር ይገፔ ስሜቴን ብቻ የሚያገለግል "ዘፈን" ሳቀንቅን ኖሬአለሁ። እናቴ፣ አባቴ፣ እህቶቼ፣ ሲፈን፣ ሰገነት፣ ሊሊ፣ ጠናጋሻው፣ ቹቹ፣ እናቱ... በእኔ ህይወት ውስጥ የስሜትና የላቦት አስተዋፅኦ እንደሌላቸው ሁሉ እንደ ሽንኅበቴ ፀጉር ተላጭቼ ጥያቸዋለሁ። ናትራ፣ ነፀብራቅ፣ ዶክተር አሮን፣ ረድ ሠርዌ፣ ጃክ፣ አፈትጉሣን... በእኔ ህይወት ውስጥ ማግኘት የሚገባቸውን አጥተው በማኅበራዊ ህይወት ኪሳራ ላይ እንዲወድቁ የፈረድኩባቸው ናቸው። አብሮ መኖርን የሚሰነክለው ጠባዬ እስከመቼ ይቀጥላል? ቡልቡላ፣ ጋሽ ቢራራ፣ ዓይነምሣ... ለእርድ እንደቀረበ ከብት ጥሩ ጥሩ ፀባይ እየሰጠሁ አንጉል ተስፋ ያሰባኟቸው ናቸው።

@OLDBOOKSPDF

ቡልቡላ ፊቴ መጥታ ቆመች፡፡

"ና ከብቶች ቤት"

"ምነው? ለምን?"

"ለከብቶች ጠባቂ ተደግሷል፡፡ ጥሪኝ አላልክም?"

"እሺ እመጣለሁ"

"ሴትዮ ዕቃዋን ጥላ ሄደች?"

ወደ ወለሉ ተመለከትኩ፡፡ ነፀብራቅ ያመጣችውን የላስቲክ ዘንቢል ትታው ሄዳለች፡፡ በዚህ ሰበብ ዳግመኛ ልትመጣ አስባ ይሆን? ስጋት ቢጤ፡፡

ቡልቡላ ከብት ለሚተናከሉ መንፈሶች መለማመኛ ቦረንትቻ ደግሳለች፡፡ አባትና ልጆቹ ተፃራሪ መንፈሶች ከእኔ የበለጡ ተተናኳዮች ይሆኑ? እኔ ስታከል አባትና ሁለት ልጆች መሆናችን ነው፡፡ ቦረን፣ ታለና ትቻ፡፡

ወጥቼ ወደ በረቱ ሄድኩ፡፡ ቦረንትቻ የቅድመ እያት፣ እያት፣ እያት… የልምምጥ ሥርዓት! ከመንፈስጋ በጋራ መቋደስ፡፡ በረቱ ልዩ ጠረን ተላብሷል! ከብቶቹ ሁሉ ግንባራቸው ላይ የሚታይ ቅቤ ተለጥፏል፡፡ ቡና እየተፈላ ነው ብዙ አይነት ቆሎ እና ቂጣ ተደርድሯል፡፡ ቦረንና ትቻ በበረት መስኮት ገብተው ከብቶች ስለሚፃረሩ መስኮቱ ሥር ከሁሉም አይነት ምግብ ተቀምጦላቸዋል፡፡

የቡልቡላ ሦስቱም ልጆች አሉ፡፡ በዚህ ሰዓት አደብ መግዛትን በድግግሞሽ ስለለመዱት አይናቸው እንኳን አይርገበገብም፡፡ ትልቁ ልጇ የአንገት ልብስ ተከናንቦ ወደ አንድ ወገን ጋለል ብሎ ተቀምጧል፡፡ ጭንቅላተ ሞላላ፣ አንገተ ሰላላ፣ አንድ አይኑ የተኮላሸች፣ ሌላይቷ አይኑ የተቅላላች ናት፡፡ እናስ? አሁን እኛን አስከትሎ አርማጌዶን ላይ ለመዋጋት ያሰፈሰፈው ሐሰተኛ ነብይ ካልተሳካለት ይሄኛው የቀጣዩን ትውልድ ሐጢያተኞች አሰባስቦ ይዋጋል? እግዚአብሔር እንዴ ድል አድርጎ መቼ ያርፋል? ሐሰተኛው ነብይ በየትውልዱ ይነሳል፣ ከፍተኛ ጦርነት ያስነሳል! ፈጣሪ በየዘመኑ ይገላላል?

@OLDBOOKSPDF

ማሙዬ እስ ታኢ" አለችኝ ቡልቡላ በልጆቿ! መደዳ የተደለደለ ትራስ ብጤ ላይ።

ተቀመጥኩ።

እጣን የሩመ ከሰል ላይ በተነችና አልጎመጎመች። የቦረንትቻ ሥርዓቷን ስታካሂድ ያቺ የማውቃት ቡልቡላ አልመሰለችኝም። ቤቱ እንደዓይነምሣ ሠርመዶ በማያስተያይ ጭጋግ ተሸፈነ። በዚህ አለመተያየት ውስጥ አባትና ልጅ መናፍስቱ ብቅ ብለው ምሥእቸውን የሚቋደሱት። እምነን ከገበርንላቸው መደባበቁ ለምን አስፈለገ? እንደ እኔ መወቃቀሱንም ሆነ መመስጋገኑን አይፈልጉት ይሆን? እርኩስ ሆነ ቅዱስ ማን የነፀብራቅን ወቀሳ ይቋቋማል? እኔ ከሥረ መሰረቴ አልተናጋሁም? ከተበቀሉ አይቀር እንዲያ ነው። በቀሏ ያበቃ አይመስልም፣ የላስቲክ ዘንቢሏን ተከትሎ ሌላ ጥቃት ትሰነዝርብኛለች። አባትና ልጅ መናፍስት ሳይከዳዱ አብረው ከብቶች ሲዓረሩ ስንት አዝማናት አሳልፈው ይሆን? በአስራታቸው ሆነ በግብራቸው ሳይጣሉ። እኔ ግን አባቴን፣ እናቴን፣ እህቶቼን ሥጋነት ሳያገደኝ..."

ጉም በመሰለው ጢሳ ጢስ ውስጥ እጅ ብቅ ብሎ ጠራኝ። አላመንኩም እነዛ ተንኮለኛ አባትና ልጅ መናፍስት በእለታቸው በጠቋር ምክር ጠርተው ጉድ ሊያደርጉኝ ቢሆንስ? መለስ ብዬ ቡልቡላን ስመለከት ጠሪዬን እጅ አይታ ኖሮ በጭንቅላቷ 'ሂድ' አለችኝ። ተነስቼ ወጣሁ።

ጋሽ ቢራራ ሐር የመሰለ ጥቁር በግ የፊት እግሩን ይዘው አገኘኋቸው።

"አሸከመኝ" አሉኝ

"ለምን? የት ልትወስዱት? እኔ ላድርስልዎት?" ሁሉም ጥያቄ የማያስፈልግ መሆኑን ከጋሽ ቢራራ ፊት ተረዳሁና የበጉን የጀርባ ቆዳ ጨምድጄ ከፍ አደረኩ። ጋሽ ቢራራ ትከሻቸውን አሞጥሙጠው በጉን ክብከብ አደረጉና ወደኋላቸው ፊታቸውን መለሱ ሄዱ። ሄዶ ብዬ ወደውስጥ ልገባ ስል በረቱን ዞረው በተቃራኒ በኩል በጉን እንደተሸከሙ መጡ። አልፈውኝ ድጋሚ የሄዱበትን መንገድ ተያያዙት። እንደመ[illegible] የሲና በረሃ ጉዞ፣ አንዱን ተራራ አርባ አመት እንደዞረ... መጡ፣ [illegible] ሄዱ፣ ትንግርት ሆነብኝ፣ መጡና በጉን አወረዱ።

"ምነው ጋሽ ቢራራ፣ መንገዱ ጠፉዎት?"

@OLDBOOKSPDF

"ደንብ ነው"

"የምን ደንብ?"

"የቦረንትቻ፣ ታቦት ቤተክርስቲያኑን ሦስት ጊዜ እንደሚዞር የቦረንትቻ እርድ በሬቱን ሦስት ጊዜ መዞር አለበት:: አንገቱን እንዲሁ ያዝልኝ"

የተጋደመውን በግ መንጋጭላውን ከመሬት ጋር አጣብቁ ያዝሉላቸው:: ባረኩት:: ትቻቻው ልገባ ሥል፦

"እግዘኝ እንጂ" አሉኝ:: በጉን ሲገፉ የኋላ እግር ያዝኩላቸው

"አባወራ የሚያደርገውን ሁሉ ለቃሊቲ አደረኩ:: ከእንግዲህ የዚህ ቤት አባወራ መሆኔ ነው:: መቼም ገሴ ገብቼ በሰፈር ጎረመንሳ ሲዘፈንብኝ አልኖርም:: እዛው እኔ ቤት ትግባ መሰለኝ:: ይሄ ሁሉ ያንተ የጠጅ ደባ ነው:: ደህና የሸሸሁትን...."

በጉን እየበለቱ እያንዳንዱን ብልት ወደ ምኒልክ ትሪ ከመጣላቸው በፊት እየቀነጠቡ በገል ላይ ያጠራቅማሉ

"የገሉ ቅንጥብጣቢ ሥጋ ለምንድነው?"

"ለጌቶቹ ነዋ፣ የእነሱ ግብር ነው::"

እነሱ በዚህ በንግሳቸው ሰዓት እዚህ ይኖሩ ይሆን? ካሉ የቱጋ ይሆናሉ? እንደውሻ ጭራቸውን እየቆሉ የጋሽ ቢራራን እጅ ይመለከቱ ይሆን? አይ-ቦረንና ትቻ!

"የሴት ዘዴ ሌላ ነው! ሆነብላ የቦረንትቻ በግ ገዝታ ጠበቀችኝ:: አባወራ የሌለበት ቤት:: ትቼ ልሄድ ስል 'አንተ ነህ የምታርደው' አለችኝ:: ያው በሌላ አነጋገሯ ገሴ ገብተሃል ማለት ነው::"

"ገሴ ምንድነው?"

"ገሴ ሴት ቤት መግባት ነው:: በኦሮሞ እንደትልቅ ጥፋት ይቆጠራል::" የበጉን ሥጋ ሳፋ ከድነው ምድጃ ማደራጀት ጀመሩ:: አመድ አንጥፈው ጉልቻ ጎለቱ:: ወደ ጓሮ ዘወር ብለው አሮጌ ብረት ምጣድ አምጥተው ጣዱ:: የማግዛቸው ግራ ገባኝ:: ያለሥራ ከእሳቸው ጋር ወዲያ ወዲህ ማለት ጀመረ:: ጠቋርን እንደማገልገል ይቆጠርብኝ

@OLDBOOKSPDF

ይሆን? ገና ከሀሰተኛው መሲህ ጎን ሆኜ የእግዚአብሔርን ሰልፍ ልገጥም አይደል? መቼነው ግን "ታጠቅ፣ ዝመት" የምባለው:: እዚህ ጦርነት ውስጥ የእኔ ፋይዳ ምንድነው? እንዴት ያለ ጥቅሜን አስከብራለሁ? አሁን ካሉኝ የኑሮ መደብ በላይ ከፍ ብሎ መገኘት እፈልጋለሁ? ሀብት፣ ንብረት፣ ሥልጣን፣ ክብር የምሻ ነኝ?

ለመቀመጫነት ማዕዘን ያለው ድንጋይ ተደርድሮ አሮጌ ጨርቅ ተደለደለበት:: አንድ አምስት የሚሆኑ እንግዶች ተገኙ:: አንዱ ሙሉ ብጤናቸው:: በኦሮምኛ ጋሽ ቢራራን አናግረው በአሽሟጣጭ ዓይን ይገረምሟችዋል:: ፊታቸው አዲስ የጭቃ ምርጊት ይመስላል:: ጭድ በመሳሰሉ ሰንበሮች የተሞላ ነው:: ያ ርዕሰ መምህር ቢያገኛቸው ጭዳቸውን ለመምዘዝ አስር ጊዜ እጁን ወደ ጉንጫቸው ይሰድድ ነበር::

የተሸፋፈነ ድፎ ዳቦ ቀረበ፣ በቂጣ፣ በሸንብራ እና በጠመኸ ቆሎ፣ በኑግ ልጥልጥና በጉሽ ጠላ ታጅቧል:: ከሁሉም እየተቀነጠበ የክብቶቹ አዛባ የሚለቀቅበት ፉካ ላይ ተበተነ:: ምርቃት የሚመስል ነገር በኦሮምኛ ይኾጎደጎዳል:: የጭሳጭስ ዘር ተደበላልቆ ጣዕም ያለው ሽታ ለመናፍሥቶቹ በግብርነት ቀርቧል:: እንግዲህ ቦረንና አባቱ ትቻ ክብቶቹን ሳለመገረር፣ ሳለማስናከልና አመላቸውን ሳለማክፋት ቃል ይገባሉ:: ይሄንንም ለላካቸው ለጠቋር ሪፖርቱን ያቀርባሉ:: እነሱ በመቅመስ የባረኩትን እኛ እንቋደሳለን:: የረጅም ዘመን የዕድሜ ባለፀጋ ሥርዓት አምልኮ ላይ የታደምኩ ሆኖ ተሰማኝ::

ጋሽ ቢራራ የሰው ዓይን ቢበላቸውም እንደ ትንሽ ልጅ ከቆሎው ያዘግናሉ፣ ከጉሽ ጠላው ይቀዳሉ፣ ከሥጋው ያስይዛሉ:: እኔጋ ሲደርሱ ማንቆርቆሪያውን ገፋ እያደረጉ ዋንጫዬን ሞሉና

"ነምኚ ሰበርባዴ ቱሬ" አሉኝ:: ሰው ፈልጎህ ነበር እንዳሉ ገብቶኛል::

"ማናት? የትናት?..."ሁሉም ጦሩን እያሾለ የሚፈልገኝ በወጥመድ የተያዝኩ አውሬነት ተሰማኝ::

"ጃማ"

ግራ ተጋባሁ

"ነማኢጆ ዳሜ"

@OLDBOOKSPDF

"ማልና ጆዳን?"

"ያልኩማ ሰውዬ ዓይነሥውር ነው።"

"ዓይነ ሥውር?"

"አዎ፣ ጨዋታ ይችላል ሰውዬ፣ ሰው ሁሉ እንዲሁ ሲስቅ ዋለ። አንተን እፈልጋለሁ አለ! ሰው ሁሉ በደሞዝ ሰሞን ሲያስቸግር ስለመሰለው ችላ አለው። ተነስቶ ሄደ" ብለውኝ ሄዱ።

ዶክተር አሮን እኔ ዘንድ ያስቀመጠውን ብር ሰምቶ ለመጠየቅ ሲፈላልገኝ ቆይቶ አሁን ያለሁበትን የተጠቀመ መሆን አለበት ስል አሰብኩ። ብሩ እንደሆነ ነፀብራቅ ዘንድ እንደተቀመጠ ቀርቷል። ይዘውት ቢመጡ ምን አለው ነበር? የቀረኝን የደሞዝ እርጋፊ ሰጥቼው ይጠቀመው ኖሯል?...

ምሽቱ እየገፋ ሲሄድ ከጋሽ ቢራራ ጋር እኔ ታዛ ሥር ቁጭ ብለን ድግሱ በሰፊው ቀጠለ። የቦረንትቻ መስዋዕት ቢተርፍም ወደቤት ስለማይገባ ቡልቡላ የበጉን ጥብስ ከነብረት ቁናው እፊታችን አስቀመጠች። ከትካዜ ጋር፣ እንደ ሐሰተኛው መሲህ መሸነፋችንን እያወቅነው ጥብሱን ገጠምን። ቆይቶ በጉሽ ጠላው ፈንታ የተደበቀ ጠርሙስ አረቂ መጥቶ ፊታችን ላይ ተገሸረ። "ይሄኔ የበግ ጥብሱ በእኛ የመሸነፉ ነገር እርግጥ ሆነ።

"የጉሽ ጠላ ወሬ ጉሽ ነው። ዝም ብሎ ሆድ ይነፋል" አሉ።

እውታቸውን ነው። እንደአረቂ የተነፋ ሆድ ሲበትን ደስ የሚያሰኝ ወሬ ተጀመረ።

"ሽምቡራን ድሮ አውቃለሁ፣ እናቷንም።"

ድምፃቸው ለበገና ይቀርባል። ከመልዕክቱ ባሻገር በዘለሰኛነት ሆድ ያንቦጫቡጫል። ቡልቡላ ሱስ የሆነባት ይሄ የበገና ውርርስ ያለው ድምፅ ይሆን?

"ያኔ ሽምቡራ ተደብቃ፣ ጓዳ ጓዳ ትል ነበር። እናቷ እንዳሁኑ እንደሽምቡራ እየተንጎማለለች በጎረምሳ ነፍስ ትጫወታለች። እኔ ክብሬን ጠብቄ ስወጣም ስገባም ድምፅ አላሰማም። ለካ የሽምቡራ እናት ከጎረምሳ ሁሉ ተለይቼባት ኖሯል። ስለእኔ ትጠይቃለች። ይነግሯታል።

@OLDBOOKSPDF

"ጉሉማ የባላባት ዘር ነው፣ ጓዳ ገብቶ ይጠጣ ትላለች:: ዘይ። ነው:: ገባሁ፣ ጓደኞቼንም አስገባሁ:: ወሬ፣ ወሬ ሲሰማ ጎረምሳ ሁሉ ለፅብ ተነሳሳ:: በዚህ መካከል አንድ ቀን ደረሰኝ:: መኝታዋ በጓዳ አልጋ ስለሆነ ተከተልኩ:: አንገራግራ፣ አንገራግራ ሰጠችኝ:: 'የትልቅ ሰው ዘርነህ እንዳትነግር' አለች ጎረምሳ አፉ ያርፋል? ነገርኩ:: አገር ተዳረሰ 'አባቢያ ኮማሪት ቤት ገሌ ገባ' ተባለ:: ያኔ ኩራት አለ፣ ኩራሁ:: እስቲ ንገረኝ የሚል በዛ:: 'ገነት ነው' አልኩ::" ቡልቡላ ስትመጣ:: ወሬ ይቋረጣል::

"ጃርሳ አዱ ጀለቱ" ትልና በተንኮል ታያቸዋለች:: "የሽምቡራ ነገር አነሳህ?"

"ኧኔ አላነሳሁም?"

"አታፍርም ግን፣ ሽማግሌ?" የቀልድ ነው:: እሷን ትተው

"ዋናውን ሳልነግርህ?"

"ኡሺ"

"ሂጂ እንጫወትበት፣ ቃምቡራ አቅርቦ አትጫወቱ አለ እንዴ?"

አፏን በእጇ ሸፍና እየሳቀች ትሄዳለች::

"ያኔ ሽምቡራ ለግላጋ ወጣት ናት:: እንዳሁን አይደለችም:: ትሳላከናለች:: ጠጁንም የምታመጣልን እሷ ናት:: 'አባቢያ' ትለኛለች:: ጓደኞቼ ሲተናከሉ እከላከልላታለሁ:: በኋላ ወሬ መጣ:: የሌለ ነገር:: አባቢያ ሽምቡራን ነካ ተባለ:: ስሰማ ኡ ኡ! አልኩ::"

"ውሸት! ውሸት!" እያለች ቡልቡላ ከተደበቀችበት ወጣች:: "እሳት የሌለበት ጭስ ይመጣል? እንደዛ ነው::"

"ማሊ? ማሊ?...." አሏት:: ሁለቱ በፍቅር ሲኮራኮሩ ደስ የሚል ስሜት ያድርብኛል:: ቡልቡላ ወሬውን በኦሮምኛ ቀጠለችው:: ጋሽ ቢራራ እየተሽቀዳደሙ አፏን ይይዛሉ:: አፏን ልታስለቅቅ እየተወራጨች ጭናቸው ላይ ትቀመጣለች::

"እረቂ አቅርቦ አትጫወቱ አለ እንዴ?" አልኳት ለወሬው መጨረሻ ጓጉቼ:: ከጭናቸው ላይ ተነስታ እየሳቀች ሄደች::

@OLDBOOKSPDF

"በኋላ ጠያቂ ሲበዛ 'እሹ ደግ አደረግኩት' ማለት ጀመርኩ። ሊያሳፍሩኝ...

" 'እናትና ልጅ?' ሲሉኝ።

"ሉኩ ኛተኒ ከሌ ሂደ በሳኒ?"

"ምን ማለት ነው?"

" 'ዶሮ በልቶ እንቁላል አይደገምም?' አልኩ። አባቢያ እንዲህ እለ እየተባለ እስከ ቅርብ ጊዜ..." አሉና ወደ ግቢው መሿለኪያ አጨነቆሩ። 'ማነው? ቡልቡላ? ሰው ይታየኛል?'

እኔ በስካር ተጭበርብሬ ማየት ተሳነኝ።

"ማነው?"

"እኔ ነኝ፣ የመሸብኝ ደካማ እንግዳ ነኝ። አሳድሩኝ። እዚህ ዘመድ አለኝ።"

ድምፁን ለየሁት።

"ረድ ሠርዌ?"

@OLDBOOKSPDF

# የዓይነምሣ ህልምና ህማም

ህልሜና የራስ ህመሜ ተጋግዘው እየወቀሩ አባነኑኝ። "ከመጽሐፍ ጋር የሚገናኝ ተሰጥዖ ያለው ሰው ከህይወት ውስጥ ከተቀዳ ህልም ይልቅ ከህልም ውስጥ ለወጣ ዕውነት ይማልላል" ይል ነበር ዶክተር እሮን። ከህልሜ ውስጥ የትኛው ዕውነት ይወጣ ይሆን?

የአረቂ ተረፈ ስካር ጭንቅላቴን እየወቀረው ህልሜን ፈተሽኩ። ሬድ ሠርዊ ይመስለኛል። ዐይኑን በአዳፋ ጨርቅ ሸፍኖ ይመጣል።

"ምነው?" ስለው

"ምነው? አልአዛር ዘአርምሞ? ነህ?"

"እዎ"

" 'በአይነብርሃን ፈልገው ያጡት በአይነሥውርነት ይከሰት' የሚባለው ተረት ይሄ ነው።

የተረቱ እንግዳነት ሲያደናግረኝ ይቆይና...

"ለምን በጨርቅ ዓይንህን ጋረድክ?"

"አይኔን ተነቅሼ"

"ዓይን ይነቀሳል?"

"ሐጢያት እንደ አይነማዝ ሽፋሽፍት የሚያረግፍ ደዌ ሲሆን ምን ያደርጉታል?" እጁን ጭንቅላቱ ላይ እንደሄሊኮፕተር እያሽከረከረ ጨርቁን ተረተረና ዓይኑን አሳየኝ። ማቀፊያው ውስጥ የፈትል ጨርቅ ተጠቅጥቆ።

የመከነ ጩኸት ጉሮሮዩን ፈጥርቶ ይይዘኛል። አልወለድ ያለ ድምፅ ያስጨንቀኛል። እንባ ብቻ ሲወርድ እነቃለሁ። በላብ

@OLDBOOKSPDF

እንደተጠመቅሁ ቤቱን ስማትር ከነፀብራቅ የላስቲክ ዘምቢል ውጭ ወለሉ ላይ ምንም የለም።

"ቡልቡላ! ቡልቡላ!" እያልኩ ተጣራሁ፣ ሰዓቱንም ለማረጋገጥ ነበር። ስትዘገይ ወደኬላ የወረደች ስለመሰለኝ ተንኳትቼ ወርጀ የነፀብራቅን ፌስታል አነሳሁ። ውስጡ ጠንከር ያለ ነገር ዳሰስሁ። ምን ይሆን? ስከፍተው ዶክተር አሮን የተወልኝ ካርቶን ነው። እውስጡ ገንዘቡ አለ ማለት ነው። ባለፈው ለልብስ መግዣ የሰጠችኝን ብር ቀንሳ ይሆን?

"መምሩ ኪያ?" ገባች።

"ጠፋሽ፣ ማለቴ ወደኬላ ሳትሄጂ ቀረሽ?"

"እንዴት አድርጌ?"

"ምነው?"

"የማታ እንግዳ ጥዬ? አንተንም ባይህ፣ አልተነሳህም። ዝም ብዬ ቀረሁ።"

"የማታ እንግዳ?" ልቤ መታ

"አዎአ"

"ማነው?"

"ጃማ"

"ጃማ የሚባል?"

"አይ"

"እ?"

"ነማ እጅ ዳሜ"

"ምንድነው የምትይው ቡልቡላ?"

"ማለትማ ዓይነሥውር... ምንም አታስታውስም?"

@OLDBOOKSPDF

ህልሜ ነው እውነቴ? ወይስ ዕውነት ነው ህልም?

"ማታ እኮ እዚህ አይመችም ብለን ትልቁ ቤት አሳደርነው።"

ለመጀመሪያ ጊዜ በረድ ሠርዌ ተማረርኩ። 'ለምንድነው የተደበቅሁበት ድረስ መሪር ሀዘን ይዞብኝ የሚመጣው? የማታው ሁኔታ እንደዓይነምሣ ጭጋግ እየጠራ የሚሄድ ግርዶሽ ያለው መሰለ። ቀስ በቀስ ተገለጠልኝ። በቃንቡራ (አረቂ) ድጋፍ ብዙ አልቅሻለሁ። እኔን ተከትላ ቡልቡላ...

"እስኪ ትልቁ ቤት ውሰጂኝ?"

"እሺ" ሳትል ፊቷን መልሳ ወጣች።

ትልቁ ቤት ለሁነኛ እንግዳ መስተናገጃ የተተወ፣ ተዘውትሮ የማይከፈት የቤተሰቡን ክብር ማስጠበቂያ እልፍኝ ነው። በሩ ከዋናው የግቢ ደጃፍ ጋር በትይዩ የተሰራ ባለግርማሞገስ ነው። ያለዛሬ አልገባሁበትም። ግድግዳው ላይ የነብር ቆዳ ተገድግዶበታል። ጦርና ጋሻ፤ ምናልባትም የቡልቡላ አባት ይለብሱት የነበረ የዝንጀሮ ለምድ ፊት ለፊት ተቀምጧል።

የህይወት ትርጉም የገባቸው፣ መድፈር ሲገባቸው ኑሮ ያሳንጓቸው ጉምቱዎች መከባበሪያቸውን ለእኛ ትተው አልፈዋል። እኛ የህይወት፣ የኑሮ፣ የፍቅር፣ የእምነት... ፍቺን ከማነብነብ ውጭ ያልኖርንበት ተተኪዎች፣ የጦር ዕቃቸውን ተከናንበን በፍርሃት ማሸለብ ውስጥ ከንቱ ዕድሜ እንቆጥራለን።

የፈሪ፣ ፈሪ፣ ፈሪ... ነኝ። የረድ ሠርዌን ዕጣ ፈንታ መጋፈጥ እንኳን ያልቻልኩ! ሁሌም ወደ ህይወት ለምለም መስክ መፈርጠጥ ግብሬ የሆነ ፈሪ ነኝ።

"ቡልቡላ" አለ ረድ ሠርዌ። በስተግራ ሳር ላይ ቁርበት ተነጥፎለት ጋደም እንዳለ ነው። በህልሜ ወይም በእውኔ ያየኋት ቁራጭ ፊትል ጨርቅ አይኑ ላይ እንደተጋረደች ነው።

"እኔ ነኝ" አልኩት።

"ጠረንህ የቡልቡላን ቁጭ" አለ። የአይኑን ሥራ አፍንጫውና ጆሮው ተረክበውታል ማለት ነው?

@OLDBOOKSPDF

“እሷም አለች” አልኩት፣ የጠረን መወራረስ ሌላ ትርጉም እንዳይኖረው በመስጋት።

“ኧረ ወዲህ ወዳንተ አቅጣጫ” ጆሮውን ወደ እኔ አቅጣጫ አቅንቶ በትክክል ያለሁበትን ጠቆመ። “እሷ እወዲያ ደጃፉጋ ናት”

የአይኑን መታወር በዚህ በአጭር ጊዜ ተቀብሎታል ማለት ነው? ይሄን ማድረግ የሚችል ሰው ሳይሆን እንስሳ ብቻ ነው። ጃክ ቢሆን ያለአንዳች ማማረር መታወሩን እንደሸምግልናው ተቀብሎ አረማመዱን ከዕጣ-ፈንታው ጋር ለማመጣጠን ብቻ ይጥር ነበር። ታዲያ? ረድ ሠርዊ?...

“ማታ አስጨነኩህ”

ዝም፣ ሆነ ብሎ ይሆን እንዴ ዓይኖቹን ያጠፋቸው? ወስኖ፣ አቅዶ፣ ተቀብሎ... ካላደረገው እንዴት ድንገቴ መታወርን በዚህ አጭር ጊዜ መቀበል ተቻለው?

“ለመንፈሳዊ አኗኗር ዓይን ትርፍ ነገር ነው። እንደውም እንቅፋት ሳይሆን ይቀራል?” ማዳመጤን ለማረጋገጥ ጆሮውን ወደኔ አቅንቶ ትንሽ ቆየ። ሆነ ብዬ ዝም አልኩት። የልቤን ምት፣ የትንፋሼን ስልት ይሆን የሚከታተለው?

“አየህ? የሙሴን ህግ እንኳን ካየን ትዕዛዛቱ የሚጣሱት በዓይን መዘዝ ነው። ካላየህ አታመነዝርም፣ ካላየህ አትሰርቅም፣ ካላየህ አትገድልም፣ ካላየህ የባልንጀራህን ሚስት፣ ከብት፣ ሎሌና ገረድ አትመኝም። ካላየህ ባልንጀራህ ላይ በሀሰት አትመሰክርም። ለሁሉም እንቅፋት ዓይን ነው። እግዚአብሔር ሰውን ሳይሆን ማየትን በመፍጠሩ ነው የተፀፀተው”

ይሄ መፅናኛ ይሆናል? ቡልቡላ መሄዷን ሳላይ የምቀመጥበት ዱካ ይዛ መጣች። እኔም ዓይኔን ሳይሆን ጆሮዬን አፍንጫዬን ብተማመን ገና ስትነቃነቅ እይዛት ነበር።

“ዓይኑን ሲገልጥ ቤት በብርሃን የተሞላለት የላሜህ ልጅ ኖህ ብቻ ነው ሳይደነቃቀፍ በፃድቅነት ህይወቱን የደመደመ። ‘እስመ ተብህለ ኖኅሰ ኮነ ፍፁመ ትውልዱ’ ተብሎለታል። የማየትንና የዓይን መልካምነትን እንቅፋት ሳይደነቃቀፍ ያለፈ እርሱ ነው።”

@OLDBOOKSPDF

የምለው የምጠይቀው ሲጠፋኝ ጥቂት ጠብቆ ጆሮውን ወደ እኔ አቀናና ቀጠለ።

"ጌታ የዓይንን እስናካይነት ጨርሶታል" ብሎ ፈገግ ሲል በደብዛዛው ብርሃን ቸንቹን ፊልጌ አጣኋት። "ዓይንህ ብታስናክልህ አውጣት ነው ያለው። ሁለት ዓይን ኖሮህ ትላቸው ወደማይሞትበት፣ እሳቱም ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነመ እሳት ከመጣል አንዲት ዓይን ኖራህ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ይሻልሃል ሲል አስተማረ።"

አንድ ነገር ከነከነኝ

"እራስህ ነህ ዓይንህን ያወጣኸው?"

በአይኑ ኳሶች ፈንታ ጆሮውን እያንከባለለ ምስል ለማጥራት የሚሞክር መሰለ።

"ነው?" ኤልዛቤል ተንቆጥቁጣ ስትሄድበት ይሆን?

"አይደለም። ዓይን እንባ የሚባል አገር ሄጄ አይኔን አጠፋኝ"

"ለምን?"

"የእናቴ ሀገር ነው። መንትያዬ በድኋቸው ኖሮ የበደሉን አፀፋ እርሱን አገኘን መስሏቸው... አገሬው እንዳለ ሽፍታ ነው። መንግሥት አያውቀው፣ ንጉስ አይደፍረው። እርስ በርሱ በጉልበቱ ብዛት ተከባብሮ የሚኖር ነው።

"አወይ ዓይን እንባ

የሁለት ፈሪ አገር

እነሱ አይመጡ

እኛም አንሻገር" ብለው በመንግሥት

የዘፈኑ ናቸው።

መንግሥት ማዶውን ሆኖ ዝም ብሎ ያያቸዋል። ለነገሩ ለማስገበርና ሥርዓት ለማስከበር ሞክሮ ብዙ ጊዜ ሳይቻለው ቀርቶ ትቶታል።"

@OLDBOOKSPDF

ዝም! ጥልቅ ዝምታ!!

" እስመ ትካዝከ ሠናይት አባዴ ደአቱ ይላል ዮሐንስ አፈወርቅ:: " ተርጉምልኝ እንድለው በጆሮው እንደምጣድ ማሰሻ ፊቴን የደባበሰኝ መሰለኝ:: ለካ 'ተርጉምልኝ' የምለው የሠላም ውይይት ስናካሂድ ነው:: ያንን የሰላም ጊዜ ጨዋታ ናፍቋል፤ ወይም አይኑ በመጥፋቱ ያስከፋኝን እንደበደል ወስዶልኛል:: ከጥልቅ ቃጠሎዬ ጥቂቱን በትንፋሼ አስወጣሁ::

"ስለእግዚአብሔር ብለው የሚቀበሏት መከራ ደግናት ሲል ነው:: አትታዘበኝና ወዲሁም እረፍት አለው:: ብርቅርቁ፣ ድንቅርቅሩ፣ ብልጭልጩ፣ አንጠባራቂው፣ እኔን አዩኝ ባዩ ሁሉ ነፍሴን አስጨንቋት ቆይቷል፣ እርፊት ነው::"

ዝም! ዝም!

"ይቅርታ" አለኝ::

የእኔን ዓይን ተውሶ ነው እንዴ ያጠፋብኝ?

"ለምኑ?"

"እለህ ሲሉኝ አላስችል ብሎኝ መጣሁ"

አይኑን ያጣ እንባ ይኖረው ይሆን? ለዝንታለሙ እንደ ሳቁ ሁሉ ለቅሶውንም ተሰናብቷት ይሆን? ሀዘን ውስጤ ሲላወስ ተሰማኝ:: ፈልጎ ከታወረ ለምን? ሳይፈልግ ከታወረ ለምን? የሚል ጥያቄ ፈጣሪው ላይ አለኝ::

ቡልቡላ የተነከረ እንቁላል ከጥቢኛ ጋር አምጥታ እፊታችን ደነቀረች:: የዕንቁላልነቱን ሽታ የእርጥብ ቅጠል ጭስ ቀምቶታል:: ሻይ እየቀዳች:-

"ጋሪዳ አከዱቢ ታናን ጀዴሜ"

"ምን አለች?" አለ ጆሮውን ከቡልቡላ ወደእኔ መልሶ

"ተርጉም" አለች ቡልቡላ ኬላ ስላልሄደች ፀሐይ የሚያጎላው ቀጭ ደብዝዞ ቀንጆ ሆናለች::

@OLDBOOKSPDF

" ኋንደነገሩ ቢሆንም ብሉ እስቲ' አለች"

ቡልቡላ ተነስታ አፏን ያዘች

"አንቴ? በቃ አንቴ ፊት ምስጢር ላናወራ ነው በቋንቋ?" ደስ ብሏታል።

"መላይካ ጃማ፣ ብላ" ወደ ረድ ሠርዌ ፊቷን መለሰች።

"ምን ማለት ነው?" እኔ ጣልቃ ገባሁ።

"የሱ ስም ነው"

"ትርጉሙስ?"

"አይነሥውሩ መላእክ ማለት ነው።"

ቶሎ ወደ ረድ ሠርዌ መለስ ብዬ አየሁት። ፈገግ ብሏል። ቸንቹ የደበዘዘው ለካ ተነቅሶት ነው። በቀሪው ህይወቱ ሁሉ ለመሳቅ መዘጋጀቱ ይሆን?

ቡልቡላ ጥቢኛውን አንስታ ቆርሳ እጁን ስባ መዳፉ ላይ አስቀመጠችው። ቀጥላ እጁን እየመራች ዕንቁላሉ ያለበትን የብረት ሰሃን አስዳሰሰችው። እሷ በተለመችለት መሰረት ለመጉረስ አልተሳሳተም።

በሰው ዓይን መጠቀም እስካለ ድረስ፣ አሳሳች ነገሮችን አለማየት ብቻ ያፀድቃል?

በልተን ስንጨርስ ወደውጭ መውጣት ፈለግ። እኔም በዱካው መቀመጫ ተከራምቼ ስለቆየሁ ፍላጎቱን ደገፍኩ። ክርኔን ይዞ የግቢውን ካብ አልፈን አነስተኛ ተክል ስር አስቀመጥኩት።

"እግዚአብሔር የወይን አታክልት ሥፍራ እንዳለው ሆኖ ተናዕሮ ይናበባል።"

ዝም አልኩ።

"ኢየሱስ የወይን ተክል ነኝ ያለው ለዚህ ነው።"

ምን ሊያስተምረኝ እንደፈለገ ግራ ሳይጋባ አልቀረም።

@OLDBOOKSPDF

"እና የወይን ተክል ባለው ሰው ተመስሎ እግዚአብሔር ስለአይነሥውራንና ስለሐንካስ እንዲህ ይላል።

"ሐንካስ በእግረ ዕውር ሖረ፣ ዕውርኒ በዐይነ ሐንካስ ነጸረ፤ "ሐንካስ በእግረ ዕውር ተመዝበረ" ማደ ማደውን የሚያይ መስሎ ወበከልዔሆሙ ወይንየ ተመዝበረ" ማደ ማደውን የሚያይ መስሎ የዓይን መሸፈኛውን አድማሱ ላይ ተክሏል። በራሪ ጆሮውን ወደ እኔ ላከ።

"ምን ማለት ነው?" ትርጓሜ መጠየቁ የልቤን መለዘብ ስላስረዳው ንቅሳታም ቸንቹን አስጎበኘኝ።

"አንካሳ በዕውሩ እግር ሄደ፤

ዕውሩም በአንካሳው ዓይን አየ፣

በሁለቱም የወይን አታክልቱ ተመዘበረ ሲል ነው። ወይኑ የኢየሱስን ሥጋና ደም ያጣቅሳል። ፅድቅ፣ በጎደለ ሲሞላሱ የምትገኝ እንደሆነች ያትታል።"

"በምን አነሳኸው?" ሳቁን ያደመቀለት የቸንቹን ንቅሳት አሳይቶኝ ቀጠለ

"አንተ እይልኝ፣ ዓይነምሣን አስጎብኘኝ። እንዴት ያለች ነች?" ደስ አለኝ። የምፅፈውን አሰብኩ።

"ሜዳዋ ግንባረ ቦቃ ላም ይመስላል"

"እንዴት?"

"ሁሌም ግንባሯ ላይ ደመና ይወርዳል።"

"እሺ"

"ታች ታቹን ከሰርፍ፣ ከወላንሳ፣ ከውጥኒ፣ ከመክሞኒ… ሁሉ የሚያስንቅ ምንባፍ ተዘርግቷል። ሽቱ በመቀባት ከመኖር የዓይነምሣን አየር መማግ ነፍስን ደስ ያሰኛል።"

"የአፈወርቅ ዮሐንስን 'ተግሳፅ' አንብበሃል?"

"ድሮ፣ ሰጥቶ[illegible]"

@OLDBOOKSPDF

"ቆይቶ፣ ተብላልቶ እንተን ሆኖ ወጥቷል። ቀጥልማ አፈወርቅ ፀሊም።"


"ዓይነምሣ ውስጧ ጠለቅላቃ ናት፣ ጉርምጥ ያለበት ሃይቅ ላይ እያጠነፈፈች ታኖረናለች። ላይ ላይዋን ህባኔ፣ ባለሻሽ ጉብታ አላት... የተከሉት፣ የእንስሳት፣ የአእዋፋት መጠጊያ ናት... አዲስ አበባ በምድር ነገሥታት ላይ የምትነግሰውን ኤልዛቤልን ተመስላ በታላቅ ከተማነት ዓይነምሣ ፊት ላይ ተጋርጣለች።"

ተመስጦ ጥቂት ከቆየ በኋላ...

"እንደ ዳዊት ከፊሉ ትንቢት፣ ከፊሉ ተግሳፅ፣ ከፊሉ ተማፅኖ፣ ከፊሉ ጥበብ... የሆነ ሥራ የምታቀርብበት ጊዜ ደርሷል። ወልደህይወት እንፍራንዛዊ "ለእመ ብከ ጥበብ ጸሐፍ" ይላል። ጥበብ ካለህ ፃፍ ማለቱ ነው። ፊት ለፊታችን እንተ ብቻ የምትፅፈው ታላቅ ታሪክ ይሰራል።"

ዝም! በዝምታ ውስጥ ብዙ፣ በጣም ብዙ ነገር የገባኝ መሰለኝ።

@OLDBOOKSPDF



# የዓይነምህ ሥንብት

ስለዓይኑ መጥፋት እኔን አፅናናኝ።

"ህማማ ለዐይን ርዕየተ ደላኢ" አለ።

"ምን ማለት ነው?" አልኩ።

"የዓይን ጠላቷ አለማየት ሳይሆን ጠላትን መመልከቷ ነው። ጠላት የሥጋ አይደለም የነፍስ ነው።"

ከብዙ ዝምታዎች እንዷ…

…ፅሞናው፣ ድማሜው ያስፈራል። ከልቡ እኔን ባረከ፣ ከልቡ ያለሁበትን ባረከ፣ ከልቡ ሁኔታውን ሁሉ ባረከ። ለመሄድም ተነሣ።

"ወዴት?"

"ወደ ዓይን አንባ እሄዳለሁ። የታጨሁበትን እፈፅማለሁ። ከተማይቱ እጮኛዋን እንደምትጠብቅ ንፅህት ሴት እኔን ለማግኘት ጓጉታለች።"

ሄደ።

እኔም የምሄድበትን መርቶኛል። ወደዚያ እሄዳለሁ። ከታሪክ ሁሉ የሚልቀው የታላቁ ህዝብ ታላቅ ታሪክ ሲፈፀም በዚያ እገኛለሁ። የድርሻዬን ተቀብዬ በዚያ የታሪክ ሥፍራ እኖራለሁ።

ጋሽ ቢራራን ጠራሁ፣ ነፀብራቅ ያመጣችውን ካርቶን እንዳለ እየሰጠኋቸው፦

"ከመምህርነት የላቀ ሥራ እዚህ አለ። እርሱም ለተማሪዎች መቀመጫ ማሰራት ነው። ይሄን ገንዘብ መነሻ አድርጉ" አልኳቸው። አዲስ ነገር የበራላቸው መሰሉ።

@OLDBOOKSPDF

የቡልቡላን ግንባር ስሜ ተሰናበትኩ። ከበስተጊላዬ የእንባዋ ምንጭ ጠራርጎ የሚወስደኝ ያህል ሲፈስ ይሰማኛል። ለመጀመሪያ ጊዜ መሰናበቱ የክህደት መሰናበት እንዳልሆነ ገባኝ። ይሁንና የፍቅር ሰቅሶዋ በቃላት ሲታጀብ እግሬን አሳሰረብኝ።

"አኒ በዴ... አኒ በዴ ማሊጎዴ፣ ማኒን በሴሴ?... አኮናቴ ጉዱ ነጎታ?... ዲፈማ ናጎዲ በሴሲስ ዮተኤ?... ጉዲ ኪያ ጉዲኪ ጉዲኪያ! ፊራዋን አርጎነታ ፊካቴ! ሠርጊ ሆ ሰርጊ ሆ ሀፊ!... አርጀማ ኪያ! ገራሰፋ ኪያ! አደበማ ኪያ!..."

@OLDBOOKSPDF

# የዓይንአንባ ህልም

ልቤ እንደ አረሆ የቃላተኛውን ቅኔ ከአፉ እየተከታተለ ለቀመ::

“ብቃኝ የኑሮ አጉራህ ጠናኝ

እፎይ የዕድሜ-አዚሜ ጠራኝ

አስለመለመ መብራቱ

በህይወት የመዋተቱ

የነግ-ነግ መንከራተቱ

መንከላወሱ ልፋቱ...

መከሬ ሻማዋ ጠፋ

መሸ ቀኔ ሳንቀሳፋ

.....”

ይሄን ቅኔ በህይወቴ ካለዘብኩ እንዴት ከባለቅኔው ሥራውን ቀላወጥኩ? ለምንድነው ከራሴ ህይወት ያላነጠብኩት? ከፀጋዬ ምናብ የእኔ ልቡና አንሶ? ወይስ...?

...ወደሐሰተኛው መሲህ መገኛ እየተቃረብኩ ነው:: ጥላቻ፣ ቁጣ፣ ጠብ፣ ክርክር፣ ቅዋሜ፣ ቂም፣ ጭቅጭቅ፣ ሽሙጥ፣ እርግማን፣ አምባጓሮ፣ ክህደት፣ መዘባበት፣ ሐኬት፣ ጥርስ ማፋጨት፣ ውሸት... ያለበት ቤተመንግሥት ይመስለኛል::

@OLDBOOKSPDF

እንኳኳሁ ተከፈተ፤ የሚንቀለቀል ገሃነመ እሳት ጠብቄ ነበር፡፡ እሳት የሚከላከል የአልሙኒየም ጃንጥላ ተይዞልኝ ልገባ... እንደ እቶን ፍንጣቂ የሚንፀባረቅ ፈገግታ ተቀበለኝ፡፡

"ታለ? ማን እየመራህ መጣህ?"

"ዋአጥቢያ ኮከብ!" ፈገግ አልኩ፡፡ "ገና ዛሬ ጉጣጉጦችሽን ፈገግታሽ በለጠች፡፡"

"ታዝበሽኝ ከርመህ፤ ጊዜው ሲደርስ አወጣህ? ግባ፤ ግባማ... ብዙ ሰዎች ጉጣጉጤ እየተቅጨለጨለባቸው እኔን አያዩኝም፡፡"

ገባሁ፤ አይኔን የተቀበለኝ ተላጭቶ እንዳቀመቀመ የጎረምሳ ጉንጭ በአጭሩ የተከረከመ የመስክ ቁጠማ ነው፡፡ እዚያ ውስጥ ለቅሶ ሳይሆን ፈገግታ ሲምነሸነሽ ታየኝ፡፡ ጥላቻ፤ ክርክር... ሳይሆን ፍቅርና መግባባት አጮልቀው ተቀብለውኛል፡፡

"ምን ሠፈር ነው?" ስል ጠየኳት የመራችኝን የቀኝ አቅጣጫ ቀጭን የንጣፍ መንገድ እየተከተልኩ፡፡

"Old airport (አሮጌ አውሮፕላን ማረፊያ) የት ብለህ መጣህ?"

የተነገረኝን የከተማ አውቶቡስ ያዝኩ፤ እዚያታች ወረድኩ፡፡ በተነገረኝ አቅጣጫ መጣሁ..." ትልልቁ ቤት ጀርባ አነስተኛ ክፍሎች ተገጥግጠዋል፡፡ አንዱን ከፍታ አስገባችኝ፡፡

"ትንሽ አረፍ በልና ቤቱን አስጎበኝሃለሁ፡፡ መታጠብ ከፈለክ ካንተ ጎን ያለው ክፍል ሙቅ ውኃ አለው፡፡ እዚያ፤ ቁም ሳጥኑ ውስጥ የስፖርት ልብስና ፎጣ አለልህ"

ድሮውንም የእግዚአብሔርና የተቃዋሚዎቹ ልዩነት ይሄው ነው፡፡ እግዚአብሔር በማትፈልጋቸው ነገሮች ይከብሃል፤ ሰይጣን በምትፈልጋቸው ነገሮች ያጠምድሃል፡፡ ይሄ ነው የእግዚአብሔር ሰባኪ የሚያስተናግደኝ ቢሆን "መጨነቅስ፤ የነፍስ ልብስ ለሆነው ስጋ ሳይሆን..." ይለኝ ነበር፡፡ ግቢ ጭር እንዳለ ነው፡፡ ምናልባትም ፈጣሪያቸው ላይ የሚዶልቱት መሬት ለመሬት በተቆፈረ መሸሽጊያ ውስጥ ሆነው ይሆናል፡፡ ኩላሊትና ልብ የሚመረምረው፤ በኩላሊትና በልብ እየተመራ የማያገኘው እንዴት ያለ የመሬት ስር ጉራንጉር ነው?

@OLDBOOKSPDF

ሙቀቱን ውኃ ትቼ በቀዝቃዛ ታጠብኩ። እድፌ ከገላዬ ላይ እንደደረቀ ቁስል እየተቀረፈፈ ወደቀ። የሰው ልጅ የተፈጠረው ለመደሰት እና እረፍትን ለማጣጣም ብቻ ነው። እላዬ ላይ ውኃ ስለተንቆረቆረ በቀላሉ ደስታና እረፍት የሚሰማኝ ከሆነ…

…በጀርባዬ ተንጋልዬ እግሬን፣ እጄንና አእምሮዬን ዘና በማድረግ ሌላ ደስታና እረፍት ቃበዝኩ። እንደደረስኩ ጠብና ክርክር ውስጥ የምጠልቅ መስሎኝ ለግላጋይነት እራሴን አዘጋጅቼ ነበር። እራሴን ለራሴ የሚተዉልኝ ሁኔታ ውስጥ እንደምገኝ በምን አውቄ?

ክፍሏ ጠባብ ናት። ይሁንና የሚያነብና የሚፅፍ ሰው እንዲኖርባት ሆና ተደራጅታለች። አንዲት ትንሽ ጠረጴዛ ከትንሽ ወንበር ጋር ፊቷን ወደ ግድግዳ መልሳ ተጠቃሚ ትጠባበቃለች። አጠገቧ በቁመት ምንም ያህል የማትበልጥ መጽሐፍ መደርደሪያ አለች። ሦስት ወይም አራት መጽሐፎች ይታዩኛል። አንዱ እኔ ለኤልዛቤል ያዋስኳት "Womens evolution" ነው። ወደመገባደጃ ገፆቹ ውስጥ ጠንካራ ወረቀት እልባት ተደርጎበታል። አጠገቡ "Mythology" የሚል ርዕስ ያለው ትልቅ መጽሐፍ ጥላውን ጥሎበታል። ሌላኛው "ገድለ ቅዱስ ላሊበላ" ነው። ረድ ሥርዌ የግዕዙን ሲተርክልኝ የአማርኛውን አምጣልኝ ብዬ አንብቤዋለሁ።

ጆሮዬን ወደ ውጭ ሳኩ። አሁንም ምድረግቢ ፀጥ እንዳለ ነው። በልበድፍንነት የሚያከሳላ አንድ ድምፅ የጎረናበት ወፍ ብቻ ይደመጣል። የእኔን ክፍል ሳይጎራብት አልቀረም።

ምን ተማምኜ እንደሆነ ሳይገባኝ እንቅልፍ ጥርሜ አድርጎ ወሰደኝ። ሰነቃ ጠረጴዛዋ ላይ የተከደነ ሰሐንና አንድ ቢራ ከነጭርኬ ተቀምጧል። የምከፍለው ሳይገባኝ የመስተንግዶ ለዓ መከፈቻው ፍርፍር እየተጣለብኝ ሆኖ ተሰማኝ። ተነስቼ ሳህኑን ከፈትኩት የእንጀራ ፍርፍር እና የተነከረ እንቁላል ጎን ለጎን ተቀምጠው ጥቂት ንጣይ ዳቦዎች ተጥሎባቸዋል። አፍንጫዬን እንዲከኬ የእርጥብ ቅጠል ጭስ ሽታ አሰስኩ፤ የለም። ቢራውን አንስቼ ወደ እልጋዬ ተመለስኩ።

ጎረምሳው ወፍ ደጋግሞ ጮኸ…

…እመሻሽ ላይ ኤልዛቤል ስትመጣ ለአርኩስ መንፈስ እምልክ ልትጋብዘኝ መስሎኝ ከአፏ እስክታወጣው ጠበቅሁ።

@OLDBOOKSPDF

"ቤታችን እንዴት ናት?" አለችኝ የመጻፊያ ወንበሩን ስባ እየተቀመጠች:: የቤት ለቤት ልብስ ብታደርግም ጌጣጌጧ እንዳለ ነው::

"ሰው ቤት የለውም"

"እንዴት?"

"ረድ ሥርዌ 'ወኢን ሕንፀ እንከ ሕንፃ በዛቲ ዓለም ዘትኀልፍ' የሚል ፅፎ ሰጥቶኝ ነበር"

"ምን ማለት ነው?" የግዕዝ ትርጓሜ ስጠየቅ ኩራት ቢጤ ነካካኝ::

" ፈጥና በምታልፍ በዚች ዓለም ቤት አንስራ ማለት ነው:: ይች ዓለም ፈጥና የማታልፈው ለልዕለ ተፈጥሮ፤ ለእግዚአብሔር ወይም ለሴጣን ነው::"

"እነ ልዕለ ተፈጥሮ ቤት ሲሰሩ ፈጥና የምታልፈው ዓለም ሳትሆን ቤቱ ነው:: ለዝንታለም ዕድሜ ቢበዛ ሃምሳ ዓመት ብቻ የሚቆይ ቤት እየሰሩ፣ እየሰሩ መኖሩ አታካች አይሆንም? የእነሱ ቤት ለእኛ ድንኳን ማለት ነው::"

ጥሩ ጭንቅላት ያለውን በነገር ይሸኙታል እንጂ አያደርሱትም:: ጀመር ካደረጉለት በቂ ነው ይቀጥለዋል:: አንዳንድ መጽሐፍ ሳነብ የሰደበኝን ያህል የምናደደው እንደህፃን እጄን ይዞ የሚፈልግበት ድረስ ሳድርስህ ሲለኝ ነው:: ለምን የሆነ ቦታ አድርሶ አይለቀኝም?

"ምን እያሰብክ?" ከመቀመጫዋ ተደላደለች::

"ስለአንቺ ጭንቅላት፤ አሪፍ ማሰብ የሚችል ጭንቅላት አለሽ::"

"የማያስብ አለ እንዴ?"

"አዎ"

ዝም ስትል...

"የእኔ" አልኳት::

"አታሹፍ" ጌጣጌጧን የሚገዳደር ብልጭታ ከወደአፏ ፍልቅ አለ:: "ይልቅ መጽሐፍህን አነበብኩት"

@OLDBOOKSPDF

ስለመጽሐፉ ሲያነሱ አልወድም:: ዝም አልኳት:: አንዳንዴ ገመናዬን አደባባይ ይገፍ የወጣሁ ይመስለኛል::

"ለምንድነው ጌጣጌጥ የምታዘወትሪው?" ጨርሼ አልጋ ላይ ያጋደምኩትን የቢራ ጠርሙስ አነሳሁ:: ጠረጴዛው ላይ አቆምኩት::

"እራትህን ለምን አልበላህም? የማትወደው አይነት ሆኖ ነው?"

ዝም ስላት ገባት::

"እየሀ፣ ጥሩ ጭንቅላት ማለት ይሄ ነው፤ የያዘውን ሲያስለቅቁት ወዲያው የሚያውቅ:: በነገራችን ላይ አንተም ስለጌጣጌጡ ያነሳኸው ባስያዝኩህ ጨዋታ ላለመቀጠል ነው:: ጌጣጌጥ ያየ ሰው ጊዜየን በሙሉ መገኘት ስለሚያናድደኝ ነው:: ጌጣጌጥ ያየ ሰው ጊዜየን በሙሉ መኪኪል ላይ አሳልፌ ለጭንቅላቴ ምንም ሳላተርፍ የቀረሁ ይመስለዋል:: ባነሰ መንገድ ሲያስተናግደኝ ማን እንደሆነ ለማወቅ ዕድል አገኛለሁ::"

"እኔ፣ ማን እንደሆንኩ ወዲያው አወቅሽ? ያኔ?"

"እይ፣ አንተን ቀድሜ አውቄህ ነው የመጣሁት::"

"ስለሳ ተሿጡፎ ነበር በይኛ"

ተሽከረመመች ነው የሚባለው?

"ጌጣጌጥሽ የተረተ ሴት ያስመስልሻል"

"ኤልዛቤልን?"

"እ"

ቡልቅ፣ ቡልቅ... የሚል ሳቅ::

"ና ግቢውንና ትልቁን ቤት ላስጎብኝህ"

ቀድማኝ ወጣች:: ነጠላ ጫማዬን ሰክቼ ተከተልኳት:: የገባሁበት ቀጭን ንጣፍ በእኛ ደጃፍ አድርጎ ያልፍና ቤቱን ዞሮ ከግቢው መስከ ጋር ያጋጥማል:: የመስኩን ጥግ ይዞ አንድ ጥንታዊ የእምነበረድ ሐውልት ቆሟል::

@OLDBOOKSPDF

"Hethor ነው?" ስል ጠየኳት::

"አይ! አቴቴ ናት:: ሁለቱም የፀሐይ አምላክ ስለሆኑ ምልክታቸው አንድ አይነት ነው:: ፀጋዬ ገብረመድህን 'አቴቴ ዱብራ አሮሞ' እያለ የተቀኘላት ርህርህት አምላኪት ናት::" ብላ ከፀጋዬ ግጥም ቆነጠበች::

"ለካ እንደትዝታ አስታምሞ
እንደዘነጉት የእናት ጡት፣ ከዘመን ጋር አገግሞ
ምንም ቢርቅ ምንም ቢሸሽ፣ ህልሜ ከህልምሽ ተዛሞ
በዓይንሽና በአይኔ መሃል፣ የሀሰት ስልጣኔ ቆሞ
ባንተያይ ባንወያይ፣ አቴቴ ዱብራ አሮሞ
እንደልጅነት ለመመን ለካስ ዕድሜም ያማል ከርሞ::
...."

ለእኔ የታየችኝ ቡልቡላ ናት:: እንባዬ መጣ? አቴቴና ቡልቡላ ይዛነቃሉ:: አቴቴም ላመለካት በእርጥብ ቅጠል ሽታ የታጠነ አይብ፣ በሸክላ ኩባያ ጥንጁት ጥንጁት የሚል ትኩስ ወተት ከማቅረብ ወዲያ የትኛው መደለቅ ፍቅሯን ይገልፀዋል?

ወደ ትልቁ ቤት ከመግባታችን በፊት አስፈትጄ ነጠላጫማዬን እውልቄ ቀምቀሞ ቂጠማ ላይ ባዶ እግሬን ቆምኩ:: እርጥብ ነው:: ወገቡ ላይ ስለታጨደ መሃል እግር ይወጋጋል:: እነሆ ወደ ዓይነምሣ በዓይነ ህሊና ደርሼ ተመለስኩ:: ኤልዛቤል በረንዳው ላይ ሆና ታየኛለች:: የጀል ሥራ የሰራሁ ያህል ተሰማኝ::

የምድር ቤቱን አሳልፎ የሚያውጣጣ ደረጃ አለ:: በረንዳው ላይ ሠፊ ባለሻተር መስኮትና ድርብ ደጃፍ ያለው በር በግርማ ሞገስ ቆሟል:: መጨሳለም የጀመረውን ጭንብስብስ ብርሃን እየተቀበለ የእምነበረዱ ቤት እጅግ ገዝፏል::

ኤልዛቤል ድርብ ደጃፉን አንዱን ወደውጭ ሌላኛውን ወደውስጥ ከፍታ አስገባችኝ:: ሠፊ አልፍኝ:: ግድግዳው ላይ የወርቅ ክፈፍ ያለው አንድ ትልቅ ምስል አለ:: የአቴቴ ነው:: በባላ እንጨት ውስጥ ፀሐይን ታቅፋ ይታያል::

@OLDBOOKSPDF

"እቴቴ ግንቢ፣ እቴቴ ሐራ፣ እቴቴ ዱሳ ነች። በሁሉም የሀገራችን አካባቢ ትከበራለች። ልጆች፣ ከብቶችንና አዝርዕትን ትባርካለች ተብሎ ይታመናል። አልልታ ትወዳለች። በለምለምና በጨፌ ቀዬ ትጠብቃለች። በሦስት አይነት ጨሌዎች በሦስቱ ስሟ ትወከላለች። አከባሪዋ ጥቁር ጥለት ያለው የጨሌ ጥብቆ በማጥለቅ ከበራውን ያከናውናል። አምታታሁብህ?" ትኩር ብላ አየችኝ።

"አሳከርሽብኝ እንጂ" ብዬ ሳቅሁ። "እንዴ ደፋሽብኝ"

"ይቅርታ"

"አውቂ ነው"

"ስለእቴቴ የተደረገ ጥናት ስላለ አሟልተህ ታነበዋለህ" ኩርፊያዋም ከጌጣጌጧ በላይ ጎልቶ የሚፈልቅ ነው።

እቴቴን ደግሜ አየኋት። ይሄንን ፀሐይ አቃፊ ባላ ቡልቡላ ይዛ እንዲህ ፊቴ ብትቆም ላልሰግድላት ይቻለኛል?

ሳሎኑ ባለሦሥት እግር ዱካዎች እንዲት ጠረጴዛ እየከበቡ ሁለት ቦታ ከመያዛቸው ውጭ ሌላ ምንም አይነት ዕቃ የለም። ፀድቶ ተወልውሎ ሲታይ ለዓይን እረፍት ይሰጣል። ኤልዛቤል እየመራችኝ ከሳሎኑ ወጥተን የግራ ግድግዳው ሲያልቅ ወደ ምድር ቤት የሚያደርስ ደረጃ አገኘን። ወርደን የሳሎኑን ወለል ጣሪያ ያደረገ አንድ ሰፊ ክፍል ውስጥ ገባን። ሙሉውን ግድግዳ በመጽሐፍ ድርድር ተሸፍኗል። ልብ የሚያርድ ድንጋጤ መታኝ። ሐሰተኛው መሲህ በመንፈሳዊ ሀይሉ ከየሀገሩ በአውታረ ነፋስ እየጠረዘ ያመጣቸው መጽሐፍት መሆን አለባቸው። ተንደርድሬ ፊታቸው ተገተርኩ። አልጋዬ እዚህ ቢዘረጋ ምን ያህል እደሰት ነበር? መጀመሪያ በተናጠል፣ ሲደክመኝ ደግሞ በጥቅል መጽሐፍቱን እያየሁ ቆየሁ።

"ይቅርታ፣ ብዙ አቆየሁሽ"

"እረ ግድ የለም፣ ያሉትን መጻሕፍት ካወቅህ በኋላ የምትፈልጋቸውን እኔ ክፍልህ ድረስ ይዤልህ እመጣለሁ። ካልፈለክም እዚሁ ጠረጴዛና ወንበር ይገባልሃል።"

ይሄ ሁሉ መስተንግዶ ዋጋው ምን መክፈል ይሆን?

@OLDBOOKSPDF

"እዚያ ጥግ በእቴቴ እና በሌሎቹም የአገር ውስጥ አማልክት ላይ የተደረጉ ጥናቶች በቅጂ ተሰብስበው ተቀምጠዋል።"

አቅጣጫውን በአይኔ ብቻ ማተርኩት።

"አማልክቶቹ በገዛ ሀገራቸውና ህዝባቸው ከውጭ በመጡ አማልክቶች 'ባዕድ አምልኮ' መባላቸው ይቆጫል።" ቁጭት በሚነበብበት ድምፀት።

እውነት ነው! ልብ አላልኩትም ነበር። ይሄንን ብሔራዊ ክፍተት መሠረት አድርጎ ሐሰተኛው መሲህ ኃይማኖታዊ ብሶት ሊያቀጣጥልበት ይሆን? መላውን ሀበሻ ከጎኑ ሊያሰልፍ?

ወደክፍሌ ስመለስ በአንዳች ሽታ ታውዶ ደረስኩ። ሽታው ወደ ዓይነምሣ የሚመልስ ትዝታ ቀሰቀሰብኝ። የኩበትና የባህርዛፍ ቅጠል ሽታ። ቡልቡላ የመጣችም መሰለኝ። በኋላ ግን ትዝ ሲለኝ ለብሼ የመጣሁትን ልብስ እዚህ ክፍል ውስጥ ጠቅልዬ አስቀምጬው ስለነበር ኖሯል። ሽታውን ስለየው ገንኖ ጠበቀኝ። ለአዲስ ሰው እንዲህ ስሽት ነበር ማለት ነው?

@OLDBOOKSPDF

# የዓይን አንባ ትልም

የአጉል ሚልኪ ተማራኪ ሆኜ መቀመጤን እየሰለቸሁ መጣሁ። ለሳምንት ከመልካም መስተንግዶ በስተቀር "ማነህ?" የሚለኝ አጣሁ።

ብሉዝ ለመዝፈን ጥቂት የሚቀረው ባለጎርናና ድምፅ ጎረምሳ ወፍ እቤት ገብቶ አይቶኝ መሄድ ጀምሯል። እንደ "ጃክ" ቤቱን መዳበል ሳይጀምር አይቀርም። ወለሉ ንፁህ ስለሚሆንበት የሚለቀም ሲያጣ በጎረምሳ ቁጣ መንቁሩን ገደድ አድርጎ ይመለከተኛል። አብረቅራቂ ጥቁር ሰማያዊ ላባው ብርቱካናማ መንቁሩን አጉልቶታል። ሌላ ወፍ የለ፣ እዚህ ግቢ ብቻውን ምን ይሰራል?

"አንተስ" ብሎ በጎርናና ድምፁ እንደጋሽ ቢራራ ቢጠይቀኝስ? መልሴ ምንድነው? "ብቻህን አንተስ እዚህ ምን ትሰራለህ?"

"ምንም!" ከማለት ውጪ እዚህ ግቢ የምመላለስበት የሥራ መደብ የለኝም። እንደ ሥራ ከተቆጠረ ብዙ መጽሐፍት ማንበቤን እስመዘግባለሁ። እኔ የመረጥኩትን መጽሐፍት እያነበብኩ ነው? ወይስ በልዩ ዘዴ አሳዳሪዎቼ የፈለጉትን እያነበብኩ? አላውቅም!

ቤቱ የዕውቀት ማዕከል ነው። የሚመረተው የማይታወቅ ማምረቻ ቦታ ሆኖ ይሰማኛል። ቅዱስ ትምህርት ክላሽና በራዥ የአጋንንቶች አለቃ ፒንሙ ከሀሰተኛው መሲህ ጋር ግንባር ፈጥሮ ይሆን? ወደቤተመጻህፍቱ ስሄድ መውጣጫ ደረጃው ላይ ፒንሙን ባገኘው ምን እላለሁ? እንደ ረድ ሠርዊ በድንገተኛ ማማተብ ሰቅዤ እይዘዋለሁ? ማማተቤ በርትቶ ወደ ዘላቂ ፀሎት ሲቀየርበት ምን፣ ምን ይላል?

"እኔም" ፍጡር ነኝ፣ አርፌ የተቀመጥኩበት የገዛ ቤቴ በፀሎት ተቃጠል የሚለኝ የለም" ይል ይሆን? መቼም እንግዳው ሆኜ ከየት እንዳመጣው በማላውቀው አጋንንታዊ ሀብቱ ተንፈላስሼ ያለህሳብ እያነበብኩ ከርሜያለሁ። እንደ አንድ እንግዳ መጠን መተላለፊያው ላይ

@OLDBOOKSPDF

ሲያጋጥመኝ "ጤና ይስጥልኝ" ብዬ ከንብንቤን እገፋለሁ? ፒንጦው ነገሬኛ ከሆነ በጥያቄ ይፈትረኛል።

"ማነው ጤና የሚሰጠኝ?" ይላል።

"እርሱ"

"እርሱ ማን?"

"ካለእርሱ ማን 'እርሱ' አለና እርሱ ማን ብለህ ትጠይቀኛለህ?"

"አንተም ካጠገቤ ከራስ 'እርሱ' ነህ"

"የእርሱ እርሱነት፣ ከሌሎች እሱዎች የተለየ እርሱነትነት መሆኑን ዘንግተህ ነው? ወይስ..."

መወጣጫው ላይ እንዳለን ስንከራከር መሽቶ ይነጋል። ሰንጋቱ ሌላ 'ጤና ይስጥልኝ' ግድ ይላል፣ ያው ክርክራችን ይደገማል፣ ይደጋገማል...

...የበላነው ስንዴ ዳግም እንደሚመጣ፣ ያረድነው በግ ዳግም ካራ የያዘ እጃችን ስር እንደሚጋደም፣ በድግግሞሽ ተአምር የሆነ ክርክር። እንደ አዝርዕቱ፣ እንደ እንስሳቱ ክርክራችን ሞቶ መነሳቱ....

...እንደ አዝርዕቱ፣ እንደ እንስሳቱ እንዲሁም እንደ ክርክሩ የግብፁ ኦሲሪስ (Osiris) ከድንግል ይወለዳል፣ ይሞታል፣ ሞትን ድል አድርጎ ወደ ህይወት ይመለሳል... ደግሞ የፔርሽያን ሚትራ (mitra) ሆኖ ከምንም ድንግልና ተወልዶ፣ በኢራኖች ምድር ሞቶ ከሙታን ተሰይቶ ይነሳል... የቻይናውን ፎሂን (Fohin) ሆኖ፣ ከድንግል ተወልዶ በሞንጎሎች ተገድሎ፣ ሞቶ ይነሳል... ወደ ጃፓን ይሄዳል? በድሩን (Beddru) ይሆናል? ካልሆነ እንዴት ከድንግል ይወለዳል? እንዴት ሲገድሉት ይነሳል? ወደግሪክ እንማትራለን አዶኒስን (Adonis) እናገኛለን፣ በአንበሳ ተሰብሮ ይሞታል፣ የነፋሱን አበባ ሆኖ ይነሳል... ወደ ሮም ይተላለፋል? ኩዩሪነስ (Quirinus) ሆኖ ከድንግል ይወለዳል? ይገደላል? ከሙታን ይነሳል? ያርጋል?... ወደፍልስጤም ምድር ይተላለፋል? ክርስቶስን ሆኖ ከድንግል ይወለዳል? ይገደላል? ከሙታን ተነጥሎ ይነሳል? ያርጋል?... እርሱ ማነው?

@OLDBOOKSPDF

ፍርሃት፤ ፔንመ መጻሕፍቱን ሳይሆን ጭንቅላቱን የከለሰና የበረዘ ሆኖ ተሰማኝ፡፡ ፍርሃቴ ውስጥ ሆኜም ጭንቅላቴ በያዘው፣ ነገር የመሰለቅ መንገድ ቀጥሎ ነበር፡፡

"...የሶሪያው ታሙዝ (Tammuz)፣ የህንዱ ክሪሽና (Krishna)፣ የሜክሲኮው ኪውዛልክት (Quetzalect)፣ የኔፓል ጃን (Jane)፣ የቲቤቱ ኢንድራ (Indra)... እነዚህ ሁሉ ከድንግል ተፈጥሮ፣ እንስሳና ሰው ተወልደው፣ ተገድለው፣ ምትን ድል አድርገው የተነሱ አይደሉምን? እናስ? የትኛው አማልክት ቃል እንደገባው ተመልሶ መጥቶ ሙታንን አስነሳ? ሃጥዕ እና ፃድቅን ዳኘ?... ነው ወይስ ሞቶ የመነሳቱ እዙሪትና ጡዘት ተከናውኖ አባቢቃ ይሆን?...

...ሹክክ ያለ ጥላ ወደቤቴ የሰረገው እግረ ፀሐይ ላይ አረፈ፡፡ ፔንመ ሊተዋወቀኝ መጣ? ወይንስ ሐሰተኛው ነብይ እንደ ወታደሩ ቆጥሮኝ ሊጎበኘኝ?...

"ሊተዋወቅህ የሚፈልግ ሰው ይዤ መጣሁ" የኤልዛቤል ድምፅ ነበር፡፡ ገርበብ ያለውን ደጃፍ ከፈተችው፡፡ ደማቅ የሚፋጅ የከንፈር ቀለሟ ቀድሟት ገባ፡፡ አንድ ሰው ከበስተኋላዋ አለ፡፡ የማነበውን Mythology መጽሐፍ ገፍቼ ከአልጋው ላይ ተነሳሁ፡፡ ለትውውቅ እራሴን አዘጋጀሁ፡፡

" ግባ፣ ተዋወቁ" አለችው ገባ፡፡ ያልጠበኩት፣ ከተአምር የሚቆጠር ነገር ሰውነቴን ከሁለት ተረተረው፡፡ በመስታወት ነፀብራቅ ውስጥ እራሴን የምመለከት መሰለኝ፡፡ እጁን ዘርግቷል፡፡ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብዬ አየሁት፡፡ እንደሱ እጄን ብዘረጋ ኖሮ የመስታወት ነፀብራቅነቱ አጠራጣሪ አይሆንብኝም ነበር፡፡

"አልአዛር" አለኝ፡፡

"አልአዛር" ካለኩ በኋላ ድንገት ልቤ ፍሬን ያዘች፡፡ "አንተም አልአዛር ነው ስምህ? ወይስ እየቀለድክ?" ስል ጠየኩት፡፡

"እኔም አልአዛር ነኝ፡፡ እንደመስታወት ፈገግታዬን ለራሴ ደገመልኝ፡፡ ሲያዩኝ ይሄን እመስላለሁ? ወደ ኤልዛቤል ፊቴን መለስኩ፡፡ በደማቅ የከንፈር ቀለሟ እና በጭንቅላቷ "አዎ" አለችኝ፡፡ የፔንመ ወይም የሀሰተኛው ነብይ ተአምር የተጀመረ መሰለኝ፡፡

"ታውቀኝ ነበር?" ስል ጠየኩት

@OLDBOOKSPDF

"በቅርቡ"

"እውነት ወንድሜ ነህ?"

"ካልሆንኩ ይሄ ሁሉ መመሳሰል ከየት መጣ ትላለህ?" ልዝብ አይነት ይመስላል፡፡ እንደእኒ አልተደነቀም፡፡

"ቆጭ በል" አልጋውን ጋበዝኩት

"ልሂድ" እኔም መሄዱን ተመኝቼዋለሁ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ፎቶውን ስመለከት የቴክኖሎጂ ተአምር ስለታወሰኝ ይሆናል እንዲህ አልተደናገጥኩም፡፡

"ነገ ስለምሄድ ልሰናበትህ ብዬ ነው"

"ወዴት?"

"ወደ ዓይን አንባ"

ሌላ ድንጋጤ መታኝ፡፡ እንደ ረድ ሠርዌ አይኑን ሊያስወጣ? ወይስ... የተንከረፈፈ እጁን ጨብጦ ሄደ፡፡ ሰውነቱ ታመሰ፡፡

ጠግቤ ብበላ ወደላይ ይለኝ ነበር፡፡ ኤልዛቤል ላይ አፈጠጥኩ፡፡ በተኳሉ አይኖቿ አጣብቃ ያዘችኝ፡፡

"እዚህ ተአምር ላይ አለቃሽ አለበት?"

"የቱ ተአምር?"

"ይሄ እኔን የማባዛቱ ተአምር"

ሳቀች፡፡ ጌጣጌጧን ያቅጨለጨለች መሰለች፡፡

"እንዴት ሊኖርበት ይችላል? ተአምሩ የተፈጥሮ ብቻ ነው፡፡ ግን... ግን አለቃዬ ማነው?" ማንበቢያ ወንበሩን ስባ ተቀመጠች፡፡ በስሱ የሚበን ሽቶ ተቀብታለች፡፡

"ሰይጣን፣ ሀሰተኛው መሲህ፣ ወይም የጋኔን አለቃ የሚባለው ፔንሙ..." ውስጤ አምፆብኛል ተፈጥሮዬ ይሄን የተፈጥሮ ተቃራኒ ቦታ ትቼ እንድሄድ ይጎተጉተኛል፡፡

@OLDBOOKSPDF

"እንደተማረ ሰው ብንነጋገር አይሻልም?" አይኖቿ አይኖቼን አጣብቀው እንደያዙ...

"ለተማረ ሰው የሚሆን ምን ምልክት አለና እንደምሁር መነጋገር ይቻላል? ምን? የረድ ሠርዌ ነገር? ወንድሙ የተባለው? ሀሰተኛው መሲሀ? አንቺ?... እዚህ የመንፈስ ድሪያ ውስጥ የእኔ ቦታ ምንድነው?"

"አትሊስት እኔ መንፈስ ነኝ?"

"ምን አውቃለሁ?"

ከመቀመጫዋ ተነስታ በእጇ ከክርኔ በላይ ዳሰሰችኝ፣

"ነኝ? መንፈስ ነኝ?"

"እንጃ!"

እጇን ከትከሻዬ በታች ባለ ጡንቻዬ በኩል አሳልፋ ደረቴ ላይ አሳረፈችው

"ነኝ?"

"እንጃ!"

እጇን ወደ አንገቴ ላከችው:: ይሞቃል:: ንዴት፣ ውኸርንብር ያበናል፣ ዓይኖቿ ተጨፍነው ወደ አይኖቼ ተጠጉ:: ጨፍኘ ተቀበልኳቸው:: እንዴት አለመቀበል ይቻላል? ሊፒስቲኳ ከንፈሬን ከከንፈሯ ጋር አጣብቆ ሲይዝ ታወቀኝ:: ስትለቀኝ ከንፈሬ ላይ የመጎተት ስሜት...

"ነኝ?"

"ይሄ ማረጋገጫ ይሆናል? ብዙ ጊዜ በጣም ብዙ ጊዜ የሌሊት ንግሥት የሆነችው ሀልመሌሊት፣ ሶፊያ፣ ስማኛለች:: ስነቃ የለችም"

"ንካኝ፣ ዳስሰኝ፣ አቀፈኝ..." ያልጠበኩት ሆኖ ግራ አጋባኝ:: ለመጀመሪያ ጊዜ ከኤልዛቤል ጋር ስተዋወቅ ካደረብኝ ለሷ የመሳብ ስሜት ውጭ አንድ ቀን... የምናወራው ርዕስ ጉዳይ ከሴት ጋር የሚያወሩት ዓይነት ስላልሆነ ይሆን?

@OLDBOOKSPDF

"መንካት፣ መዳሰስ፣ ማቀፍ... ሳይኖር ህልመ ሌሊት ያለ ይመስልሻል?" ወደ ወንበሩዋ ተመልሳ ተቀመጠች። መተፋፈር የሚተካ መስሎኝ ቶሎ እንድትወጣ ፈለኩ።

"ይሄንን ሦስት ቀን ስብሰባ በዝቶብኝ እያመሸሁ ነበር የመጣሁት። እንዳልረብሽህ ብዬ ቀጥታ ወደክፍሌ መሄዴ ትክክል አልነበረም። ይሄ ሳይሆን አይቀርም ፀባይህን የለዋወጠው"

"ማለት?"

"ማለትማ ናፍቆት፣ እኔም ናፍቄሃለሁ።"

ጭራሽ ልታሳፍረኝ? ቀና ብዬ ልያት እስኪ... አዳገተኝ። አልጋው ላይ ተቀምጬ ወሬ ማስቀሪያ ነገሮች አሰብኩ።

"ይሄ ጌጣ ጌጥሽ..."

ክት ብላ ሳቀች።

"ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ልንገርህ? ይሄንን ቤት ስንከራይ የሚገባ የሚወጣው ሰው ሁሉ ድቁስቁስ ያለ ስለሆነ በሰው ዘንድ ጥርጣሬ በዛ። ስለዚህ እኔ መድመቅ ጀመርኩ። ጥርጣሬው አከተመ። እንጂ ጌጣጌጥ መሰካካት ያንተን ያህል ሳይከብደኝ ቀርቶ አይደለም። ገባህ?"

"ገባኝ" ስነዛነዝ ወደነበረው መጽሐፍ ዞርኩ። "ነገ መሄድ አለብኝ?"

"ወዴት?"

"እንጃ! ወደ አንዱ"

"ለምን?"

"እዚህ ቤት ውስጥ አስፈላጊነቴ አልታይህ እያለኝ ነው።የአንገቱል ምልኪ ተማራኪ... "ቀና ብዬ አየኋት።

"ምን እንዲሆን ትፈልጋለህ?" የሳመችኝ አልመስል አለችኝ።

"ምን እንድሆን እንደምትፈልጉ ያልነገራችሁኝ እናንተ ናችሁ"

@OLDBOOKSPDF

"ትንሽ ከራስህ ጋር ቆይ ተብሎ ነው። አንብብ፣ አምሰልስል..."

"ዛሬ ነው ማንበብና ማምሰልሰል የምጀምረው? ህይወቴን ሙሉ ሳነብና ሳምሰለስል አልነበረም?..."

"እኛን ከተዋወቅህ በኋላ ማንበብና ማምሰልሰል ከቀድሞው አይለይም?"

"ይበቃኛል"

"እሺ፣ ነገ ሀሙስ አይደል?"

እራሴን በአዎንታ ነቅንቅሁላት

"የሳምንቱ የጋራ ሜዲቴሽን ፕሮግራም እዚህ ግቢ ውስጥ አለ፣ ሳሩ ላይ። ከፈለክ ትሳተፋለህ፣ ካልፈለክ ፕሮግራሙ ሲያልቅ ከአባሉቹ ጋር እንገናኝሃለሁ።" ተነሳች። ቁልቁል ስታየኝ የከንፈሯ ቀለም መድማማቁን ትቶ ተስለምልሟል፣ መፋጀቱን እኔ ሳልካፈለው አልቀረሁም። ሳቅሁ።

"ምነው?"


"ከንፈሬ ቀልቷል?" በደረቴ ተንበለበልኩ። ጆርባዬ ላይ ስታቅፈኝ ታወቀኝ። በቀኝ እጇ ቀኝ መንጋጭላዬን ደግፋ ወደግራ አዞረችኝ። ግማሽ ከንፈሬ ላይ ሳመችኝ። ለምን እንዲህ ያሉ የተፋጠኑ ሰውጦች ልቦለድ ላይ አይፈቀዱም? ይኸው በህይወት ውስጥ እየተከናወኑ አይደለም? ልቦለድ ብፅፍ ኖሮ የኤልዛቤልን ልብ የሚያስገዘብና ለመሳሳም የሚያበቃ መሳብ ለመፍጠር ጥቂት መቸገሬ ይቀር ነበር? እንኳንም ህይወት ሆነ።

"አንድ ቀን፣ አይነምሳ ሄደን እዛቹ አንተ ቤት ውስጥ በፍርሃት ተቃቅፈን እናድራለን፣ ጭለማ ውስጥ - እሺ?"

ከአርማጌዶን በፊት? ወይስ በኋላ? ሐሰተኛው መሲህ ወግንን፣ አሸንፈን... ማለት??....

ሳቅ!!

@OLDBOOKSPDF



# የዓይነአንባ ዘክር

ከዓይነምሣ የተረፈ ደመና ሳይሆን አይቀርም፣ ቁልቁል አዲስ አበባን ጀቡኖ ይዟል። ቤቱ መጨላለም ሲበዛበት ማንበብ ተሳነኝ። መብራቱን ለሞከረው ኃይል ስለተቋረጠበት አምፑሉ በምንላድርግህ ዝም ብሉ የሚመለከተኝ መሰለኝ። ጨነቀኝ።

መብራት ኖረ አልኖረ፣ ጭጋግ ወረደ አልወረደ፣ ግድ የማይሰጠው ጎረምሳ ወፍ ማጉረምረሙን ትቶ በጊዜ ወደጎጆው ገብቶ ተወሽቋል። አልፎ አልፎ በእንቅልፍ ልቡ ሚዛኑን ሲስት መሆን አለበት ክንፉን እያርገበገበ ከመውደቅ ይተርፋል። በዚህ አጋጣሚ በቅጡ የተደለደለ ጎጆ እንደሌለው ገባኝ። የሆነ ቀጭን ነገር (ምናልባትም የኤሌክትሪክ ገመድ) በጣቶቹ ቆንጥጦ በወደኩ፣ አልወደኩ ሥጋት ደጋግሞ እየባነነ ያድራል ማለት ነው።

ቤቱ ውስጥ ተለኳሽ ነገር እንደሌለ አወቅሁ። ሻማም ሆነ የእጅ ባትሪ በድንግዝግዙ ፈልጌ አጣሁ። ነባራዊ ሁኔታውን መቀበል ተሳነኝ። የሰው ልጅ ከሌላው ፍጡር የሚለየው እዚህ ላይ ነው።ተፈጥሯዊ ጉዳዮች ሲቃወም መኖሩ። እንደጃኬ ወይም እንደጎረምሳው ወፍ ከተፈጥሯዊ ነገሮች ጋር ተስማምቶ ፀጥተኛ ህይወት መምራትን የሰው ልጅ ተነፍጓል። ለዚህ ነው ቅድስና ከተፈጥሯችን ውስጥ ተንጠፍጥፎ ማለቁ። በተመስጦ ሆነ በፆም ፀሎት ብዛት ቅድስናን ወደማናገኝበት እርቀት ተጉዘን ከተፈጥሮ ጋር ተጠፋፍተናል።

የጎረምሳው ወፍ አከናፋት ለሚዛን መጠበቂያ ባሉበት ተርገበገቡ። በሩን ከፍት ትቼ ጮልጧላ ብርሃን እቃርማለሁ። ቡልቡላ ቤት ሳለሁ ከጀንበር መጥለቅ ጋር ብርሃን ማለሴ ያበቃ አልነበር?

በጨለማው ውስጥ ጭጋጉ ሲጥመለመል እንጻች ነፍስ ያለው ልዩ ፍጡር ይመስላል። ዮሐንስ በራዕዩ ከዘንዶው፣ ከአውሬውና ከሐሰተኛው ነብይ አፍ ሲወጡ ያያቸው ጓጉንቸር የሚመስሉ ሦስት እርኩሳን መናፍስት ትዝ አሉኝ። እኚም ራዕዩን ልፃፍ ብዬ ብነሳ ዛሬ እነዚህ ጓጉንቸር የመሰሉ መናፍስት መደጋገማቸው ነበር ማለት ነው?

@OLDBOOKSPDF

እዚህ ደጃፌ ላይ ማንም፣ ምንም ተአምር ቢያደርግ ልቤ የሚደነግጥ አልመሰለ እያለኝ መጥቷል። መጽሐፉ ብዙ ያለለት ሐሰተኛው መሲህ ከእኔ እንደ ምዕራፍ የማይሞላ እርቀት ተመሳሳይ ብርሃን ማጣት ውስጥ፣ ተመሳሳይ ቁዘማ ላይ አይደለ? ደግሞስ ሃያ አራት ሰዓት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ፊት ለፊት ልጋፈጠው ቀጠሮ ይዤ የለም? እናስ?...

...ሐሰተኛው መሲህ የተሰጠው መለኮታዊ ኃይል ምን ይሆን? እንደሙሴ በትር ተሰጥቶታል? ባህር እንዲከፍልበት? ከድንጋይ ላይ ውኃ እንዲፈልቅበት? የፈርኦንን ቃላተኛ በትር የሚውጥ በትር? ወይስ እንደ ዚየስ እና እንደ አቡየ ጣዲቁ ገደል እንደአክርማ የሚሰነጥቁበት መብረቅ?...

...የት እንዳነበብኩት ጠፍቶኛል፤ ጉዳዩ ግን አብሮኝ አለ። ስለሐሰተኛው መሲህ ነው... ሥሙ ሐሰል ከተባለው ተራራ ውስጥ ከሴቲቱ ይወለዳል። "እኔ አምላክ ነኝ" እያለ እራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ያመሳስላል። በፀሐይ ላይ፣ በጨረቃ ላይ፣ በከዋክብት ላይ በሚያደርገው ተአምርና ድንቅ ብዙዎች ይከተሉታል። ሙታንን ያስነሳ ዘንድ ሥልጣን ይሰጠዋል.."

ሐሳዊ መሲህ ከዋክብት ላይ የተሰጠውን ሥልጣን በማርገፍ ሲጠቀምበት ያየሁ መሰለኝ። ከዋክብቱ እየተብለጨለጩ ወደእኔ ቤት ተጠጉ... ቀረቡ... ደጃፌ ላይ ተገተሩ።

"ተኝተሃል?" የኤልዛቤል ጊጣጊጦች እንደረገፉ ከዋክብት የብርሃን ርጋፊ እየቃረሙ ደረቷ፣ ጆሮዎቿ፣ ጣቶቿ፣ ፀጉሯ፣ እጇ... ላይ ይፈልቃሉ።

"ተኝተሃል-አለህ?"

"አለሁ፣

የትውልድ ቅዠት እያባበልሁ

የገና ለገና ዕንስ እያረምሁ

የልብ እባጭ እያፈራረጥሁ

አለሁ!" ልቤ ተቆኝ?

@OLDBOOKSPDF

"የፈራሁት የዓይነምሣ ጨለማ እዚህ ድረስ መጣ፤ አንተጋ ልሁን? ወይ ጨለማ ስፈራ!"

"ግቢ"

ገባች፣ በስሱ የተቀባችው ሽቱ በነፋስ ሲወሰድ ውሎ እንደአንከትካች በየልብሷ የክር መጋጠሚያ ተወሽቆ እዚህ ደረሰ:: በአፍንጫዬ አሳደድኩት::"

"ዓይነምሣ እንዳለን አስበን፣ በፍርሃት ተቃቅፈን፣ በፀጥታ እንተኛ?"

ልጅ መስላ ታየችኝ::

"እኔን ለማቀፍ ምን ሰበብ ያስፈልጋል?" ስል አሰብኩ

"ጥሩ" ጠናጋሻው ይችን 'ጥሩ' መታወሻው አድርጎ ጥሎልኝ ሄዷል::

"አይነጥላቸው ያለው ከንፈራቸው ላይ ነው:: አንዴ ሴትን ከሳሙና ከተሳሙ በኋላ ተመለሱ ቢባሉ የማይመለሱ ተጋፊ ይሆናሉ"

"እና?"

"አንተ ግን ስመህም፣ ተስመህም ዓይነጥላህ አይለቅህም::"

"አይናፋር ነህ እያልሽኝ ነው?"

"እ"

እውነት ይሆን?

"ሌሎቹ ወንዶች ቢሆኑ አንዴ ከተሳሙ መኝታ ክፍሌ ድረስ መጥተው ጎትተው..."

እንዲህ አድርጌ አውቃለሁ? ትዝ አልለኝ አለ

"እና የምትፈልጊው በወንድ መጎተት ነው?" ነገር ነገር ብሎኛል እንዴ?

@OLDBOOKSPDF

"አንተ ስትናገረው እንዴት ያስጠላል? ከድርጊቱ በላይ ከአፍህ ሲወጣ ክብረነክ ይሆናል"

"ቆይ ለምን መጣሽ?"

"በጨለማም፣ በጅብ መከበብም የማትፈራ ስለሆንክ አንተ ጎን ተወሽቄ፣ በሙሉ ከለላ መተኛት"

ዝም ብየ አየኋትና "ዓይነምሣ መጥተሽ ያልሽውን ታስታውሻለሽ?"

"አዎ"

"እራስሽን አትቃረኚ"

"ያኛው ፍርሃትና፣ ይሄኛው ድፍረት ይለያያል"

ጉንጭ አልፋ ክርክር ውስጥ የገባሁ መሰለኝ።

"እዚህ ሁኔታ ውስጥ፣ በምን የልጅነት ተዕዕኖ እልፈን እንደመጣን አይታወቅም። ለምን ጨለማን እንደምፈራ አልገባኝም።"

ጋሽ ቢራራ ትዝ አሉኝ "ኡልፊና ዱክና እሲኒ ሀኬኑ" አልኩ

"ምን ማለት ነው?"

"ኦሮምኛ ነው፤ የጨለማን ግርማ ሞገስ ይስጥህ የሚል ምረቃ ነው። ይሄንን አውቃለሁ" አልኩና ሳቅሁ። እራሴን ቀጥቼ

"ችግሩ የትጋ እንዳለ የኋላ ህይወትሽ ውስጥ ፈልገው። ከነመፍትሔው ታገኚዋለሽ"

"ሲመስለኝ፣ እናት የለኝም። ያሳደገኝ አባቴ ብቻውን ነው። አዘውትሮ ያመሻል። እሱ እስኪመጣ እንቅልፍ አይወስደኝም ነበር። በራሱ ቁልፍ በሩን ከፍቶ የሚገባ ቢሆንም ነቅቼ እጠብቀዋለሁ። ሲመጣ ነው እፎይ የምለው። እቅፉ ውስጥ ስሆን ነው እንቅልፍ የሚወስደኝ።"

ድምጿም፣ ሁኔታዋም ወደ ትንሽ ልጅነት የተለወጠ መሰለኝ። አልጋ ላይ ወጣች። ጥጉን ይዛ እንደመተኛት አለች።

@OLDBOOKSPDF

"ብሩን ዝጋው፣ አጠገቤ ተኛና እቀፈኝ፣ ጨለማን መጋፈጥ አልችልም። ሬድ ሠርቪን እንዳናግር በጨለማ በሳክ አራት ሰው ተመድቦልኝ በአትራቢያዬ ሆነው እየጠበቁኝ ነበር። አቤት ስፈራ… ግ እቀፈኝ… እንደሱ… ዝም ብለን ትኝት። ትንሽ ቆይቶ እንቅልፍ ይወስደኛል። ቀድሞ እንቅልፍ እንዳይወስድህ፣ እሺ?… እም፣… በቃ፣… ተው ሌላ ቦታ እንዳትኀነኝ፣ አባት ይነካል?… ዝም!"

ዝናቡ እንደ አወረደው። ነጎድጓድ ተጨመረ፣ ድምፅና ብርሃን ወደ ጦርመሣሪያነት የተቀየሩ መሰሉ። አባ ነጎድጓድ ዘ ግሪክ (ዜየስ) ትዕግሥቱ ተሟጦ በምድርና በፍጡራኖቿ ላይ የተቆጣ መሰለ። ኤልዛቤል እትፌ እንዲበቃት ሆኖ ተጨባብጣ ደረቴ ውስጥ ገብታለች። ደረት ይከታል? የፈራን ሰው ማስጠለል በራሱ የሚሰጠው የዕርካታ ስሜት አለ። ለበረደው ሰው የገላን ሙቀት እንደሚጋራት የፈራም ሰው ፍርሃቱ ወደ አስጠላዩ ሰው ይተላለፋል።

ነጎድጓድ….

…ነገ የያዝኩት ቀጠሮ ለሰለተ ምጽአት እንድ በመሆኑ ቀኑን ሰማይ በለቅሶ እየተቀበለው ይሆን? ምድርስ? ሬድ ሠርቪን አሰፌ ካጠናኋቸው የግዕዝ ጥቅሶች አንዱን አስታወስኩ።

"እስመ ሰማይኒ ይጽዋዕ" ሰማይ ለምስክርነት ይጠራል፤ "ወይትናበቦሙ ለኑ ጽናፈ ምድር" ምደርም ለምስክርነት ትጠራለች። እና? ከሚፈረድበት ሰው በላይ ለምስክርነት የሚጠሩት ሰማይና ምድር ይጨነቃሉ?

ዝናቡ ጋብ ሲል መብራቱ ተከታትሎ መጣ። ኤልዛቤል በኤሌክትሪክ ትሰራ ይመስል ነትታ አይኗን እያንከባለለች ዙሪያውን ማተረች።

"እንዴት ደስ ይላል"

"ምኑ?"

"በአንተ መታቀፉ፣ ጨለማን ማለፉ፤ አመሰግናለሁ!" ተለጥፋ ከነበረበት ደረቴ ላይ ተንኳታ ከንፈሬ ላይ ሳመችኝ።

"እኔም አመሰግናለሁ"


@OLDBOOKSPDF

"ለምኑ?"

"ስለሳምሺኝ:: መሳምሽ እንደበሰለ ወይን የሰው ልብ ደስ ያሰኛል::"

ስትደግመኝ በመሳሟ ተጣብቃ ጥቂት ቆየች:: ዘለግ ያለ ደስታ:: ደስታም ቁመት አለው?

"ዝም ብዬ ሳስብ ፍርሃት ያለብህ አይመስለኝም:: ሌላው ቀርቶ ሐሳዊ መሲህ፣ የአጋንንት አለቃ፣ ምናምን... እዚህ ግቢ እንዳሉ አምነህ እንኳ አትፈራም:: እንደውም እነሱን ለማግኘት ትገፋፋለህ:: እስኪ ለራስህ አስበው? አትገርምም?"

"እገርማለሁ"

"አታሹፍ!"

"እውቴን ነው፤ የነገው ቀጠሮ እንደተከበረ ነው አይደል? ከነገ ማለፍ አልፈልግም"

"ስታገኛቸው ምን ትላቸዋለህ?"

"እነሱ የሚሉኝን ለመስማት ብቻ!"

"በሚሉህ ትስማማለህ?"

"እንዴት?"

"እኛን ምሰልና..."

"የሚያሳምን ነገር ካለው..."

"የማትስማማ ከሆነ ከጅምሩ በሚነግሩህ ላይ ተመስርተህ ወስን"

"ማለት?"

"ምስጢር አትስማ"

"የምን ምስጢር?"

@OLDBOOKSPDF

"አ! አ!" ከላዬ ተነሳች "ምስጢር ነዋ! አብሯቸው የሚዘልቅ፣ በሚሉት ያመነ ብቻ የሚሰማው ምስጢር አላቸው። ያንን ምስጢር ካወቁ በኋላ ማፈግፈግ አደጋ አለው።"

"የምን አደጋ?"

"ኡፋ! አደጋ ነዋ!" ፊቷን ከእይታዬ ለመሸሸግ ወደ ደረቴ ተመልሳ በጣቷ ጫፍ የመቧጠጥ ያህል እየፋጨረች ቆየች

"ስለምወድህ ነው"

"ጥሩ"

"አልተዋጠልህም አይደል? ምስጢር ከሰሙ በኋላ መለየት አደጋ አለው። ዓይንአንባ አካባቢ ገዳም ውስጥ ያሉ ሽማግሌዎች ሁሉንም ነገር ይቆጣጠራሉ። "የአባቶች ጉባኤ" ይባላሉ። እንዴ መስማማትህ ተገልፆ ለእነሱ መልእክት ከተላለፈ በኋላ ብታፈገፍግ አደጋ አለው።"

"የምን አደጋ? አደጋ-አደጋ ትይኛለሽ ይገድሉኛል?"

"አትጩህ! አዎ። ይገድሉሃል። አንድ ጋዜጠኛ ከተስማማ በኋላ ምስጢር ሰምቶ ስለጠፋ ገድለውታል"

"ማን ይባላል?"

"እኔእንጃ! አለሙ፣ አለምሰገድ..."

"ዓለማየሁ?"

"አዎ፣ መሰለኝ"

"የአባቱን ስም ታስታውሻለሽ?"

"ያልተለመደ አይነት ነው"

"ገላጋይ?"

"አዎ፣ መሰለኝ"

"እሱ'ኮ እራሱን አጠፋ ነው የተባለው"

@OLDBOOKSPDF

"እንደዚያ እንዲመስል ያደርጋሉ፣ኡ-ፋ!"

ህይወቴ የተራ ልቦለድ ታሪክ የተከተለ መሰለኝ። ቢሆንም ለየትኛው ተስፋ ወደኋላ እፈገፍጋለሁ? ሪድ ሠርዌ የሄደበት መንገድ ለእኔ ያስፈራኛል?

"አንድ ነገር ልጠይቅሽ?"

"ጠይቀኝ"

"ሪድ ሠርዌ መታወሩን ታውቂያለሽ?"

"አዎ" በረጅሙ ተንፍሳ በጣቷ ደረቴን እጥብቃ መፋጨር ጀመረች።

"ማነው አይኑን ያጠፋው?"

"ምስጢር ያልኩህ ይሄንንም ይጨምራል። ለአንተ እያሰብኩልህ እኔን አደጋ ላይ ትጥለኛለህ?"


ዝም! መቀመቅ የሆነ ዝምታ!

ነገ ሁሉንም ነገር ከእነሱ ስማ፣ ከመናገር ተቆጠብ፣ ውይይታችሁ እጅግ ጥልቅ እንዳይሆን ተከላከል፤ እንድታውቀው አልተፈቀደልህም የተባልከውን ሳታንገራግር ተቀበል፣ አትፍራ! ለነገሩ ፍራ ብልህም አትፈራም። ነገር ግን አጓጉል አትዳፈር..."

ከምትወደኝ ሴት፣ ለእኔ በማሰብ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ አልመሰል አለኝ። እንደመውደዷ ድንገተኛነት ሁሉ ተልዕኮዋ ልቤን ማግኘትና ፍቅር መሻት ሳይሆን እኔን ለመጪው ውይይት ማመቻቸት ሳይሆን አይቀርም። በነገሩ አውቄ እንድገባበት ማድረግ የሚቻለው አሁን ኤልዛቤል እንዳደረገችው በመውደድ ቀርቦ አሳሳቢነትን ማንፀባረቅ ሲቻል ነው።

ልቤ ኤልዛቤልን ከደረቴ ላይ ገፍትሮ ለማስነሳት ተፍጨረጨረ።

@OLDBOOKSPDF



## ፳



ከብሉያት ዘመን አንዱ ነብይ ወገቡን አሸንፍጦ በቁጣ ከእንቅልፌ አነቃኝ:: "እስከመቼ በሁለት ሀሳብ ታነክሳላችሁ? ዳይ! ቀጥሉ! ቀጥሉ" ከኋላችን ሆኖ ይነዳናል::

"ወደየት?" እኔ እጠይቃለሁ::

"ወደቂሶን ወንዝ!" ነብዩ ቁጡው ኤልያስ እንደሆነ ገባኝ:: ሐሰተኛ ነብያትን እየነዳ ወስዶ የአሳረደበት ቦታ ነው ቂሶን ወንዝ!"

"ዳይ! ዳይ! ቀጥሉ!"

ነብይ 'ዳይ' ይላል? ምን አጩቃጨቀኝ? ከእንቅልፌ ብነቃስ? ነቃሁ:: ይሁንና የህልሜን ጭንቀት ህይወቴ ላይ አጋባሁ:: በእርግጥ ህልሜ ህልም ብቻ ነው? ለምን በዚህ ሰዓት ኤልያስ ወገቡን አሸንፍጦ መጣ? መልዕክት ይኖረው ይሆን? ወይስ የእኔ ፍርሃት የፈጠረው የምናብ ትርኢት ብቻ ነው?...

ተነስቼ አጠገቤ ያለው ባዶ ክፍል ውስጥ በቀዝቃዛ ውኃ ገላዬን ተለቃለቅሁ:: ስመለስ ኤልዛቤል መፃፊያ ወንበሬ ላይ ተቀምጣ አገኘኋት::

"መናፈሻው እንዴት እንዳማረ..."

ዝም ስላት እጄን ይዛ ወደውጭ መራችኝ::የእጇ የወርቅ ሸዋሊያ አጥብቃ በያዘችበት መዳፏ በኩል አድርጎ ወደ እጄ የተጋባ መሰለኝ:: ቅጭልጭልታው ልቤ ላይ ተሰማኝ:: በቀጭኑ የኀሮ መንገድ ሄደን ከመናፈሻው ጋር ስንገጣጠም ድንጋጤ መታኝ::

እንደጎረምሳ ላሩን በአጭሩ የተከረከመው መናፈሻ እንደናትራ ደማቅ ቀለም ያለው የውስጥ ልብስ በለበሱ አበቦች ተሸፍኗል:: እኛ ክፍል መድረስ የማይችለው የጠዋት ፀሐይ አካባቢውን አድምቆት

@OLDBOOKSPDF

አበቦቹን ቀልብ እንዲማርኩ ወደተመልካች ልብ አዝምቷቸዋል። እንደቢራቢሮ ሠራዊት አበቦቹ እየበረሩ መጥተው መናፈሻውን ወረሩት? ወይስ እንደ አቤሜሌክ አበቦቹ እስኪዘረዘሩ በእንቅልፍ ብዙ ዘመን አሳለፍኩ?...

...ኤልዛቤልን አየኋት።

በአበባ ግቢ የሚያሳምሩ መጥተው እንዲህ ...አይገርምም...

...የማደጎ ቤት አበቦች ናቸው ማለት ነው። ተሿሿሪና ተንከላዋሽ ውብቶች። እንደአበቃቀል ዘዬአቸው መልሰው ተተክለዋል። አሚጭሮቹ የመናፈሻውን ዳር ዳር ይዘዋል። በረጅሙ ተመንድገው፣ ሐረግ ላይ ለሚበቅሉት አበቦች ከበላይ የሞተ እንጨት ተረብርቦላቸው መንጠላጠያ ሆኗቸዋል። ከኤልዛቤል ጋር አዳብዬ መናፈሻውን ሳየው የብሉይ ዘመን ህይወት የምመራ መሰለኝ።

"ደስ አይልም?"

እንደዛሬው ብርሃን ተውቦ ሲወጣ ረድ ሠርዌ ቆም ብሎ አካባቢውን እያየ ያደንቃል።

"እንድቅትዮን"

"ምን ማለት ነው?"

"ብርሃን የተፈጠረበት የልደት ቀኑ ነው። አታዩም ጨረሩ እንደ አበባ በአፍላነት ሲፈነድቅ?"

እንደትናንቱ ዝናብ፣ እንደትናንቱ ጨለማና ቅዝቃዜ ዛሬ እንዲህ ውብ እና ብርሃናማ ይሆናል አላልኩም። የዛሬ እንዲህ አሽቃብጦ እለቱን መቀበል ምን ፍቺ ይኖረው ይሆን?

"የዛሬ የጋራ ተመስጦ እዚህ መናፈሻ ውስጥ ነው። Meditel አታደርግም?"

"አይመስለኝም" ቅር ያላት መሰለች። በጋራ መመሰጥ፣ በጋራ መስመጥ እየመሰለ ታይቶኛል እንደውም። ጫማዬን አውልቄ ሳሩ ላይ ቆምኩ። ውስጤ ያለው የተፈጥሮ መራኮት ፀጥ ሲል ተሰማኝ። ለነ ልብ እንደብረታ ብረት ትርክምክም ምቱ የባቡር ባጠገብ መንገን ይመስላል? ፀጥ ሲል ነው የታወቀኝ። ለካ ጨንጋራ የሚያፈላ የእርጎ

@OLDBOOKSPDF

መኪና ምትር ነው? ውጋ! ውጋ! ውጋ!... ደም ለምን ፀጥ ብሎ አይንጓጓዝም? ምን እንደ አዋሽ ወንዝ አስገነፈለው?...

"ለእኔ ተመሰጦ ይሄ ነው" አልኳት ኤልዛቤልን፣ ጠልቻታለሁ? ምንድነው? ስትስቅ፣ ሲከፋት፣ ስትስመኝ... በራሷ ስሜት ተመርታ ሳይሆን ተልዕኮዋ ግድ ስለሚላት እየሆነ ተሰምቶኛል።

"ዛሬ በህልሜ ኤልያስን አየሁት"

"ኤልያስ? ኤልያስ?

"ኤልዛቤል የዛተችበት። ነገ በዚህ ጊዜ ነፍስህን ከእነዚህ እንደአንዷቱ ነፍስ ባላደርጋት አማልክት ይህን ያድርጉብኝ፣ ይህን ይጨምሩብኝ ብላ የላከችበት። አስታወሽው? በዛቻው ፈርቶ የተነሳው፣ ነፍሱንም ሊያድን የሄደው..."

"እኔ አላውቀውም፤ ከአንተ ጋር ትተዋወቁ ነበር?" ይሄንን ፊት የማውቀው የት ነበር? ከፋት የተኳሰበት፣ በቀል በቅርብ እንደሚመጣ ዝናብ ያጉረመረመበት... ፊት። ጫማዬን አድርጌ ወደ ክፍሌ አመራሁ። የመናፈሻው ውበት አእምሮዬ ላይ በመድበቡና ብርሃኑ በመደብዘዙ እየከፋኝ።

ለምንድነው ሁሉንም ነገር ጣጥዬ የማልሄደው? ምን ቀረኝ?... ረድ ሠርዌ 'ፊት ለፊታችን አንተ ብቻ የምትፅፈው ታላቅ ታሪክ ይሰራል' ያለኝ ምኑን ነው? ይሄን ሳላረጋግጥ መሸሽ... የሞት ሞት ሞት አይሆንም?

"ወደ ዓይንአንባ እሄዳለሁ... የታጨሁብትን እፈፅማለሁ... ከተማይቱ እጮኛዋን እንደምትጠብቅ ንፅህት ሴት... እኔን ለማግኘት... ጓጉታለች..." ረድ ሠርዌን እያሰብኩ አሸለበኝ። እንደድሯችን ሆነን፣ እየተሿሿፍን መሄድን ስንሄድ ከእውን ወደህልም እያወትሁት ተሸጋገርኩ። በመጨረሻ የረድ ሠርዌን መታወር አስታውሼ በአይናማነቱ እጅግ አድርጌ ደነገጥኩ። አይኑ ጠፍቶ ካየሁት በላይ አስደነገጠኝ። ነቃሁ፣ ይሄስ ምን ማለት ነው። ከዛሬዋ ዕለት አኳያ ስትታይ ቅዠት ናት? መልዕክት?

ወዲያው ደጃፌ ላይ ከባድ ጥላ ወድቆ ቤቱን አጨለመው። የኤልዛቤልን ድምፅ ስጠብቅ ጎርነን ያለ ድምፅ ተከተለ።

@OLDBOOKSPDF

"ወንድምዬ፣ ወንድሜነህ፣ ወንድምዓለም..."

እምላያዬ ትዝ ብሎኝ ከአልጋዬ ላይ ተፈናጥሬ ተነሳሁ:: እውነቴን በውሸት ሊበርዝብኝ፣ ህይወቴን የተምታታ ቅጥ ውስጥ ሊከትብኝ...

...ልቆጣ ስወጣ ፊት ለፊቴ ሀሰተኛው ነብይ ቆሟል:: ጭንቅላተ ሞላላ፣ አንገተ ሠላላ፣ አንድ አይኑ የተቅላላ፣ ክናደ ረጅም... በትንቢት ሆነ በሌላ እንዲህ ትሆናለህ ተብሎ እንዲሁ መሆን በደል አይደለም? በድንጋጤ ፊቱ ላይ አይኖቼን ለጥፌ ቀረሁ::

"ወንድምዬ፣ የአንተም የእኔም ክፍል ለመአድም፣ ለወግም አይሆንም፣ ጠባብ ነው:: እዚያ መጽሐፍቱ ቤት አስነጥፌልሀሁና ልጠራህ ነበር አመጣጤ:: አንጉል ከእንቅልፍህ አናጠብኩህ?

"አረ የለም" ከትንቢት ጋር ፊት ለፊት ተጋፈጥኩ::አንድ አይኑ የጠፋች ብትሆንም የፊቱ ሚዛን አልተዛባም:: ወደምታየው አይኑ ገደድ ብሎ እይታ ለማጥራት አይሞክርም::

"እንግዲያው እንሂድማ፣ እሺ በለኝ፣ አብረን ምሳችንን በልተን እናውጋ" አለና የእጀን እፅቅ አጫጭር ጣቶቹን ጠምጥሞ ያዘ:: ከከቦች የሚረግፉበትን፣ መሬትና ሰማይ አንደ ነት የሚጠቀለሉበትን ጦርነት የሚመራ ጀግና ቢሆን ነው:: ታላቅ ጀግንነት ከእንዲህ ያለ ትህትና ጋር አልገጥምልህ ብሎኝ ተቸገርኩ::

"አንድ ቀን እንኳ መለስ ብዬ ባላይህ ወንድምዓለም" አለኝ::

ሰማይና ምድር ጆሮአቸውን ወደኛ አዘነበሉ፣ የምፅአት ቀን ምስክሮች ናቸውና:: ወንድሜ፣ ወንድሜ ሲባባሉ ሰምተናል ይላሉ የህይወት መዝገብ በተገለጠበት ታላቁ ችሎት ፊት::

ዝም አልኩ:: አጠገቤ ሲራመድ በእጠና ላይ ቆሞ ትርኢት የሚያሳይ ሆኖ ተሰማኝ:: እንደምንም ፊቱን ለማየት ቀና አልኩ:: ቁጣ ነበር:: ግና አይደለም:: ፊቱ ላይ የርህራሄ ጀምበር መስጠም አቅቷት ቆማ እንደቀረች አየሁ:: ይሄንንም ሰማይና ምድር ለምስክርነት በቆሙበት ችሎት ላይ የምናገረው እውነቱ ነው:: የትኛውም የሰለጠነ ቢያለባብሷት የሆነ በታ ላይ፣ የሆነ አካሏ ተጋልጦ ይታያል::

@OLDBOOKSPDF

እጁ እጄን እንደያዘ ለገበታ የተመቻቹ ሰዎች የተደረደሩበት ክፍል ገባን። እቀማመጣቸው ለተመስጦ እንደሆነ ሁሉ እግራቸውን አጣጥፈው ጭኖቻቸው ላይ አስቀምጠው ነው። በአክብሮት ተነሱ።

"ቁጭ በሉ፣ ወንድሞች" አለ። ለእኔና ለእሱ ሁለት ስፍራዎች ክፍት ተትተዋል።ፊት ለፊት የሚያፋጥጡ መቀመጫዎች ናቸው። ሰዎቹ እስክንቀመጥ ጠብቀው ተቀመጡ እንጂ የኖላዊን ፈቃድ ተቀብለው አልተደላደሉም። ጠቡሳ? እምባንሮውሳ? የሰው ሥጋ መቋደሱሳ? መታበይና እብሪቱሳ?...

...መካከል ላይ በረጅሙ የተነጠፈ የወፍራም ጨርቅ ገበታ አለ። እዚያ ላይ ብዙዓይነት የብርቅ ቀን ምግቦች ተደርድረዋል። አስተናጋጅ መጥቶ ከተደረደሩት ሰሃኖች አንዱን አነሳ፣ ዓይኑን ወደሐሰተኛው መሲህ ሲያቀና

"ከእንግዳው ይጀመር" ብሎ ወደእኔ ጠቆመ። ከሁኔታው ይልቅ ሥርዓቱ ምስጢር ሆነብኝ።

አስተናጋጁ እኔን እያየ የደረሰበትን ወጥ ይጠቁመኛል። አሺታዬን በአንገቴ ሳሳይ ይጨልፍልኛል። ዶሮ ወጥ፣ ክትፎና ጥብሳጥብስ አለ። ከዚያ በተጨማሪ የፆም ምግቦችም በየመካከሉ ተሰክተዋል። ጥቅልል እንጀራና ዳቦ ተጨመረ። ፊቴ ያለ የበቅሎ የማዕረግ ልብስ መረሻት የመሰለ፣ በወርቅ የተጠለፈ አራት መአዘን ጨርቅ ላይ ሰሀኑ ተቀመጠልኝ። ምግቡን መመገብ ሳልጀምር የገበታ አሰያየም ሥርዓቱን ማጤን ጀመርኩ።

አስተናጋጁ የኖላዊን ሰሐን እንደእኔ ሳያስፈቅድ ይጨልፍ ጀመር። ሽሮ፣ ቅጠላቅጠል፣ እና ጥቂት ቲማቲም ቁርጥ አድርጎ እፊቱ አኖረለት። ከዚህ በኋላ ቤተኛ የሆኑ እራሳቸው ተነስተው የራሳቸውን ሰሐን በሚፈልጉት ምግብ ሞሉና ተቀመጡ።

መብላት እንድንጀምር ይታወጃል ብዬ ስጠብቅ አስተናጋጁ አንድ በጨርቅ የተጠቀለለ ነገር በክብር አምጥቶ ሐሰተኛው ነብይ ፊት አኖረው። በጥንቃቄ ፈትቶ አጫጭር መዳፎቹ ላይ በደረቱ ትይዩ ያዘ። ህብስት ነበር።

"የአባቶች ጉባኤ በጥንቃቄ የሚያስጋግረው ህብስት ነው።" አለ ኖላዊ ወደ እኔ እያየ።

@OLDBOOKSPDF

ገበታው ላይ የታደሙት በአድናቆት አጉረመረሙ።

"ብጥንት ስርዓት ከወይራ ዘይት ጋር ምድር ላይ ያሉ ቅመሞች ሁሉ ተጨምረው፣ በሲጋው ሳይሆመጥጥ የሚጋገር ህብስት ነው። አባቶች ይሄንን ህብስት በሳምንት አንድ ቀን ከበሉ ሌላ ነገር ሳይቀምሱ እስከሚቀጥለው ሳምንት መቆየት ይችላሉ።"

አስተያየት መስጠት ወይም ጥያቄ ማቅረብ ይፈቀድ አይፈቀድ ስላልገባኝ ዝም አልኩ። ህብስቱን ቆርሶ አጠገቡ ግራና ቀኝ ለተቀመጡት አቀበለ። በስተቀኙ የተቀመጠው የብረት ቆብ የመሰለ ከባድ ምንጭር ያለው ነው። ምንጭሩ ሌላው ቀርቶ ጥይት እንኳን የሚመክት ይመስል የደደረ ነው። ህብስቱን ቆርሶ ለራሱ አስቀርቶ ለሚቀጥለው አስተላለፈ።

"የመጨረሻውን እራት" አስታወሰኝ። የቡራኬ ጸድቁ በሁለት አቅጣጫ ዞሮ እኔጋ ደርሶ ቆመ። ከሁለቱም ቆርሼ የማደርገው ሳጣ ኖላዊ ተነስቶ አንዱን ተቀበለኝ። ሥርዓቱ ለካ ይህ ነበር? ግን ትዕምርቱ ምን ይሆን? ለማይና ምድር ይሄንንም ለመመስከር ይንሺክኩ ይሆናል።

ኖላዊ የተቀበለውን ወደአፉ ሳያደርግ "የምንበላው ለነፍሳችንና ለቃላችን የሚደርስ ይሁን" አለ።

"ይህ ምን ማለት ነው?" ስል አሰብኩ።

"ከሥጋ ፍርሃት፣ ከመንፈስ ሞት የሚታደግ የነፍስ ቁርስ ያደርግልን"

አሜን አልተባለም። የቡራኬውን ጸድቅ ወደአፉ ሲያደርግ ሁላችንም ቀመስን። ወዲያው የፀጥታው ምሳ ቀጠለ። የሚጠጣ ነገር ያው አንዱ አስተናጋጅ ይዞ መዞር ጀመረ። ኖላዊ ውኃ ተቀዳለት። ቢራ፣ ስሰሳሳ፣ ወይን… አለ፤ ለምን ውኃ? የተጨሰፈለት ወጥም ጥያቄ ፈጥሮብኛል። ይሄንን ለማረጋገጥ ተቁነጠነጥኩ።

ጥቂት እንደቀማመስን ወስጄ ተነሳሁ። አንዱን የሥጋ ወጥ ያለበትን ሳህን አንስቼ ወደኖላዊ ሰሐን ተንጠራራሁ። ረጅም ክናዱን ዘርግቶ ተከላከለኝ።

"ባልደግስም የአክብሮቴን…" የሌላውን ሰው ስሜት መከታተል አላስፈለገኝም። ኖላዊ የትህትና ጀንበር ፊቱን ነክሳ እንደቆመች

@OLDBOOKSPDF

"ይቅርብኝ፣ ወንድምዬ"

"እረ በሞቴ" ደረቅሁ።

"ከሆነም ከሽሮው አድርግልኝ"

አካባቢ ላይ ማላመጥ በመቆሙ ያልተለመደ ነገር እንዳደረኩ ገብቶኛል። ቢሆንም...

"ለምን?"

"ሥጋ አልበላም፣ ወንድሜነህ"

"ለምን?" ህፃን ሆንኩ።

"Vegetarian ነኝ። አትክልት ብቻ ነው የምበላው።"

ከሽሮውም ሳላደርግለት ቁጭ አልኩ። የጠረጠርኩት ቢሆንም ለመቀበል ተናንቆኝ ነበር። የሰው ልጅ ቅድስናውን ከተፈጥሮ ህግ በላይ አሳልፎ መልአክትነትን ሲቋምጥ ለመብላት ነፍስ ማጥፋትን ተፀየፈ። የዘር ውርስ ሐጢያት መባል የነበረበት ይሄ ለመብላት ነፍስ ማጥፋት ግድ የሆነበት የተፈጥሮ ሥርዓት ነበር። ከእግዚአብሔር ይልቅ የሰው ልጅ ተፈጥሮን ቢዳኝ ይሄን የመበላላት ሥርዓት ያስቀጥላል? እንዲያውስ መብላት የሚሉት መቅሰፍት በተፈጣሪዎች ላይ እንዲጫን ይፈቅዳል? 'ለፍተህ ጥረህ ግረህ፣ በላብህ ወዝ ብላ' የሚለው የአዳም ውርስ እርግማን፣ መቅሰፍትነቱ ፣መልፋት፣ መጣር፣ መጋሩ ላይ ነው? አይደለም "ብላ" የሚለው የመበላላት አዋጅ ላይ ይመስላል።

"ወንድምዬ ብላ እንጂ፣ እረ በሞቴ"

ተናደድኩ በራሴ።

"በቃኝ"

"መች በልተህ?"

ዝም! ለንትና ስንት ወቀሳ ያለበት ዝምታ!

@OLDBOOKSPDF

"ወንድምዬ፣ አፈር ስሆን፣ አስቀየምኩህ? ሥጋ መብላት ካቆምኩ ስንትና ስንት ዘመን ሆኖብኝኮ ነው። ኧረ ወንድምአለም፣ ይቅር በለኝና..."

"በቃኝ! በቃኝ"

"ቢቃ እንግዲህ እንሱት"

ያለመድኩት ተጣጥፎ መቀመጥ ህመም ለቆብኛል። መነሳት ፈልጌአለሁ።

የሁሉም ገበታ ተነሳ።

"እንደ ፆም የሥጋ ግድፈት፣ እንደፀሎት የነፍስ ብርታት ያድርግልን" ኖላዊ አሳረገ። አራት ሰዎች ብቻ ስንቀር ሌሎቹ እየተሰናበቱ ወጡ። አስተናጋጁ የጨርቅ ገበታውን ከመካከላችን ልጦ አወጣው። የክፍሉ ድባብ ተለወጠ። ለከንዳችን መከዳ መጣ። የምንጠጣበት ብርጭቆ ሲቀር የምግብ ሰሐኑን ሁሉ በተቀመጠበት ጨርቅ ጎትቶ ድምፅና እንቅስቃሴ ሳይኖር ልጦ አነሳው። ነገሩ ሁሉ እየገረመኝ ግራ ተጋባሁ። ያኔ በተሳሳተው ረድ ሠርዌ እየተመራሁ ብዙ ነገሮችን አክፋፍቼ ስጠብቅ መቆየቴ ስህተት ይሆን? ሐሰተኛው መሲህ በእርግጥ ሐሰተኛ ነብይ አይደለም? ታዲያ?... ወይስ ፈፅሞ በማይመረመር መለኮታዊ ማስመሰል ውስጥ እየተታለልኩ ነው?

የሰው የምላ ሥርዓት ረበሸኩ። ፀፀት።

"ይቅርታ"

"ኧረ ምን አልክ ወንድምዬ?"

ያስቀዳሁትን ቢራ ያለሃፍረት ጨለጥኩ። አቀማመጤን ቀይሬ መከዳውን ደገፍ አልኩና ወደጎን አዘመምኩ። አካባቢያችን በመጽሐፍት መደርደሪያ የታጠረ ነው። ጥቂት ቆይቶ የሚቃም ጫት መጣ። አሁንም ግራ ተጋባሁ። ከኖላዊ ቀኝ ጎን የተቀመጠው ድድር ምንጭር ጫቱን አንስቶ እንደማሽሞንሞን አደረገና ከእኔ ጀምሮ ለሁላችንም አደለን።

"ለበከት?" ሐሰተኛው መሲህ ተጣራ።

"ለበይክ" አለ በቀኝ ጎኑ የተቀመጠው ምንጭሮ

@OLDBOOKSPDF

“ቅድም የነገርከኝን ደግመህ አጫውተን እስኪ”

“እይ፣ ምን ይረባል ብለህ?” አለ። ምንጭሮ ሲናገር ጥይት የማይበሳው የብረት ቆብ የመሰለው ምንጭሩ እንደልቡ አልንቀሳቀስ እያለ ሳያስቸግረው አልቀረም። ንግግሩ እንግዳ ነገር አለበት።

“እኔን አስደንቆኛል መቼም፣ ወንድሞችም ይስሙትና የራሳቸውን ብይን ይስጡ”

“ከሆነ ደግ” ለራሱ ያስቀረውን ቀንበጥ እንቆለጻጸለ ንግግሩን ቀጠለ።

“የካቶሊኮች ካህን የነበረው አልፎንሴ ኃይማኖታዊ ክርክር መግጠም እንደሚፈልግ ገልፆ ለንጉሡ አስታወቀ አሉ። ንጉሡም ክርክር እንዲገጥሙ ለቤተ-ክህነት መልእክት ላኩ። የቤተ-ክህነት ሰዎችም ተከራካሪያቸው እጨጌ ወልደጊዮርጊስን አቀረቡ። ክርክሩ ተጀመረ። አልፎንሴ ደጋግሞ ይጠይቃል እጨጌ ይመልሳሉ። በኋላ አንድ ጥያቄ አቀረበ።”

“ምንን?” አለ ኖላዊ እንዳልሰማ ሆኖ

“የእግዚአብሔር ፊቱ ወዴት ነው?” ብሎ። ጉባኤው ላይ ፀጥታ ሰፈነ። ጥያቄው ከምን እንደመነጨ እጨጌ ገብቷቸዋል። በኋላ “መቅረዝ አምጡ” ብለው አዘዙ። ለእጨጌ መቅረዝ ከነ ጧፉ ቀረበ። “ለኩሱ” አሉ። ተለኮሰ። ወደ አልፎንሴ ዞረው እንዲህ ሲሉ ጠየቁ።

“የዚህ መብራት ፊቱ ወዴት ነው?”

ኖላዊ አዲስ እንደሰማ ሆኖ ሳቀ።

“Brilliant! Brilliant!” እያለ ጥቂት ቆየና ወደ እኔ በአንድ አይኑ እየተመለከተ “እጨጌ እንዲህ መመለሳቸው የሚገርም ቢሆንም የአልፎንሴ ጥያቄም መነሻ አለው። በዚያ ዘመን እግዚአብሔር ወደ እስራኤል እንጂ ወደ ኢትዮጵያ አይመለከትም የሚል ጉምጉምታ ተነስቶ ነበር። መቼም ሳታውቀው አይቀርም በዚያ ዘመን “ሐሰተኛ መሲህ” ተብሎ የተንቋሸሸ ሰው ተነስቶ “እኔ ጥቁር ኢየሱስ ነኝ” ብሎ ነበር። “ከጥቁሪቷ ድንግል ማሪያም ተወልጄ” እያለ አስተምሮ ብዙ ተከታይ አፍርቶ ነበር። በኋላ አፄ ዘድንግል አስይዘው ቢጠይቁት ሳይፈራ እኔ ክርስቶስ ነኝ አለ። የምትኩ የተነሣሁ፣ ወደ ሰማይ

@OLDBOOKSPDF

ያረግሁ፣ ከድንግል ማሪያም የተወለድሁ እኔ ነኝ። አሁን ደሞ ከቤተ እስራኤል ተወልዶ እኛን ባዕድ አደረገን እይበሉኝ ብዬ ከኢትዮጵያዊቷ (አሬ እንደውም ከቤተ አህዛብ ነው ያለው) ከመርዓተ ወንጌል ተወለድሁ አለ። ንጉሡ ጭንቅላቱን አስቆረጡ። ተከታዮቹ ጌታችን ከሙታን ተነስቷል የሚል ልፋፌ ሰጡ። መቶም ሳታነበው አልቀረህም"።"

እራሴን በአዎንታ ነቀነቅሁ።

"የጥቁሩ ኢየሱስን ከሙታን መነሳት እንዴት አየኸው?"

ተንሸራትቼ፣ ሥነ ተረት በመሰለው ትረካ በኩል እዚህ፣የኛ ጥያቄጋ እንደደረስኩ ገባኝ። ትክ ብዬ ሐሰተኛውን አየሁ። ፊቱ አሁንም ርህራሄና መውደድ እንጂ ስፌተና ማቆብቆቡን አያሳብቅም።

"ሥነ ተረት ለመሆን ተቃትቶ የከሸፈ ታሪክ ይመስለኛል።"

ተደንቆ በአንድ አይኑ አየኝ። ብርሃን ከበስተጀርባው ሰላለ እንገቱ የበለጠ ሰልሳለች። የተሰጠኝን ቀንበጥ አንስቼ መቀነጣጠብ ጀመርኩ።

"ሥነ ተረትነቱ ቢሳከስ ኖሮ?"

"እንዴት ሊሳካ ይችላል?"

"ቢሳካስ?"

"በዚች ዓለም ከተፈጥሮ ህግ ውጪ መሆን እንኳ ለሰው ለራሱ ለፈጣሪ የሚቻል አይመስለኝም። ይሄንን ስለማውቅ አላምንም ነበር።"

ቤቱን ፀጥታ መታው። ኤልዛቤል ያስጠነቀቀችኝ ትዝ አለኝ። ምን ለማትረፍ ወደኋላ እላለሁ? ከቻለ ሞቶ ይነሳና ያሳምነኝ።

"የኢየሱስ ሞቶ መነሳትስ?"

ሳናውቀው ተንሸራተን የክርክሩ ጡዘት ውስጥ የገባን መሰለኝ። ማርገብ አልፈለኩም።

"የኢየሱስ በሁለት ይታያል። በማመንና ባለማመን።"

"ማለት?" ወንድምየን እረሳት? "እኔ ማወቅ የምፈልገው ያንተን ነው።"

@OLDBOOKSPDF

"በእኔ ተነስቷልም አልተነሳምም"

"ተነስቷል የምትለውን ይዘህ አስረዳኝ። ለእግዚአብሔርም ያልተፈቀደውን የዚች ዓለም የተፈጥሮ ህግ መጣስ ሳትረሳ"

የምለው ጠፍቶኝ ፈገግ አልኩ። አላስጨነቀኝም። እዚህ ላይ ጨዋነቱን ያዝኩለት።

"አንድ አስር ዓመት ይሆነዋል። ከፀጋዬ ጋር ተገናኝተን እንደዚሁ፣ በዚህ ርዕስ ላይ ተከራክረን ነበር"

"ፀጋዬ?"

"ሎሬቱ፣ ፀጋዬ ገብረመድህን። እሱም ኢየሱስ ተነስቷል ብሎ መከራከሪያ ያቀረበልኝ የእኛኑ ሥነ ተረት። ነባሩንና የመጀመሪያውን የአባቶች አምልኮተ ትርክት ነበር።"

"እንዴት?" የቀነጣጠብኩትን ጎረስኩ።

"ከሙታን የመነሳት ትውፊት የጀመረው በካም እናት አድባር አቴቴ ከአሥር ሺህ ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ ነው ይላል። ልጇ ይገዳደላሉ። አራ ወይም ሳቦ የተባለው ልጆቿ በወንድሙ በሴት ወይም ጉና ተገደለ። አቴቴ ከእህቷ ከነፍትየስ ጋር ሆና አራን ወደ ትንሳኤ ልደት ይቀሰቅሱታል። አቴቴ ከጥንታዊ ኢትዮጵያ ወደ ጥንታዊ ግብፅ ከሄደች በኋላም ይሄው የወንድማማቾች መገዳደል ዕጣ ፈንታ ተከትሏታል። ግብፆች ኸስኸስ(ኢስስ) ይሏታል። ባሏን ኦሲስን ወንድሙ ታይፎን (Typhon) በቅናት ይገድለዋል። አቴቴ ባሏን ወቅት እየጠበቀ እንደ አዝርት ደጋግሞ የሚነሳ ተምሳሌት አድርጋዋለች። እየህ ከዚያ በኋላ ነው ትውፊቱ፣ ሞትን የማሸነፍ ሥነ ተረቱ ወደግሪክ፣ ወደ ሮምና የተለያዩ ክፍለ አለማት እየተሸጋገረ መጥቶ ኢየሱስ ጋ የደረሰው። አቴቴ(አስስ) በድንግል ማሪያም ተተክታ መክሰም እስከትጀምር ድረስ ብቸኛዋ የሰውልጅ፣ የአዝርእትና የእንስሳት ሁሉ እናት ተደርጋ ተገቢው አምልኮት ይሰጣት ነበር።"

ቤቱ ፀጥታ ዋጠው፤ እንዲህ ያሉ ክርክሮች ሲያበቁ የሚከተለውን ፀጥታ ተመላልሼበታለሁ። አውቀዋለሁ። በማሸነፍ የበላይነትና በመሸነፍ የበታችነት የሚፈጠሩ ተቃራኒ ስሜቶች ውስጥ ውስጡን ይፍለቀለቁበታል። ዛሬ እንደዚያ አልሆነም።

@OLDBOOKSPDF

"በፊት ተራ የሥነ ተረት ቅብብሎሽ ትራፊ ትርክት ይመስለኝ ነበር"

"ምን.?" ንግግራችን ያበቃ መሰሎኝ ነበር።

"የፀጋዬ Mythology፣ ግን በውቅር የድንጋይ ላይ ፅሁፎች፣ በሀውልቶችና በፍርስራሽ ቤተመቅደሶች የተደገፈ የጨለማው ዘመን ታሪክ ሆኖ አገኘሁት። እነ ዴ.ኤ.ሐሪስ፣ እነ ጆርጅ ፓዝኔ፣ እነ ኤ.ዋሊስ ባዥ... ብዙ ተመራማሪዎች በመረጃ አስደግፈው ጥናታቸውን ያቀረቡበት ነው። እራ የመጀመሪያው የመለኮት ልጅ፣ የትንሣኤ ልደት እውነት፣ የበቀል ሳይሆን የይቅርታ ማስተማሪያ ገበታ...ነው።"

በስተቀኝ ያለው ምንጭሮ እንዴት አስፈቅዶ፣ እንዴት ተፈቅዶለት እንደሆን ሳላውቅ ንግግራችን መካከል ተሰንቅሮ የራሱን አስተያየት መስጠት ጀመረ።

"ዩንግ (የሥነ ልቡናው ምሁር) ስለ ሥነተረት የሚሰጠው ድምዳሜ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው 'ሥነ ተረት የተገኘበትን ምድርና የተራኪውን ማህበረሰብ ባህርያት ያንፀባርቃል' ይላል። በሥነ ተረት የተራኪውን ማህበረሰብ ባህርያት ያንፀባርቃል' ይላል። በሥነ ተረት ትርክት ውስጥ እራ ትንሳኤ ሙታንን ለይቅርታ የተጠቀመ ብቸኛው የሁለንተና ልጅ ነው።" ሲናገር አፍንጫው ውስጥ የደረቀ ቁስል ያለ የሚያስመስለው እንደ ብረት ቆብ የደደረ ምንጭሩ ይሆን? በግራ በኩል ያለው ሰው ፀጥ እንዳለ ቀጥሏል። ሌላው ቀርቶ የሚያዳምጥ አይመስልም።

ኖላዊ ጫቱን ይቀነጣጥባል እንጂ ወደአፉ አይልም። እኔ ወደምፈልገው ምስጢር የምመራበትን የሀሳብ መክፈቻ ሳስብ ቆይቼ ያገኘሁ ሲመስለኝ፦

"ታዲያ መቼ ይሆን የእኛን ትውፊት ትተን በሌሎች ህዝቦች ሥነ ተረት የተጠመድነው? ማለቴ..." ኖላዊ ቀና ብሎ አየኝ። ፊቱ ላይ አሁንም የርህራሄ ጀምበር ተገትራ እንደቆመች ነው።

"የሥነ ፅሁፍ መምህር አይደለህ?"

"አዎ"

"ጥሩ" አለና ወደ አፉ የማይቃጣውን ጫት መቀነጣጠብ ቀጠለ።

@OLDBOOKSPDF

"የመጀመሪያው የአማርኛ ልቦለድ..." ሲል

"ጦቢያ" አልኩት ተሽቀዳድሜ

"አዎ፤ ጭብጡን እንደምታውቀው ተራኪው "አረመኔ" በሚላቸውና በክርስቲያኖቹ መካከል በሚካሄደው ማባሪያ የሌለው ጦርነት ላይ ነው። ያኔ ንጉሱ የ 'አረመኔዎቹ' ነበር። ውቢቱን ጦቢያ አይቶ በመውደዱ አገር ክርስትናን ተቀብሎ ጠቡ ያበቃል። ትርክቱ ተራ ቢመስልም የሆነው እንዲሁ ነው። የአፈወርቅን ንግግር እንጥቀስ፤ 'ባንድ ነጋዴ ሰበብ ሁሉ ዳነ፤ በአንዲት እሴት ምክንያት ሁሉ አመነ፤ በአንድ ንጉሥ ቃል ኢትዮጵያ ቆመ' ማለት ምንድነው? የራስን ማንነት ትቶ በባእድ፤ ያውም ከእኛ የተቀዳ ትውፊት መተሳወጥ እራስን የመናቅና ሌሎች እግር ሥር በፈቃድ የመውደቅ ጅማሬ ነው። ሀገሩንና ህዝቡን ለሚወድ ሰው ሞት የሚያስመርጥ ህመም አለው።"

ህመሙን ኖላዊ ላይ ያየሁ መሰለኝ።

"ያ በአፄ ዘድንግል ጭንቅላቱን የተቆረጠው ሀሰተኛ መሲህ ይሄንን ውርደት ለመቀልበስ የተነሳ አገር ወዳድ ነበር።"

ዝም! ተያይዘን ወደ ዝምታ አዘቅት ወደቅን።

ኖላዊ ድንገት ድምፅ አውጥቶ ሳቀ። ቀና ብዬ አየሁት። ወዲያውም አቀማመጤን ቀየርኩ።

"የንግሥተ ሳባ ትርክት አለ ደሞ። ጥበብ ፍለጋ ወደ ንጉሥ ሰለሞን ሄደች፤ ትሂድ! ከእርሱ ጋር ወድቃ አረገዘች፤ ታርግዝ! ልጇን ለአቅመ አዳም ሲበቃ ወደአባቱ ላከች፤ ትላክ! ይሄ ሁሉ ችግር የለውም። ግን እንዴት ልጁ አገሩ ላይ እንዲነግሥ የአባቱን ቡራኬ ትጠይቃለች? ያኔ'ኮ ሰሎሞን የአንድ የተከማተረች ቀበሌ ትንሽ ንጉሥ ነው። እንዴት ይሄንን ታላቅ ህዝብና ሀገር፤ ለዛ በአካባቢው ለተናቀና እንዳለ ለማይቆጠር ስርዎ መንግሥት አሳልፋ ትሰጣለች? ያኔ እኮ ኢትዮጵያ እስከ ህንድ ውቅያኖስ የምታስገብር ታላቅ ሀገር ነበረች። ወንድምዓለም ይሄ ነው የሆነው፤ ይሄ መሆኑ ደግሞ ያምማል፤ በጣም ያማል!"

ንዴቱ ፊንቅሎ ፊቱ ላይ ታየኝ።

@OLDBOOKSPDF

"ይሄንን ነቅፈው የፃፉ ብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደሥላሴ ብቻ ናቸው:: ታላቅ ሕዝብ እዚህ ግባ የማይባል ትንሽ ሀገር እግር ሥር የሆነው ይሄ ነው::" ማንበርከክ ተቀባይነት የማይኖረው ስህተት ነው አሉት:: ወንድማለም

ዝም!

"በእስራኤሎች ትውፊት ሥር በመሆናችን ምን አተረፍን? እንደውም ተናቅን፣ ተዋረድን! የእስራኤል ስርዎ መንግሥት ማቋቋማችን ከይዘታችን አሳነሰን፣ ከቦታችን አስነሳን:: ይሄ ነው የሆነው"

ጥያቄ ማቅረብ የሰው ንዴት ማግለብለብ ሆኖ ተሰማኝ፤ ቢሆንም አላስቻለኝም::

"ይሄንን ለመቀልበስ የተሞከረ ነገር የለም? ማለቴ ህዝቡን..."

"ነበሩ"

ያልጠበኩት መልስ ሆነብኝ

"የመራ ወንድማማቾች ይባላሉ:: ሴማዊያኑ ሰለሞናውያን ነገሥታት ተዳክመው የኩሽ ስርዎ መንግሥት ሲቋቋም በመጀመሪያው ንጉሠ ነገሥት በመራ ተክለሃይማኖት ስም የተመሰረቱ ነበሩ:: ዓላማቸው የባዕዱን ትውፊት አጥፍተው ነባሩን፣ የራሳችንን ሥነ ተረት በህዝቡ መካከል ማቆም ነበር:: መራ ተክለሃይማኖት ጉዳዩ ለሥልጣኑም የሚያሰጋውና በግዛቱ ሁከት የሚያስነሳ ስለመሰለው ፊት ነሳቸው:: እነርሱም የመራ ወንድማማቾች መባላቸውን ትተው የሮሃ ባለታልኪዳን በሚል ሥያሜያቸውን ቀይረው ንጉሡን ሳይቀር በጠላትነት ፈረጁ:: ነገር ግን ብዙም ሳይቆዩ መካከላቸው ልዩነት ተፈጥሮ አለመግባባቱ እየከረረ አንድ አዲስ አስተሳሰብ የሚያራምዱ ብቅ አሉ:: ነባሩን ትውፊት በአዲሱ ክርስቲያናዊ አስተምህሮ ውስጥ በመሰግሰግ፣ በተደባለቀ ሥነ ተረት ኢትዮጵያ የኢየሩሳሌምን ሥፍራ እንድትወርስ ማስቻል::"

ወዴት፣ ወዴት ሄድን? ኖላዊ ፊቱ እየረጋ የቀድሞው ርህራኄ ፍንትው ብሎ መታየት ጀመረ::

@OLDBOOKSPDF

"ያ በአፄ ዘድንግል ጭንቅላቱን የተቆረጠው፣ ከኢትዮጵያዊቷ ከመርዓተ ወንጌል ተወለድሁ ያለው ፕቁር መሲህ የአዲሱ ድብልት አስተምህሮ ተርጓሚ ነበር። 'ማኅበረ ላሊበላ' ይባላሉ። የአጼ ላሊበላ ድጋፍ ስለነበራቸው ብዙ ሥራዎችን ሰርተዋል። የላሊበላ አብያተክርስቲያናት ሲታነፁ የራሳቸውን ነባር እምነት ምልክት ደባልቀዋል። ለምሳሌ የአቴቴ አድባር የፀሐይ መታቀፊያ በትር የሚወክለውን ኦጃይቭ (Ogive) ወይም አጊ ቅርፅ ቤተ ገብርኤል እና ቤተጊዮርጊስን ጨምሮ መቀሰቻ ሆኖ እንዲገባ አድርገዋል።የመቀሰቻ ትርጉሙና ሚናው የቤተ እምነቱ ዋስትና እስከመሆን የሚያደርስው እንደሆነ የታወቀ ነው። የማኅበረ ላሊበላዎች እንቅስቃሴ የምድራዊት ኢየሩሳሌምና የሰማያዊት ኢየሩሳሌምን ትውፊት ወደ ኢትዮጵያ በማዞር ቤተ እምነቶቹን ለሁለት ከፍለው ሰይመዋል።"

ቀጥ ብሎ እንደተቀመጠ ነው። እንደእኔ አልተቁነጠነጠም። አቀማመጡ ለጨዋታው ያለውን ማቆብቆብ የሚያስታውቅ ሆኖ ተሰማኝ።

"የማኅበረ ላሊበላ ሥራ ተደጋጋፊ ሆኖ በሁሉም ረገድ አላማቸውን እንዲያሳካ ታስቦበት የተከናወነ ነበር ማለት ይቻላል። ኪን-ህንፃውን በትውፊት ደግፈውታል። አንብበኸው ከሆነ ገድለ ቅዱስ ላሊበላ ለዚህ ማሳያ ነው። "ወደ ቤተክርስቲያንህም የገሰገሰ ሁሉ ወደ መቃብሬ እንደገሰገሰ ይሆናል" የሚል ቃልኪዳን ከኢየሱስ ለቅዱስ ላሊበላ ይተላለፋል። ይህ ምን ማለት ነው? "ሥጋህ የተቀበረበት መቃብርህንም እጅ የነሳ ሥጋዬ የተቀበረባት መቃብሬን እጅ እንደነሳን ይሁን።" ይህስ? ቀጥታ የኢየሩሳሌም ወራሽነት በሮሃ አካባቢ ተከናውኗል ማለት ይቻላል።" ንግግሩን አቋርጦ ሳቅ አለ። ቸንቹ እንደ ረድ ሠርዌ የተነቀሰ ነው።

"ምነው?" በሚል እየሁት።

"ዝም ብዬ አኻጎደጎድኩብህ። ተመሳሳይ ርዕስ ሲነሳ ይኸው ነኝ። አንድ ስለአለቃ ገብረሃና የሰማሁት ቀልድ መሰል ትምህርት የማኅበረ ላሊበላን አላማ ያስተነትናል።"

"እንዴት?"

"እንደዚህ ነው ወንድምዓለም። አለቃ ገብረሃና ታዛቸው ሥር ቁጭ እንዳሉ አንድ ያስተማሩት ዲያቆን መጣ። ጉልበት ስሞ ሲያበቃ

@OLDBOOKSPDF

'ልሰናበትዎ ነው የመጣሁ' አላቸው።

'የት ትሄድ ነው?' አሉት።

'ኢየሩሳሌም'

'ለምን?'

'የጌታን መቃብር ተሳልሜ ልመለስ'

'እክክክክ-ጥሩ ነው፤ ጥሩ! ግን ባለፈው ቆረብኩ ያልከኝ መሰለኝ'

'አዎ ብያለሁ'

'የጌታን ሥጋ ወደም ተቀብለህ?'

'አዎ ተቀብዩ'

'እንግዲያውኮ የጌታ መቃብሩ እዚህ ነው' ብለው ሆዱን ሳሙት።

ሳላስበው ሳቅሁ። ሳስበው ተደመምኩ።

"እለቃ ገብረሃና የሚታሙትን ትተን፣ ግብራቸውን ስንመለከት የማኅበረ ሳሊበላ ሀቡዕ ተሳታፊ መሆናቸው ይገለጥልናል።"

"ያ ቅኔያቸውም'ኮ ዋዛ አይደለም" የደረቀ ቁስል አፍንጫውን የደፈነው ምንጭራም።

"የቱ?" አለ ኖላዊ፤ ሳይሰማው ቀርቶ ሳይሆን ለእኔ እንዲደገም ስለፈለገ መሰለኝ።

"ክንኖ ኃጥእን እምላክ አይረብሐከምንተ

እፍቅሩ ጸለዕተክሙ እንዘ ትብል አንተ"

"Brilliant! Brilliant! አየህልኝ ወንድማለም? ኢየሱስን በራሱ ቃል ሲከሱት? ጠላቶቻችሁን ውደዱ ትላለህ አንተ ግን ጠላትህን ወደ እሳት ትከታለህ እንደማለት ነው። Brilliant! Brilliant!"-

ፀጥ አልኩ። ጫቱን እየቀነጣጠብኩ ለማሰብ ሞከርኩ። ይሄ ሁሉ መነሻ እንደምን ወደ... ደረሰ?

@OLDBOOKSPDF

"ላሊበላ የተፀነሰበትና የተወለደበት ቀን ከኢየሱስ ጋር አንድ ሆኖ ገድሉ ላይ ሠፍሯል። ይሄም የአጋጣሚ አይመስለኝም። ገድሉ በሙሉ የኢየሩሳሌም ቅዱሳንን ተገዳዳሪ ሆኖ እናገኘዋለን። የማስታውሰውን እንኳ ብነግርህ ከአብርሃም ጋር እንግዳ በመቀበል፣ ከሙሴ ጋር በፀሎት መና በማግኘት፤ ከዳዊት ጋር በወንድሙ በመሳደዱ፣ ከሰሎሞን ጋር በቤተ መቅደስ እነፃ... ላሊበላ ቀደምቶቹን ቅዱሳን ተጭኖ እንዲወጣ መደረጉ ያለምክንያት አይደለም።"

እዚህ ለመድረስ የት አካባቢ ነን? እራሴን ጠየኩ።

"የሐሰተኛው ነብይ ትርክትና ጭንቅላቱ ከተቀረጠ በኋላ የመነሳቱ ተአምር እንደቅዱሳኑ ሁሉ መሲሁንም ወደ ኢትዮጵያ የማዞር ፍላጎት አለበት?" ጋዜጠኛ የሆንኩ መሰለኝ። ያውም ቀሽም ጋዜጠኛ።

"አዎ"

"በዚህ ዘመን ይሄንን ከሙታን የመነሳት ተአምር የመድገም ትልም አለ?"

"በትክክል!"

"እንዴት?"

"ሙታንን የሚያስነሳ፣ እውር የሚያበራ፣ ሽባ የሚተረትር... መሲህ አለ"

"አንተነህ?"

ዝም! ፀጥ! መበርገግና መደንገፅ ያለበት

"አንተ ግን መሲህ ነህ?"

"አንተ አልክ" ብሎ በግራና በቀኙ ወደተቀመጡት ማተረ። በኢየሱስ ሙሽዙር "ነኝ" ማለት አይደለምን? ከሆነ...?

"እንደ ኢየሱስ እየተሂሂርክ ታስተምራለህ?" የጠየቅሁትን ሳይመልስ

"ለበከት?" ብሎ ምንጭራሙን ጠራ


@OLDBOOKSPDF

"ለበይክ" አለ:: ግን የሚታዘዘው ከመነገሩ በፊት ታዘዘ:: ተነስቶ፣ ሌላኛውን ፀጥተኛ ሰው አስነስቶ ክፍሉን ለቀው ወጡ::

"ምን ነበር የጠየከኝ?"

"ታስተምራለህ?"

"እዎ"

"እውር ታበራለህ?"

"እዎ"

"ጎባጣ ታቀናለህ?"

"እዎ"

"ሙታን ታስነሳለህ?"

"እዎ"

"ትወገራለህ?"

"እዎ" አንድ አይና መሆኑ በጀኝ እንጂ በሁለት ዓይኑ ነክሶ ቢይዘኝ ይጥለኝ ነበር::

"ትሞታለህ?"

"እዎ"

"ከሙታን ተነጥለህ ትነሳለህ?"

"እዎ"

"ይህ ሁሉ እንደምን ይሆናል?"

"እርሱ ምስጢር ካልተገለፀልህ በስተቀር ልትረዳው አትችልም::"

"ይገለፅልኝ፣ ምስጢር ይገለፅልኝ::"

"በቃል መቁረብ ስለሆነ የቁርባን መሻር አደጋ አለው::"

"ይሆንብሃል የተባለው ሁሉ ይሁንብኝ"

ከወቀሳ በስተቀር እዚህ ምድር ላይ ምን አለኝ?

"እምነት ካለህ በፆምና በፀሎት፣ ካልሆነም በፅሞናና በተአቅቦ ሰሦስት ቀን ከራስህ ጋር ምከር"

@OLDBOOKSPDF

እስካሁን በፅሞና አልነበርኩም? በተአቅቦስ አልቆየሁም? ሦስት ቀን? ረጃጅም ሦስት ቀኖች?...

...ተአቅቦው እንዲፀና ለሦስት ቀናት ኤልዛቤል ደጃፌን ሳትረግጥ ቆየች፡፡ ማን ነገራት?

በሦስተኛው ቀን ኖላዊ መኝታ ክፍሌ ድረስ መጣ፡፡ ጎብደድ ብሎ ገብቶ፣ ጎብደድ እንዳለ ተቀመጠ፡፡ ከረጃጅም ክናዱ ጋር በማይመጣጠን አጫጭር ጣቶቹ እንደ ትልቅ መጽሐፍ ይዟል፡፡ ምስጢር የሚገለጥለትን የሚያስምልበት መስሎኝ ነበር፡፡ ልብ ብዬ ሳየው "On the nature of things" የሚል ርዕስ አለው፡፡ ሮማዊው ባለቅኔ ሉክሪቲየስ የፃፈው የኢፒኩረስ ፍልስፍናን የሚያስተነትን ግጥም ነው፡፡ ስድስት ጥራዝ አለው፡፡ ልቤን አስንፎት ሳላነበው የተውኩት መጽሐፍ፡፡

"ከልብህ ጋር ምን ወሰናችሁ?" ሲል ጠየቀኝ፡፡

"ምስጢሩን ለመስማት ቆረጥኩ"

ሰማሁት...

...የጠበኩት ተአምር የለም፡፡

"ተአምራችን መንትያነታችን ላይ ነው፡፡ ሁላችንም አብረውን ያላደጉ አምሳያ ወንድሞች አሉን" አለኝ፡፡

"አንተም?" ስል ግር ብሎኝ ጠየኩት

"አዎ፣ እኔ መስቀል ላይ ስሞት እርሱ፣ መንትያዬ በሦስተኛው ቀን ትንሳኤዬን ይፈፅማል፡፡ ረድ ሠርዌን ያሳወሩት ዓይንአምባዎች በአምሳያ ወንድሙ ዓይኑብርቶ እንዲያዩት ይደረጋል፡፡ የአንተ መንትያ አልአዛርን ሆኖ ይሞታል፣ በአንተ ከሙታን ሲነሳ የገነዙት ሁሉ ተአምረ ትንሳኤውን ለዓለም ሁሉ ይመሰክራሉ፡፡"

መጀመሪያ እጅግ አድርጎ ግር አለኝ፡፡ መቃወምም አሰኘኝ፡፡ Albert Camus "The only serious philosophical problem is that of suicide" እንዳለው እየሆነ መሰለኝ፡፡ እራስን የማጥፋት ፍልስፍናዊ ችግር ዓይኑን አፍጦ ሲመጣ ታየኝ፡፡

"ብዙሃኑ ሳያውቁት ቀደም እንዲህ ሆኗል፤ አሁንም እንዲሁ ይሆናል" አለ ያሰብኩትን የተረዳ ይመስል፡፡

@OLDBOOKSPDF

ረድ ሠርዌ "..ወበከሌዔሆሙ ወይንየ ተመዘበረ" (በሁለቱም አታክልቴ ተመዘበረ) ያለው ይሄን ሲያመሰጥር ይሆን?

ጭንቅላቴ ግራቀኝ ገርምሞ የተገናዘበ ድምዳሜ ላይ ስመድረስ የማይችል ጋባቢ እንደሆነ ተረዳሁ:: ሰው የተነገረውንና ያየውን ቀርቶ የተሸሸገበትን ቆፍሮ አውጥቶ አንዳች መጠርጠሪያ ላይ ይደርስ የለም? ታዲያ? እኔ ምንድነኝ?...

...ጭንቅላቴ በተአምር ደዌ ተይዟል:: የተማርኩና በአመክንዮ የማምን እንደሆንኩ ለራሴ ብነግርም፤ ከእናቴ የማልሻል ጭፍን አማኝ ነኝ:: ጋሊሊዮ ከስንት መቶ አመታት በፊት የደረሰበትን የህዋ ቁመና ሥጋዬ እንጂ ነፍሴ አልተቀበለችውም:: ዛሬም ለእኔ ሰማይ ማህሌታይ ያሬድ እንደተቀኘበት ያለ ባለሰባት ደርብ ከምድር በላይ ያለ ስገነት ነው:: ጠፈር... ምጽንዐት... ሰማይውዱድ... ሔኖስ... ኢዮር... እርያም... መንበረ ፀባዖት... የእኔ ሰማይ ምንዛሪዎች ናቸው:: መላእክታት ሱራፌል ካህናተ ሰማይ፣ መብረቅ ለብሰው ለምሥጋናና ለሰው ልጅ ምህረት ይዘምራሉ... ይወርባሉ::

...ምድር የለማያት እድፍ ጉድፍ መጣያ ገሃነም ናት:: የተሰናከሉና የወደቁ ሁሉ እክናፋቸውን ተቀጭተው ይጣላሉ በአዳም ደም እንጥልጥሎሽ፣ እንደፈትል ኳኳላ ትውልድ በመውደቅ እጣ ፈንታ፣ ከላይ ወደታች ተደርድሮ - - ይ

ም

ዘ

ገ

ዘ

ጋ

ል::

@OLDBOOKSPDF




@OLDBOOKSPDF